አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች፣ የጆርናሊዝምና የኮሚኒኬሽን ኮሌጅ
የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍ እና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት
የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

# [illegible] በምስለ ዓመቱ መባቻ በታተሙ አምስት የአማርኛ ድርሰቶች ውስጥ

በ
መአዛ ገብሩ

አዲስ አበባ
ሚያዝያ 2005 ዓ.ም

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች፣ የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍ እና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

# ወሲባዊ ፍንገጣ በምዕተ ዓመቱ መባቻ በታተሙ አምስት የአማርኛ ድርሰቶች ውስጥ

በ

መአዛ ገብሩ

አዲስ አበባ

ሚያዝያ 2005 ዓ.ም.

# ወሲባዊ ፍንገጣ በምዕተ ዓመቱ መባቻ በታተሙ አምስት የአማርኛ ድርሰቶች ውስጥ


አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች፣ የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍ እና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት


የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር


በ

መአዛ ገብሩ

የጥናቱ አማካሪ

አቶ ቴዎድሮስ ገብሬ (ረዳት ፕሮፌሰር)


አዲስ አበባ

ሚያዝያ 2005 ዓ.ም.

# ወሲባዊ ፍንገጣ በምዕተ ዓመቱ መባቻ በታተሙ አምስት የአማርኛ ድርሰቶች ውስጥ

በ

መአዛ ገብሩ


አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች፣ የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍ እና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር


የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

አማካሪ ______________________ ፊርማ ______________________

የውስጥ ፈታኝ ______________________ ፊርማ ______________________

የውጭ ፈታኝ ______________________ ፊርማ ______________________


አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
ILS LIBRARY

## ማውጫ


ምስጋና ---------------------------------------------------------------- v
አጠቃሎ ----------------------------------------------------------------- vi

**ምዕራፍ አንድ1 መግቢያ** ------------------------------------------------ 1

1.1. የጥናቱ ዓላማ ---------------------------------------- 3
1. 2.የምርምር ጥያቄዎች ---------------------------------- 4
1.3.የጥናቱ ወሰን ----------------------------------------- 4
1.4.የጥናቱ ዘዴ ------------------------------------------ 4
1.5.የጥናቱ ፋይዳ ----------------------------------------- 7

**ምዕራፍ ሁለት1 ንድፈ ሐሳባዊ ዳራና የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት** ---------- **8**

2.1. ንድፈ ሐሳባዊ ዳራ1 የባህል ጥናት ------------------------ 8
2.1.1. ነገረ ወሲብ! አጠቃላይ ዳራ ---------------------------- 11
2.1.2. ወሲባዊ ፍንገጣ --------------------------------------- 19
2.1.3. ሥነ ጽሑፍና ነገረ ወሲብ ------------------------------- 23
2.2. የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት ------------------------------------ 25

**ምዕራፍ ሦስት1 ትንተና** ---------------------------------------------- **31**

3.1. ሴተኛ አዳሪነት ---------------------------------------------- 31
3.1.1. ሴተኛ አዳሪነት በኢትዮጵያ ---------------------------------- 36
3.1. 2.ሴተኛ አዳሪነት በተመረጡ የከፍለ ዘመኑ ድርሰቶች ውስጥ - 38
3.1.2. 1. ተጎጂ ወገኖች ------------------------------------- 39
3.1.2.2. ነጻ ሰዎች ------------------------------------------- 45
3.2. በተመሳሳይ ጾታ መኃል የሚፈጠር ፍትወት ----------------- 57
3.3. በጭካኔና በጥላቻ የተቃኙ ወሲባዊ ባሕርያት ---------------- 67
3.4. መልከአ ተባእት በሴተኛ አዳሪዎች መንደር ------------------ 79

**ምዕራፍ አራት1 ማጠቃለያ** -------------------------------------------- **87**

**ዋቢ ጽሑፎች** ---------------------------------------------------- **91**

## ምስጋና

በቅድሚያ ይህን ጥናት እከናውን ዘንድ የፈቀዱልኝን የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የድኅረ ምረቃ ትምህርት ቤትን እንዲሁም የምርምርና ቴክኖሎጂ ሽግግር ምክትል ፕሬዚደንት ቢሮን (VPRTT) ላመሰግን እወዳለሁ፡፡ በተጨማሪም የትምህርት ክፍሉ፣ በተለይ የጥናት ርእሴ እንዲጸድቅ በወቅቱ የትምህርት ክፍሉ ሊቀ መንበር የነበሩት የአቶ አብርሃም አለሙ ትብብር አስፈላጊ ነበር፡፡ ሐሳቤን ተረድተው በቀና ልብ ላደረጉልኝ ድጋፍ ያለኝ ምስጋናና አክብሮት ከፍ ያለ ነው፡፡

ከርእስ መረጣው ጀምሮ አጠቃላይ የጥናት ጽሑፉ ተጠናቆ አሁን የያዘውን መልክ እንዲይዝ የአቶ ቴዎድሮስ ገብሬ ሚና የላቀ ነበር፡፡ ያልታተሙ ተያያዥ ሥራዎቹን እንዳነብ በመፍቀድ፣ አስፈላጊ መጻሕፍትን በማዋስና ልዩ ልዩ መንገዶችን በማመላከት፣ ያለመሰልቸት በማረምና ሥርአት በማስያዝ ላደረገው ሁሉ እግዜር ጤናና እድሜ ይስጥልኝ፡፡ ሁሉም እንዲህ ዕውቀት እና ቀናነትን ቢታደል ምን መሥራት ይቻል ነበር?

በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ይሄን ጥናት ለማጠናቀቅ እንድችል በዙሪያዬ የነበሩ ሁሉ ተመስጋኝ ናቸው፡፡ በተለይ ቤተሰቦቼና ጓደኞቼ ስማችሁን በዝርዝር ባልጠራም ታውቁታላችሁና ምስጋናዬን ተቀበሉ፡፡

በስተመጨረሻም የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የድኅረ ምረቃ እና የኢትዮጵያ ጥናት ተቋም ቤተ መጻሕፍት ሠራተኞች ለነበራቸው ቀና ትብብር ከፍ ያለ ምስጋና ይገባቸዋል፡፡

## አጠቃሎ

"ወሲባዊ ፍንገጣ በምዕተ ዓመቱ መባቻ በታተሙ የአማርኛ ድርሰቶች ውስጥ" የሚል ርእስ የሰጠሁት ይህ ጥናት፣በምዕተ ዓመቱ መባቻ በታተሙ አምስት ድርሰቶች ላይ--*መኃልየ መኃልየ ዘ ቼቼኒ*/2001/፣*ሰዓት አላፊ*/2002/፣*የቼቼኒያ ምስጢራዊ ለሊቶች*/2003/፣*የሰዶም ነፍሳት*/2003/ እና *ሰዓት አላፊ 2*/2004/ ላይ--የሚያተኩር ነው፡፡ይህን ጥናት በወጉ ለማከናወን በዓብይነት የተገለገልኩበት የሥነ ጽሑፍ አንጻር "የባህል ጥናቶች" የሚባለው ሲሆን፣በስሩ የሚካተተውን ነገረ ወሲብን በጽንሰ ሃሳብና በንድፈ ሃሳብ ምንጭነት፣ቴክስታዊ ትንተናን ደግሞ በዓቢይ ዘዴት ተገልግዬባቸዋለሁ፡፡ በዚህም መሠረት በድርሰቹ ውስጥ የተስተማሰሉ ዓበይት ሰብዓዊ ጉዳዮች የትኞቹ እንደሆኑ ለየቼ ለማመልከት ሞክሬያለሁ፡፡በትንታኔዬ ውጤቶች ላይ በመንተራስም የድርሰቶቹንና ድርሰቶቹ የበቀሉበትን ዐውድ ባህላዊ፣ ማህበራዊ፣ርዕዮተ ዓለማዊና ሥነ ልቡናዊ ቁርኝት በአንድምታ አሳይቻለሁ፡፡

ለምርምር የተመረጡት የሥነ ጽሑፍ ሥራዎች በጭብጥም በአከያየን ቅጥም ለአማርኛ የሥነ ጽሑፍ ልማድ አዲስ የሚባሉ ገጽታዎችን አስተዋውቀዋል፣ቀድመው የተዋወቁትንም ገነው እንዲታዩ አድርገዋል፡፡ገጽታዎቹ በተለይ ጭብጦቹ በአንድ በኩል፣ አካባቢያችንን በዓዲስ ዐይን እንመለከት ዘንድ የሚጋብዙ፣ በሌላ በኩል በይነ ዲስፕሊናዊ የሆነ የነገረ ሰብእ ምርመርን የሚቀሰቅሱ ናቸው፡፡

በመጨረሻም በጥናቱ ለማረጋገጥ እንደቻልኩት፣ ለጥናት በተመረጡት የሥነ ጽሑፍ ሥራዎች ውስጥ ጎልተው የወጡት ዓበይት ነገረ ወሲባዊ ጉዳዮች ተከትዮቹ ናቸው፡፡ አንደኛ፣ በዓብይነቱ ለየትና ወሰብሰብ ያለ ሴተኛ አዳሪነት እየገነነ መጥቷል፤ ሁለተኛ በተመሳሳይ ጾታ መኃል የሚፈጠር ፍትወታዊ መሳሳብ እጅግ ደርቷል፤ ሦስተኛ፣ ሴተኛ አዳሪነት "ተለምዷዊ" የሚባለው ዓለም ደብቆና ሸሽጎ የሚያኖራቸው፣በጭካኔና በጥላቻ የተቃኙ ወሲባዊ ባህሪያት መገለጫ ሆኗል፡፡ በዚህ ሁሉ ውስጥ የምናረጋግጠው እውነታ፣ለባህሉ "እንግዳ" የሆኑ አዳዲስ ወሲባዊ (ማህበራዊ--ልቡናዊ) ምንትነቶች በመመስረት ላይ መገኘታቸውን ነው፡፡

ሦስቱ ጉዳዮች ማህበረሰቡ የሚኮንናቸው ከፍ ሲልም ወንጀል ብሎ የሚፋረዳቸው ናቸው፡፡ይሁንና በድርሰቶቹ አማካይነት ማህበረሰቡን ነኝ ብሎ የሚያስበውን ወይም የነበረውን ነው ብሎ መቀበል እንደማይቻል ማስየት ተችሏል፡፡ በገፊው እና በተገፊው፤ በተለምዷዊው እና በአፈንጋጩ መካከል የነበረው ድንበር ተቃይጧል፡፡ አዳዲስ ወሲባዊ፣ ማህበራዊና ልቡናዊ ምንትነቶች በዘመን ከሚጋሯቸው ሌሎች የባህል ውጤቶች ጋር ተዛምደው በቀሪዎቹ የባህል ጥናት ዘዴዎች፣ በተለይም በ "ኢትኖግራፊያዊ" እና በ"ፖለቲካዊ-ኢኮኖሚያዊ" ዘዴዎች በወጉ እንዲመረመሩ የሚያሳስቡ ናቸው፡፡

## ምዕራፍ አንድ፤ መግቢያ

በአገራችን ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ የነገረ ወሲብ ጉዳዮች ከቀድሞ በተለየ መልኩ ገነው ታይተዋል ማለት ይቻላል፡፡ ባለፉት ሃያ እና አስራ አምስት አመታት ውስጥ የኤችአይቪ፣ የቤተሰብ ወሊድ ቁጥጥር፣ ወሲባዊ የኃይል ጥቃቶች፣ ወዘተ. በሰፊው የሚወራላቸው ማኅበራዊ ጉዳዮች ሆነው ከርመዋል፡፡ አሁን አሁን ደግሞ በተጨማሪነት "እንግዳ"ና "አፈንጋጭ" የወሲብ ምንትነቶችና ዝንባሌዎች በባህል ቢነወሩም፣ በሕግ ቢወነጀሉም ባለፍን ባገደምንበት፣ በምናይ በምንሰማው ሁሉ የማይቀሩ "ቅመሞች" ሆነዋል፡፡ ይህንን ለማረጋገጥ የማገገሚያ ጣቢያዎችን (*rehabilitation centres and foster care*)፣ ፍርድ ቤቶችንና የማረሚያ ሥፍራዎችን መጎብኘቱ ብቻ በቂ ነው፡፡ ሰርከ በተቀመጥንበት ልብና እእምሯችንን የሚጎበኘው የብዙኀን መገናኛዎች የ"ወንድ ልጆቻችሁን ከጥቃት ጠብቁ" ተማጽኖም በይፋ የሚነግረን ቁም ነገር ያለው ይመስለኛል፡፡ ታዳጊ ወጣቶች በዕውቀት በሚታነጹባቸው ትምህርት ቤቶች--በተለይም እኔ ባስተዋልኳቸው የአዲስ አበባ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች--የሚካሄዱ ጭውውቶች በእነዚሁ ጉዳዮች የተቃኙ ናቸው፡፡[1] ልማድና ወግ ይጠብቅባቸዋል የሚባሉት ሃይማኖታዊ ተቋማት ሳይቀሩ በየዐውደ ምኅረቱ በሚደረጉ ስብከቶች ውስጥ--በመጻሕፍት ቅጽ በተሰናዱ ጽሑፎች ጭምር--ጉዳዮቹን ሲያነሱ እየሰማንና እያየን ብዙም አንደነቅም፡፡ ቴሌቪዥንና ራዲዮኖቻችን፣ ጋዜጦቻችን፣ መጽሔቶቻችን፣ በየመንገዱ የምንሰቅላቸው ማስታወቂያዎችና የምንበትናቸው በራሪ ወረቀቶች፣ ድረ-ገፃችን፣ የኪነ ጥበብ ውጤቶቻችን፣ ወዘተ. ያለንበትን፣ የደረስንበትን አፍ አውጥተው ይመሰክራሉ፡፡ ይህ ብቻ አይደለም፣ የምንጓዝበትን ጭምር የሚተነብዩም ይመስለኛል፡፡

ሥነ ጽሑፍም ቢሆን የተገኘበት ባህል እና ዘመን ውጤትና መገለጫ እንደመሆኑ ከዚህ ይለያል ተብሎ አይጠበቅም፡፡ ቴዎድሮስ ገብሬ፣ ከነገረ ወሲብ አንጻር የአማርኛን ሥነ ጽሑፍ በመረመረበት ለህትመት የተዘጋጀ መጣጥፉ "The State of Non-Normative Sexuality in Modern Amharic Literature"፣ በሃያኛው ክፍለ ዘመን የመጨረሻ አስርት በክፍለ ዘመኑ መባቻ ዓቢይ ጉዳዮቻቸውን "ፍትወተ ወሲብ" (*sexual desire*) እና "ነገረ ወሲብ" (*sexuality*) ያደረጉ፣ በ"በፍንገጣ (*sexual perversity*)፣ በብካችና ድቀት (*decay and decadence*) ላይ የተመሠረቱ፣ አዲስ ዓይነት የኃይል እሰላለፍ (*power relation*) የሚታይባቸው ሥራዎች"፣ በአማርኛ የሥነ ጽሑፍ ኪን ውስጥ ግዛት እያሰፉ፣ መሠረት እያጠበቁ መምጣታቸውን ያስረዳል (ያለቀን፣ ገጽ 11)፡፡ እነዚህ ድርሰቶች በአብዛኛው "ሴተኛ አዳሪነትን"፣ አስገድዶ መድፈርን፣ ኤችአይቪን፣ ኢ-ተለምዷዊ የግብረ ሥጋ ግንኙነቶችን፣

---

[1] ለዝርዝር መረጃ፣ "በተመረጡ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚነገሩ ቀልዶች፣ ፍካሬ ልቡናዊ ጥናት" የሚለውን የመአዛ ገብሩን ጥናት (አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 2001) ይመለከቷል፡፡

በወሲብ የተቃኘ የራስ ግድያን በርእሰ ጉዳይነት ያነሳሉ፡፡ እዚህ ጋ የአማርኛ ሥነ ጽሑፍ እንዲህ ያለው ደረጃ ላይ ይደርስ ዘንድ ያስቻሉ ሁነቶች ምን ምን እንደሆኑ መጠየቅ የሚገባን ይመስለኛል፡፡ በእኔ ግምት እንደ መነገድ ጠራጊ ሊቆጠር የሚችለው ዓቢይ ሁነት የሳንሱር መነሳት ነው፡፡ የሳንሱር መነሳትን ተከትሎ ባልተለመደ መልኩ ወሲብ የገነነባቸው መጽሔቶችና ጋዜጦች በየሥፍራው ፈሉ፡፡ በውጭ ቋንቋ የተጻፉ "ፖርኖግራፊያዊ" ሥራዎች በብዛት በአገር ውስጥ ቋንቋ እየተተረጎሙ አገሪቱን አጥለቀለቁ.፡፡ በተለይ ደግሞ፣ "ገደብ ተጥሎባቸው" የኖሩ ቀደምት ድርሰቶች ታትመው ለንባብ በቁ፡፡ በዚህ ረገድ ዓቢይ ተጠቃሹ ስብሐት ገብረ እግዚአብሔር ይመስለኛል፡፡ ስብሐት በልቅ ዘይቤውና በኢተለምዷዊ /አፈንጋጭና እንግዳ/ ነገረ ወሲባዊ ጭብጦቹ በኋለኞቹ ድርሰቶች ላይ ያሳደረው ተጽእኖ አቻ የሚገኝለት አይመስለኝም፡፡[2] የአገራችን አንባቢ በእነዚህ ሥራዎች ተሟሽቶ ነው እንግዲህ አሁን እኔ ለጥናት የመረጥኳቸው "የሥነ ጽሑፍ ሥራዎች" ላይ የደረሰው፡፡

ማኅበረሰባችን ወሲባዊ ጉዳዮችን በሚመለከት ድብቅ ምናልባትም ዝግ ሊባል የሚችል ልማድ አለው፡፡ ድርሰቶቹ ከዚህ ዓይነቱ ልማድ የወጡ፣ ማኅበራቸው ከኃጢአት፣ ከነውርና ከወንጀል ጭምር በሚፈርጃቸው ጉዳዮች የተሞሉ ናቸው፡፡ ይህ ዓይነቱ ተቃርኖ ለምርምር የሚያነቃ ይመስለኛል፡፡ ተቃርኖው ግን በዚህ አያቢቃም፡፡ እንዲህ "ዝግ" ነው ባልነው ማኅበር ውስጥ መሰል ደራስያን እየበዙ ነው፡፡ አሁን ድርሰቶቹን ወስጄ፣ ርእሴን ቁርጩ ምርምር እያካሄድኩ ባለሁበት ወቅት እንኳ ለህትመት የበቁ ተመሳሳይ ድርሰቶች በቁጥር ቀላል አይደሉም፡፡ የደራስያኑ መብዛት፣ የድርሰቶቹ ተደጋግሞ መታተም (በቅጽ ተከፋፍለው በተከታታይ ሥራነት የወጡም አሉባቸው) ቢያንስ ቢያንስ የድርሰቶቹን ተቀባይነት ማግኘትና የገበያውን መድራት ይነግሩናል፡፡ እንደ አንዲት የሥነ ጽሑፍ ተማሪ ይህንን ዓይነቱን የጦዘ ተቃርኖ ዓይቼ ማለፍ አልቻልኩም፡፡ በዚሁ ትይዩ በአገራችን በነገረ ሰብእና በማኅበረሰብ መስኮች፣ በተለይም በሥነ ጽሑፍ ትምህርት ቤቶች ቸልታ ግራ መጋባቴ አልቀረም፡፡ እንደነዚህ ያሉ ተቃርኖዎችን ማስተዋሌ ከፍ ያለ ጥያቄ ፈጥሮብኛል፡፡

ቴዎድሮስ፣ የአገራችን የሥነ ጽሑፍ ትምህርት ቤቶች "ዛሬም ድረስ ለአዳዲስ ኪናዊ ፍልስፍናዎችና የአከያየን ስልቶች፣ በተለይም እንደ ፍትወት (*desire*) ፣ ነገረ ወሲብ (*sexuality*) ፣ ወዘተ ላሉ ተደጋጊ ሐቲቶች በራቸውን ዘግተዋል" ሲል ይተቻል፡፡ በልዩ ልዩ ባህላዊ፣ ማኅበራዊና ሰብአዊ ከስተቶች ቀሲቃሽነት አዲስ ለሚበቅሉ ዘውጎች ሥፍራ መንፈግ የአገሪቱን የሥነ ጽሑፍ ኪን ሂደትም ይሁን ትምህርት ቤቶቹን እንደሚጎዳ የሚያሳስበው ቴዎድሮስ፣ ሥራዎቹን ያለጥናት በ"ብልግና

---

[2] ይህንን የእኔን እቋም የሚጋራው ቴዎድሮስ፣ ጻሩ ግን በኢተለምዷዊ ነገረ ወሲብ ረገድ ስብሐት ታላቅ ተጽእኖ ፈጣሪ እንጂ ጀማሪና ተላሚ አይደለም ሲል ይከራከራል፡፡ ለቴዎድሮስ በተለይ የተመሳሳይ ጾታ መሳሳብ ፍትወት (*homoerotic desire*) በአማርኛ ሥነ ጽሑፍ ውስጥ ከስብሐትም፣ ከታደሰ ሊበንም የቀደመ ታሪክ አለው ("The State of Non-Normative Sexuality in Modern Amharic Literature" ከገጽ 2-3፡፡)

ፊርጆ ፊት ከመንሳት ይልቅ" በጥንቃቄ እንመርምር ሲል ይማጸናል፡፡ በተማጽኖ ብቻ አያበቃም፤ ድርሰቶቹን ነቅሶ በወጉ ለማንበብ "የባህል ጥናት" የሚባለው የትችት አንጻር የተሻለ አማራጭ ሊሆን እደሚችል ጭምር ይመክራል (23)፡፡

"ወሲባዊ ፍንገጣ በምዕተ ዓመቱ መባቻ በታተሙ አምስት የአማርኛ ድርሰቶች ውስጥ" የሚል ርዕስ የሰጠሁት የእኔ ጥናት እንግዲህ፣ እንድም ከፍ አድርጌ በዘረዘርኳቸው አስተውሎቶቼ የነቃ፣ አንድም በቴዎድሮስ ተማጽኖ የተቀሰቀሰ (እና ደግሞ "የባህል ጥናት" ምቹ የማንበቢያ አንጻር ነው በሚለው ምክሩ ላይ የተመሠረተ) ነው፡፡ ይሆን ልበል እንጂ በአጠናን ስልት፣ በአንጻር ምርጫና በትኩረት የእኔ ጥናት ይለያል፡፡ የቴዎድሮስ ምርምር ራሱ እንደሚጠቁመው፣ "ሒሳዊ ታሪካዊ ቅኝት" ("*critical historical review*") ሲሆን የእኔ "የቴክስት ትንተና" ነው፡፡ ቴዎድሮስ ረጅም ዘመንን ወስዶ በመረጣቸው በርካታ ድርሰቶች አማካይነት የየጊዜውን ነገረ ወሲባዊ አዝማሚያ እየለየ በጥቅሉ የሥነ ጽሑፍ ታሪካችን ውስጥ የፈጠሩትን ቅጥንበር (*pattern*) ለመንደፍ ሲሞክር፣ እኔ ደግሞ ከ2000 እስከ 2004 በታተሙ አምስት ድርሰቶች ላይ ተወስኜ ጥልቅ ቴክስታዊ ትንተና ለማካሄድ ነው ጥረት ያደረኩት፡፡

## 1.1.የጥናቱ ዓላማ

ለምርምር በመረጥኳቸው አምስት ድርሰቶች ውስጥ የተስተማሰሉ (*represented* )[3] ዓበይት ሰብዓዊ--ነገረ ወሲባዊ--ጉዳዮች የትኞቹ እንደሆኑ ጥብቅ በሆነ ቴክስታዊ ንባብ ተንትኖና ተርጉሞ ማሳየት የዚህ ጥናት ዓቢይ ዓላማ ሲሆን፤ ከዚህ በተጨማሪም ተከታዮቹ ንኡሳን ዓላማዎች ይኖሩታል፡፡ አንደኛ፣ በምርምሬ ግኝቶች ላይ በመንተራስ በድርሰቶቹ ውስጥ የተስተማሰሉትን ጉዳዮች ባህላዊ፣ ማኅበራዊ፣ ርዕዮተ ዓለማዊና ሥነ ልቡናዊ እንድምታዎችን አረቅቃለሁ፡፡ ሁለተኛ፣ ድርሰቶቹ ለአካዳሚያዊ ተግባር፣ በተለይም ለሥነ ጽሑፍ ትምህርትና ምርምር ያላቸውን ተገቢነት አሳያለሁ፡፡

---

[3] ቃሉን የተዋስኩት ከዶክተር ዮናስ ነው፡፡ ዮናስ እስተማስሉን የ"*representation*" እቻ አድርገው የሚገለገሉበት ሲሆን፣ የእርስቶትልን የእስተማስሉ ንድፈ ሐሳብ በመውሰድ ቃሉን በተከታዩ መንገድ ያረባሉ፡፡ ሀ. የተስተማሰለው/ሚስተማሰለው ጉዳይ */object of representation: that which is represented/*፤ ለ.የተስተማሰለበት/የሚስተማሰልበት ቅጥ */manner of representation: the way the object is represented/*፤ ሐ. የተስተማሰለበት/ያስተማሰልንበት መሣሪያ */means of representation: the material that is used/* ("ETLI 611: *Representation* (እስተማስሉ)" ከሚለው የክፍል ውስጥ ማስታወሻ የተወሰደ)

## 1.2.የምርምር ጥያቄዎች

ጥናቱ በጥቅሉ አንድ ዓቢይ ጥያቄንና አራት ንኡሳን ጥያቄዎችን ለመመለስ ይሞክራል፡፡ ዓቢይ ጥያቄ፤ ለምርምር በተመረጡት ድርሰቶች ውስጥ የተስተማሰሉ ዓበይት ሰብዓዊና ነገረ ወሲባዊ ጉዳዮች የትኞቹ ናቸው?

ንኡሳን ጥያቄዎች፤ አንደኛ፣ ነገረ ወሲብ በድርሰቶቹ ውስጥ የሚቀርብበት መንገድ ምን ይመስላል? ሁለተኛ፣ ደራስያኑ በዚህ መንገድ ይገለገሉ ዘንድ ያስገደዳቸው ኪናዊ ምክንያት ይኖር ይሆን? ሦስተኛ፣ በድርሰቶቹ ውስጥ የተስተማሰሉት ሰብዓዊ ጉዳዮች ባህላዊ፣ ማኅበራዊ፣ ርእዮተ ዓለማዊና ሥነ ልቡናዊ እንድምታዎች ምንድን ናቸው? አራተኛ፣ ድርሰቶቹ ለዘመናዊው የአማርኛ የሥነ ጽሑፍ ትምህርትና ምርምር የሚኖራቸው ተገቢነትና ፋይዳስ እምን ድረስ ነው?

## 1.3.የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት በቤተ መጻሕፍት ውስጥ በሚካሄድ ምርምር ላይ ተመሥርቶ የሚከናወን ነው፡፡ ጥናቱ የሚመረምራቸው የሥነ ጽሑፍ ሥራዎች በቁጥር አምስት ሲሆኑ ሁሉም በምዕተ ዓመቱ መባቻ ባሉ አራት ዓመታት ውስጥ ለህትመት የበቁ ናቸው፤ *መቃልየ መቃልየ ወ ቹቹኒያ* (2001)፣ *ሰዓት እላፊ* (2002)፣ *የቹቹኒያ ምስጢራዊ ለሊቶች* (2003)፣ *የሰዶም ነፍሳት* (2003) እና *ሰዓት እላፊ 2* (2004)፡፡ እነዚህ ሥራዎች ተዛምደው ይጠኑ ዘንድ ያስቻሉ ልዩ ልዩ ምክንያቶች አሉ፡፡ ቀዳሚው ምክንያት እጅግ ተቀራራቢ በሆነ ጊዜ ውስጥ መገኘታቸው ነው፡፡ በእርግጥ በተጠቀሰው የጊዜ ቅንብብ ውስጥ የታተሙ ሌሎች በርካታ ድርሰቶች አሉ፡፡ ነገር ግን፣ አምስቱ ድርሰቶች ከሌሎቹ ይልቅ ቆየት አድርጌ በትንታኔዬ ውስጥ በስፋት በማሳየቸው ገጽታዎቻቸው--በአከያየን ዘይቤ፣ በርእሰ ጉዳይ ምርጫና በመንፈስ--የጠበቀ ቁርኝት አላቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ "እውነተኛ ታሪክ" መሆናቸውን፣ አልያም "በእውነተኛ ታሪክ ላይ" መመሥረታቸውን በጥብቅ ማሳወቃቸው የጋራ መለያቸው ነው፡፡ እነዚህ ነጥቦች ድርሰቶቹ ከዘመነኞቻቸው ተለይተው በወል ይጠኑ ዘንድ ያስቻሉ ምክንያቶች ሆነዋል፡፡

## 1.4.የጥናቱ ዘዴ

ከፍ አድርጌ እንደጠቆምኩት የዚህ ጥናት ዓቢይ መታገሪያ "የባህል ጥናት" የተባለው የትችት እንጻር ነው፡፡ ቆየት አድርጌ በንድፈ ሐሳባዊ ዳራ ሥር በስፋት ለማሳየት እንደምሞክረው ለጥናት የመረጥኳቸው ድርሰቶች የባህል ጥናት በሚሳብባቸው ዓበይት የቴክስት ገጽታዎች ላይ የተመሠረቱ ናቸው፡፡ አንደኛ ድርሰቶቹ በህትመት ዘመንም ይሁን በመቼት "የዛሬ" (*contemporary*) ከመሆናቸው

በተጨማሪ፣ በይዘትም ይሁን በአኪያየን ልማድ "አዲስ በቀል" የሚባሉ ዓይነት ናቸው (ቴዎድሮስን፣ ያለቀን፣ ገጽ 21 ይመልከቱ)፡፡ ሁለተኛ፣ ድርሰቶቹ በማኅበራቸውም ይሁን አካዳሚው ሥፍራ ተነፍገው የኖሩ በሚመስሉኝ "ሰብዓዊ ጉዳዮች" ላይ የተመሠረቱ ናቸው፡፡ ሦስተኛ፣ ብዙዎቹ ድርሰቶች በይነ ዲሲፕሊናዊ ንባብን የመቀስቀስ አቅምም አላቸው ብዬ አምናለሁ፡፡ እነዚህ ገጽታዎች ድርሰቶቹን ለባህል ጥናት እንዲመቹ ያደርጓቸዋል፡፡

በባህል ጥናት ላይ ምርምር ያደረጉ ባለሙያዎች እንደሚናገሩት የትችት አንጻሩ ባለብዙ ዘዴ ነው፡፡ እነዚህ ዘዴዎች በአመዛኙ "ኢትኖግራፊያዊ" (ethnographic) ፣ "ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊ" (political economy) እና "ቴክስታዊ ትንተና" (textual analysis) በሚሉ ሦስት ፈርጆች ተመድበው ይገኛሉ (እንጅንሰን 2004፣ 26፣ ዴቪስ 2008፣ 53-67)፡፡ ለባህል ጥናት የሥነ ጽሑፍ ቴክስት፣ እንደየትኛውም ቴክስት የባህል ውጤት ወይንም ምርት (cultural product) ሲሆን፣ ደራሲው እንደ አምራች ተደራስያኑ ደግሞ እንደ ሸማች ተደርገው ይቆጠራሉ፡፡ በዚህም መሠረት፣ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊ ዘዴ ደራሲው ቴክስቱን "ያመርት" ዘንድ ሊቀሰቅሱ፣ ሊገፋፉና አንዳንዴም ሊያስገድዱ ይችላሉ ብሎ በሚያምንባቸው የባህሉ አውዶች ላይ ማትኮርን ይመርጣል፡፡ ይህ ዘዴ እጅጉን ከፖለቲካ ሳይንስ፣ ከኢኮኖሚክስና ከፍልስፍና በመነጩ ጽንሰ ሐሳቦችና ርእዮቶች ይታገዛል፡፡ የኢትኖግራፊያዊ ዘዴ ትኩረቱ ተደራሲ /ሸማች/ በመሆኑ ("audience reception" ተብሎ የሚጠራበት አጋጣሚ አለ) ከመስክ በሚገኝ መረጃ አማካይነት አንባብያንንና ንባብን፣ እንድም ከተገኙበት የጊዜና የሥፍራ መንፈስ አኳያ፣ አንድም ደግሞ ከወልና ከግል ልቡናዊ ሁኔታዎቻቸው አንጻር ለመመርመር የሚሞክር ነው፡፡ ይህ ዘዴ ሁሌም ከመስክ በተገኙ መረጃዎች ላይ ብቻ የሚመሠረት አይደለም፤ አልፎ አልፎም ቢሆን አንባቢውንና ንባባቸውን በቴክስቱ ውስጥ በሚከሰቱ ትእምርቶች አማካይነት ለመንደፍ ይሞክራል፡፡ እነ ጆንሰንም ይህንኑ ሐሳብ በተከታዩ መንገድ ያጠናክራሉ፤ "*Audience research may link text and readership by exploring how particular kinds of texts – television soap operas, women's magazines – are consumed by particular kinds of audiences or interrogate how such audiences are produced*" (2004, 42)፡፡ ይህ ዘዴም በፊንታው ከሶሲዮሎጂና ከሥነ ልቡና በተገኙ ሐቲቶች ይታገዛል፡፡

የመጨረሻው ዘዴ ቴክስታዊ ትንተና ነው፡፡ ይህ ዘዴ በእርግጥ መሠረቱ በነባሩ የሥነ ጽሑፍ ጥናት ውስጥ እጅግ የተለመደው፣ በአንድ ድርሰት ሥነ ልሳናዊና ቴክኒካዊ ገጽታዎች ላይ ማትኮርን ብቻ የሚያከረው "ነቂስ" ወይም "ውስጣዊ" የአነባበብ ቅጥ (close or intrinsic reading) ነው፡፡ በባህል ጥናት ውስጥ የሚገኘው የቴክስት ትንተና[4] በእርግጥም በዚህ ነባር የአነባበብ ልማድ ተገርቶና ሰልቶ መሠረት የያዘና የባህል ጥናት ባልነው አንጻር አማካይነት ወደ ተለያዩ የጥናት መሥኮች የተዛመተ ነው፡፡

---

[4] የቴክስት ትንተናን አንዳንድ የባህል አጥኚዎች "የሐቲት ትንተና" (*discourse analysis*) /ሳርዳር 1997/፣ ሌሎች ደግሞ "ባህላዊ ትንተና" (*Cultural analysis*) /ግሪንብላት 1990/ በሚል ስያሜ ሲገለገሉ ይገኛሉ፡፡

ይሁንና ነባር ጠባዩን እንደያዘ አልጸናም፤ በምላሹ ከየዘመተበት መሥክ በነጠቃቸው አዳዲስ እሴቶች አማካይነት በልጽጓል፡፡ በዚህም ምክንያት የአፍኣዊ ንባብ (*extrinsic reading*) ተቃራኒ መሆኑ እንዳበቃለት የመስኩ ተመራማሪዎች ያስረዳሉ፡፡ ለምሳሌ ሥነ ጽሑፍን ከባህልና ከታሪክ ጋር አቆራኝቶ በማጥናት የሚታወቀው ስቴፈን ግሪንብላት (Stephen Greenblatt) ተከታዩን አስተያየት ይሰጣል፤

> *Cultural analysis then is not by definition an extrinsic analysis, as opposed to an internal formal analysis of works of art. At the same time, cultural analysis must be opposed on principle to the rigid distinction between that which is within a text and that which lies outside. It is necessary to use whatever is available to construct a vision of the ''complex whole'' to which Tylor referred. And if an exploration of a particular culture will lead to a heightened understanding of a work of literature produced within that culture, so too a careful reading of a work of literature will lead to a heightened understanding of the culture within which it was produced.* (1990, 227)

በባህል ጥናት መታጊያንት በሚካሄዱ ምርምሮች ውስጥ እነዚህ ከላይ የዘረዘርኳቸው ሦስት ዘዴዎች--ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊ ዘዴ፣ ኢትኖግራፊያዊ ዘዴ እና ቴክስታዊ ትንተና--ለምርምር እንደተመረጠው ቴክስት ባሕርይ፣ እንደ ርእሰ ጉዳዩ ዓይነት፣ እንደ ባህላዊ ዐውዱ አመቺነት፣ እንደ አጥኚው ቅኝት፣ የጊዜ ገደብና የገንዘብ አቅም በተናጠል አለበለዚያም በጥምረት ግልጋሎት ሊውሉ ይችላሉ፡፡ በዚህ መሠረት በአንድ በኩል፣ በቴክስቶቹ "እንግዳነት"ና "አፈንጋጭነት"፣ በምርምሬ ርእሰ ጉዳይ "ተጋፊነት"ና በስልጠናና ቅኝትም ባለኝ ቅርበት፤ በሌላ በኩል ባለው የጊዜና የገንዘብ ገደብ ምክንያት የዘዴ ምርጫዬን ቴክስታዊ ትንተና አድርጌያለሁ፡፡ እንዲህ ብልም ግን ባስፈለገኝ ጊዜ ሁሉ ወደ ባህላዊ ዓወዱ ወጣ ገባ ማለቴ አይቀርም፡፡ ይህን የማደርገው የምርጫ ጉዳይ ሆኖብኝ ብቻ አይደለም፡፡ እላይ ከጠቀስኩት ከግሪንብላት ማጠቃለያ እንደምንረዳው፣ ሌሎቹም ተመራማሪዎች፣ ለአብነት እንጆንሰንን መጥቀስ እችላለሁ፣ በግልጽ እንደሚሉት በዘመናችን የባህል ጥናት ውስጥ በቴክስትና በዐውድ መኃል አለ የሚባለው ነባር ድንበር ተደበላልቋል፤ "*in the course of such an analysis, the text/context distinction itself tends to break down as contextual elements appear in the text, either directly or as symptoms, while the text itself comes to appear as a particular concrete instance of the wider cultural field*" (እንጆንሰን፣2004፣ 187)፡፡ ስለዚህ አንዱ ያለሌላው መቆም አይችልም፤ መሠረታዊው ልዩነት የሚመነጨው ለመረጥነው ዘዴ ከምንሰጠው የትኩረት መጠን ነው፡፡ ይህ ብቻ አይደለም ከፍ አድርጌ እንደጠቆምኩት እያንዳንዱ ዘዴ እንጻረ ብዙ (*multi-perspectival*) ጭምርም ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ምርምር ውስጥ የእኔ ተግባር፣ ከተለያዩ ደሲፕሊኖች በተወሰዱ፣ ነገር ግን በባህል ጥናት በሚዘውተሩ፣ ከሁሉም በላይ ደግሞ ድርሰቶቹ "እፍ አውጥተው"

በሚጠሯቸው ጽንሰ ሐሳቦችና ንድፈ ሐሳቦች መተንተኛነትና መተርጎሚያነት ቴክስቷዊ ትንተና ማካሄድ ይሆናል፡፡

## 1.5.የጥናቱ ፋይዳ

ጂኦርጅ ዋትሰን (George Watson) የተባለ የነገረሰብና የማኅበረሰብ ሥነ ዘዴዎች አጥኚ፣ *Writing a Thesis: A Guide to Long Essays and Dissertations* በሚለው መጽሐፉ ዕውቀትና አካዳሚያዊ ድፍረት ጥናትና ምርምርን በሚገባ ለማከናወን የሚያስችሉ መሠረታዊ ጉዳዮች ናቸው ሲል ያስረዳል፡፡ በዋትሰን እምነት ድፍረት--በዕውቀት ላይ የተመሠረተ ድፍረት--የሚጀምረው ለምርምር በምንመርጠው ርዕሰ ጉዳይ ነው፤ *"Courage enters the question even at its first stage, in the choice of a subject"* (1993, 13)፡፡ እኔ ለምርምር የመረጥኳቸው መጻሕፍት ማኅበሩ በኃጢአት፣ በነውር፣ በፍንገጣ፣ ወዘተ. እየፈረጀ በሚወነጅላቸውና በሚያነውራቸው የተገፉ ስብዓዊ ጉዳዮች ላይ የተመሠረቱ ናቸው፡፡ መጻሕፍቱ መልሰው መላልሰው እየታተሙ በብዙ ሺህ ኮፒዎች እንደሚሸጡ ብናውቅም በየአደባባዩ በሰው እጅ ላይ አናያቸውም፡፡ ሲገዙ በስውር፣ ሲነበቡም በድብቅ ነው፡፡ እነዚህን መጻሕፍት ለመመር (አደባባይ ለማውጣት) መወሰን ዋትሰን የሚለውን ድፍረት የሚጠይቅ ይመስለኛል፡፡በመሆኑም እንዲህ ያለው ድፍረት እምብዛም በማይስተዋልበት የትምህርት ክፍላችን ውስጥ እንዲለመድ የራሱን ድርሻ ማከል የዚህ ጥናት ቀዳሚ ፋይዳ ነው፡፡ ሁለተኛው ፋይዳ ደግሞ ከምርምር ዘዴ ጋር ይዛመዳል፡፡ ከፍ አድርጌ እንደጠቆምኩት የዚህ ምርምር ዓቢይ መታገቢያ "የባህል ጥናት" የሚባለው አንጻር ሲሆን፣ በሥሩ ከነገረ ወሲብ ጋር የተዛመዱ ጽንሰ ሐሳቦችና ንድፈ ሐሳቦች በመተንተኛነት ያገለግላሉ፡፡ መታገቢያውም ይሁን በተለይ ጽንሰ ሐሳቦቹና ንድፈ ሐሳቦቹ በአገራችን የሥነ ጽሑፍ ትምህርትና ምርምር ውስጥ እጅግም የተለመዱ አይመስለኝም፡፡ ይህ ጥናት እነዚህን ጉዳዮች፣ ቀድሞውኑ ተዋውቀዋል ብለን ብናስብ እንኳ፣ አጠንክሮ የማስተዋወቅ ሚናም ሊኖረው ይችላል ብዬ እገምታለሁ፡፡

# ምዕራፍ ሁለት፤ ንድፈ ሐሳባዊ ዳራና የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት

## 2.1. ንድፈ ሐሳባዊ ዳራ፤ የባህል ጥናት

በዚህ ዘመን፣ በዓለም የነገረ ሰብእ ትምህርትና ምርምር ውስጥ እጅግ ከገነኑ፣ የሥነ ጽሑፍ ትምህርት ቤቶች ራሳቸውን ይመረምሩ ዘንድ ካስገደዱ የትችት አንጻሮች መኃል ዓቢዩ "የባህል ጥናት" (*cultural studies*) መሆኑን በርካታ የዘርፉ ምሁራን ያስረዳሉ (ለምሳሌ ኢስት ሆፐ 1991፣ ዴቪስ 1997፤ ካቫላሮ 2001፤ እነጆንሰን 2004) ። በ1960ዎቹ መጀመሪያ በእንግሊዝ በበርኒንግሃም ዩኒቨርሲቲ ዘመናዊ የሆነውን ስያሜውን ያገኘው የባህል ጥናት ዋነኛ ጉዳይ  በተለይ ዘመናዊ በሚባለው አለም ውስጥ ባህል የሚጫወተውን ሚና መረዳት ነው።ይህም ሲባል እጅግ በጣም በተዛነቀ እና ልዩነት በበዛበት አለም ውስጥ በግለሰብም ይሁን በማህበራዊው ደረጃ እንዴት ባህላዊ ምንትነቶች ይገነባሉ ፣ ይዋቀራሉ ወይም ጠቅለል ባለ መልኩ የባህል ውጤቶች እንዴት በተግባር ይታያሉ የሚለውን ይመለከታል (ካለር ፤1997፤43)።የባህል ጥናት መቀስቀስ መሰረታዊው ግፊትም የተነሳው "የተርታውን" ህዝብ ባህል (*popular cultuer*) እና መገለጫ ከተረሳበት እዲያንሰራራ ለማስቻል ወይም ድምፅ አልባ ተደርገው የተቀመጡትን የተገፉ ወገኞች (*marginalized grupes*)ድምፅ ለማሰማት በሚል ነበር (ዝኒ ከማሁ 44-45)።

ባህል ጥናት ውስጥ ለሚነሱ ጭብጦች በሙሉ በመሠረትነትም በማቀንቀኛነትም የሚያገለግሉ ሁለት ተዛማጅ ጽንሰ ሐሳቦች አሉ። የመጀመሪያው ጽንሰ ሐሳብ ምንትነት (*identity*)[5] ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ኃይል ወይንም የኃይል አሰላለፍ (*power/ power relation*) ነው። "ምንትነት" በመልከዓ ምድር፣ በግብረ-ከል፤ በሥነ ልቡና፣ በርዕዮተ ዓለም፣ በወሲብ፣ ወዘተ. ላይ የሚመሠረት ባህል ሠራሽ ክስተት ነው፤ "*For cultural studies, identity is a cultural construction because the discursive resources that form the material for identity formation are cultural in character*" (ክሪስ

[5] ይህ ቃል፤ ዶክተር ዮናስ አድማሱ የአለቃ ኪዳን ወልድ ክፍሌን *መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገ ቃላት ሐዲስ መሠረት* አድርገው ለ"*identity*" በአቻነት የሚገለገሉበት ነው። ከተለመደው "ማንነት" ይልቅ በ"ምንትነት" ለመገልገል የወሰንኩት በሁለት ምክንያቶች ነው። አንደኛ "ምንትነት" "ማንነትን" እና "ምንነትን" እኩል ያሳስባል። ሁለተኛውና ዓቢዩ ምክንያት "ምንትነት" በቋንቋው የእርባታ ሥርዓት ከ"ሴትነት" ጋር መዛመዱ ነው። እንዲህ ይላሉ ዮናስ፤ "አለቃ ኪዳን ወልድ---- 'መኑ'ን ይዘው ቃል ከቃል እያማዘዙ 'ምንት' ላይ ሲደርሱ፣ በሰዋስው እርባታ ሲዘረዝሩ 'መኑ' የወንድ፣ 'ምንት' የሴት መሆኑን ይነግሩ[ናል]---። እኔም፤ 'ምንት' በሴት አንቀጽ የሚዘረዘረውን፣ እንደ 'ሥላሴ' በወንድም፣ በሴትም ተራ እስኪበቄ፤ ረቂቅ ነገር አመልካችነቱንም ጭምር ብዬ ሁሉቱንም እንዲጠቀልል አድርጌ እገለገልበታለሁ" (2001፤ 8)። የጥናቱ ዓቢይ ትኩረት ሴትነትና የሴት ምንትነት በመሆኑ በቃሉ መገልገሌን እጅግ ተገቢ ያደርገዋል።

ባርከር 2004፣93). ምንትነት ባህል ሠራሽ ከስተት በመሆኑ አንድ ሥፍራ ላይ አይረጋም፤ ተደላድሎ አይቀመጥም፤ ሁሌም በማያልቅ ሂደት ውስጥ ይኖራል፡፡ ከባህል ጥናት መሥራቾች መኃል አንዱ የሆነው ስትዋርት ሆል (Stuart Hall) ይህንን እውነታ በተከታዩ መንገድ ይገልጸዋል፤

> *Identity is not as transparent or unproblematic as we think. Perhaps instead of thinking of identity as an already accomplished fact, which the new cultural practices then represent, we should think, instead, of identity as a 'production', which is never complete, always in process, and always constituted within, not outside, representation(*1990, 222).

ምንትነት ሁሌም በምሥረታ ላይ የሚገኝ ባህላዊ ከስተት ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ሰዎች ይህ ከሌሎች ተለይተው የሚታወቁበት ባህላዊ ምልከት ገንኖ እንዲታይላቸው፣ ታግሎ እንዲያሸንፍላቸው፣ ብሎም ጸንቶ እንዲኖርላቸው ሰርከ እሴቶቻቸውንና ፍላጎቶቻውን በመግለጽ ይጠመዳሉ፡፡ ይህንን ተግባር ለማከናወን የሚገለገሉባቸው መንገዶች--ቋንቋ፣ ኪነ ጥበብ፣ ዕደ ጥበብ፣ ወዘተ.--በሙሉ የባህል ውጤቶች ናቸው፡፡ ይህን እንበል እንጂ በምንትነት አመሠራረት (*identity construction*) እና አገላለጽ (*identity expression*) መኃል ይህ ነው ተብሎ በሙሉ አፍ የሚነገርለት ድንበር የለም፡፡ ለምሳሌ፣ ታሪከ የመንገርን ሂደት፤ ትረካን ማሰብ እንችላለን፡፡ ታሪከ መንገር በአመዛኙ ምንትነትን መንገር፣ መግለጽ፣ ሥሎና ቀርፆ ማሳየት፤ በዚህም ምንትነትን ማለማመድና ማፀንበር ተደርጎ ነው የሚወሰደው፡፡ በእርግጥም ከትረካ ዓበይት ተግባራት መኃል ጥቂቶቹ እነዚሁ ናቸው፡፡ ነገር ግን በትረካ ሂደት በገሃድ ከሚከናወኑት ከእነዚህ ተግባራት በተጓዳኝ ተራኪውም ይሁን ተደራስያኑ በየእርከኑ በስውር እንደ አዲስ እሴቶቻቸውን ይፈትላሉ፤ ፍላጎቶቻቸውን ያደራሉ፤ ምንትነታቸውን ይሸምናሉ፤ በፍጻሜው ለህልውናቸው መሠረት የሚሆኑ አዳዲስ ፍቺዎችን ይጥራሉ (ለሰፊ ማብራሪያ የBrockmeierንና የCarbaughን *Narrative and Identity፡ Studies in Autobiography, Self and Culture* /20001/ይመልከቱ)፡፡ የባህል ጥናት፣ ካለር እንደሚለው፤ እንዲህ ባሉ ደርዝ የለሽ ጉዳዮች እጅጉን ይሳባል፤

> *Work in cultural studies has been particularly attuned to the problematical character of identity and to the multiple ways in which identities are formed, experienced, and transmitted. Particularly important, therefore, has been the study of the unstable cultures and cultural identities that arise for groups* [---] *that may have trouble identifying with the larger culture in which they find themselves – a culture which is itself a shifting ideological construction* (1997, 45-46).

በአንድ ጉዳይ ላይ በተመሠረቱ ጥንድ ምንትነቶች መኃል--ለምሳሌ፣ በወንድነትና በሴትነት መኃል ያለ ዝምድና በኃይል ትስስር ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ ኃይል ሁል ጊዜም በምንትነቶች መኃል ያለን፣ ሚዛን ለመጠበቅ የሚደረግ ትግልን ያመለክታል፡፡ የባህል ጥናት አንዱ ተግባር ይህንን ዓይነቱን ትግል

ማስተንተን ነው፡፡ በመሆኑም በምንትነት ምሥረታ ውስጥ የስበት ማእከሉ ኃይልና የኃይል አሰላለፍ ነው ብለን ማጠቃለል እንችላለን፡፡ ኃይል በአብዛኛው እንደሚታሰበው የፖለቲካ ጣጣ ብቻ አይደለም፡፡ ነገረ ጎሳ፣ ነገረ ፆታ፣ ወዘተ. የኃይል ጣጣ የፈጠራቸው ሐቲቶች ናቸው፡፡ ሌላው ቀርቶ የእኔ ጉዳይ የሆነው ነገረ ወሲብ እንኳ ከዚህ የተለየ ህልውና እንደሌለው ዳኒ ካቫላሮ፣ "*Sexuality is inextricably intertwined with power and power*" (2001, 137) በማለት ታረጋግጣለች፡፡

የባህል ጥናት በተለይ በሥነ ጽሑፍ ጥናት ውስጥ እጅግ ከፍ ያለ ሥፍራ ያገኝ ዘንድ ያስቻሉ በርካታ ምክንያቶችን መጥቀስ ይቻላል፡፡ ከነዚህ ምክንያቶች መካከል ቀዳሚው አዲስ ለሚበቅሉ ድርሰቶች፣ አዳዲስ ለሚፈጠሩ ዘውጎችና በልዩ ልዩ ምክንያቶች በየዘመኑ ለሚቀሰቀሱ የአከያየን ቅጦች ትልቅ ግምት የሚሰጥ በመሆኑ ነው፡፡ ቀደም ድርጌ ለመጠቆም እንደ ሞከርኩት የባህል ጥናቶች ዋነኛ ትኩረት ዘመናዊ የሆኑ የባህል ውጤቶች ናቸው፡፡ ሥነ ጽሑፍም እንደ አንድ የባህል ምርትነቱ አዳዲስ እና ዘመናዊ ገጽታው ትልቅ ትኩረት ይሰጠዋል፡፡ ይህን ደግሞ አንቶኒ ኢስትሆፕ (Antony Easthope)፣ "*Cultural studies must take the contemporary as its point of departure*" ሲል ያጠናክረዋል (1991፣167)፡፡ ሌላው ምክንያት፣ በአንድ ማኅበራዊ-ባህላዊ ዐውድ ውስጥ በልዩ ልዩ ምክንያቶች--ለምሳሌ፣ በቀደመው ዘመን በመደብ፣ በዘር፣ በሙያ፣ ወዘተ. ዛሬ ደግሞ በነገረ ፆታዊና ነገረ ወሲባዊ ምክንያቶች--ተገፍተው የኖሩ ወገኖችና ሰብዓዊ እሴቶቻቸው የሚጠኑባቸው አዳዲስ አንጻሮች እንዲፈጠሩ እድል መስጠቱ ነው (ካለር 1997፣ 45-46) ፡፡ የባህል ጥናት ዛሬን ከማክበሩና ለተገፉት የሚሆን ሥፍራ ከማደላደሉ በተጨማሪ በበይነ ዲሲፕሊናዊነቱ እጅጉን ይታወቃል፡፡ ህልውናውም በሥነ ጽሑፍ፣ ወይም እናስፋውና በኪነ ጥበብ ትምህርትና ምርምር ውስጥ ብቻ የተወሰነ አይደለም፡፡ ለዚህ ነው ብዙውን ጊዜ ከነጠላ ቁጥር ይልቅ በብዙ ቁጥር የባህል ጥናቶች "*cultural studies*" እየተባለ ሲጠራ የሚስተዋለው፡፡

የባህል ጥናት በሚገባባቸው የጥናት መስኮች ውስጥ የሚቀሰቅሳቸውና የሚፈጥራቸው ዲሲፕሊናዊ ጉዳዮች በርካታ ናቸው፡፡ በምላሹም ከየዘለቀበት የጥናት መስክ የሚወርሳቸው እሴቶች ያንኑ ያህላሉ፡፡ ቁም ነገሩ የባህል ጥናት ወደ ሌሎች የጥናት መስኮች መዝለቁ አይደለም፡፡ ፍሬ ነገሩ በዘለቀባቸው መስኮች ውስጥ አዳዲስ ሐቲቶች ይቀሰቀሱ ዘንድ ጫና መፍጠሩ፤ የሥነ ጽሑፍ ጥናትም በምላሹ በእነዚህ፣ በየመስኩ ተቀሰቀሱ ባልናቸው አዳዲስ ሐቲቶች ይገለገል ዘንድ እድል ማግኘቱ ነው፡፡ በሌላ ቋንቋ የባህል ጥናት ለሥነ ጽሑፍ ጥናት አዲስ ዐይንና ኃይል (*insight and power*) መሆኑን መካድ አይቻልም፡፡ ስለዚህ የባህል ጥናት በትችት አንጻርነት (*as a critical perspective*) ፣ እንድም ለበይነ ዲሲፕሊናዊ የሥነ ጽሑፍ ምርምር፣ እንድም፣ በካቫላሮ አገላለጽ ልገልገልና (2001፣ ix) "ለመልከ ብዙ ፍካሬዎች" (*heterogeneous interpretations*) እጅጉን የተመቸ ነው፡፡

ለጥናት የመረጥኳቸውም ድርሰቶች ለዚህ ዓይነቱ “መልከ ብዙ ፍካሬ” የተመቹ እና ከላይ ባነሳሁት የምንትነትና የሃይል አሰላለፍ መንፈስ የተቃኙ ይመስሉኛል፡፡ እነዚህ ድርሰቶች በአንድ በኩል፣ የተገፉ ሰብዓዊ ጉዳዮች የተስተማሰሉባቸው ናቸው፡፡ በሌላ በኩል ከነገረ ወሲብ አንጻር ባህሉ የሚያጸድቃቸውን እሴቶች የሚያራክሱ፣ በእሴቶቹ ላይ ተመሥረተ የሚባለውን ምንትነት “ፋርሽ መሆን” ለማሳየት የሚታገሉም ይመስላሉ፡፡ አንዳንዶቹ እንዲያውም ከብር ተነፍጓቸው የኖሩ ድርጊቶችንና ጉዳዮችን ወደ ተደራጀ እሴትነት ለመለወጥ አጥብቀው ይሠራሉ፡፡ በዚህ አይወሰኑም፤ በእንዲህ ዓይነቱ እሴት ላይ የተመሠረተና ሙሉ ህልውና ያለውን ምንትነት ለመፍጠር ይሞክራሉ፡፡ በመሆኑም ድርሰቶቹ የነገረ ወሲብ ምንትነትና ኃይል ተጠላልፈው በሚፈጥሩት ሐቲት ላይ የተመሠረቱ የሥነ ጽሑፍ ሥራዎች (*literature of sexuality*) ናቸው ብሎ መናገር ይቻላል፡፡በዚህም መሠረት በማስከተል ድርሰቶቹን በወጉ ለማንበብ የሚያስችሉኝን ንድፈ ሐሳባዊና ጽንሰ ሐሳባዊ ጉዳዮች ለማስተዋወቅ እሞክራለሁ፡፡

### 2.1.1. ነገረ ወሲብ፤ አጠቃላይ ዳራ

“ወሲብ” በጥቂቱ ማኅበራዊ፣ ባህላዊ፣ ሥነ ልቡናዊ እና ፖለቲካዊ ገጽታዎች አሉት፡፡ እነዚህ ገጽታዎች ደግሞ በራሣቸው ሠፋፊና ብዙ የተባለባቸው፣ ብዙ የሚባልባቸው ጉዳዮች ናቸውና፣ ሁሉንም አዳርሶ ሁሉንም የሚያግባባ ሐሳብ ማምጣቱ ፈታኝ መሆኑ አይቀርም፡፡ በመሆኑም መሠረታዊ ከሆኑት ጉዳዮች በመነሣት በመጠኑ የሚያግባባ መነሻ ለማበጀት እንሞክር፡፡

ነገረ ወሲብን አብዝቶ በማጥናት የሚታወቀው፣ ጄፍሬይ ዊክስ (Jeffrey Weeks) “*sex*”[6] የሚለው የእግሊዝኛ ቃል፣ በአንድ ጊዜ በርካታ ጉዳዮችን ስለሚያመለክት እጅግ አሻሚ መሆኑን ይገልፃል፡፡ ቀዳሚ ወይም ተለምዷዊ የሆነው የቃሉ አጠቃቀም ግብረካላዊ ጾታዊ ማንነትን--ሴትነትን እና ወንድነትን--፣ ጾታ የሚገልፁ የሰውነት አካላት መኖርን፣ የመራባት ችሎታን፣ እንዲሁም ተለምዷዊ የሆነ የጾታ ግንኙነት ባህርይን የሚገልፅ ነበር (2003፤4)፡፡ ሆኖም ከላይ የተገለፁትን *'sex'* ፍቺዎች ስንፈትሽ የሚታዩ ጉድለቶች ወይም ቁንፅልነቶች አሉ፡፡ ከጾታ መገለጫነት ወይም ከሴትነትና ወንድነት ጋር የተሠጠው ፍቺ የሚገልፀው ተፈጥሯዊ የሆነውን አካላዊ ልዩነት ብቻ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ማኅበራዊ

---

[6] የአማርኛው “ወሲብ” እና “ጾታ”ም ተመሣሣይ ቁንፅልነት ይታይባቸዋል፡፡ ሐሳቦቹ እንደ እንግሊዝኛው ‘sex’ በአንድ ቃል ተወክለው ባይቀርቡም በተናጠል የተሠጣቸው ማኅበራዊ እና መዝገበ ቃላዊ ፍቺ ከእንግሊዝኛው እንብዛም የተለየ ሚባል አይደለም። “ወሲብ” የሚለውን ቃል የአማርኛ መዝገበ ቃላት ሲፈታ፣ “በወንድ እና በሴት መካከል የሚፈፀም ፍትወት፣ ሲጋዊ ስራ፣ ግብረ ስጋ” (1993፤407) ይለዋል፡፡ ግብረ ሥጋ ሚለውን ደግሞ በተመሳሳይ ደስታ ተከለ ወልድ “የሥጋ ግብር፣ ወንድና ሴት የሚሰሩት ጽምረት፣ ሩካቤ” (1962፤ 525) ሲሉ ይፈቱታል፡፡ “ጾታ” ለሚለው ደግሞ “ወገን / የእንስት ወይም የተባዕት/ ” (1993፤583) ሲል ይፈታዋል። በመሆኑም “sex” የሚለውን ቃል እንደ አገባቡ “ወሲብ” ወይም ጾታ እያልኩ እገለገልበታለው።

የሆነውን፣ ሥርዓተ ጾታን (*gender*) እንዲገድፍ ያደርገዋል፡፡ ከዚህም በመነሳት ለሥርዓተፆታ መፈጠር መሠረቱ ተፈጥሯዊ (*biological*) የሆነው ጾታ ነው የሚል አመለካከት እንዲፈጠር ምክንያት ሆኖ ቆይቷል (ዊክስ 2003፣4)፡፡

የጾታ እና የሥርዓተ ጾታ ትስስር ራሱን የቻለ አከራካሪ ነጥብ ሆኖ ለዘመናት የዘለቀ ርዕሰ ጉዳይ ነው፡፡ ቀዳሚ በነበረው አስተሳሰብ በጾታ እና በሥርዓተ ጾታ መካከል ልዩነት አይታይም፡፡ የመጀመሪያው የጾታ ጥናት (*gender study*) በተፈጥሮ ሳይንስ አማካይነት የተደረገ በመሆኑ ተፈጥሯዊ በሆኑት መረጃዎች ላይ በመመሥረት ሁለት ዓይነት ጾታ (ወንድ እና ሴት) ብቻ እንዳለ ይታመን ነበር፡፡ በዚህ እምነት መሠረት ጾታ የማይለዋወጥ እና ሁለንተናዊ ከስተት ነው፡፡ ይህ አመለካከት ግን ከ1960ዎቹ እና ከ1970ዎቹ በኋላ እየተለወጠ ትኩረቱ ከጾታ ወደ ሥርዓተ ጾታ ዞረ ፡፡ በጾታ እና በሥርዓተ ጾታ መካከልም ልዩነት ተበጀ፡፡ በመሆኑም "ጾታ" ተፈጥሯዊ የሆነውን፣ በግልፅ የሚታየውን የወንድነትና የሴትነትን የመራቢያ አካላት የሚወከል ሲሆን፤ ሥርዓተ ጾታ ደግሞ የተባእትነትንና እንስትነትን ማኅበረ ባህላዊ ከፍፍል የሚያመለከት እንደሆነ ጥናቶች ማሳየት ጀመሩ (ሪቻርድሰን ፣ 5)፡፡ ይሁንና አስቀድሜ ለመጠቆም እንደሞከርኩት ይህ ልዩነት ሚዛናዊ ሳይሆን አስገኚቱን ለጾታ የሰጠ ነበር፡፡ በመሆኑም ይሄ አመለካከት ለመለወጥ የተለያዩ ተመራማሪዎች መሞገት ጀመሩ፡፡ አመለካከቱን ከለወጡ የዘርፉ ተመራማሪዎች መካከል ዓቢይ የሆነችውን፣ የጁዲዝ በትለርን (Judith Butler) ሐሳብ በመጥቀስ አስተሳሰቡን ለማብራራት እሞክራለሁ፡፡ እንዲህ ትላለች በትለር፤

> *. . . whatever biological intractability sex appears to have, gender is culturally constructed: hence, gender is neither the causal result of sex nor as seemingly fixed as sex. The unity of the subject is thus already potentially contested by the distinction that permits of gender as a multiple interpretation of sex* (2008, 8).

በበትለር አመለካከት አካላዊ የሆነው ጾታ የፈለገውን ዓይነት ቢሆን ሥርዓተ ጾታ ባህላዊ /ሠው ሠራሽ በመሆኑ እንደፈለገው ተለዋዋጭና ከጾታ እስር ውጪ ነው፡፡ ሲጀመር ተፈጥሯዊ የሆነው "ወንድነት"ና "ሴትነት" ዓይነቱ ሁሌም ሁለት አይደለም፡፡ ሁለት ነው ብንል እንኳ በመኃል ያለው ልዩነት ያለው እንደምናስበው ፍጹማዊ አይደለም (ሌላው ሁሉ ቢቀር ፍናፍንትነትን "*hermaphroditism*" ማሰብ እንችላን)፡፡ ልዩነቱ ፍጹም ነው ብለን ብናምን እንኳን ሥርዓተ ጾታዊ የሆነው ተባእትነት ጾታዊ የሆነውን ወንድነት ወይም ሥርዓተ ጾታዊው እንስትነት ተፈጥሯዊ የሆነውን ሴትነት እንዲገልፅ ብቻ ሆኖ የሚገባ አይደለም፡፡ ቢሆን እና ተፈጥሯዊ የሆነው አካላዊ ሁኔታና ሥርዓተ ጾታው አንዱ አንዱን እንዲገልፅ ሆኖ ሠመረም ቢባል ትላለች በትለር፣ ሥርዓተ ጾታ ሁልጊዜም ሁለት ዓይነት ብቻ ሆኖ የሚኖር፣ ከላይ በጥቅሱ እንደ ተገለፀው የተወሰነ ትርጉም ያለው አይደለም፡፡ በመሆኑም ሥርዓተ ጾታን ከጾታ መሠረት

ውጪ ለብቻው (የራሷን የበትለርን ቋንቋ ልገልግልና) "እንዲንሣፈፍ ስንፈቅድ" ሥርዓተ ጾታዊው ተባእትነት በቀላሉ ተፈጥሯዊ ወንድነትን እና ተባእታዊ አካልን እንደሚገልፅ ሁሉ ተፈጥሯዊ ሴትነትንና እንስታዊ አካልንም ሊገልፅ ይችላል፤ ወይም ደግሞ በተዘዋዋሪ የሴቷ የወንዱን ሊገልፅ ይችላል (ዝኒ ከማሁ፤ 9)::

የአመለካከት ለውጦቹ በዚህ ብቻ የሚያበቁ አልሆኑም:: በዚህ ዘመን በተለይ ጾታን ከተፈጥሮ፣ ሥርዓተ ጾታን ደግሞ ከማኅበረሰብ ጋር አዛምዶ የሚመለከተው ልማድ፣ ጾታ ልክ እንደ ሥርዓተ ጾታ ሁሉ የማኅበረሰብ ውጤት የሚል ሙግት በሚያነሱ ወገኖች ፈተና ላይ ወድቋል:: የሙግቱ መሠረት ተፈጥሯዊው የአካል ልዩነት ከማኅበራዊ ተጽእኖ የጸዳ አይደለም የሚል አስተሳሰብ ነው:: ምክንያቱም፣ እንደ አስተሳሰቡ አራማጆች እምነት አካላዊ የሆነውን ልዩነት ለመበየን እና ትርጉም ለመስጠት ሥርዓተ ጾታውን በሚገባ መረዳት ያስፈልጋልና ነው:: ይህን ሐሳብ የሚያጠናክር አንድ ጥቅስ ላቅርብ፤ "*Its gender that provides the categories of meaning for us to interpret how a body appears to us as 'sexed'. In other words, gender creates sex*" (ሪቻርድሰን፤7) :: ጉዳዩ አስቀድሜ ካነሳሁት የበትለር ሀሳብ ጋር የተሳሰረ ይመስለኛል::ተፈጥሯዊው ጾታ በየትኛውም መልኩ ቢመጣ መገለጫው ካስፈለገም ህልውናው ከሥርአተ ፆታው በሚያገኘው ትርጓሜ ላይ የተንተራሰ ነው ማለት ይቻላል::ከዛም በላይ የጾታን የሁለትዮሽ አስተሳሰብ አመጣጥ መጠየቅ ተገቢ እንደ ሆነ በትለር ትጠቁማለች::ምክንያቱም ሁለቱን ጾታዎች ብቻ እያገነነ፣ ፍጹም የተለያዩ ተቃራኒ ጉዳዮች እንደሆኑ የሚነግረን ሳይንሳዊ "እውነታ" በተለያዩ ሳይንሳዊ ሀቲቶች ለሌሎች ፖለቲካዊና ማህበራዊ ጥቅም ሲባል የተሰራ ቢሆንስ? እንደዚህ ከሆነ ደግሞ ትላለች በትለር ተፈጥሯዊ ብለን ያሰብነው ጾታ እንደ ሥርአተ ጾታው ሁሉ በባህል የተገነባ ይሆናል፤ልዩነት ብለን ያሰብነው የጾታ እና የሥርአተ ጾታ ልዩነት ልዩነት መሆኑ ይቀራል (2008፤10) ::

ሌላው ተያያዥ የሆነው የቃሉ ፍቺ ደግሞ የሚገልፀው ከብዙ ወሲባዊ ተግባሮች መካከል፣ ከመራባት ጋር ተያይዞ የሚፈፀመውን በተቃራኒ ጾታ መፈቃቀድ ላይ የተመሠረተ ሩካቤን "*heterosexuality*" ብቻ ነው:: ይህ ደግሞ ሌሎቹን ወሲባዊ ተራክቦዎችን የገፋ በመሆኑ አድሏዊ ነው ብለው የሚተቹ ወገኖች በርካታ ናቸው:: ከዚህ ጋር በተያያዘ በርካታ ጥያቄዎች ይነሳሉ:: "ወሲብ ከመራባት ጋር ብቻ የግድ መያያዝ ያስፈልገዋል ወይ?" ብለው የሚጠይቁ በርካታ ናቸው:: በተለይ በዚህ ዘመን ዲኮንስትራክሽናዊ በሆነ መንገድ፤ "ከነጭራሹስ ወሲባዊ የሚባለው ተግባር የትኛው ነው?" ብለው የሚጠይቁ ወገኖች እየገነኑ መጥተዋል:: ከእነዚህ ጥያቄዎች መኃል የመጀመሪያውን ብናነሳ እንኳ የሰው ልጅ ሩካቤን ለርቢ ብቻ እንደማይፈፅም የሚያሳምኑ በርካታ ክርክሮች ይቀርባሉ:: ክርክሮቹን ጠቅለሎ እንዲያሳይልኝ ከሸዋርትዝ (Schwartz) የወሰድኩትን ሐሳብ ልጥቀስ፤

*It should be obvious, however, the people engage in sex even when they do not intend to reproduce. They have sex for fun, as a way to communicate their feelings to each other. As a way to satisfy their egos, and for any number of other reasons relation to the way they see themselves and interact with others* (2000, 2) .

ከጥቅሱ መረዳት እንደምንችለው ሰው በወሲብ አማካይነት እጅግ በርካታ ልቡናዊና አካላዊ ተግባራትን ይፈጽማል፡፡ ከእርባታና ከአካዊ እርካታ በተጨማሪ በወሲብ ልዩ ልዩ ስሜቶች፣ አመለካከቶችና እምነቶች ይገለጣሉ፡፡ በመሆኑም ወሲባዊ ግንኙነቶችን ሁሉ ከመራባት ጋር ብቻ አስቦ መበየን እንደስህተት ይቆጠራል፡፡

እንደ ታምሲን ዊልተን (Tamsin Wilton) እምነት ደግሞ የወሲብ ትርጉም በባህል፣ በዘመንና በታሪካዊ ሁኔታዎች የሚወሰን ነው፡፡ ከአንዱ ትውልድ ሌላኛው፣ በዛው ባህልና ዘመን ውስጥ በሚኖሩ ንዑሳን ባህሎች እና ቡድኖች፤ እንዲሁም እንደየግለሡቡ የሥነ ልቡናዊ ዘይቤ ዓይነት ሊለያይ ይችላል (2004፤ 55)፡፡ ይህን ሐሳብ ዊከስ ሲያጠናክር ፐሎመርን ጠቅሶ እንደሚከተለው ይላል፡-

> *'Who restrictions' are concerned with the gender of the partners, the species, age, kin ,race, caste or class which limit whom we may take as partners. 'How restrictions' have to do with the organs that we use, the orifices we may enter, the manner of sexual involvement and sexual intercourse; what we may touch, when we may touch, with what frequency , and so on* (2004, 21) .

ከጥቅሱ መረዳት እንደሚቻለው ስለ ወሲባዊ ግንኙነት ሲታሰብ የሚታሰበው ስለ ግለሡብ ብቻ አይደለም፡፡ በአጠቃላይ ወሲባዊ ተግባሩ ላይ የማኅበረሰብ እና የባህል እጁ ረዥም የሚባል ዓይነት ነው፡፡ "ፍትወታዊ" *'erotic'* የሆነውን ጉዳይ የሚዘነጋ ባህል የለም፡፡ እያንዳንዱ ባህል ከማን እና እንዴት ወሲባዊ ተግባር መፈፀም እንዳለበት ይወስናል፡፡ ውሳኔው ተጓዳኝን ከመምረጥ አንስቶ አጠቃላይ የተግባር ሂደት ማካሄጃ ሥርዓት እስከ መስጠት ይዘልቃል፡፡ ይህም ሁለንተናዊ የሆነ መስፈሪያ እና መዳኛ እንዳይኖር ምክንያት ይሆናል፡፡

ጠቅለል ባለመልኩ የዚህን ጉዳይ አጨቃጫቂነትና ዋላይነት ዊልተን ስትገልፅ "ማንኛውም ድርጊት ወይም ሁነት፤ ፈፃሚዎቹ 'ነው' እስካሉ ድረስ ወሲብ ወይም ወሲባዊ ተግባር ነው" እስከማለት የሚደርስ ነው (2004፤55)፡፡ ሆኖም ይህ ሪሡ ጥያቄን የሚያስነሣ ጉዳይ ነው፡፡ በዚህ አቋም ተቺዎች አመለካከት ወሲብን እንደየ ግለሰቡ የምናየው ከሆነ ቢጋራ የሚፈፀሙና የተለያዩ ግለሡቦችን የሚያሣትፈውን አንድ ተግባር እንደየግለሡቦቹ ብያኔ መስጠት ሊኖርብን ነው፡፡ ለአንዱ ወሲብ የሆነው ተግባር ደግሞ ለሌላው የሀይል ጥቃት፤ መደፈር፣ ገደቡን የጣሰ ተግባር፣ ወዘተ ተደርጎ ሊታሠብ

ይችላል፡፡ ዊክስ ይሄን ሀሳብ ሲያጠናክረው እንዲህ ይላል፡፡ "*... the very mobility of sexuality, its chameleon – like ability to take many guises and forms, so that what for one might be a source of warmth and attraction, for another might be one of fear and hate, ...*" (2003, 2).

ከዚህም በተጨማሪ "ለድርጊቱ ምንነት ወሳኞቹ ፈጻሚዎቹ ይሆናሉ" የሚለው አመለካከት ተቺዎች፣ ይህ አቋም በግለሠብ ደረጃ መፈፀም ለሚችሉ እንደ "ግብራውኖን" (*masturbation*) ላሉ ወሲቦች የተሻለ ብያኔ ቢመስልም የራሱ የሆኑ ውስብስብ ጉዳዮች አሉት ይላሉ፡፡ ምክንያቱም የግለሰቡ ነገረ ወሲብ የተሠራባቸው ተፈጥሯዊ፣ ማኅበራዊና ሥነ ልቡናዊ ጉዳዮች ለማንፀሪያነት መጠራታቸው አይቀርምና፡፡ በመሆኑም ጉዳዩ የግለሠብ ከመሆን ይዘላል (ዝኒ ከማሁ)፡፡

ልክ እንደ '*Sex*' ሁሉ '*Sexuality*'የሚለውም የእንግሊዝኛ ቃል አወዛጋቢነት የሚታይበት ነው፡፡ በተነፃፃሪ ዘመናዊ ሊባል የሚችለው ይህ ቃል በ1970ዎቹ መጀመሪያ በተለያዩ ፅሁፎች ውስጥ ሩካቤን (*having sex*) ለመግለፅ አገልግሎት ላይ ይውል ነበር፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ አንድ ሰው ወሲብ የማይፈፅም ከሆነ ወሲባዊ ፍጡር አይደለም ወይም ነገረ ወሲብ የለውም የሚል እንድምታን አብሮ የያዘ ነበር፡፡ ይህ ሐሳብ ግን እየቆየ ውድቅ ሆኗል፡፡ ምክንያቱም አንድ ሠው ለረዥም ጊዜያት ምናልባትም በአጠቃላይ የሕይወት ዘመኑ ወሲብን ሣይፈፅም ሊቆይ ይችላል፣ ሆኖም ያንን ሠው ወሲባዊ ፍጡር ከመሆን የሚያግደው አይደለም፡፡ በቀጣይም ከ18ኛው ክፍለ ዘመን መገባደጃ እስከ 19ኛው ክፍለ ዘመን መባቻ በአውሮፓ እና በአሜሪካ የነገረ ሰብእ፣ የተፈጥሮ እና ማኅበራዊ ሳይንሶች ከዚህ ቀደም ታይቶ በማይታወቅ መልኩ የነገረ ወሲብ ጥናቶችን በሰፊው ማካሔድ ጀመሩ፡፡ በመሆኑም ቃሉ ከተወሰነ ፍቺ በተጨማሪ ሰፊ ጉዳዮችን በመያዝ ግልጋሎት ላይ ዋለ (ዳንፊ፣ 2000፣ 4)፡፡

ብዙዎች ከተለያየ አቅጣጫ የሚመነዝሩት እና የሚበይኑት ዘመናዊው የነገረ ወሲብ እሳቤ ልቅ እና ለመሰብሰብ አስቸጋሪ የሚባል ዓይነት ነው፡፡ ይሁንና የሰርክ አጠቃቀሙ ሦስት ዓበይት ጉዳዮችን ጠቅልሎ የሚይዝ ነው-- "ኤሮቲካዊ" ፍትወቶችን (*erotic desires*)፣ "ኤሮቲካዊ" ከንዋኔዎችን እና "ኤሮቲካዊ" ምንትነቶችን፡፡ ሆኖም ይህ ሐሳብ ራሱ አከራካሪ ጉዳይ ነው፡፡ ምክንያቱም "ኤሮቲካዊ" ተብሎ የሚታሰበው ጉዳይ በራሱ ወጥ ምላሽ የለውም፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ነገረ ወሲብን አስቸጋሪ የሚያደርገው ጉዳይ ከወሲባዊ ስሜትና ግንኙነት በዘለለ ከብዙ ጠንከር ካሉ የሰው ልጅ ስሜቶችና ምንትነቶች በጥብቅ የተሳሰረ በመሆኑ ነው፡፡

> *The strong emotions it undoubtedly arouses gives to the world of sexuality a seismic sensitivity making it transmission belt for a wide variety of needs and desires; for love and anger, tenderness and aggression, intimacy and*

*adventure, romance and predatoriness , pleasure and pain, empathy and power (ዝኔ ከማሁ፤1) .*

ከጥቅሡ መመልከት እንደሚቻለው በሠው ልጅ ሕይወትና ማንነት ውስጥ ትልቅ ሚና ያላቸው ስሜቶች ሁሉ በአብዛኛው በነገረ ወሲብ ውስጥ ይገለጣሉ፡፡ ከዚያም በላይ እነዚህ ስሜቶች አንዳንዶቹ በፍፁም ተቃርኖ የቆሙ እንዲሁ በውርድ ስንመለከታቸው እርስ በርሳቸው የሚጠፋፉ የሚመስሉ፣ ዳሩ ግን የሚቃለጡ (*fussion of opposites*) ጭምር ናቸው፡፡ ስለሆነም ድንበር አበጅቶ እንደ አንድ ጉዳይ ለመመልከት እና ለመበየን አስቸጋሪ ይሆናል፡፡

በጥቅሉ ብዙ የተወሣሠበና አከራካሪ ጉዳዮች ቢኖሩትም እንደ መነሻ ብዙዎች ነገረ ወሲብን ለመበየን ሲሞክሩ የሚጠቅሷቸው ተደጋጋሚ ሐሳቦቸ አሉ፡፡ ተፈጥሯዊ የሆነውን የጾታ ልዩነት (*genes, cromosomes, hormon and …*)፣ ወሲባዊ ባህሕርያትን (*sexual behavior*) (እንዴት ወሲባዊ ስሜታችንን እንገልፃለን)፣ ወሲባዊ ስሜትን (*sexual feeling*)፣ ወሲባዊ ዝንባሌን (*sexual orientation*)፣ ወሲባዊ ፍትወትን (*sexual desire*)፣ ወሲባዊ ምንትነት (*sexual identity*) እና ወሲባዊ ተራክቦን (*sexual intercourse*) ማንሳት እንችላለን፡፡ እነዚህ ጉዳዮች ደግሞ በተናጠል ሰፊና ውስብስብ በመሆናቸው በዚህ ጥናት ሁሉንም ለመመልከት መሞከሩ የማይታሰብ ነው፡፡ ስለዚህ ቀናው መንገድ እስካሁን ሳደርግ እንደቆየሁት፣ ለጥናት የተመረጡትን ድርሰቶች የሚመለከቱትን ጽንሰ ሐሳቦች ብቻ ለይቶ ማስተዋወቅ ነው፡፡

አብዛኛዎቹ ነገረ ወሲብ ላይ የሚደረጉ ጥናቶች የሚከተሏቸው አቅጣጫዎችና ትኩረት የሚያደርጉባቸው ርዕሠ ጉዳዮች ይለያያሉ፡፡ ሆኖም አጠቃላይ የነገረ ወሲብ ምንጭ ብለው የሚከተሉት አቅጣጫ አጠቃላይ መንገዳቸውን ሲቃኝ ይታያል፡፡ ለነገረ ወሲብ ምንጭነት ወይም ፈጣሪነት ደግሞ ሁለት ምክንያቶች በተለይ ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ተፈጥሮ እና ማኅበረሰብ፡፡ ተፈጥሮን መሠረት ያደረገው አቅጣጫ "*Essentialism*" በመባል ሚታወቅ ሲሆን ማኅበራዊ ሕይወትን መሰረት ያደረገው ደግሞ፣ "*social constructionism*" በመባል ይታወቃል፡፡ እንደሚከተሏቸው አቅጣጫዎች ተመራማሪዎቹ "ተፈጥሯውያን" (*essentialists*) እና "ማኅበራዊ ግንባታውያን" (*constructionists*) በመባል ይጠራሉ፡፡

**"ተፈጥሯውያን"**፡- ተፈጥሯውያን ከወሲብ ጋር ለሚያያዙ ጉዳዮች ሁሉ ተፈጥሯዊ ፍቺ ወይም ማስረጃ ለማምጣት የሚሞክሩ ናቸው፡፡ ዊክስ፣ ሲንገር የተባለውን አጥኚ ጠቅሶ እንደሚያስረዳው፣ በተፈጥሯውያን አመለካከት ነገረ ወሲብን አስመልከተው ለሚነሱ ጥያቄዎች በሙሉ ምላሽ የሚሆን በተፈጥሮ በራሷ የተበጀ ሁለንተናዊ ሥርዓት አለ (2004፤7)፡፡ ይህ ሥርዓት፣ በሰው ልጅ ሥነ ሕይወታዊ አላባዎች፣ ለምሳሌ፣ በደመ ነፍስ፣ በጂን፣ በሆርሞኖች፣ ወዘተ. ኅብረትና በኢንቁ ልቡና እገዛ የተበጀ

ነው፡፡ ለምሳሌ በዚህ ዘመን እየገነነ በመጣው "የጂን ንድፈ ሐሳብ" አቀንቃኞች እምነት የሰው ልጅ ወሲባዊ ባሕርይ ብቻ ሳይሆን፣ ከተፈጥሮ ተቃርነው የሚነሱት ግለሰባዊ፣ ማኅበራዊና ባህላዊ ህልውናዎቹ ጭምር የጂን ተገርዎች ናቸው፡፡ ዊልተን ይህንን አቋም በተከታዩ መንገድ ጠቅለል አድርጋ ልታሳየን ትሞክራለች፤ *"There is, at present, no aspect of social or individual life that is not claimed for the genes…. Every physical, psychical or social ill, every perturbation of the body corporeal or politic, is said to be genetic"* (20041, 9).

የዚህ አቋም አራማጆች የጂን ንድፈ ሐሳብ ምሁራን ብቻ አይደሉም፡፡ ወሲብን ከሞት ጋር አቆራኝተው፣ ሁለቱ ተፈጥሯዊ ከስተቶች--ወሲብና ሞት--ከደመነፍስ መቃለጥ (*fusion of instinct*) የሚመነጩ፣ የልቡናዊ ኃይል (*psychic energy*) መንታ ገፅ ናቸው ብሎ የሚያምነው ፍሮይድም (1953፤ 123–245) ጎራው ይሄው ነው፡፡ ነገረ ወሲብን ከጉልምስና ጋር አቆራኝቶ የሚያየውን ነባር ልማድ የሻሩት የፍሮይድ ንድፈ ሐሳቦች፣ መልከ ብዙ ፍትወቶች፣ ጨከን ካልን ወሲባዊ "ከንውኖቹ" ጭምር፣ ከሰው ልጅ ጋር በማሕጸን ውስጥ አብረው ተጸንሰው አብረውት እንደሚያድጉ ያስተምራሉ፡፡ እነዚህ ደመነፍሳዊ ከስተቶች በባህል ጫና ተጨቁነውና ተደብቀው ይኖሩ፣ አልፎ አልፎም መልካቸውን ግብራቸውን እየቀየሩ ይገለጡ እንደሆን ነው እንጂ በየትኛውም ሰው ሰራሽ መንገድ ሊጠፉ አይችሉም፡፡

**ማኅበራዊ ግንባታውያን፡-**እነዚህ ወገኖች ከተፈጥሯውያን በተቃራኒ የሆነ አቋም በመያዝ የሰው ልጅን በተመለከተ ለሚደረግ ጥናት ማኅበርዊ እና ባህላዊ ምላሽ ፈላጊዎች ናችው፡፡ የሰውን ልጅ በጂን ኃይልና ፈቃድ ወሲብን እንደተሞላ "ማሽን"—"*a selfish machine, programmed to do what ever is best for his genes as a whole*" (ዳውኪን፣ በዊክስ የተጠቀሰ፣ ገጽ 45) አድርጎ የሚቆጥረውን አመለካከት የሚጻረረው ሁለተኛው ወገን፣ ወሲባዊ ብቃት ከተፈጥሮ በደም የሚወረስ ይሁን እንጂ፣ ወሲብ "በትክክለኛ" ቅርፁና ፍቺው የሚከሰተው በባህል ተሞርዶና ተስተካክሎ ሲያልፍ ብቻ ነው የሚል አቋም ያራምዳል፡፡ ለማኅበራዊ ግንባታውያን ለነገረ ወሲብ ህልውና መሠረቶቹ ባህልና ማኅበረሰብ ናቸው፡፡ ወሲብ፣ የሰው ልጅ ያስፈልገኛል ሲል የሚሠራው፣ ካላስፈለገው የሚያቆመው፣ ካልተመቸው ቸል የሚለው "ፈጠራ" ነው (ዊክስ "*a fictional unity*" ሲል ይጠራዋል /ገጽ፣ 6/)፡፡ ፈጠራ ሲባል ደግሞ የባህል ብሎም የራሡ የማኅበረሡብ ፈጣሪና መሣሪያ ቋንቋ እንዲሁም ሐቲት ትልቁን ሚና ይጫወታሉ፡፡ ነገረ ወሲብ በመሠረቱ ከሌሎች ጋር በሚኖረን መስተጋብር የሚፈጠር ነው፡፡ ይህ ዓይነቱ መስተጋብር ደግሞ ቀደም አድርጌ ለማሳየት እንደሞከርኩት በባህሉ ውስጥ ባለ የኃይል አሰላለፍና ሐቲት ምንነት ከሚመሠረትባቸውና ከሚገለጽባቸው የባህል ውጤቶች በሚመነጭ ሐቲት ይወሰናል፡፡ ማኅበራዊ ግባታውያን እምነት እንደ ፍትወት ወሲብ (የወሲብ ፈቃድ፣ ምርጫና ዝንባሌ) ያሉ የነገ ወሲብ ጣጣዎች በዚህ ዓይነቱ ሐቲት ላይ የሚመሠረቱ ናቸው፡፡ ይህ ሁሉ ለማከናወን ቁልፉ ጉዳይ ቋንቋ

መሆኑን እነዚሁ ወገኖች ያስረዳሉ፡፡ የነገረ ወሲብ መሠረት ነው ያልነው ሐቲት ራሱ ከተለየዩ ዐውዶች በሚቀዱ ቋንቋዎች ጥምረት የሚበጅ ነው፡፡ ዊክስ ከቋንቋ ዐውዶቹ መኃል በሕግ ደረጃ ተፅፈው አልያም አብሮ በመኖር በስምምነት የተያዙ ደንቦችና ስምምነቶች፣ ልዩ ልዩ የዕውቀት ዘርፎች፣ ማኅበራዊ ሥርዓቶች፣ ከብረ በዓሎች፣ የኪነ ጥበብ ውጤቶች ዓበይቱ እንደሆኑ ያስረዳል (2003፣8)፡፡ እነዚህ የቋንቋ ዐውዶች ለነገረ ወሲብ ግንባታም ይሁን ፍቺና ትርጓሜ የየራሣቸው አስተዋጽኦ አላቸው፡፡

ቀደም አድርጌ ለማሳየት እንደሞከርኩት ምንትነት የርዕዮተ ዓለም ተገገር ነው፡፡ ምንትነት ሁሌም "እኔ/እኛ"ን ከ"ሌሎች" (*the Others*) ጋ በትይዩ አቃርኖ ያመጣል፡፡ በዚህ ውስጥ መሠረታው ነጥብ፣ "ሌሎች"የምንላቸው ወገኖች ሁሌም በተቃርኖ እራሳችን የምናገዝፍባቸው ብቻ ሳይሆኑ በትይዩ እራሣችንን የምንቀርፅባቸው ጭምር መሆናቸውን ማጤን ነው፡፡ በወሲባዊ ምንትነትም ውስጥ ይህ ዓይነቱ "ሌላነት" የላቀ ሚና እንዳለው ማኅበራዊ ግንባታውያን ያምናሉ፡፡ ተከታዩ የማርችባንክ (Marchbank) ሐሳብ ይህንን አመለካከት ተጨባጭ የሚያደርግልን ይመስለኛል፤ "*We are all encouraged to measure our sexual identity and sexual behavior against a politically and popularly supported ideal and images of this ideal predominate in cultural representation*" (2007,255)፡፡ የእነዚህን ገኖን "እርእያዎች" (በዊልተን አገላለጽ ልገልገልና፣ "*significant others*") ሌላነት በአንድ በኩል፣ በመኃላችን ካለ የዘመን፣ የባህል፣ የአኗኗር ዘይቤና ደረጃ ልዩነት ይመነጫል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በዓለማቱ ልዩነት ላይ ይመሠረታል፤ አውናዊ/ምናባዊ፣ ገቢራዊ/ልብ ወለዳዊ እየተባለ፡፡ እርእያዎቹ ራሳቸው እንደትልቅ ትዕምርት የሚቆሙ ብቻ ሳይሆኑ የምንትነቱን ፍቺ ጭምር የሚያቀብሉ ናቸው፡፡ ዊልተን እንደምታስረዳው (2004፣ 8)፣ ይህ ማለት፣ በሌላ ቋንቋ በምንትነታቸው ምንትነታችንን ይቀርጻሉ፣ ይገልጻሉ፤ በህልውናቸው ህልውናችንን ይተረጉማሉ ማለት ነው፡፡

ልከ እንደተፈጥሯውያኑ እሳቢዎች ሁሉ በማኅበራውያኑ ዘንድም እስከ ጽንፍ ተጉዘው የነገረ ወሲብን ህልውና ባህላዊና ማኅበራዊ ብቻ የሚያደርጉ፤ በዚህም ተፈጥሮን ከቁጥር የማይከቱ ወገኖች አሉባቸው፡፡ በመሆኑም የነገረ ወሲብ ጥናታቸውን ሁለንተናዊ ከማድረግ ይልቅ ስፋቱንና ዋላይነቱን በባህልና በታሪካዊ ሁኔታው ውስጥ ብቻ ለማጤን ይሞክራሉ፡፡ ይህ ዓይነቱ ጽንፈኝነት በብዙ ተመራማሪዎች ዘንድ ትችት ይሰነዘርበታል (ለምሳሌ፣ ቶኒ ፐርቪስን /Tony Purvis/ 2006፣ 437/ ይመልከቱ)፡፡ በብዙዎች እምነት የተሻለው አማራጭ "ወሲብን" የተፈጥሮና የባህል ድምር ውጤት አድርጎ መውሰዱ ነው፡፡ እኔም በዚሁ መንፈስ እቀጥላለሁ፡፡

ደጋግሜ ለመጠቆም እንደሞከርኩት፣ ለጥናት የመረጥኳቸው ድርሰቶች በአመዛኙ ኢ-ተለምዷዊ ፍትወት (*non-normative sexual desire*) ባህል የሚያነውራቸውን፣ ሃይማኖት የሚያወግዛቸውን፣

እንደ ማኅበሩ ሁኔታ ሕግ ጭምር የሚወነጅላቸውን፣ በጥቅሉ ከፍንገጣ የሚቆጠሩትን ወሲባዊ መፈቃቀዶች አቅፈው ይይዛሉ። እነዚህ ጉዳዮች አንድም፣ የባህል ጥናቶች የሚያተኩሩባቸው የነገረ ወሲብ ማቀንቀኛዎች ናቸው። አንድም ደግሞ ለጥናት የመረጥኳቸውን ድርሰቶች ለማስተንተን የተመቹ ናቸው። ምንም እንኳን ዝርዝር የሆኑት በነዚህ ድርሰቶች ውስጥ ገነው የታዩኝ ወሲባዊ ፍንገጣዎች በቀጣዩ ማእራፍ ከትንተናዩ ጋር ተሰናስነው የሚመጡ ቢሆንም የጥቅል ማደሪያና መጠሪያቸው የሆነውን ወሲባዊ ፍንገጣን በአጭሩ አስከትዬ ለማስተዋወቅ እሞክራለሁ።

### 2.1.1.1. ወሲባዊ ፍንገጣ

ወሲባዊ ፍንገጣ (*sexual perversion*) የኢ-ተለምዷዊ ፍትወቶች ሁሉ የጋራ ባሕርይ ነው። የላቲን ቋንቋ ቢቃሉ ምንጭነት ተዘውትሮ ይጠቀሳል፤ "*Pervertere*" (*to pervert*) "ወደ ኋላ መዞር" (*to turn around*) ወይም "ከላይ ወደታች መገልበጥ" (*to turn up side down*) የሚል ፍቺ አለው።[7] ቃሉ አብዝቶ ግልጋሎት ላይ የሚውልበት ዐውድ ወግ የሚጠብቅበት፣ ልማድ የሚገንበት ማኅበረ-ሃይማኖታዊው ዐውድ ሲሆን፣ በመቀጠል ህክምና በፍቺ አስፍቶት ጭምር ከወሲብ ጋር የተገናኙ እንግዳ ባሕርያትን ለመጥሪያነት ግልጋሎት ላይ አውሎታል። በዚህ ደረጃም ቢሆን ቃሉ ከነባር ማኅበራዊና ሃይማታዊ እሴቶቹ መላቀቅ የቻለ አይመስልም። በዚህም ህክምና ከህግ ጋር ተቆራኝቶ በፈጠረው ዐውድ (*medico-legal context*) ቃሉ እንግዳ፣ ከተለምዶ ለወጣ፣ እንደ ስህተትና ሕገ ወጥ ለሚቆጠር ወሲባዊ ባሕርይ መጠሪያነት ይውል ጀመር። እነዚህ የተለያዩ እሴቶች የተጫኗቸው የቃሉ ፍቺዎች እንዳሉ ሆነው፣ በጥቅሉ ግን "*perversion*" "ሌላ የመሆንን" ("*the other being*") ሁኔታ የሚገልጽ ቃል ነው (ኖቡስና ዳውኒንግ 2006፣ 5-7)። "ሌላነቱ" በጥቅሉ ማኅበረ-ልቡናዊ-ወሲባዊ (*Psycho-social-sexual*) የሆነውን የሰው ልጆች ሕይወት ይመለከታል።

ወሲባዊ ፍንገጣን በስፋት ካጠኑ ተመራማሪዎች መካከል ዓቢዩ ፍሮይድ ነው። ለጉዳዩ ባለው እመለካከት ይህ ሰው ከዘመነኞቹ ይለያል። ፍሮይድ ወሲባዊ ፍንገጣን ለመበየን የሚሞክረው ዓላማ (*aim*) እና "ኦብጀክት" ላይ ተመሥርቶ ነው። በዚህም መሠረት፣ ወሲባዊ ፍንገጣ የሚባለው የትኛውም ወሲባዊ ከንውን፣ አንድም አካላዊ (*anatomical*) በሆነ ፍቺው ለወሲባዊ ግንኙነት ከተፈጠሩት የሠውነት ከፍሎች ውጪ የወጣ /ያለፈ ሲሆን፤ አንድም ደግሞ ለ"ዋናው" ድርጊት እንደ መንደርደሪያ ከሚያገለግሉ ተግባራት--መንካት፣ ማየት፣ መሳም፣ ወዘተ.--ጋር የሚኖር ግንኙነት ከተለመደው በላይ ሲጠብቅ ወይም

---

[7] "ፍንገጣ" "ፈነጠ" ከሚለው ግስ የረባ ሲሆን ርባታውን ደስታ ተክለ ወልድ ሲደነግጉ እንዲህ ይላሉ፤ "ፈነጠ ፤ፈነረ፤ወጣ፤ገጠጠ የድንጋይ የብረት-አፈንጋጭ ያፈነጠ የሚያፈነግጥ" (ገጽ 1304)።

ሲረዝም ነው (1905፣ 1476)፡፡ ፍሮይድ ነባር ተመራማሪዎች ወሲባዊ ፍንገጣን እንደ በሽታ መመልከታቸውን ይተቻል፡፡ ለዚህም ምክንያቱን ሲያስረዳ እንደሚከተለው ይላል፡-

> *"No healthy person; it appears, can fail to make some addition that might be called perverse to the normal sexual aim; and the universality of this finding is in itself enough to show how inappropriate it is to use the word perversion as a term of reproach"* (ዝኒ ከማሁ ፣ 1486)፡፡

በፍሮይድ እምነት፣ ፍንገጣ በመጠን ይለያይ እንጂ፣ ተለምዷዊ ወይም "ጤነኛ" በምንለው በየትኛውም ወሲባዊ ግንኙነት ውስጥ ሊከሰት የሚችል ሰብዓዊ ጉዳይ ነው፡፡ ለምሳሌ፣ እንደ መሣም፣ ማየት እና መንካት ያሉ ቅድመ ወሲባዊ ዓላማዎች (*preliminary sexual aims*) እና ወሲባዊ ተጓዳኝ (*sexual object*) በራሣቸው የሚፈጥሩት እርካታ ይኑር እንጂ፣ ወደ ዓቢዩ ዓላማ፣ ማለትም በመራቢያ አካላት ወደሚፈፀም ሩካቤ መንደርደሪያ ከንዋኔዎች ናቸው፡፡ ሆኖም እነዚህ ከንዋኔዎች በተለያዩ ምክንያቶች ቢዘገዩ እና ወደ ዋናው ግብ ማድረሣቸውን ትተው ራሣቸውን ግብ ቢያደርጉ ፍንገጣ የሚሆኑበት ሁኔታ ሠፊ ነው፡፡ ይህ ዓይነቱ ሁኔታ ደግሞ በየትኛቸውም ሰው "ጤናማ" የወሲብ ግንኙነት ውስጥ ሊከሰት ይችላል፡፡ ይህ ብቻ አይደለም፡፡ በፍሮይድ እምነት፣ እንደ "ግብረ ሰዶም" "ግብረ-ምኖን" (*incest*) ያሉ "ገናን" ፍንገጣዎች በሰው ልጅ ነገረ ወሲባዊ ህልውና ውስጥ ተፈጥሯዊና ሁለንተናዊ የባሕሪ ከስተቶች ናቸው፡፡ ነገር ግን፣ ባሕርያቱ ከልጅነት ወደ አውቀት በሚደረግ ሽግግር ባህል በሚባለው ገደብ አማካይነት እየተገሩ፣ እየተሰወሩ፣ ቅርጻቸውን እየቀየሩ ይሄዳሉ፤ይህን ጉዳይ ፍሮይድ በሚከተለው መልኩ ይገልጸዋል፡-

> *"Perversion is an original and universal disposition of the human sexual instinct and that normal sexual behavior is developed out of it as a result of organic changes and psychical inhibitions occurring in the course of maturation; we hoped to be able to show the presence of this original disposition in childhood"* (1905,1542).

"ወሲባዊ ፍንገጣ" ለሰው ልጅ ተፈጥሯዊ ባሕርይ ነው ብሎ ለሚያምነው ፍሮይድ፣ ግምትን የሚፈጥረው ጉዳይ ባሕርይ ተገርተው፣ ተሰልተው፣ አዲስ ቅርጽ መያዛቸው ተዘንግቶ እንደ እንግዳ፣ እንደአዲስ መጥ፣ እንደ ኢ-ተለምዷዊና ኢ-ተፈጥሯዊ መቆጠራቸው ነው፡፡ በመሆኑም ወሲባዊ ፍንገጣን እንደ አእምሮ ህመም ወይም እንደ ባሕርይ መዛነፍ የሚቆጥረውን ነባር ባህላዊም ይሁን ሳይንሳዊ ልማድ ይተቻል፡፡

የፍሮይድን አስተሳሰብ ተከትለው የሚያቀነቅኑ የመኖራቸውን ያህል ሞጋቾችም አልጠፉም፡፡ ሙግቱ የሚመጣው ከፍካሬ ልቡና ውጪ ካሉ የሥነ ልቡና ትምህርት ቤቶች ብቻ አይደለም፡፡ ጥቂት

በማይባሉ፣ በተለይ በክሊኒካዊ ምርምር ላይ ለተጠመዱ ፈካርያነ ልቡና የፍሮይድ ሙግቶች ሳይንሳዊ መሠረት የሌላው ምናብ ሠራሽ መላ ምት ነው፡፡ ምክንያቱም ንድፈ ሐሳቦቹ ከሳይንሳዊ ግኝቶች ይልቅ ለማኅበራዊ እሴቶች የተጋነነ ሥፍራ የሰጡ፣ ወሲባዊ ፍንገጣን ከልማድ መነጽር ውጪ በራሱ በነገሩ ተፈጥሮ አንጻር መመልከት የተሳናቸው ናቸው፡፡ ልማዳዊውን ወሲባዊ ባህሪ እንደመመዘኛ ወስዶ፣ የባህልን ጉዳይ ከግምት ውስጥ ከቶ የሠው ልጆችን ወሲባዊ ሕይወት የሚዳኝ ከሆነ ህክምናው ራሱ ከጤንነት አንፃር መፍትሄን ከማቀበል ይልቅ ተለምዷዊነትን እንደሚያስተዋውቅ እንደ ማኅበራዊ ተቋም ይቆጠራል፡፡ ልማዳዊው ወሲባዊ ሕይወት የራሱ የሆነ ልክ ብሎ ያስቀመጣቸው የቢሆን (*ideal* ) የስምምነት ስርአቶች አሉት፡፡ በመሆኑም ልማዳዊውን መንገድ ስንከተል ይላሉ እነዚህ ተቺዎች፣ አጠቃላይ የሰው ልጆችን ነገረ ወሲብ መገለጫ ተመሳሳይ መሆን አለበት ብለን በማመን ለወሲባዊ ደስታና ግንኙነት ገደብ እናበጃለን ፡፡ በመሆኑም እንደነሱ አመለካከት ከልማድ ድጋፍና ማንፀሪያነት ውጪ የሆነ ሣይንሣዊ "የጤንነት" እና የልክነት መለኪያ ማበጀት ይገባል (ኖበሰ 2006 ፣19)፡፡ ሌላው በፍሮይድ ላይ የሚሰነዘር ትችት፣ ከጉዳዩ አንጻር ለሴቶች ትኩረት በመንፈጉም በዚህ ዘመን በሚደረጉ የነገረ ወሲብ ጥናቶች ውስጥ በተደጋጋሚ ይወቀሳል፡፡[8] ይህ ሀሳብ በተለይ ከወሲባዊ ፍንገጣ ጋር የሚደረጉ የዘርፉ ጥናቶችና ተመራማሪዎች ላይ የሚታይ ችግር ነው፡፡

ጥናቶች እንደሚያመለክቱት ብዙ ማኅበረሰብ ከተለምዷዊው የወንድና የሴት ወሲባዊ ግንኙነት ውጪ የሚገኝ የትኛውንም አዝማሚያ በጥርጣሬ ይመለከታል፡፡ በዚህም ምክንያት ባመዛኙ አዝማሚያውን በአንድ በኩል፣ ከአፈንጋጭነት ቆጥሮ ያነውራል አልያም ይወነጅላል፤ በሌላ በኩል ደግሞ ከጤና ማጣት ቆጥሮ ህክምናን ያፈላልጋል ወይንም ገለል፣ ገሸሽ ያደርጋል፡፡ ማኅበራዊው የወሲብ ልማድ (*Sexual tradition*) በመሠረታዊነት ለወሲብ ያለው አመለካከት በሁለት ቅኝቶች የሚገዛ ነው፡፡ የመጀመሪያው ቅኝት፣ ወሲብ በመሠረቱ አደገኛ ነው ብሎ የሚያስብ ነው፡፡ ወሲብ "በትክክለኛ" መንገድ ተገርቶ፣ ልጅ በሚገኝበት የጋብቻ ስርአት ሲታነጽ ተቀባይነት ይኖረዋል ብሎ ያምናል፡፡ ሁለተኛው ቅኝት ወሲብ በመሠረቱ "ጥሩ"ና "ጤነኛ" ሰብዓዊ ባሕርይ ነው የሚል አቋም አለው፡፡ ዳሩ ግን፣ ይህ ጤነኛ ባሕርይ በተሳሳተ ማኅበራዊ አስተሳሰብ ጫና እርፎበታል ብሎ ያምናል (ዊክስ ፣2003፣ 84)፡፡ በመሆኑም

---

[8] ለነገሩ ይህ ዓይነቱ ወቀሳ በዘርፉ ምርምር ባደረጉ ብዙ ባለሙያዎች ላይ የሚያርፍ ነው፡፡ እነዚህ ባለሙያዎች የሴትን ነገረ ወሲባዊ ባሕርይ ለመግለጽ የሚሞክሩት /የሚፈልጉትም ጭምር/ ከወንድ ልጅ ልብና አእምሮ አንጻር ነው፤ ይህንን አስመልቶ ዊክስ ተከታዩን ወቀሳ ያቀርባል "*Female breaches with the norm were fitted in to a dichotomized picture of male activity and female passivity. Not surprisingly, the most commonly recognized female sexual deviations include servicing men in prostitution or pornography, or 'provoking' men, as in accounts of rape and lesbianism, the most common form of female sexual variation, has generally been speculated about in terms which derived entirely from the male* (75-76)፡፡

ፍንገጣ መደቡ ባህላዊ ነው ብለን ማጠቃለል እችላለን፡፡ አንዱ ትክክል ብሎ የተቀበለውንና የሚኖርበትን ነገረ ወሲባዊ ሥርዓት ሌላው በአፈንጋጭነት ይቆጥረዋል፡፡

በዚህ ዘመን፣ በተለይ በድኅረ መዋቅራዊነት በተቀሰቀሱ አዳዲስ የሥነ ልሳን አስተሳሰቦች ላይ የሚመሠረቱና ወሲባዊ ፍንገጣን የቋንቋና የሐቲት ጉዳይ አድርገው የሚመለከቱ ተመራማሪዎች በርካታ ናቸው፡፡ "ተለምዷዊ" "ኢተለምዷዊ" የሚለው ጥንድ ተቃርኖ (*binary opposition*) መሠረቱ ተፈጥሮ ሣይሆን ቋንቋ ነው፡፡ ዊክስ የቋንቋን ሚና በተከታዩ መንገድ ያስረዳል፤ "*The language of perversion divided the sexual world in to the normal and the abnormal, the elect and the damned, and rarely did they meet*" (ዝኒ ከማሁ፣76)፡፡ የጥንድ ተቃርኖዎቹ ድንበር የተበጀው ደግሞ በቋንቋ ኃይል ነው፡፡ ቋንቋችን ደግሞ፣ ከፍ አድርጌ እንደጠቆምኩት፣ የልዩ ልዩ ርዕዮተ ዓለሞች እስረኛ ሲሆን፣ ይህ ዓይነቱ ርዕዮተ ዓለም በቋንቋ የምናበጃቸውን የሥነ ምግባር ደንቦች በሙሉ ጠቅልሎ የመግዛት ባሕርይ አለው ( ካለር ፣1997፣ 6-7 )፡፡ ድንበር መለያ አጥሮችን እጠንክረን ባቆምን ቁጥር የምንፈጥረው ወይም የምናስጠብቀው ልማድ የሚገዛው ከቅጥሩ ውስጥ ያለውን ብቻ ሣይሆን ከቅጥሩ ውጪ ያለውንም ጭምር ነው፡፡ በመሆኑም ያው አንድ ሐቲት፣ ያው አንድ ልማድ ጠባቂና አጥባቂውን ብቻ ሳይሆን "አፍራሽ"ና "አፈንጋጭ" የሚለውንም ጭምር ያበጃል፡፡

በመሆኑም መነሳት ያለበት ጥያቄ "የትኛው ነው ተገቢ? የትኛውስ ነው ስህተት?" የሚለው አይደለም፡፡ መጠየቅና መመርመር ያለባቸው "አንድን ወሲባዊ ተግባር ልክ ወይም ስህተት ያደርገው ምንድን ነው?"፣ "የትኞቹ ማኅበራዊ ጉዳዮች ናቸው ለእነዚህ ተግባራት ተገቢነትና ኢ-ተገቢነት የፍቺ መሠረት የሚሆኑት?"፣ እንዲሁም "የኃይል አሰላለፉስ ምን ይመስላል?" የሚሉት ጉዳዮች ናቸው (ዊክስ፣ 2003፣86)፡፡ በወሲባዊ ፍንገጣ ላይ በስፋት የጻፈው ዊክስ፣ ከወሲብ ጋር ተዛምደው የሚነሱ አስገድዶ መድፈርን፣ የሕጻናት ጥቃትን፣ ወዘተ. የመሳሰሉ፣ ከሞላ ጎደል ዓለም በኢ-ሰብዓዊ ድርጊትነት የተስማማባቸው ፍንገጣዎች መሆናቸውን ያስረዳል (ዝኒ ከማሁ፣90)፡፡

ሌላው፣ ከወሲባዊ ፍንገጣ ጋር ተዛምዶ በወጉ መነሳት ያለበት ማኅበራዊ ጉዳይ በተቃራኒ ጾታዎች መኃል የሚኖር መሳሳብ (*heterosexuality*) ነው፡፡ እልፎ አልፎ፣ በተቃራኒ ጾታዎች መኃል የሚኖር መሳሳብ በተለምዷዊ ነገረ ወሲብ ላይ እንደተመሠረተ፣ የማይለወጥ፣ ተፈጥሯዊና ሁለንተናዊ ማኅበራዊ ሥርዓት ተደርጎ ሲቆጠር ይገጥመናል፡፡ በመሆኑም ይህ ሥርዓት፣ በነገረ ወሲብ ውስጥ "ሌሎች" ተብለው የሚጠሩ ወገኖች በማንነፀሪያ የሚገለፁበት እና የሚብራሩበት ቋሚ ዐውድ ሆኖ ቆይቷል (ሪቻርድሰን 2008፣19-20)፡፡ "ሄትሮሴክሽዋሊቲ" የአንድና ነጠላ ድርጊትና ሁኔታ መጠሪያ ሳይሆን፣ የተለያዩ ተግባራት ጥምረት ነው፡፡ በፍቅር ላይ ከተመሠረተ ወሲብ እንስቶ እስከ አስገድዶ መድፈር፣ ከተለመደው በመራቢያ አካላት ከሚፈጸም ሩካቤ እንስቶ በአፍና በመቀመጫ እስከሚከናወኑ ወሲባዊ ተግባራት ድረስ

የሚካተቱበት የነገረ ወሲብ መደብ ነው፡፡ በወንድና ሴት ዘመዳማቾች መኃል የሚኖር መፈቃቀድ--ግብረ አምኖን (*inscest*)፣ አንድ ጊዜ ወይንም፣ በተወሰነ የጊዜ ልዩነት ከበርካታ ሰዎች ጋር የሚከናወን ወሲብ እዚህ መደብ ውስጥ ይጠቃለላል ( ይህ ብቻ አይደለም፤ ሌላው ላይ በሚፈጸሙ ጭካኔ የተቀየጠባቸው ወሲቦችና በራስ ጥላቻ የተቃኙ ፍትወቶች --"ሳዲዝም"፣ "ማሶቺዝም"፣ "ሳዶማሶቺዝም" መደባቸው ይሄው ይመስለኛል) ስለዚህ "ሄትሮሴክሽዋሊቲ" ተለምዷዊ ፍትወት ከኢተለምዷዊው ጋር ተዳብሎ የሚኖርበት ሥርዓት ነው ማለት ይቻላል (ደንፌ ፣2000፣ 65፤ቴዎድሮስ፣ 4)፡፡

"ሄትሮሴክሽዋሊቲ" ከፍ አድርገን እንደተመለከትናቸው የነገረ ወሲብ ጉዳዮች ሁሉ ሥሪቱ ባህላዊና ማኅበራዊ የሆነ የቋንቋና የሐቲት ጣጣ ነው የሚል ሙግት--በተለይ ከእንስታውያን ተቺዎች ይቀርብበታል፡፡ በተቺዎቹ እምነት "ሄትሮሴክሽዋሊቲ" ወንዶችንና ተባእትነትን (*masculinity*) የበላይ እና ተጠቃሚ ለማድረግ የተቋቋመ በመሆኑ፣ ሴትን ወደ ጋብቻና ወደ እናትነት በመግፋት በስሜት፣ በወሲብ እና በጉልበት አገልጋሎት እንድትሠጥ ያስገድዳል፡፡ ይህን አስመልከታ ማርች ባንክ (2007፣258) ስታስረዳ፣ እዲህ ባለው ሥርዓት ውስጥ የሴት ልጅ ዓቢይ ተግባር የወንድ ልጅን ስሜት ማገዝ ሲሆን፣ ለዚህም ተግባሯ የምታገኘው ምላሽ ወይንም ከፍያ በጋብቻ አማካይነት ልጅ መውለድንና ተንከባክቦ ማሳደግን ይሆናል፡፡ ከዚህ፣ ማኅበሩ ከደነገገላት ባሕርይና ሚና ውጪ ሆና እንደወንዱ በወሲባዊ ህይወቷ ንቁ (*active*) ለመሆን ብትሞክር የሴትነት ሥፍራዋን ትነጠቃለች፤ መጠሪያዋም ሌላ ይሆናል፡፡

### 2.1.2. ሥነ ጽሑፍና ነገረ ወሲብ

እስካሁን ስንመለከት እንደቆየነው በነገረ ወሲብ ጥናት ውስጥ የሚነሱት ጉዳዮች ሰፋፊ ናቸው፡፡ በመሆኑም ለጉዳዩ ከፍ ያለ ትኩረት ሰጥተው የሚመረምሩ የጥናት ዘርፎችና ተመራማሪዎች ብዙ ናቸው፡፡ ተመራማሪዎቹንም ይሁን የምርምር ዘርፎቹን ወስኖ መደንገግ አስቸጋሪ ቢሆንም፣ በጥቂቱ ግን፣ የሥነ ወሲብ (*sexology*)፣ የሥነ ልቡና፣ የነገረ ፆታ (*gender study*) ፣ የሥነ ጽሑፍ፣ የታሪክ፣ የፖለቲካ፣ የሶሲዮሎጂ፣ ወዘተ. የጥናት ዘርፎች ትኩረትና አካል ነው፡፡ እነዚህ የጥናት ዘርፎች የየራሳቸው ዲሲፕሊናዊ ልማድ፣ ፍልስፍናና ሥነ ዘዴ ያላቸው ቢሆንም የሚጋሯቸውና የሚደጋገፉባቸው ጉዳዮች በርካታ ናቸው፡፡ በተለይ ሥነ ጽሑፍ እንደተቀሩት ዘርፎች ሁሉ ነገረ ወሲብን የምርምሩ ዓቢይ ትኩረት ከማድረጉ ባሻገር በኪነት ኃይል በሚያስተማስላቸው ነገረ ወሲባዊ ጭብጦቹ አማካይነት ለብዙዎቹ የጥናት ዘርፎች፣ በተለይም ለነገረ ፆታና ለፍካሬ ልቡና በመረጃ ምንጭነት ያገለግላል፡፡ ዘርፎቹ ደግሞ በምላሹ በሥነ ጽሑፍ ውስጥ ለሚካሄደው የነገረ ወሲብ ጥናት ጽንሰ ሐሳቦችንና ንድፈ ሐሳቦችን ያቀብላሉ፡፡

ለፍካሬ ልቡናና ለሥነ ጽሑፍ ዝምድና ትልቁ እጅ የፍሮይድ ነበር፡፡ ፍሮይድ፣ በተለይ በኋለኛ ዘመኑ የሥነ ጽሑፍ ኪንን በጥሬ መረጃነት ወይም በገቢርነት (*as a fact*) ከመቀበል ይልቅ ትእምርታዊና ውክልናዊ በሆነ መንገድ እየመረመረ፤ "ሁለንተናዊ" ለሚላቸው የሰው ልጆች ባሕርያት ማስተንተኛነትና መፈክሪያነት ሲገለገልበት ኖሯል፡፡ በዓለም የነገረ ሰብእ እና የማኅበረሰብ ሐቲቶች የሚዘወተሩት እንደ "*eros*"፣ "*psyche*"፣ "*narcissism*"፣ "*Oedipus complex*"፣ ወዘተ. ያሉ ጽንሰ ሐሳቦችና ንድፈ ሐሳቦች በዚህ ዓይነቱ መንገድ የተገኙ ናቸው፡፡

የሥነ ጽሑፍ እና የፍካሬ ልቡና ዝምድና በዚህ ብቻ የሚያበቃ አይደለም፡፡ ሥነ ጽሑፋዊ ሥራዎች ከንድፈ ሐሳባዊው የፍካሬ ልቡና ምርምር ባሻገር በህክምናውም (*psychotherapy*) ውስጥ ሥፍራ አላቸው፡፡ ለህክምናው የሚያገለግል መረጃ ከህሙማኑ አለበለዚያም "ገሀድ" ከሚባለው ዓለም በቀላሉ ማግኘት በማይቻልበት ሁኔታ ውስጥ ሥራዎቹ ከ"*case study*" ተቆጥረው ጭምር ግልጋሎት ላይ ይውላሉ፡፡ በዚህ ረገድ በተለይ ከወሲብ ፍንገጣ ጋ የተያያዙ ምርምሮችና ህክምናዎች ተጠቃሽ መሆናቸውን ባለሙያዎች ያስረዳሉ፡፡ ይህን ሐሳብ ኖቡስና ዳውኒንግ (Nobus *and* Downing) ሲያጠናክሩ እንደሚከተለው ይላሉ፡-

> *In the face of poor clinical materials, the erotic literary imagination has always provided a welcome source of relief. This is not only true for psychoanalysts, but for all theoreticians of perversion.... Psychoanalysts throughout the 20thc have elaborated and illustrated their theories of perversion in constant allegiance to the great (and sometimes minor) works of literature, there by willfully exchanging their clinical research laboratory for the museums of artistic representation* ( 2006,16).

በጥቅሱ እንደተገለፀው ፈካርያነ ልቡናን ጨምሮ የተለያዩ የወሲባዊ ፍንገጣ ተመራማሪዎች ሥራዎቻቸውን ከሥነ ጽሑፍ ጋር አዛምደው አሳድገዋል፡፡ ከዚህም ባሻገር በምላሹ የህክምና ውጤቶቻቸውና እና የንድፈ ሐሳብ ግኝቶቻቸው ለሥነ ጽሑፍ ኪነት መመርመሪያነት እንዲውሉ አስችለዋል፡፡

ከፈካርያነ ልቡና ባልተናነሰ ነገረ ወሲብን ዋነኛ ጉዳያቸው አድርገው ለሚያጠኑ ባለሙያዎች የሥነ ጽሑፍ ድጋፍ የጐላ ነው፡፡ በተለይ ቀደምት የሆኑት የዘርፉ ተመራማሪዎች፣ ለምሳሌ በዚህ ጥናት ውስጥ መላልሼ የማነሳውን ከራፍት ኤቢንግን (Krafft- Ebing) የመሠሉ፣ የሥነ ጽሑፍ ሥራዎችን በመረጃነት ይገለገሉ ነበር፡፡ እነዚህ ተመራማሪዎች ለዘርፉ የሚያገለግሉ የተለያዩ መጠሪያዎችንና ጽንሰ ሐሳቦችን (ለምሳሌ እንደ *sadism* እና *masochism* ያሉ) ከመውሰድ እና ከማርቀቅ በተጨማሪ የሥነ ጽሑፍ ሥራዎችን፣ የፈጠራ ውክልናዎችን እንደ ማስረጃ (*case study*) ጭምር ይገለገሉባቸዋል (ካታሪና፣ 2011፣ 165)፡፡ እነዚህ የተለያዩ የሥነ ጽሑፍ ውጤቶች ከተለያዩ የነገረ ወሲብ ጥናቶች የሚገኙ ሐሳቦችን

ስንዶ ለማስቀመጥና ለማብራራት ያላቸው አስተዋፅኦ ከፍተኛ ነው፡፡ ከዚህም በላይ ደግሞ በገሀዱ ዓለም በወጉ ያልተገለጡ ወይም እንግዳ የሆኑ አዳዲስ ከወሲብ ጋር የተዛመዱ ጽንሰ ሐሳቦችን በመቅረፅ፣ ስያሜዎችን ጭምር በማቀበል ነገረ ወሲብን ተከለው አንፀው አቁመዋል የሚባልላቸውን ሐቲቶች ወግ በማስያዝና በማጎልበት መሪ ናቸው ማለት ይቻላል፡፡

## 2.2. የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት

ከእኔ ጥናት ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን የመጀመሪያ ዲግሪ፣ ሁለተኛ ዲግሪና የዶክትሬት ዲግሪ የመመረቂያ ጽሑፎችን በዩኒቨርሲቲው ውስጥ በሚገኙ አብያተ መጻሕፍት ያሰስኩ ሲሆን፣ ለእኔ ጥናት ቅርበት ያላቸውን ሦስት ሥራዎች መርጬ በነቂስ ለመቃኘት ሞክሬያለሁ፡፡ እነዚህ ሥራዎች ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረቡ ሲሆኑ አንዱ በአማርኛ፣ ሁለቱ በእንግሊዝኛ ቋንቋ የተዘጋጁ ናቸው፡፡ ከእነዚህ ውጪ በርዕሠ ጉዳይ በመጠኑ የሚቀራረቡ፣ ነገር ግን በቅኝት፣ በአንጻር ምርጫና በዓላማ ግንኙነት የሌላቸው ሥራዎችን በየደረጃው አግኝቻለሁ፡፡ እነዚህ ሥራዎች በአመዛኙ የመስክ ጥናት ላይ ተመርኩዘው የመፍትሄ ሐሳብ ለማቀበል፤ በተለይም ሴተኛ አዳሪነትን ለመቅረፍ የተሠሩ ናቸው፡፡ የእኔ ጽሑፍ እንደ ሥነ ጽሑፍ ጥናትነቱ ግቡና መንገዱ መረጃዎችን እንደ ጥሬ "እውነት" ሣይሆን በትርጉም እና በፍካሬ እንደሚደረስባቸው ሐሳቦች መመርመር እና ማሳየት ነው፡፡ በመሆኑም እነዚህን ሥራዎች መቃኘቱ አስፈላጊ ሆኖ አላገኘሁትም፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ሥነ ጽሑፍ ላይ መሠረት አድርገው የተሠሩ ሁለት የመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ጽሑፎችን ተመልክቻለሁ፡፡ በፀዳለ ዘውዴ "ዝሙት አዳሪነት በአርባና በሃምሣ አስርት አመታት የአማርኛ ልቦለዶች" በሚል ርዕስ በ1976 ዓ.ም የተሠራ እና በደምሰው ገ/ኢየሱስ "ሴተኛ አዳሪነት በአራት የአማርኛ ረዥም ልቦለዶች ውስጥ" በሚል በ1996 ዓ.ም የቀረበ ሥራ፡፡ እነዚህም ስራዎች ቢሆኑ መነሻቸው ሥነ ጽሑፍ ይሁን እንጂ ከላይኞቹ ጋር ተመሳሳይ ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ ሴተኛ አዳሪነትን ከተለያዩ ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች አንጻር ተመልክተው መፍትሄ ለማምጣት የሚሞክሩ ናቸው፡፡ የእኔ ጥናት ዓላማ ግን ከዚህ በተለየ መልኩ ሴተኛ አዳሪነትንና ሌሎች በርካታ ነገረ ወሲባዊ ጉዳዮችን በኪናዊ ጭብጥነት መመርመር ነው፡፡ በመሆኑም እነዚህን ጽሑፎች የቅኝቴ አካል አላደረኳቸውም፡፡ ወደ ቅኝቴ ላምራ፡፡

የመጀመሪያው፣ በአየነው ጓዱ ለውጪ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍል "Psychoanalytic Reading of Sibhat Gebreigziabher's *Tikusat* and *Letum Aynegallign*" በሚል ርእስ እ.ኤ.አ በ2004 ለድህረ ምረቃ ፕሮግራም የቀረበ ጽሑፍ፡፡ የዚህ ጥናት ዓቢይ ጉዳይ በስብሐት ገብረ

እግዚአብሔር ሁለት ልብ ወለዶች ላይ በትኩሣት እና በሌቱም አይነጋልኝ ላይ ፍሮይዳዊ መሠረት ያለው ፍካሬ ልቡናዊ ንባብ (*Freudian-based Psychoanalytic Reading*) ማካሄድ ነው፡፡ ልብ ወለዶቹ መሠረታዊ በሚባሉ የንድፈ ሐሳቡ እሣቤዎችና ምርመር ተካሂዶባቸዋል፡፡ አየነው በምዕራፍ ሦስት ላካሄደው ትንተና በምዕራፍ ሁለተ ያበጀው ንድፈ ሐሳባዊ ዳራ ሠፊ ግልጋሎት ነበረው፡፡ አጥኚው በሁለቱ ልብ ወለዶች ውስጥ የሚገኙትን ዋና ዋና ገጸ ባሕርያት ወስዶ የ '*psychosexual*' ባህርያቸውን ፈለግ አሳይቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በትረካ የሚገለፁትን ቁልፍ ቁልፍ ሁነቶች እና ምስሎች ከፍካሬ ልቡና ጽንስ ሐሳች አንጻር መርምሯል፡፡ በማጠቃለያውም ልብ ወለዶቹ ለፍካሬ ልቡና ንድፈ አንጻር የቀረቡና የተሙቱ በመሆናቸው በዚህ መንገድ በማንበብ ይበልጥ መረዳት እንደሚቻል አረጋግጧል፡፡

አየነው በዚህ ሥራው ከተለመደው ገለፃ ላይ ብቻ ትኩረት ካደረገ የአጠናን ዘዴ ወጥቶ ሥራዎቹን ወደ ጽንሰ ሐሳብነት ማሣደግ ችሏል፡፡ ይህ ጉዳይ ሊያመሳስለን ይችላል፡፡ ምክንያቱም የስብሐት ልብ ወለዶች እኔ ለጥናት እንደመረጥኳቸው ድርሰቶች አላግባብ ሲገፉ የከረሙ ናቸው፡፡ ይሁንና የንባብ ደረጃችን ሲልቅ ከባዶ ብልግና በላይ ስለሠው ልጅነት ባህሪ እና ማንነት ብዙ የሚናገሩት ቁምነገር እንዳለ መመልከት ይቻላል፡፡ ይህም ስራ አንድ ማሣያ መሆን የሚችል ይመስለኛል፡፡ የእርሱ የጥናት ትኩረት የመረጠው ንድፈ ሀሳብ ፍሮይዳዊ መሰረት ያለው ፍካሬ ልቡናዊ ንባብ ማካሄድ ነው፡፡ ፍሮይድ ደግሞ በነገረ ወሲብ ጥናት ውስጥ ቀደምት እና ተጽእኖ ፈጣሪ ከነበሩት ተመራማሪዎች መካከል ይጠቀሳል፡፡በመሆኑም በትንታኔ መንገዳችን ውስጥ መቀራረብ ይኖራል፡፡ ይህን ብልም ግን፣ በእኔና በአየነው ጥናቶች መካከል ያለው ግንኙነት ውሱን ነው፡፡ አስቀድሜ እናዳነሳሁት የአየነው ዋነኛ ጉዳይ በመረጣቸው የስብሃት ስራዎች ውስጥ ስነ ልቡናዊ ፈለጎችን ማውጣት ነው፡፡በመሆኑም በመጀመሪያ የእኔ ጥናት የሥነ ልቡናን ወይም የፍካሬ ልቡናን ንድፈ ሀሳቦች እና ጽንሰ ሃሳቦች እንደ አንድ ግብአትና አቅጣጫ እንጂ እንደ አንድ ብቸኛ የመመርመሪያ ፈለግ ተከትሎ የሚቆም አይደለም፡፡ምክንያቱም የጥናቴ ርእሰ ጉዳይ ነገረ ወሲብ ሲሆን የማጥኛ መታገኒያውም የባህል ጥናት ነው፡፡ ይህ ደግሞ ደጋግሜ እንዳነሳሁት ጥናቴን በአንድ ጽንሰ ሃሳብ እና ንድፈ ሃሳብ ተወስኖ እንዳይቆም ያስገድደዋል፡፡ሲቀጥል ደግሞ አየነው በአንድ ደራሲ የተለያዩ ስራዎች ላይ ፍካሬ ልቡናዊ ምርምር ሲያካሂድ እኔ ደግሞ ትኩረቴን ዘመን ላይ በማድረግ የስብሃት ስራዎች ከተጻፉበት እና ከታተሙበት ዘመን በኋላ በተቀራራቢ እመታት በተለያዩ ጸሐፍት( ከሁለቱ ሰዓት አላፊዎች በቀር) የተጻፉ አምስት ስራዎችን በመያዝ ስለተገኙበት ዘመን ነገረ ወሲብ ምን ይላሉ የሚለውን ለመመርመር ነው የሞከርኩት፡፡ስለሆነም እነዚህ ሁለት እንኳር ልዩነቶች ሊኖሩ የሚችሉትን ሌሎች ዝርዝር ልዩነቶች የሚጠቁሙ ይመስለኛል

ሁለተኛው የዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ በአወት ገብረ እግዚአብሔር በ2006 እ.ኤ.አ. "Sibhat G/Egziabhher's Tikusat and Letum Aynegalgn, Sublimated Expressions of The Autor's

Sexual Insinict" በሚል ርእስ ለውጪ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ የድሕረ ምረቃ ክፍል የቀረበ ነው:: የዚህ ጥናት ዋነኛ አላማ በስብሐት ገብረ እግዚአብሔር ልብ ወለዶች፣ በሌቱም አይነጋልኝ እና በትኩሳት ላይ ፍካሬ ልቡናዊ ጥናት በማድረግ ሥራዎቹ የደራሲውን ልቡና መግለጥ ችለው እንደሆነ ማረጋገጥ ነው:: በዚያውም በሥነ ጽሑፍና በፍካሬ ልቡና ንድፈ ሃሳብ መካከል ያለውን ትስስር ማሳየት ነው:: ለዚህ ዓላማ መሳካት ደግሞ ሲግመንድ ፍሮይድ ኢ-ንቁ የሆነውን የልቡና ክፍል ለመመርመር በተገለገለባቸው የህልም እና የትእምርቶች ፍካሬ ለመገልገል ሞክራለች:: አወት በመረጠቻቸው ሁለት ልብወለዶች ውስጥ ያሉትን ተራኪዎች በመያዝ ወሲባዊ ቅዠቶቻቸውን (*sexual fantasies*) እና የትእምርት አጠቃቀማቸው (*use of symbolism*) ትመረምራለች:: ከዚያም "ማስታወሻ"በሚል በዘነበ ወላ አማካይነት ከተጻፈው የደራሲው ሕይወት ታሪክ ጋር በማመሳከር ካነፃፀረች በኋላ ሁለቱ ተራኪዎች የጸሐፊውን "ወሲባዊ ደመ ነብሣዊ" ስሜት ገላጮች መሆናቸውን ለማረጋገጥ ትሞክራለች::

ይህ ጥናት ጥሩ ሊባል የሚችል ንድፈ ሐሳባዊ መታገቢያ ተበጅቶለታል:: ትንታኔውም በመታገቢያው ከመጡ ጽንሰ ሐሳቦችና ንድፈ ሐሳቦች ጋር ይናበባል:: ነገር ግን በትንታኔ ውስጥ የሚነሡት ሐሳቦች ከሁለቱ ልብ ወለዶች የተወሰዱ ሲሆኑ፣ ለማነፃፀሪያነት የቀረበው የደራሲው የሕይወት ታሪክ አነስተኛ ነው:: የሕይወት ታሪካዊ መረጃዎቹ በልበወዱ የተነሱትን ሐሳቦች ለማረጋገጥ በቂ ይሆኑ ዘንድ የደራሲውን ልዩ ልዩ ቃለምልልሶች እና በገጠመኝ ላይ የተመሠረቱ ጽሑፎች ማካተት ቢቻል የተሻለ ይሆን ነበር:: ከዚህም በተጨማሪ አጥኚዋ በትንታኔዋ ወቅት የሁለቱን ልብ ወለዶች ተራኪ ገጸ ባሕሪያት ወሲባዊ ቅዠት እና ትእምርታዊ መገለጫዎችን ከፋፍላ አቅርባለች:: ወሲባዊ ቅዠቱን ጥሩ ፍሰት ባለው መልኩ ከተነተነች በኋላ ትእምርታዊ ገለጻዎቹን ግን ዝም ብላ ከመሀል እየመዘዘች አውጥታ በሰንጠረዥ ታስቀምጣለች:: ይህ ደግሞ እንደ ሥነ ጽሑፍ ምርምር ላለ ሐቲት ብዙም የሚበጅ አልመሰለኝም:: ምክንያቱም ሁለቱ ጉዳዮች ተቆራኝተው ሊተነተኑ የሚችሉ ነበሩ::

ይህ ጥናት በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ልክ እንደ እየነው ሁሉ የፍካሬ ልቡናን ንድፈ ሐሳብ የሚከተል በመሆኑ ከእኔ ጽሑፍ ጋር ተቀራራቢነት አለው:: ቀደም ብዬ እንደገለጽኩት ነገረ ወሲብ ከተሠራባቸው ሐቲቶች እና በንድፈ ሐሳብነት ለጥናትና ምርምር ከሚገለገልባቸው አቅጣጫዎች አንደኛው ፍካሬ ልቡና ነው::በዚህም አወት ለጥናቷ መድረሻ ያደረገችው የደራሲውን ልቡና ሲሆን እኔ ደግሞ በድርሰቶቹ አማካይነት በዘመን ውስጥ የሚታዩ ባህላዊ እና ማህበራዊ መነሻ እና መድረሻ ያላቸው ነገረ ወሲባዊ ጉዳዮች ናቸው::ቢሆንም በአንድም ሆነ በሌላም መንገድ እነዚህ ጉዳዮች የጥናት ጽሑፎቻችንን ያስተሳስራሉ:: ምክንያቱም ደራሲም ልክ እንደ ሥራዎቹ ከማኅበረሰቡ ውጪ መሆን አይችልምና:: ይሁንና ደጋግሜ ለመንሳት እንደሞከርኩት እኔ በመታገቢያነት ለምገለገልበት ለባህል ጥናቶች የትችት እንጻር ፍካሬ ልቡና ከብዙዎቹ አንዱ እንጂ ብቸኛው የመመርመሪያ መንገድ አይደለም::

ከዛም በላይ ለጥናት የመረጥናቸው ድርሰቶችም ይሁኑ በአላማነት የያዝነው የጥናት መድረሻ በሰፊው ይለያያል፡፡አወት በመድረሻዋ የደራሲውን ልቡና በድርሰቶቹ አማካይነት መመርመር ሲሆን የእኔ ጉዳይ ግን በድርሰቶቹ አማካይነት ማህበረ-ባህላዊውን ነገረ ወሲባዊ ተስተማስሎ ማሳየት ነው፡፡

በተከታይ የምቃኘው ጥናት፣ "ሴተኛ አዳሪነት እና የስብአዊነት ጥያቄ በሶስት ልብ ወለዶች ውስጥ" በሚል ርእስ፣ በ1999 ዓ.ም፣ በአያሌው አስፋው ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍለ ትምህርት ለድሕረ ምረቃ መርሐ ግብር የቀረበ ነው፡፡ ለጥናት የተመረጡት ልብ ወለዶች *ሴተኛ አዳሪ፣ ሌቱም አይነጋልኝ* እና *ሙንልየ ሙንልየ ዘካዛንቺስ* የተሰኙት ናቸው፡፡ የነዚህ የሥነ ጽሑፍ ውጤቶች ዋነኛ የመባያ ጉዳይ ሴተኛ አዳሪነት ነው፡፡ የጥናቱ ዋና ዓላማ የሴተኛ አዳሪዎችን የሰብዓዊነት መንጠፍ ሥራዎቹን አንብቦ ጠቋሚ ቃሎችን፣ ሀገረጎችን እና ዐረፍተ ነገሮችን በፍካሬ በማምጣት ማሳየት ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በባህላችን ያልተለመዱ አሁን ግን እየታዩ ያሉ ድርጊቶች በብርሃን ታምቀው በጨለማ ሲወጡ የማኅበረሰቡን ማኅበራዊ "ህመም" በሥነ ጽሑፍ አማካይነት አይቶ ለማሳየት የተነሳ ጥናት ነው፡፡ እኔ ለጥናት በመረጥኳቸው የሥነ ጽሑፍ ሥራዎች ውስጥም ከሚታዩ ዓበይት ርእሠ ጉዳዮች መኻል አንዱ ሴተኛ አዳሪነት መሆኑ ትልቁ የጋራ ጉዳያችን ነው፡፡

የአያሌው ጥናት በጥቅሉ ሦስት ምዕራፎች አሉት፡፡ በመጀመሪያው የጥናቱ መንስኤ፣ ዓለማ፣ የአጠናን ዘዴ እና የጥናቱ አደረጃጀት የተገለፀበት ሲሆን የጥናቱ የምርምር ጥያቄዎች፣ የጥናቱ አስፈላጊነት አልተካተቱም፡፡ ጥናቱ የሥነ ጽሑፍ እንደመሆኑ በአንድ ቋሚ ህግና ሥርዓት አሥሮ እንዳይንቀሳቀስ ማገዱ ተገቢ ባይሆንም፣ አለበቂ ምክንያት ግን ከልማድና ሥምምነት ማፈንገጡ ትክክል አይመስለኝም፡፡ ምዕራፍ ሁለት ከለሳ ድርሳን ነው፡፡ በዚህ ምዕራፍ የተካተተው የመጀመሪያ ጉዳይ የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ሲሆን ከአስር በላይ በሴተኛ አዳሪነት ዙሪያ የተሰሩ ድሑፎችን የቃኘበት ነው፡፡ ሥራዎቹን በጣም በሰፊው ምናልባትም ከተገቢው በላይ ሊባል በሚችል መልኩ መርምሯል፡፡ ድክመትና ጥንካሬያቸውን ነቅሶ ከርሡ ጥናትና ምርምር ጋር ያላቸውን ቅርበትና ልዩነትም አሳይቷል፡፡ በዚህ ምእራፍ ውስጥ በአገራችን ሴተኛ አዳሪነት ምን እንደሚመስል ታሪካዊ ዳራ ስጥቷል፡፡ ለዚህ እንዲያግዙት እኔ በተገለገልኩበት፣ የሪቻርድ ፓንክረስት መጣጥፍ እና አንዳርጋቸው ተሰፋዬ በ1959 በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ማኅበር መጽሄት ላይ ባቀረበው ጽሑፍ ተገልግሏል፡፡ አያሌው ቀድሞ የፓንክረስትን መጣጥፍ በተዛማጅ ጽሑሮች ቅኝት በሰፊው የመረመረ ቢሆንም በድጋሚ በዚሁ ርእስ ውስጥም ያነሳዋል፡፡ በዚህ የጥናት ጽሑፍ ውስጥ እንደ ንድፈ ሃሳባዊ ዳራ ሊቆጠር የሚችለው ክፍል በጣም ውሡንና ሴተኛ አዳሪነትን ለመበየን ብቻ የቀረበ ነው፡፡ንድፈ ሃሳባዊ ዳራ ተመራማሪው የሚመራባቸውን መርሆዎች ቀድሞ በመትከል አንድን ጥናት ሥርዓት ለማስያዝ ያስችላል፡፡ እንደ ሥነ ጽሑፍ ጥናት ባለ ሐቲት ውስጥ አንድ ዓይነተኛ የመተንተኛና የመተርጎሚያ ዐውድ ካልተበጀ በቀር

የአንድ ጉዳይ መፍሰሻው ብዙ ነውና መገናኛው አስቸጋሪ መሆኑ አይቀርም፡፡ የዚህ ጥናት ዋነኛ ሀሣብ የሰብዓዊነት መንጠፍ (*dehumanization*) ሲሆን ለዚህ ጽንሐ ሃሳብ መስፈርት ማበጀትና ብያኔ መስጠት አስፈላጊ ነበር፡፡ ምክንያቱም የሰብአዊነት ትርጉም ቋሚና አንድ አይደለም፡፡ የህሊና ሚዛን፣ የሥነ ምግባር ፍርድ ነውና በጊዜና በባህል፣ በዐውድ ይወሰናል፡፡

በምእራፍ ሶስት ልቦለዶቹን በጋራና በተናጠል በመተንተን፣ ሴተኛ አዳሪዎች በማኅበረሰቡ ጉዳት የደረሰባቸው (*victim*) እንደሆኑ ለማሳየት ሞክሯል፡፡ እንደ እቃ/ሸቀጥ የሚቆጠሩ፣ ሳይፈልጉ ተገፍተው በገቡበት ዓለም ምንም ምርጫና ተቆጣጣሪነት የሌላቸው መሆናቸውን ድርሰቶቹ ላይ ተመስርቶ ያስረዳል፡፡ ወንዶቹና ማኅበረሰቡ የጥፋት መሠረቶች ሆነው እያለ ነፃነታቸው የታወጀላቸው፣ ደጋግመው እንዲያጠፉ የተፈቀደላቸው ሆነው እንደተገለፁ ይናገራል፡፡ ይህ ጉዳይ የሁለታችንም ጥናቶች የጋራ መድረሻ ነው፡፡ ይሁንና የሴቶቹ ባህሪ ልዩነት አምጥቷል፡፡ በአያሌው ሥራ ውስጥ የተካተቱት የሥነ ጽሑፍ ስራዎች በዘመን እኔ ለጥናት ከመረጥኳቸው ድርሰቶች በተለይ ሁለቱ እርቀት አላቸው ፡፡ የነገረ ወሲብ ጉዳዮች ደግሞ በዘመን እና በባህል የሚዳኙ በየጊዜው የሚለዋወጡ ናቸው፡፡ በመሆኑም አያሌው በመረጣቸው የሥነ ጽሑፍ ሥራዎች ውስጥ የሚታዩት ሴተኛ አዳሪዎች ከእኔዎቹ ይለያሉ፡፡ የቀድሞዎቹ አያሌው እንደገለፀው ምስኪኖች፣ ሰውነታቸው የተዘነጋ፣ ለሰውነት ክብር የማይበቁ፣ ወንድ ልጅ ስለከፈላቸው ብቻ እንደፈለገ የሚያደርጋቸው፣ እራሳቸው ለራሳቸው እያዘኑ እራሳቸውን በማኅበረሰብ ዓይን እያዩ እራሳቸው ላይ የሚፈርዱ ናቸው፡፡ እኔ በመረጥኳቸው ሥራዎች ውስጥ ያሉት ሴተኛ አዳሪዎች ጉዳት የደረሰባቸው ቢሆኑ እንኳን ሥራውን ኑሮ አድርገው ከገቡ በኋላ ብዙዎቹ ነፃነታቸውን የሚያስከብሩ፣ በምርጫና በፍላጐታቸው ለመንቀሳቀስ የሚሞክሩ ናቸው፡፡ ይህን ማድረግ ቢሣናቸው እንኳን ውድቀታቸው የዝምታ አይቀበሉም፡፡ማኅበረሰቡንና ስርአቱን ይጠይቃሉ፣አለበለዚያም በፀፀትና በመጠየፍ እራሳቸውን ከመውቀስ ይልቅ የናቃቸውን ማኅበር በምላሹ ንቀው የሚርቁ ናቸው፡፡ ሌሎቹና አዳዲሶቹ ደግሞ በፍፁም ተቃርኖ የተቀመጡ ናቸው፡፡ሴተኛ አዳሪነትም ቢሆን በተጎጂነት እንደመጨረሻው የውድቀትና የባርነት ማረጋገጫ የሚታይ ሳይሆን የሴትነት አሸናፊነት፣ ማኅበራዊ የበላይነትን የሚታይበት ተደርጎ ሲገለጽ ይገጥመናል፡፡ እነዚህ ሴቶች የስሜታቸው፣ የአካላቸው፣ ካስፈለጋቸውም የደንበኞቻቸው በተራዛሚው ደግሞ የማኅበረሰቡ የበላይ ናቸው፡፡ የእኔና የአያሌው ጥናት እንደሚያሳየው ማኅበረሰቡ /በወንዶቹ የተወከለው/ የወሲባዊ ፍንገጣው ዋነኛ ፈጣሪ እንዲሁም ከሳሽ ነው፡፡ ይሁንና እንደ አያሌው እምነት ወንዶቹ ሴተኛ አዳሪዋን ሰብዓዊነቷ እንዲነጥፍ አድርጓል፡፡ እንደ እኔ እምነት ግን ሰብዓዊነት የነጠፈው /እሁንም የሰብዓዊነት መንጠፍ አንድ ዓይነት መለኪያ ባይኖረውም/ አያሌው ለመመዘን በሞከረበት መንገድ ተጉገ ስመለከተው ወንድ ሠራሽ ከሆነው ማኅበርና የማኅበራቸው መገለጫ ከሆኑት ከራሳቸው ከወንዶች ውስጥ እንጂ ከሴቶቹ አይደለም፡፡ ይህንን ዓይነቱን እውነታ ነው Andrea Dworkin "*In the male system, women are sex; sex is the whore.*

*The whore is porne, the lowest whore, the whore who belongs to all male citizens: the slut, the cunt. Buying her is buying pornography. Having her is having pornography*" ስትል የምትገልጸው (በካሻላሮ የተጠቀሰ ፤2001፤ 110)፡፡ በድርሰቶቹ ውስጥ፣ ወንዶቹ በገንዘብ "ሊገዙ" የሚመጡት ማኅበረሰቡ እጅግ ሰብዓዊ አድርጎ የሚቆጥረውን "ስሜት" ነው፡፡ ይሁንና ይህን "ሰብዓዊ" ተደርጎ የሚቆጠረውን ጉዳይ አግኝተው ለመርካት የሚሞከሩበት መንገድ አንድም ማኅበሩ "ኢሰብዓዊ" ብሎ የሚፈርጀው ነው፤ አንድም ደግሞ ለሰብዓዊ ተጓዳኛቸው (ለሴተኛ አዳሪዋ) ስሜት ዓይንና ጆሮ የሌለው ነው፡፡ "ለምን?" ቢባል፤ ምክንያቱም በማኅበሩ እንደሚታመነው ሴተኛ አዳሪ በገንዘብ ገዝተው ስሜት "የሚከፍሉባት" ዕቃ ናትና፡፡ ማኅበራቸው ሰብዓዊ ህልውናዋን ከዶ ከዕቃ ከሚቆጥራት ሴት ጋር አልጋ የሚጋሩ ወንዶች፣ በገዛ ራሳቸው የሥነ ምግባር መመዘኛ ሰብዓዊነቱን ተነጠቀ ማለት ነው፡፡ ስለሆነም ሴቷ ላይ በደል እና ጉዳት ሊደርስ ቢችልም በማኅበረሰቡ ሚዛን ሲታይ ሰብዓዊነት የነጠፈው ከራሱ ከማኅበረሰቡ ውስጥ ነው፡፡

የአያሌው የጥናት ጽሑፍ ከእኔ የጥናት ጽሑፍ ጋር በዘመንም በርእሠ ጉዳይም የተሻለ ቅርበት አለው፡፡ይሁንና ልዩነትም እንዳለን ግን ከላይ ያነሳኋቸው ሀሳቦች ጠቋሚ ይመስሉኛል፡፡ ቀዳሚው እና ፊትለፊት የሚታየው ልዩነት ለጥናት የመረጥናቸው የድርሰት ስራዎች ናቸው፡፡ሌላውና ትልቁ ግን እነዚህን ስራዎች ለመመርመር ከመረጥነው አንጻር ይመነጫል፡፡ አያሌው ደጋግሜ ለመጠቆም እንደ ሞከርኩት ጥናቱን ሲያካሂድ ይሄ ነው የሚባል የንድፈ ሃሳብ መታገዚያ አላስቀመጠም፤የእኔ ጥናት ግን በዋናነት በባህል ጥናቶች የትችትነት አንጻር ላይ ተመስርቶ በተለያዩ ንድፈ ሃሳቦች እና ጽንሰ ሃሳቦች እየታገዘ የሚጓዝ ነው፡፡

የአያሌውን ጥናት ጠቅለል አድርጌ ስመለከተው በተለይ ከፀጋዬ ገብረ መድህን "ማነው ምንትስ" እና ከዮሐንስ አድማሱ "እስኪ እንነጋገር" የተሰኙ ግጥሞች ጋር ተሰናስኖ መቅረቡ የተሻለ ጥንካሬ የሚሠጠው እና በጐ ገጽታውን ያጐላ ይመስለኛል፡፡በማጠቃለያዬ ለመጠቆም እንደሞከርኩት እንደነዚህ ያሉ ማህበረ-ባህላዊ ጉዳዮች ሲጠኑ ከሌሎቹ በአውድ ከሚጋሯቸው ጉዳዮች ጋር ተሳስረው ቢሆን ጥንካሬ ይኖረዋል፡፡ በመሆኑም ወደሌሎቹ መድረስ ባይችልም እንኳን በሥነ ጽሑፍ ውስጥ ከሚገኝ ሌላ ዘምንተኛ ዘውግ ጋር ማዛመዱ መልካም ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የቋንቋ አጠቃቀሙ እና ከተለመደው የገለፃ ስልት ወጣ ብሎ ለመተንተንና ለመፈከር መሞከሩ ከጥንካሬ ሊታይ የሚገባው ይመስለኛል፡፡

## ምዕራፍ ሦስት፤ ትንተና

ይህ ምዕራፍ፣ በምዕራፍ አንድ በተለምኩት የመተንተኛ ዘዴና የመፈከሪያ ስልቶች፤ በምዕራፍ ሁለት ባደራጀኋቸው አንጻሮች አማካይነት ለጥናት የመረጥኳቸውን ድርሰቶች ለመመርመር የምሞክርበት ነው፡፡ ምዕራፉ "ሴተኛ አዳሪነት"፣ "በተመሳሳይ ጾታ መኃል የሚፈጠር ፍትወት"፣ "በጭካኔና በጥላቻ የተቃኙ ወሲባዊ ባሕርያት" እና "መልከአ ተባእት በሴተኛ አዳሪዎች መንደር" የሚሉ ርዕሶች በተሰጧቸው አራት ዓበይት ክፍሎች ላይ የተደራጀ ነው፡፡ የእያንዳንዱ ክፍል ሚና ከባህል ጥናት የተቀዱ የነገረ ወሲብ አንጻሮችን ከልዩ ልዩ ነገረ ሰብአዊና ማኅበረሰባዊ ጽንሰ ሐሳቦች እና ንድፈ ሐሳቦች ጋር በማጣመር ንባብ የማካሄድ ይሆናል፡፡ በመሆኑም ምንም እንኳን በምዕራፍ ሁለት ጥቅል የሆነውን ወሲባዊ ፍንገጣን በጽንሰ ሀሳብ ደረጃ ለማስተዋወቅ የሞከርኩ ቢሆንም በዚህ ምዕራፍ የማነሳቸውን ለጥናት በመረጥኳቸው ድርሰቶች ውስጥ የገነኑ የወሲባዊ ፍንገጣ ተናጠላዊ እና ተያያዥ ጉዳዮች ከትንተናው ጋር እያይገና የምመለከት ይሆናል፡፡ ለትንተና ከድርሰቶቹ የወሰድኳቸውን ጥቅሶች የመረጥኩት የሚያነሷቸውን ርእሰ ጉዳዩች ለመግለጽ በተሻለ አቅም አላቸው በሚል ያመንኩባቸውን ነው፡፡ማለትም በትንተናው ያልተካተቱት የድርሰቶቹ አካላት የተደጋገሙና ለትንተና በመረጥኳቸው ሊወከሉ የሚችሉ ናቸው የሚል እምነት አለኝ፡፡ በምዕራፉ የማነሳቸው ጉዳዮች ከወሲባዊ ፍንገጣ ጋር የተዛመዱ፣ በእንግዳ ድርጊቶች፣ አመለካከቶችና አስተሳሰቦች የተቃኙ በመሆናቸው፣ ከትንታኔዬ በትይዩ ከድርሰቶቹ አብዝቼ በመጥቀስ እውነታውን እንዳለ ለማሳየትም እሞክራለሁ፡፡

## 3.1. ሴተኛ አዳሪነት

በሌሎች አገራት የሥነ ጽሑፍ ልማዶች ውስጥ እንደምናስተውለው "ሴተኛ አዳሪነት"፣ ሥነ ጽሑፍን በዘውግ ለመከፈል የሚያስችል ርእሰ ጉዳይ ነው፡፡ ለአገራችን የኪን ልማድም እንግዳ አይመስልም፡፡ በአማርኛ ሥነ ጽሑፍ በአንደወጣች ቀረች፣ በሴተኛ አዳሪ፣ በ"ማነው .... ምንትስ"፣ በብዙዎቹ የበዓሉ ግርማ ሥራዎች፣ በሌቱም አይነጋልኝ በበርካታዎቹ የስብሐት አጫጭር ልብ ወለዶች ውስጥ ተመላልሶ ገጥሞናል፡፡ በኋለኛውም ዘመን በተለይ በ1990ዎቹና አሁን ባለንበት ዘመን ሴተኛ አዳሪነት ቋሚ መቢያ ጉዳይ ነው፡፡ ይህ ማለት በርእሰ ጉዳዩ ላይ የአማርኛ ሥነ ጽሑፍ ረጅም ዘመን ያስቆጠረ ልማድና በቂ ሊባል የሚችል መረጃ (ቴክስት) አለው ማለት ነው፡፡ ይህ የልማድ ጥልቀትና የመረጃ ሙሉነት ደግሞ ሴተኛ አዳሪነትን በጽንሰ ሐሳብ ደረጃ እንድንመለከት የሚያስገድድ ይመስለኛል፡፡

ሴተኛ አዳሪነት (*prostitution*)፣ በሰው ልጅ የነገረ ወሲብ ታሪክ ውስጥ እድሜ ጠገብና ሁለንተናዊ ሊባሉ ከሚችሉ ጉዳዮች መካከል አንዱ ነው፡፡ ይህ ጉዳይ፣ እንደሌሎች የነገረ ወሲብ ጉዳዮች ሁሉ ለየዘመኑ፣ ለየባህሉ የእሴት ሥርዓቶች እየተገዛ "በከፋም--በደጉም" ሲዳኝ ኖሯል፡፡ ዛሬ በምናውቃቸው በርካታ ባህሎች ውስጥ ሴተኛ አዳሪነት ገደብ የሚወድቅበት፣ ቁጥጥር የሚደረግበት ባስ ሲልም ከፍ ያለ ቅጣት የሚጣልበት "ወሲባዊ ፍንገጣ" ነው፡፡ ነገር ግን፣ እንዲህ ያለው ማኅበረ-ባህላዊ አቋም ሁለንተናዊ እንዳልሆነ የታሪክ መዛግብት ያስረዳሉ፡፡ ለዚህ ደግሞ ጥሩ ማሳያ የሚሆነን ጥንት በሜዲትራንያን አካባቢ ይከናወን የነበረው ሴተኛ አዳሪነት ነው፡፡ በተጠቀሰው አካባቢ በነበሩ አገራት በወቅቱ ሴተኛ አዳሪነት ተለምዷዊ ተቀባይነት ካለው የጋብቻ ሕይወት የሚልቅ ማኅበራዊ ደረጃና ሥፍራ ያስጥ ነበር፡፡ ቀደምት የዓለም ስልጣኔ ማሣያ በነበሩት በሮምና በግሪክ ሚቶች ሳይቀር ሴተኛ አዳሪነት ነባር ሙያ ቢሆንም በሜዲትራንያን አካባቢ ግን ልዩ የሆነ የቅድስና ገጽታን ተላብሶ ይከወን ነበር፡፡ "*sacred*", "*cultic*", "*ritual*", "*temple*" በሚሉ ቅጽሎች የሚታጀበው ይህ ዓይነቱ ሴተኛ አዳሪነት፣ እንደ ቅዱስ ሃይማኖታዊ አገልግሎት ተቆጥሮ በተለያዩ መንፈሳዊ ክብረ በዓላት በአብያተ መቅደሳት ይፈጸም፤ ገቢውም በመባነት ለአብያተ መቅደሣቱ የአስተዳደር ሥራ ይውል እንደነበር ይነገራል (ደ ቦቭዋ 1993፣ 95-97፤ በዲን፣ 2008፣ 1-2)፡፡ ቆየት ብለን የምንመለከተው፣ በአገራችን በ17ኛው መቶ ክፍለ ዘመን፤ ጎንደር በመናገሻ ከተማነት ባገለገለችበት ወቅት ታይቶ የነበረው ሴተኛ አዳሪነትም ተጨማሪ ማሳያ ሊሆነን ይችላል፡፡ ሪቻርድ ፓንክረስት፣ኮምበስ (Combes) እና ታሚሲር (Tamisier) የተባሉ ፈረንሳውያንን ጠቅሰው እንደሚያስረዱት እነዚህ ሴቶች በዘመኑ በአውሮፓ ባህል እንደነበሩት ሴተኛ አዳሪዎች የሚናቁ እና የሚኮነኑ ሳይሆኑ ከፍ ያለ ማኅበራዊ ደረጃ ነበራቸው፡፡ እነዚህ ሴቶች ጋር መሄድም አያሸማቅቅም፤ አያሳፍርም፤ አያወርድም (ገጽ 1974፣160)፡፡

ሴተኛ አዳሪነት እንደ ሌሎች ወሲባዊ ፍንገጣዎች ሁሉ ለፈርጀ ብዙ ፍቺ የተጋለጠ ነው፡፡ እንደ አንድ ማኅበራዊ ተቋም፣ እንደ የወል እና የግል ምንትነት፤ እንደ የሕግ፣ የፖለቲካ፣ የኤኮኖሚ፣ የሥርዓተ ጾታ፣ ወዘተ. ጣጣ እየታየ በየገጹ ሊመነዘር ይችላል፡፡ በመሆኑም እንደተነሱበት መሠረተ ሐሳብ እና አቅጣጫ እንዳመቸ ይበየናል፡፡ በጥቅሉ ግን በብዙዎች ስምምነት ያገኘው ጉዳይ ሴተኛ አዳሪነት፣ ለገንዘብ ወይም ለሌሎች ጥቅማጥቅሞች ሲባል የሚሰጥ የወሲብ አገልግሎት ነው፡፡

የእግሊዝኛው "*prostitution*"፣ የቃሉ ፍቺም ይሁን ተግባሩ ለወንድም ለሴትም ያገለግላል፡፡ ይሁን እንጂ ሠፊውን እጅ የሚይዙትና በብዙ ባህሎች ውስጥ ይህን ተግባር የሚፈፅሙት ሴቶች ስለሆኑ ስያሜውም ይሁን ተግባሩ ከሴትነት ጋር ጥብቅ ቁርኝነት አለው፡፡ ስለሆነም በእንስታውያን ዘንድ ትኩረት ተሰጥቶት ሲመረመር ሲጠና ቆይቷል፡፡ እንስታውያን ባለፉባቸው የተለያዩ የለውጥ ሂደቶች ውስጥ ካልዘነጓቸው ርእስ ጉዳዮች መካከል አንዱም ነው፡፡ ይህ ማለት ግን በርእስ ጉዳዩ ዙሪያ ተመሳሳይ አቋም

አለ ማለት አይደለም፡፡ በርካታ ልዩነቶች አሉ፡፡ ዳሩ ግን፣ ልዩነቶቹ በሁለት መሠረታዊና ተቃራኒ አቋሞች ላይ የተመሠረቱ ናቸው፡፡ የመጀመሪያው አቋም አራማጆች ሴተኛ አዳሪነት የሴቶችን የሰውነት ክብር የሚያዘቅጥ ለብዝበዛና ለባርነት የሚዳርግ በመሆኑ ሕጋዊ ገደብ ሊበጅለት ከተቻለም ሊጠፋ ይገባል ሲሉ ይሟገታሉ፡፡ በሌላ በኩል፣ በተለይ ከቅርብ ጊዜያት በኋላ የተነሱና ከዚህ አቋም በተቃራኒው የቆሙ እንስታውያን፣ ሴተኛ አዳሪነት ምክንያታዊና አሳማኝ የሴቶች ምርጫ እንደሆነ ይገልፃሉ፡፡ ወንዶችን ብቻ ለማኖር ተመቻችቶ በተሠራው ባህልና ማኅበራዊ ሥርዓት ውስጥ ለማኅበረ ኢኮኖሚያዊው ፍላጐታቸው መሟላት ሴተኛ አዳሪነት አንዱ አማራጭ ነው፡፡ ሴቷ በዚህ ሥርዓት ውስጥ ፈቃድና ምርጫዋን በነጻነት የምትፈፅም፣ የምትሠራውን የምታውቅ፣ ለድርጊቶቿ ኃላፊነት መውሰድ የምትችል፣ በጥቅሉ ሙሉ ሕልውና ያላት "*agent*" ናት ይላሉ (ፒቼር፣ 2009፣ 4) ፡፡ በሁለቱ ወገኖች መኃል የሚካሄዱ ክርክሮች ሠፊና ጥልቅ በመሆናቸው ሁሉንም ጠቅልሎ ማንሳት ይከብዳል፡፡ ይሁንና ጥቅል መንፈሱን ለማሳየት ጥቂት ነጥቦችን እነሳለሁ፡፡

የተጐጂነት (*victim*) ሐሳብን ይዘው የሚከራከሩ እንስታውያን ሴተኛ አዳሪነት የሴት ልጅን የሰውነት ክብር ያጠፋል፣ ያረከሳል ሲሉ ከሚያነሷቸው ጉዳዮች አንዱ በደንበኛውና በሴቷ መካከል ያለው ግንኙነት ኢ-ሰብዓዊ (*impersonal*) መሆኑ ነው፡፡ ደንበኞቿ (ወንዶቹ) እንደሰው ተገቢውን ቦታና ክብር መስጠት ቀርቶ በትክክል ገጽታዋን እንኳን አይመለከቱም፡፡ ሚናዋ የደንበኞቿ ወሲባዊ እርካታ ማረጋገጥ ብቻ ነው ሲሉ ይሟገታሉ (ፕሪማራትገዝ፣ 1993፣171)፡፡ ይህን ሙግት የነጻ ሰውነት (*agent*) ሐሳብ አራማጆች አይቀበሉትም፡፡ በዚህ ሕይወት ውስጥ አዘውትረው የሚመጡ ደንበኞች ስላሉ "ሰብዓዊ" የሆኑ ግንኙነቶች ይፈጠራሉ፡፡ ስለሆነም አጠቃላይ ግንኙነቱን ወይም ሙያውን "ኢ-ሰብዓዊ" ብሎ መፈረጅ ተገቢ አይሆንም፡፡ ከዚህ ባለፈ ግን ሲጀመር ሥራው ራሱ "ሰብዓዊ" መሆን ያለበት ለምንድ ነው? ሲሉ ጥያቄ ያነሳሉ፡፡ ምክንያቱም በሰርከ ሕይወታችን ባሉን ፈርጀ ብዙ መስተጋብሮች ውስጥ 'ሰብአዊ' ግንኙነቶች ውሱን ናቸው፡፡ ለምሳሌ፡-በምንገዛቸው በምንሸጣቸው እቃዎች እና በእኛ መካከል "ሰብአዊ" ግንኙነት በአብዛኛው የለም፡፡ እርግጥ ነው ሲጀመር እቃ ስለሆነ ሰብአዊ የሆነ ጥያቄ ላይነሳበት ይችላል፡፡ ወሲብ ሲባል ግን ወዲያው "ሰብአዊ" የሆነው ጉዳይ አብሮ ይነሳል፡፡ ለዚህ ደግሞ ምክንያቱ ለአጠቃላይ ወሲብ ያለን ባህላዊ እና ማኅበራዊ አመለካከት ነው- ወሲብን ከጋብቻና ከፍቅር ጋር ብቻ አቆራኝቶ መመልከት፡፡ ይህ ደግሞ ሁለንተናዊ እውነት አይደለም፡፡ ከፍቅር ውጪ የሚመሠረቱ ትዳሮች የተለመዱና እረዥም ጊዜን ያስቆጠሩ ናቸው፡፡ (ለምሳሌ በተጋቢዎቹ ሳይሆን በቤተሰቦች መፈቃቀድ ለተለያየ ማኅበራዊ ትርፍ ሲባል የሚመሠረት ትዳርን ማሰብ ይቻላል፡፡) በፍቅር ላይ በተመሠረቱ ትዳሮችም ውስጥም ቢሆን ወሲብ የፍቅር መገለጫ የማይሆንባቸው አጋጣሚዎች ጥቂት አይደሉም፡፡ ስለሆነም ይህ መመዘኛ ሴተኛ አዳሪነትን ለይቶ የሚያስኮንን አይሆንም ሲሉ ይከራከራሉ (ዝኒ ከማሁ፣ 172)፡፡

ሴቷን ለወሲባዊ እርካታ ብቻ እንደሚውል እንደ አንድ መሣሪያ ወይም መገልገያ የሚያስቆጥር፣ የሰውነት ክብርን አሣጥቶ ጥቅም ላይ ከዋለ በኋላ ከሚወረወር እቃ ጋር የሚያስተካክላት ነው መባሉም ተገቢ እንዳልሆነ የ"*agent*" ሐሳብ አቀንቃኞች ይናገራሉ፡፡ ምክንያቱም ወሲብ የተፈፀመው በግዳጅ እስካልሆነ ድረስ ይህ ጥያቄ ያለቦታው የተነሳ ይሆናል፡፡ በዚህ ዓይነቱ ግብይት ውስጥ ደንበኛው (ወንዱ) ወሲብን የሚያገኘው በበላይነት፣ የባለቤትነት ስሜትና በግዳጅ ሳይሆን በጋራ መግባባትና በገበያ ስምምነት ነው፡፡ በዚህ ተግባር ውስጥ ሴቷ ወሲባዊ እርካታን ልታገኝም ላታገኝም ትችላለች፡፡ በመሆኑም "ለሴቷ ወሲባዊ እርካታ የለውም" የሚል ማጠቃለያ ላይ መድረሱ ተገቢ አይሆንም፡፡ ከዚህ በላይ ዋና ነጥብ ግን በግብይት ድርድሩ ወቅት የሴቷ ወሲባዊ እርካታ እስካልተካተተ ድረስ እርካታውን ከግንኙነቱ መጠበቅ ተገቢ አይሆንም፡፡ ወንዱ የጠበቀውን (የከፈለበትን) ወሲባዊ እርካታ ወይም አገልግሎት ከሴቷ እስካገኘና በምላሹም የሚፈለግበትን ክፍያ እስካከናወነ ድረስ በፈቃድ ያደረገችው ተግባር ሰብዓዊነቷን የሚነፍግ ሊሆን አይችልም (ዝኒ ከማሁ፣ 173)፡፡ [9]

ብዙ ጊዜ ሴተኛ አዳሪነት "የትክክለኛ" ሴትነት ተፃራሪ ተደርጐ ይታያል፡፡ በመሆኑም የተገኟ "*victim*" ሐሳብ አቀንቃኞች አባዊው ሥርዓት ረቂቅና አስገዳጅ የሆኑ ሥነ ልቡናዊና ማኅበራዊና ሁኔታዎችን በመፍጠር ሴተኛ አዳሪዎች የራሳቸውን እና የአጠቃላይ ሴትነትን ሥዕል እንዲያበላሹ እንደ መሣሪያ ይገለገልባቸዋል ሲሉ ይከስሳሉ፡፡ ይህን ሐሳብ አውትሹርን (Outshoorn) እንዲህ ሲል ያጠናክረዋል፤ "*The prostitute is not deemed to perpetrate an immoral act; rather she is taken to be the victim of an immoral institution, the existence of which flows from unjust social structures within which women are exploited as sex object*" (2004፣ 527)፡፡ በጥቅሱ እንደተገለፀው የሴተኛ አዳሪነት ተግባር ከሥነ ምግባር ውጪ መሆን የሚያሳየው ሴትነት ወደ መገልገያ ዕቃነት እንዲወርድ የፈቀደን ፍርደ ገምድል ማኅበራዊ ሥርዓት ነው፡፡ አባዊ ሥርዓት በገነነበት ሁኔታ ውስጥ ወንዱ የሴትነትን ትርጉምና ሚና፣ የሥነ ምግባር ሚዛኑንም ጭምር ባስፈለገው ጊዜ ሁሉ መለወጥ ይችላል፡፡ የሴት ገላም ወንዱ እንዳሻው የሚያዝበት "ንብረቱ" ነው፡፡ ይህንን አስመልክቶ ኮርኔል (Cornel) ተከታዮቹን ሞጋች ጥያቄዎች ይሰነዝራል፤

> *Can't we make the argument that someone who has violated her own bodily integrity no longer has a self to represent? To put it somewhat differently, hasn't*

---

[9] ለምርምር በመረጥኳቸው የአማርኛ ድርሰቶች ውስጥ ይህንን ሁኔታ ማጤን ይቻላል፡፡ ለአንዳንዶች በሴተኛ አዳሪነት ውስጥ ወሲባዊ እርካታ የማይታሰብ ነው፡፡ ለምሳሌ፣ *ሰለት አላፊ* ውስጥ የምትገጥመን ሴት አራት አመት በኖረችበት በዚህ ሥራ ውስጥ እርካታ የሚባል ነገር አግኝታ እንደማታውቅ፣ እንዲያውም ከደንበኞቿ ጋር ስትተኛ ወደ በድንነት እንደምትቀየር ትናገራለች (ገጽ፣ 325)፡፡ በ*ሰለት አላፊ -2* የምናገኛት ሴተኛ አዳሪ ደግሞ ሥራዋን በትክክል ለመሥራት እና ደንበኛው የከፍያውን ያህል ደስታና እርካታ እንዲያገኝ ሴቷ እራሷ ልትደሰትና ልትረካ እንደሚገባ ትገልፃለች (ገጽ 134)፡፡

*she shown that her imaginary domain has been completely shattered, that she has not been able to become a self, a subject of a life, and thus cannot represent herself because she has reduced herself to an object, herself?* (1998,53)

የነጻ ሰውነት አስተሳሰብ አራማጆች በወሲባዊ ተጓዳኞች መካከል የጋራ ታማኝነት አልያም በስምምነት የአንድ ወገን ብቻ ታማኝነት ያለ ቢሆንም ታማኝነቱ ከሴቷ ብቻ መጠበቅ የለበትም ይላሉ፡፡ ለዚህ ደግሞ የሚያቀርቡት ምክንያት ብዙዎቹ የሴተኛ አዳሪ ደንበኞች ባለትዳር ወንዶች መሆናቸውን ነው፡፡ እንደ ሴት ልጅ ከብር መገለጫ ተደርጐ የሚታሰበው የትዳር ሕይወትም ቢሆን ሲጀመር ሴተኛ አዳሪነትን ለማስኮነን አቅም ያለው አይደለም፡፡ ምክንያቱም ከላይ እንደተገለፀው የተቋሙ ህልውና የሴቷ ታማኝነት ላይ ስለሚመሠረት፡፡ እንደዚያ ከሆነ ደግሞ ባለትዳር ሴት ሁሉ እንድትታመንና ለፍቅር ስትል ብቻ ያገባች እንድትሆን ይጠበቅባታል፡፡ ይህን የሚያፈርሱ በርካታ አጋጣሚዎችና ሁኔታዎች አሉ፡፡ ለምሳሌ፣ ቁጥራቸው ቀላል የማይባል ሴቶች ጋብቻን የሚፈጽሙት ለማኅበራዊ ከለላ አልያም ለኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታው ሲሉ ነው፡፡ አሸር (Ussher) እንደምታስረዳው፣ ስለዚህ ሴተኛ አዳሪነትም ልክ እንደ ሌሎቹ ወሲባዊ ስምምነቶች ሊቆጠር ይገባል፡፡ በሴተኛ አዳሪነት ሕይወት ውስጥ ያሉ ሴቶች በደላሎች፣ በወሲብ መንደር ጠባቂዎች (*brothel keepers*) ፣ በቡና ቤት ባለቤቶች ወዘተ ጫና እስካልደረሰባቸውና እራሳቸው የራሳቸውን መንገድ የሚወስኑ እስከሆኑ ድረስ ሴትነትን አላዋረዱም (2006፣527)፡፡ ይህንኑ ሐሳብ Heather እንደሚከተለው ታጠናክረዋለች፤

> "*Although most feminists would agree that women's ability to work outside the home for wages is positive step forward for women, many are decidedly conflicted when women chose prostitution as their employments. Despite the fact that it is still one of the few professions in which women earn as much, if not more than men*" (2004,149) .

እነዚህ ነጥቦች በዘርፉ ስርከ ከሚመላለሱ ሙግቶች መኻል ጥቂቱ ብቻ ናቸው፡፡ በሐሳቦቹ አማካይነት ለጥናት የተመረጡትን ድርሰቶች መመርመር ከመጀመሬ በፊት፣ በዘመናዊው ነገረ ፆታና ነገረ ወሲብ ውስጥ ዓቢይ ማቀንቀኛ የሆነውን ጽንሰ ሐሳብ፣ "*agency*"ን በጥቂቱ ማብራራት የሚገባ ይመስለኛል፡፡ ዛሬ ላይ እንስታውያን ቢቃሉ አብዝተው ሲገለገሉ ይግጠመን እንጂ፣ ጽንሰ ሐሳቡ የሰው ልጆችን አጠቃላይ ነጻነት ለማስረዳት በባህል ጥናት ውስጥ ጥቅም ላይ ሲውል የኖረ ነው፡፡ "ኤጀንሲ"ን ለመደንገግ በሚሞክሩ ብያኔዎች ውስጥ ተደጋግመው የሚገጥሙን ነጥቦች አሉ፡፡ ከእነዚህ ውስጥ በተለይ ነጻነት፣ ሉዓላዊነት፣ አመክንዮ፣ ኃላፊነት፣ ምርጫ፣ በፈቃድና በዕውቀት የሚፈጸም ድርጊት ተጠቃሾች ናቸው፡፡ እነዚህ ጉዳዮች የነገረ ሰብእ (የሰው ልጅነት) መከሰቻዎች በመሆናቸው ኤጀንሲን "የተሟላ ሰብዓዊ ህልውና" ብለን ማሰብ የምንችል ይመስለኛል፡፡ ይህንን ለማጤን በሥነ ጽሑፍ ጥናትና በባህል

ጥናት አጅግ የገነኑትን የካለርንና የቤከርን ብያኔዎች አንመልከት፡፡ በካለር ብያኔ እንጀምር፤ *"The question of 'agency'* [---] *is the question of how far we can be subjects responsible for our actions and how far our apparent choices are constrained by forces we do not control"* (45)፡፡ ቤከር በፊንታው እንዲህ ይላል፤ *"Agency has commonly been associated with notions of freedom, free will, action, creativity, originality and the possibility of change brought about through the actions of sovereign individuals"* (2004 ,4).

## 3.1.1. ሴተኛ አዳሪነት በኢትዮጵያ

በባህል ጥናት የሚከናወን ቴክስታዊ ትንተና በተሟላ ሁኔታ ይፈጸም ዘንድ ቴክስቱ ከተመሠረተበት ባህል የሚጠይቀው የመተርጎሚያ ዐውድ አለ፡፡ ይህንን ዐውድ ለመፍጠር ያግዘኝ ዘንድ ሴተኛ አዳሪነት በኢትዮጵያ ምን እንደሚመስል አጭር የታሪክና የባህል ቅኝት አካሂዳለሁ፡፡ ሴተኛ አዳሪነት በአገራችን መች እንደተጀመረ በእርግጠኝነት መናገር አይቻልም፡፡ ነገር ግን፣ ለጉብኝት፣ ለሃይማኖት አገልግሎትና ለሌሎች ተልእኮዎች ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ከነበሩ የውጭ ሰዎች የጉዞ ማስታወሻዎች የተገኙ መረጃዎች እደሚጠቁሙት ሴተኛ አዳሪነት በባህላችን ውስጥ ረጅም ዕድሜ አለው፡፡ ሪቻርድ ፓንክረስት በእነዚህ መረጃዎች ላይ ተመሥርተው ባዘጋጁት መጣጥፍ፤ "The History of Prostitution in Ethiopia" (1974)፤ አሁን የምናውቀውን ዓይነት ሴተኛ አዳሪነት ይምሰል አይምሰል ማረጋገጥ ባይቻልም፣ ከመካከለኛው ዘመን አንስቶ መሰል ተግባር በአገሪቱ የተለያዩ ክፍሎች ይከናወን እንደነበር ያስረዳሉ፡፡

በፓንክረስት እምነት መሠረት፣ ለሴተኛ አዳሪነት መስፋፋት ቀዳሚው ምክንያት በመካከለኛው ዘመን ቋሚ የሆነ የመንግሥት መቀመጫ ባለመኖሩ ነገሥታቱን ተከትሎ በርካታ ሰው ከሥፍራ ሥፍራ መንቀሳቀሱ ነው፡፡ ፓንክረስት አልቫሬዝን ጠቅሰው እንደሚያስረዱት፣ ነገሥታቱን ተከትለው ከሚንቀሳቀሱ ሰዎች መኃል "አማሪት" እየተባሉ የሚጠሩ፣ ዓቢይ መተዳደሪያቸው ዘፈንና ጭፈራ ቢሆንም፣ ሴተኛ አዳሪነትን ደብለው የሚሠሩ ሴቶች ነበሩበት፡፡ ጎንደር በቋሚ መናገሻነት ከተሰየመች በኋላ ከነገሥታቱ ጋር በየቦታው ሲዘዋወር የነበረው ሕዝብ አንድ ሥፍራ ከትሞ በልዩ ልዩ ሥራዎች ተሰማራ፡፡ ከእነዚህ ሥራዎች መኃል አንዱ ሴተኛ አዳሪነት ነበር፡፡ ይህን ተከትሎም ሴቶች ከተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች ለዚሁ ተግባር ወደ ከተማዋ መግባት ከመጀመራቸው በተጨማሪ በቀሪዎቹም የአገሪቱ የፖለቲካ እና የንግድ ከተሞች ሙያው እየደራ መጣ፡፡ ወደየከተሞቹ በልዩ ልዩ ምክንያቶች ከሚጓዙ ወንዶች መኃል በደረጃ ከፍ ያሉት ሚስቶቻቸውን ይዘው ሲሄዱ፣ በደረጃቸው ዝቅ ያሉት ግን በየደረሱበት ከነዚህ ሴቶች ጋር ይወዳጃሉ፡፡ በወታደር ካምፖችና በወደብ ከተሞች የነበረው ሁኔታ

ከዚህ ይብስ እንደሆን እንጂ በጭራሽ አያንስም፡፡ በእነዚህ ሥፍራዎች ዋና ሥራቸው ሴተኛ አዳሪነት ከሆኑት በተጨማሪ መጠጥ በመሸጥ ይተዳደሩ የነበሩት ሴቶች በተደራቢነት ያከናውኑት ነበር፡፡ ፓንክረስት የኤርትራ በጣልያን ቅኝ መውደቅ በኋላኛው ዘመን ለታየው የሴተኛ አዳሪነት መስፋፋት ትልቅ ሚና እንደነበረው ያስረዳሉ፡፡ ብዛት ያላቸው የጣልያን ወታደሮች በከተማዋ መቀመጥ የሴተኛ አዳሪዎችን ተፈላጊነት እንዲጨምር አድርጓል፡፡ በስተመጨረሻም አዲስ አበባ መናገሻነቱን ስትረከብ ሴተኛ አዳሪነትም አብሮ መድራት ጀመረ፡፡ በአዲስ አበባ ሴተኛ አዳሪነት በተለየ ሁኔታ ከጠጅ እና ከጠላ ቤቶች ጋር የተቆራኘ ነበር፡፡ ይህም ለዘመናዊ ገጽታው ትልቁን ሚና እንደተጫወተ ይገመታል፡፡

ከላይ በተጠቀሱት ዘመናት ሴተኛ አዳሪነት የተለያየ ገጽታ፣ ማኅበራዊ ደረጃና ስያሜ እየተሰጠው ቆይቷል፡፡በሌሎች የአገር ውስጥ ቋንቋዎች የሚሰጡትን ትተን በአማርኛ የተሰጡትን ብቻ እንኳን ስናይ ትንሽ የሚባሉ አይደሉም፡፡ አልቫሬዥ ከጠቀሳቸው "አማሪቶች" አንስቶ "ጋለሞታ"፣ "ዘማ"፣ "ሸርሙጣ" እና "ሴተኛ አዳሪ" ጥቂቶቹ ናቸው፡፡ ነገረ ወሲብ በባህል እና በዘመን የሚዳኝ እንደመሆኑ ዛሬ ከእነዚህ ሁሉ መጠሪያዎች ለጥናት በመረጥኳቸው ድርሰቶች ውስጥ ግልጋሎት ላይ ሲውሉ የሚታዩት ሸርሙጣ እና ሴተኛ አዳሪ የሚሉት ብቻ ናቸው፡፡ "ሴተኛ አዳሪ" የሚለውን ቃል ደስታ ተክለ ወልድ "መበለት፣ ባል አልባ፣ ብቻዋን የምታድር፣ የምትኖር" (ገጽ 1210) ሲሉ ይፈቱታል፡፡ በዘመን ለድርሰቶቹ የሚቀርበው *የአማርኛ መዝገበ ቃላት* ደግሞ "ሴተኛ አዳሪ" የሚለውን ተመሳሳይ መጠሪያ፣ "በሸርሙጥና የምትተዳደር ሴት፣ ሸርሙጣ" ሲል ይፈታዋል (1993፣ 134)፡፡ ሪቻርድ ፓንክረስት፣ "ሸርሙጣ" የሚለው መጠሪያ ከአረብኛ የተወሰደ መሆኑን በመጀመሪያ በኤርትራ የነበሩ ጣልያኖች ይገለገሉበት እንደነበር፣ ከዚያም በአረብ ነጋዴዎች አማካይነት እየተስፋፋ ቆይቶ ወደ አማርኛ መድበለ ቃላት እንደዘለቀ ያስረዳሉ (ገጽ 169)፡፡ "ሸርሙጣ" የሚለውን ቃል *የአማርኛ መዝገበ ቃላት* ሲፈታው፣ "1.እምንዝራ 2.ሴተኛ አዳሪ 3. በባህርይው አንዴ ከአንዱ ሌላ ጊዜ ከሌላው የሚሆንና ነገር የሚያወሳስብ ወረተኛ" ይለዋል (ገጽ144)፡፡ የደስታ ተክለ ወልድ የሴተኛ አዳሪ ፍቺ በ*የአማርኛ መዝገበ ቃላት* ከቀረበው የዛሬ ፍቺ የተለየ ነው፡፡ ይህ እውነታ የነገረ ወሲብን በዘመንና በባህል መለዋወጥ ጠቋሚ ሊሆን ይችላል፡፡

ይህ ጥናት ከሴት ሴተኛ አዳሪዎች በተጨማሪ ተመሳሳይ ግብር ያላቸውን ወንዶችም ይመለከታል፡፡ ይሁንና ለወንዶቹ የተሰጠ ስያሜ በባህሉ ውስጥ ማግኘት አልቻልኩም፡፡ "ሸርሙጣ" የሚለው መጠሪያ በቋንቋ ደረጃ ጾታ ባለመለየቱ ለግልጋሎት የተመቸ ቢመስልም፣ በፍቺ ደረጃ ከሴተኛ አዳሪ የበለጠ አሉታዊነት የሚታይበት ስለመሰለኝ ልገለገልበት አልፈቀድኩም፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ሴተኛ አዳሪ ከሚለው መጠሪያ "ወንደኛ አዳሪ" የሚል ሐረግ መምዘዙ ቀና ቢመስልም ባህላዊ ተገቢነት የሚጎድለው ይመስለኛል፡፡ ምክንያቱም በባህሉ ከተለመደው የወንድነት ፍቺ ጋር አይገጥምም፡፡ ወንድነት

የጾታ ብቻ ሳይሆን የማኅበራዊ ሚናና ሥፍራም ጉዳይ ነው:: ስለሆነም ወንዶቹ ("ግብረ ሰረዶማውያኑ") በተለምዶ የሴት የሆነውን ተግባር ስለወረሱ[10] ሴተኛ አዳሪ በሚለው ቃል መገልገሉ የተሻለ አማራጭ እና ተገቢም ይመስለኛል::

### 3.1.2. ሴተኛ አዳሪነት በምዕተ ዓመቱ መባቻ በታተሙ አምስት የአማርኛ ድርሰቶች ውስጥ

በቅድሚያ ከድርሰቶቹ፣ በተለይም ከ*መኃልየ መኃልየ ዘ ቺቺኒያ*፣ ከ*ሰዓት እላፊ*፣ ከ*የቺቺኒያ ሚስጥራዊ ሲሊቶች*እና ከ*ሰዓት እላፊ 2*፣ ለቅመን የምንገምደውን መንፈስ በመንደፍ ልጀምር:: ድርሰቶቹ የበቀሉበት ባህል "በወሲባዊ አፈንጋጭነት" የሚያነውራቸውን፣ የሚወነጅላቸውንና ሥፍራ ነስቶ የገፋቸውን ወገኖች ራሱ ሠርቶ እንዳቋቋማቸው፣ አቅም አጥተው እንዳይጠፉም በስውር ጉልበት እየሰጠ እንደሚያለመልማቸው በዘይቤ፣ በትዕምርት ያሳያሉ:: በዚህ ብቻ አይወሰኑም:: ይህ አድራጊና ፈጣሪ ዓለም ራሱ ፈጥሮ መልሶ በሚኮንናቸው ወገኖች ኃይሉን እንደሚነጠቅ ይተነብያሉ::

በድርሰቶቹ ውስጥ ሴተኛ አዳሪነት በዓይነቱ በዝቶ፣ በባሕርይው ተወሳስቦ፣ በደረጃ ልቆ በእርከን እየተከፋፈለ ጭምር ነው የሚገጥመን:: በነባሮቹ በ"ገዳም" እና በ"በረሃ" አምሳያ መንደር አደራጅተው የሚሠሩ ሴተኛ አዳሪዎችን (*brothel prostitutes*)፣ በየጐዳናዎቹ በየጥጋጥጐቹ የሚቆሙ ሴተኛ አዳሪዎችን (*street prostitutes*) እንዲሁም በተለያዩ ቡና ቤቶች ውስጥ የሚገኙ ሴተኛ አዳሪዎችን (*bar ladies*) በዓይነት በዓይነት እናያለን:: ለብዙዎቹ ሴቶች የሴተኛ አዳሪነት ሕይወት፣ ሲከፋቸው ለመሸሸጊያ፣ ሲቸግራቸው ቀን ለማሳለፊያ ፈጥኖ ወደ ጭንቅላታቸው የሚደርስ አማራጭ ነው:: አለበለዚያ ቀድመው የመረጡትን ሌላ ሥራ በሽፋንነት፣ በማደናገሪያነትና በድልድይነት ይሠራሉ:: ለዚህ ደግሞ የተመረጡት የሥራ ዘርፎች፣ የኪከና የሆቴል ቤት አስተናጋጅነት፣ ፓርኪንግ እና የቤት ውስጥ ሠራተኛነት ናቸው:: ሴቶች ፈጥነው ወደ ሴተኛ አዳሪነቱ ባያመሩ እንኳን እነዚህ የሥራ ዘርፎች ያለጥርጥር በቀጥታይነት ያደርሷቸዋል::

ለተወሰኑት የሴተኛ አዳሪነት ሕይወት ከእናት፣ ከአክስት፣ ከእህት፣ ከጐረቤት አልያም ከአካባቢ የሚወረስ ይሆናል:: ለሌሎቹ ደግሞ ጥብቅ ከሆነ ቁጥጥር ካለበት ሕይወት ወጥተው የሚቀላቀሉት ነው:: እነዚህ ሴቶች በጠበቀ ማኅበር ውስጥ አድገው፣ ያደጉበት ማኅበር "ጥፋት" ብሎ የፈረጀውን፣ "እርኩስ" እያለ ያወገዘውን ሕይወት በቀዳሚነት፣ "የተሻለ" ብለው ይመርጣሉ:: አልያም ወደዚህ

[10] ለዚህ ማረጋገጫ ለጥናት ከተመረጡት መጻሕፍት መካከል ይህ ጉዳይ በስፋት የታየበት *የሰዶም ነፍሳትን መመልከት* ይቻላል:: ለሴተኛ አዳሪነት የሚመረጡት የሴት ባሕርይ ያላቸው እና እራሳቸውን እንደ ሴት የሚቆጥሩት "ወጪ" ግብረ ሰዶማውያን ናቸው (ገጽ 154)::

ሕይወት የሚወስደው መንገድ ሲቀርብላቸው ያለምንም ማንገራገር ይቀበላሉ፤ መቀበል ብቻ ሳይሆን ሥራውን፣ ሕይወቱን በቀላሉ ይለምዳሉ፡፡

"ተጎጂ" እና "ነጻ ሰውነት" በማለት ከፍ አድርጌ ለማስረዳት የሞከርኩት የሴተኛ አዳሪነት ሁለት ገጽታ በድርሰቶቹ ውስጥ ከተስተማሰሉ ዓበይት ጉዳዮች መኃል አንዱ ነው፡፡ በንድፈ ሐሳብ ደረጃ እንዳየነው ሴተኛ አዳሪነት በአንድ በኩል፣ በማኅበረሰቡ የተሠናዳ፣ የከፋ በደል የሚፈፀምበት የአባዊው ሥርዓት አካል ስለሆነ መቅረት አለበት የሚሉ ወገኖች የሚያወግዙት፤ በሌላ በኩል ደግሞ ሴቶች ከሌላው የተሻለ አማራጭ የሚያገኙበት፣ ከአባዊው ማኅበራዊ ሥርዓት አርነት የሚወጡበት ስለሆነ የመንግሥት ጥላ ከለላ ተደርጐለት እንደ ማንኛውም ሙያ እውቅና ሊሰጠው ይገባል የሚሉ ክፍሎች የሚያወድሱት ባህላዊ ተቋም ነው፡፡ በድርሰቶቹ ውስጥ የሚገጥሙን ሴቶች ከተወሰኑት በቀር ብዙዎቹ ልዩ ልዩ ማኅበራዊና እና ሥነ ልቡናዊ በደል የደረሰባቸው፣ የተሻለ አማራጭ አጥተው ወደ ሴተኛ አዳሪነት ሕይወት የገቡ ናቸው፡፡ ይሁንና ሥራውን ከጀመሩ በኋላ በዛው ለሕይወቱ የሚኖራቸው ግምትና አመለካከት አንድ ዓይነት አይደለም፡፡ ሕይወቱንና ሴቶቹን በጥቅሉ ቁርጥ አድርጐ ተጐጂ (*victim*) ማድረግም ይሁን ነፃ ሰው (*agent*) ማለት አስቸጋሪ ነው፡፡ ጥቂቶች ብቻ ጠቅልለው በአንድ ጐራ የሚገቡ ይሆናሉ፡፡ በመሆኑም አንድ አቋም ከመያዝ ይልቅ ሁለቱንም ወገኖች እንዳመዛኘነታቸው በመከፈል በድርሰቶቹ ውስጥ እንዴት እንደተሳሉ ለማሳየት እሞክራለሁ፡፡

### 3.1.2.1. ተጐጂ ወገኖች

"ተጎጂነት" በዚህ ዐውድ ውስጥ የባህሉ ሰለባ (*victim*) መሆንን የሚያመለክት ቃል ነው፡፡ በአማርኛ የሥነ ጽሑፍ ልማድ ውስጥ መላልሰው የሚገጥሙን ሴተኛ አዳሪ ገጸ ባሕርያት አንደኛ፣ ራሮት የተጫናቸው፣ መገለልን፣ መነጠልን የሚያዘምሩ፤ መናቅን፣ ከቁጥር መጉደልን፣ ከሰው አለመቆጠርን የሚያሳስቡ፣ በታዋቂዋ የእንስታዊነት አቀንቃኝ በ ደ ቦቭዋ ቃል ልገልገልና፣ "ፍጹም ሌላ" (*The absolute Other)* ናቸው፡፡ ሴቶቹ ስም አይኖራቸውም፣ ወይንም ቢኖራቸውም የ"በረሃ" መጠሪያ እንጂ የምር ስማቸው አይደለም፡፡ ይህ የሚነግረን ብዙ ነገር ይኖራል--በተለይ እንደ ግዑዝ አካል የወል መጠሪያ እና መታወቂያ እንጂ ግለሰብ ምንትነት ማጣታቸውን፡፡ ብዙዎቹን በ"ትክክለኛ" ስማቸው ብቻ ሳይሆን በግብርም ለይተን እናውቃቸውም፡፡ በብዙዎቹ የአማርኛ ድርሰቶች ውስጥ የመገኘታቸው ምክንያት በአንድ በኩል፣ ለዓበይቱ ወንድ ገጸ ባሕርያት "ቅጥ ያጣ" ፍትወት መገልገያነት ለመዋል፤ በሌላ በኩል፣ በእነርሱ ማንጸሪያነት ከሰው ቆጥረን የተቀበልናቸውን ወንድ ገጸ ባሕርያት በሥነ ምግባር ደንቦች መመዘን እንድንችል እድል ለመስጠት ነው፡፡ ይህ ደግሞ በባህሉ ብቻ ሳይሆን፣ ባህሉን በቀዱት ድርሰቶች ውስጥ ሥፍራ መነፈጋቸውን፤ ወይንም ከሁለተኛ "ዜጋ" መቆጠራቸውን የሚያሳይ ይመስለኛል፡፡

ለምርምር በመረጥኳቸው ድርሰቶች ውስጥ ከሚገጥሙን ሴተኛ አዳሪ ገጸ ባሕርያት መኃል ከፊሎቹ የዚሁ መንፈስ እስረኞች ናቸው፡፡ እነዚህ ሴቶች የገቡበትን ሕይወት ጠልተው፣ ኑሮውን እንደ እርካሽና ኃጢአት ቆጥረው፣ ራሳቸውን ተጠይፈው በማኅበራቸውም ተንቀው የሚኖሩ ናቸው፡፡ አንዳንዶቹ ይሄን የጠሉትን ሕይወት ለመለወጥ ይፈልጋሉ ግን መውጫው ጠፍቷቸው የሌላን አካል እርዳታ (ብዙ ጊዜ ለጋብቻ የሚጠይቅን ባል) ይጠብቃሉ፡፡ አልያም ሕይወቴ አይለወጥም ብለው ተስፋ ቆርጠው ይቀመጣሉ፡፡ የተወሰኑ ምሳሌዎችን በመጥቀስ ሐሳቡን ለማብራራት ልሞክር፡-

**ምሳሌ አንድ፡-** *መኃልየ // ቹቹኒያ* ፡፡ በዚህ ድርሰት ውስጥ "ሚጢጢ" በሚል ርእስ የቀረበ አንድ ታሪክ አለ፡፡ በዚህ ታሪክ ውስጥ የምናገኛት ሴተኛ አዳሪ አስራ ስድስት አመት እንኳ በቅጡ ያልሞላት ነች፡፡ አባትዋን የማታውቅ፣ ሴተኛ አዳሪ እናቷን በሞት ያጣች በመሆኗ የራሷን እና የታናሽ ወንድሟን ሕይወት የማቆየት ኃላፊነት ወድቆባታል፡፡

> እናቷ ስትሞት ወንድሟ የሶስት አመት ሕጻን እንደነበረ አስታወሰችና ቀጠለች [ይለናል ተራኪው]፤
>
> "ብርድ መቷት ሳንባዋ ተነክቶ ሞተች እድርም ማኅበርም ዘመድም ስላልነበራት ጎረቤትና መንገደኛ ተባብሮ ነው ያስቀበራት ወንድሜን አዝዬ ቀብር ቦታ ድረስ ሄጃለሁ ግን አላለቀስኩም ያኔ ምን እንደነካኝ አላውቅም አንዲት ፍሬ እንባ እንኳን አላፈሰስኩላትም ከቀብር ስንመለስ የምንገባበት ቤት እንደሌለን ሳውቅ ነው ማልቀስ የጀመርኩት" (ገጽ 70)

ሴተኛ አዳሪነት የመጀመሪያ ምርጫዋ ስላልነበረ ችግሯን በሌላ መንገድ ለማምለጥ ሞክራለች፡፡ ይሁንና ማምለጫ ይሁኑኝ ያለቻቸው ሥራዎች ችግሯን አቃለው ከማሳረፍ ይልቅ ወደዚህ ሥራ የገፏት ነበሩ፡፡

> እድሜዋን ለማስላት ሞከርኩ አስራ አንድ አመት ቢሆናት ነው፡፡
>
> "ያኔ ማታም ቀንም የቻልኩትን ያህል እያዘጋጀሁ በየቦታው እያዞርኩኝ እሸጥ ነበር ቆሎ፣ ለውዝ፣ ሲጋራ፣ ማስቲካ፣ ሳንቡሳ እያልኩ ጥሩ ተንቀሳቅሼ ነበር እሳቸው ደግሞ ልጅ አስቸገረኝ ኑሮም ተወደደ እያሉ ገንዘብ ይጨመሩብኛል ልጁ ደግሞ በየቀኑ ጉዳት ይደርስበታል ግራ ሲገባኝ አንዱ ደላላ ከነወንድምሽ የሚያኖርሽ ስራ ላስገባሽ ብሎ የሆነ ሰውዬ ቤት አስቀጠረኝ ሰውየው "ሚስትና ልጆች አሉኝ ሲመጡ እንደቤተሰብ እናሳድጋችኋለን ለጊዜው ቤት ካፀዳሽና የምትችይውን ምግብ ካበሰልሽ "ይበቃል" ብሎ ነበር ያስገባኝ ሳይውል ሳያድር ግን ሰው የመሰለኝ ሰውዬ ወደ አውሬነት ተለውጦ ተጫወተብኝ"
>
> የደረሰባትን መከራ ለማሰብ ሞከርኩ ወሲብ፣ ዱላ፣ ጭንቀት፣ ስቃይ፣ ብቸኝነት፣ ብሶት ፡፡ [---]
>
> "ሴትየዋ ጋር ሄጄ እግራቸው ላይ ወደቅኩ! ለምን እንደሆነ አልገባኝም ግን አልጨከኑብኝም በመምጣቴ ደስ ያላቸው መሰለኝ አቅም አንሶኛል መስራት አልቻልኩም ያቺኑ ቤት አከራይቼ የማገኘው አይበቃኝም አንቺንም ወንድምሽንም ያሳደግነው እኛ ነን እኔ ጋር ሁኑና እየሰራሽ ደግፊኝ አሉኝ ምን መስራት እንደሚያዋጣኝም ነገሩኝ፡፡ "ልጅ ነሽ ቆንጆ ነሽ እንደሌሎቹ ወጣ ብለሽ ስራውን ልመጂው" አሉኝ ያን ጊዜ ያለኝ ብቸኛ አማራጭ ምን እንደሆነ ገባኝ እዚያው ቤት ውስጥ እንዳልሰራ፡፡ እድሜሽ ያስጠይቀኛል፡፡ ስላሉኝ እንጂ በናቴ ቦታ ለመተካት ፈቃደኛ ነበርኩ ሴትየዋ ትንሽ ብር አበደሩኝ ልብስ ገዛሁበት ሽርሙጥና ምን እንደሚመስል አላውቅም

ነበር ሌሊት እንዴት እንደሚሰራ የት ቦታ እንደሚቆም ምን እንደሚባል አላውቅም መስራት እንዳለብኝ ግን አውቅ ነበርና ወጣሁ፡፡" (ገጽ 71-73)

ሥራውን ከጀመረች በኋላም ቢሆን ምንም ዓይነት የራስ መተማመን የማይታይባት፣ እራሷን የምትጠላ እና ሕይወቱን የምትጠየፍ ሴት ነች፡፡ ብዙዎች ለሥራቸው መሣሪያ አድርገው የሚጠቀሙበትን አካሏን ሣይቀር ታፍርበታለች (ገጽ 68)፡፡ ድንገት ሳት ብሏት በምትጠላው በምትጠየፈው ሕይወት ውስጥ ደስታና እርካታን ያገኘች ሲመስላት እንኳ በታዛቢ ፍራቻ ታበላሸዋለች (ገጽ 82)፡፡ በራሷ ላይ እምነት ማጣቷና ጥላቻዋ ጫፍ ከመድረሱ የተነሳ በሞት አፋፍ ላይ ሆና እንኳ ለእርዳታ የመጡላትን እጆች በመግፋት በራሷ ላይ ታምጻለች፡፡ እናም እራስን ማጥፋት በሚመስል መልኩ በሕይወቷ ገፍታበት እስከ መሞት ትደርሳለች፡፡ ይህን በደብዳቤዋ ማየት ይቻላል፤ ሽንፈቷን፣ በማኅበረሰቡ የተቀመጠላት እጣ ፈንታዋን መቀየር የማትችል ጉዳተኛ መሆኗን ትገልፃለች (ገጽ 97)፡፡

**ምሳሌ ሁለት፡-** *ሰዓት አላፊ 2*፡፡ "ከኤች አይ ቪ ጋር እኖራለሁ፣ ሆን ብዬ ያስያዝኩት ወንድ ግን የለም-ኮንዶም አልፈልግም ብለው የደፈሩኝ ተሸልመው ይሆናል" በሚል ንኡስ ርእስ ስር የቀረበ ታሪክ አለ፡፡ "የእሰላ ልጅ ነኝ፡፡ አባቴ ትራፊክ ፖሊስ ነበር፡፡ እናቴን አላውቃትም፡፡ 3 ሴቶች ወልዳ ጥላን ጠፋች፡፡ ሲቸግረን ታላቅ እህቴ፣ 'ሁሩታ' የሚባል አገር ይዛኝ ሄደች፡፡ አንዱ ግሮሰሪ ውስጥ ተቀጥራ እየሰራች ሳለ ሲቸግረን እህቴ ድንግልናሽን እንሸጥ አለችኝና ሸጥነው" (96) በሚል መንደርደሪያ መከራ የተነደፈበትን ታሪኳን የምትነግረን 18 ዓመት ያልተሞላት ባለታሪከ አምስት ትዳሮችን ይዛ ተፈታለች (ፈትታለች አላኩም)፡፡ በ12 ዓመቷ የሴተኛ አዳሪነት ሕይወት ስትጀምር እንስቶ በሌሎች ውሳኔ ሰጭነትና ምርጫ ነው የኖረችው፡፡ ሌሎች ባስቀመጧት ቦታ ከመገኘትና ቦታው እንደሚፈቅደው ከመሆን የዘለለ የራስ ባለቤትነት እና የውሳኔ ሰጪነት እንዲሁም የምርጫ ፈጻሚነት ብቃት አይታይባትም፡፡ ሁሉም ባሎቿ ስለማትወልድ ከቤት ያባርሯታል (ይፈቷታል)፡፡ ይህ ደግሞ የሚያሳየው ማኅበረሰባዊ የሆነውን ሴትን ልጅ ከእናትነት ጋር ብቻ አቆራኝቶ የሚመለከትበትን ሥርዓት ነው፡፡ በመሆኑም የተፈጠረችበትን ልጅ የመውለድ አገልግሎት የማትሰጥ ከሆነ ብቻዋን ሥፍራ የላትም የሚለውን አባዊ አስተሳሰብ ያሳያል፡፡ አራተኛ ባልዋን ወዳው እንደተጋቡ ትገልፃለች፡፡ ይህ ምናልባት የምርጫ ችሎታዋን የሚያሳይ ይምሰል እንጂ ነው ለማለት አይቻልም፡፡ ምክንያቱም በነፃነት የተፈፀመ አይደለም፡፡ "እስከ 3 ወር ድረስ በየቀኑ 100 ብር እየሰጠሁት እኖረው ነበር" የምትለው ይህ ባሏ ሲጀምር ጋብቻው እውን እንዲሆን ገንዘቧን በቅድመ ሁኔታነት አስቀምጧል፡፡ መውደዷ ማሰሪያ ሆኖ መጠቀሚያ የሆነችበት ነው፡፡ እዚህ ላይ እድሜዋም ከግምት ውስጥ መግባት ያለበት ይመስለኛል፡፡ የተለመደ ውሳኔ አልባነቷ እንዳልሆነ፣ ውሳኔም ስትሰጥ የምትሰጠው ውሳኔ ትክክለኛ መሆኑን መለየት የሚከብድ ዓይነት ነው፡፡ አጠቃላይ ታሪኩን ስንቃኘው ለሕይወቷ መበላሸት እና ወደ ሴተኛ አዳሪነት ሕይወት ለመግባቷ ዋነኛ ተጠያቂ የምታደርገው

እናቷን ይሁን እንጂ ከዛ በኋላ ወንዶች እንደ "ባሪያ" ያለ ፈቃድዋ ሲያሽከረክሯት፣ የባሪያን ያህል እንኳ ከብር ነፍገው ከዕቃ ቆጥረው ህመሟን ማሰብ፣ ስቃይዋን ማየት፣ ሰቆቃዋን ማድመጥ እየተሳናቸው ሲያሰቃይዋት ኖረዋል፤ ፡

"... ሰውዬው ኃይለኛ ሴከስ ያደረገኝ ነበር፡፡ በየቀኑ ማታ ማታ የወሲብ ፊልም ላይ እንደሚታየው ዓይነት እንደፈለገው ያደርገኝ ነበር፡፡ ህመሙ እያለብኝ ሕገ ወጥ ወሲብ ይፈፅምብኝ ነበር፡፡ ከ12 ዓመቴ ጀምሮ ቡና ቤና ስሰራ እንደዚያ ሰውዬ መጥፎ ወሲብ የፈፀመብኝ የለም፡፡ ብልቱ በጣም ትልቅ ነው፡፡ አንድ ጊዜ ብቻ ወሲብ ፈፅሞ አይበቃውም፡፡ ስቅይት ያደርገኝ ነበር፡፡ 'አላህ አይፈቅድም ተውሼከ ሆነህ' ስለው አይሰማኝም ነበር፡፡ በቡና ቤት ህይወቴ ያላየሁትን የወሲብ ስቃይ እዚያ ነው ያየሁት"

ሆኖም ከዚህ ሁሉ ውስጥ ጉልቶ የሚታያት የእናቷ ጥፋት ነው፡፡ እናም እሷን ይቅር ማለት ሳትችል ወንዶቹን ይቅር ትላለች፤ ሼኪውን ጭምር፡፡

"... ወንዶች ጨካኞች ስለሆኑ ይለቁ አልልም በእኛ ቤተሰብ ውስጥ በእናታችን ምክንያት ሶስታችን ሴተኛ አዳሪ ለመሆን ተገደን ነበር፡፡"

"... ወንዶች ጨካኞች ናቸው፡፡ ሼኪው አፍዛል ቁርዓን ናቸው፡፡ ሼከ ማለት ከብር ነው፡፡ ስቅይት ቢያደርጉኝም ቂም አልያዝኩባቸውም፡፡..." (ገጽ 102)

ሌላው ቀርቶ ኤች አይ ቪ እንዳለባት እያወቁ በግድ ሊገናኙዋት የሚፈልጉትን ወንዶች ለራሷ ሳይሆን ለነሱ ጤንነት አስባ በጉልበት ጭምር ታግላ ትታደጋቸዋለች (ገጽ 100)፡፡ ለወንዶች ወደ ሴተኛ አዳሪዎቹ መምጣት ተጠያቂዎቹ ሴቶቹ (ሚስቶቻቸው) ራሳቸው እንደሆኑ ትገልፃለች፡፡ በመሆኑም ሴቶች ለባሎቻቸው እንደፈለጉት እንዲሆኑላቸው ትመከራለች፡፡ የኖረችበት ወንዳዊ ዓለም ነውና እራሷንም ሌሎቹንም ሴቶች የምታየው የምትመዝነው በአባዊው ሥርዓት ዐይን ነው፡፡ ለወንዶች ፍላጎት ሙሉነት ሲባል ሴቶች መሸነፍ እንዳለባቸው ትመከራለች፡፡ ስትለብስ እንኳን የምትለብሰው በፈቃዷ አይደለም፡፡ እናም ሴትነቷን ሸፍና ፍላጎቷን ተጭና "ከጥፋት" ወንዶችን ትከልላለች፡፡

በዚሁ ድርሰት ውስጥ፣ "እናትና አባቴ በኤች አይ ቪ ሞተዋል... ሆድ ዚኘ ኖሮት ተከፍቶ የሚታይ ቢሆን ሁላችሁም ታዝኑልን ነበር..." በሚል ርዕስ የቀረበ ሌላም ታሪክ አለ፡፡ ባለታሪኳ ለቤተሰቦችዋ ሦስተኛ ልጅ ነች፤ በቤት ውስጥ ታላቋ እያለ ቤተሰቦቿን ስታጣ ራሷንና ታላቅ ወንድሟን ለማስተዳደር ኃላፊነት ትወስዳለች፡፡ ኃላፊነቱ ግዳጅ ጭምር ነው፡፡ የወደቀ ጣሳ የማያቀና ወንድሟ በገዛ ገንዘቧ እየከፈለች በምታኖረው ቤት ውስጥ አድራጊ ፈጣሪ ነው፡፡ እረፍቷን ጭምር ፈቅዶ የሚሰጣት እርሱው በመሆኑ ድካሟን ማመን አለበት፡፡ ካላመናት ሥራውን ለመሥራት ባልፈለገችበት ጊዜ ሁሉ በጉልበት እንድትሰራ ያስገድዳታል፡፡ ከራሷ እንደበት እንስማው፤

"ታላቅ ወንድም አለኝ፡፡ ግን በሕይወት እንዳለ አይቆጠርም፡፡ አንተም እንዳለ አትቁጠረው፡፡ የሱ ታናሽ ራሱን ገድሏል፡፡ ሶስተኛ ልጅ ደግሞ እኔ ነኝ" [---]

"ዕድሜው ስንት ይሆናል?"

"ስላሳ አልፎታል"

"ስራ አለው?"

"የለውም"

"በምን ይኖራል?"

"በእኔ በሽርሙጣዋ እህቱ"

"ትረጂዋለሽ?"

"ምን አደርጋለሁ..."

"ስራሽን ያውቃል?"

"ማጥም አድርጎ ያውቃል! እንደሱ ዓይነት ጨካኝና ሞራል የሌለው ወንድም ይኖራል ብዬ አልገምትም:: 'ሂጅና ሽርሙጪ' ብሎ ከቤት የሚያስወጣ ወንድም ነው:: ሴቶች ቤት ስልችት ሲለኝ እቤቴ እመጣለሁ:: ቤት መኖሬን ካየ 'ከኔ ጋር ተፋጠሽ ምን ልትፈጥሪ ነው... ሂጅና ሽርሙጠሽ ምናምን አምጪ' ይለኛል:: ውስጤ እያለቀሰ ወጥቼ እሄዳለሁ"

"ምንም አይሰማውም- እንደወንድም?"

"እሱ የሚሰማው ወንድ አይደለም:: 'ሽርሙጠሽ ብር ይዘሽ ነይ' የሚል ወንድም ነው:: አንድ ጊዜ ሴቶች ቤት ስልችት ብሎኝ ስከፊ ወደቤቴ ገባሁ:: 'መሽርሞጥ ሲገባሽ በዚህ ሰዓት እቤት ውስጥ ምን ታደርጊያለሽ' ብሎ ቢላዋ አውጥቶ ሊያርደኝ ሊጨርሰኝ ሲል አስጣልኩት:: ጧት ላይ ይቅርታ ጠየቀኝ" (ገጽ 206-208)

በአባዊው ሥርዓት ቤተሰባዊ ኃላፊነትን መሸከም የሴት ልጅ ሚና ነው:: ይህን ባህል ራሱ የሚፈጥረውን ማኅበራዊ ሚናና ኃላፊነት ሴት ልጅ የተፈጥሮ ጣጣ አድርጋ ትወስደው ዘንድ ማኅበሩ ከልጅነት ጀምሮ እየቀረጸ ያሳድጋታል:: እናም ኃላፊነቱን ሁሉ ለብቻዋ ጠቅል ትወስድ ዘንድ ራሷን ታስገድዳለች፤

"አሁን እሱንም የምታስተዳድሪው አንቺ ነሽ ማለት ነው?"

"አዎ! ግዴታዬ ነው:: እንደነገርኩህ ታላቅ ወንድሜ ታንቆ ሞተ:: እናቴ ቀድማ በኤች አይ ቪ ሞተች:: አባቴ ተከተላት:: የአባቴ የመጀመሪያ ሚስት ጅማ ትኖር ነበር እሷም ቆይታ ሞተች:: አሁን የቀረነው እኔና ብኩኑ ወንድሜ ብቻ ነን:: እሱ ከሞተ ብቻዬን እቀራለሁ:: ስለዚህ ስጋ ነውና እረዳዋለሁ:: የሚባላ ነገር አቀርባለሁ:: ለጫቱ ብር እሰጠዋለሁ:: ሲታመም አሳክመዋለሁ:: (ገጽ 208)

ሌላው ከላይ ያነሳሁትን ሐሳብ የሚያጠናክረው ታሪክ ደግሞ ከሷ ከ200ሺ. ብር በላይ የወሰደው የፍቅረኛዋ ታሪክ ነው:: ብሩን የሠጠችው ስለወደደችው እንደሆነ ትናገር እንጂ ምርጫዋ የሷን ጥቅም ባስጠበቀ መልኩ አገናዝባ ያደረገችው ሳይሆን ባለማስተዋል የተደረገ እንደሆነ በቁጭቷ ታረጋግጣለች:: ሕይወቷ ደስታ የራቀው ነው፤ ከዛ ለመደበቅ የምትሸሸው ወደተለያዩ ሱሶች ነው:: ሌላው ቀርቶ ሥራዋን ጠልታ ለማቆም ስትፈልግ ለውሳኔ ራሷን ብቁ እንዳልሆነች አድርጋ ስለምታስብ የተራኪውን ጭምር እርዳታ ትፈልጋለች:: ምርጫና ውሳኔ በሰው ልጅ ህልውና ውስጥ መሠረታዊ ጉዳዮች ናቸው:: መምረጥ አለመቻልና፣ ለውሳኔ አለመብቃት የሰው ልጅን ህልውና ጎዶሎ ያደርጋሉ:: በሴተኛ አዳሪነት ሕይወት

ውስጥ ያለች ሴት የአባዊ ሥርዓት ሰለባ ናት የሚለውን መከራከሪያ የሚያነሱ እንስታውያን ሙግታቸውን ለማጽናት ከሚያነሷቸው ነጥቦች መኃል አንዱ ለምርጫና ለውሳኔ መብቃት አለመቻልን ነው፡፡ ሴቶች በሚያልፉባቸው የሕይወት መንገዶች ሁሉ ከሰውነታቸው በፊት ሴትነታቸው ይቀድማል፡፡ እንደሙሉ ሰው ምርጫን ለመምረጥ ከመድረሳቸው በፊት በሴትነታቸው ምክንያት ወንዳዊው ሥርዓት መንገዳቸውን ሠርቶ ያቀበላቸዋል፡፡

**ምሳሌ ሦስት፡-** *ሰዓት አላፊ* ፡፡ በሰዓት አላፊ የመጀመሪያ ቅጽ "ሕይወቴን ያመስቃቀለውና ዕድሌን ያበላሸው መምህሬ ነው" በሚል ርዕስ ከገጽ 65 ጀምሮ የቀረበ ታሪክ ሴት ልጅ እንደ ሙሉ ሰው ለመምረጥ ከመድረሷ በፊት ወንዳዊው ሥርዓት መንገድ ሠርቶ ያቀብላታል ላልኩት እውነታ ጥሩ ማሳያ የሚሆን ይመስለኛል፡፡ አንድ መምህር የተማሪውን በእድሜ አለመብሰል ተመልክቶ ውሳኔ መወሰን በማትችልበት ሁኔታ ውስጥ ሕይወቷን የሚያበላሽ ስህተት እንድትሰራ ያስገድዳታል፡፡ ሁለቱ በነበራቸው ግንኙነት በማርገዟ የተፈጠረው "ስህተት" ውስጥ የወንድ እጅ እንዳለበት የታወቀ ቢሆንም ለጥፋቱ ማስረጃ የሆነው እርግዝና በሴትነት ስለሚገለጥ ማኀበራዊ ነቀፌታ የሚደርሰው ሴቷ ላይ ብቻ ነው፡፡ በመሆኑም ይህን ለመሸሽ የመረጠችው የሴተኛ አዳሪነት ሕይወትም በሷ ምርጫ ተከናውኗል ለማለት የሚያስደፍር አይሆንም፡፡ ምክንያቱም ይህ ውሳኔ ያለፈ ህይወቷ ውጤት እንደሆነ ተስፋ ማጣቷና የበቀል ስሜቷ ይሄኑ የሚጠቁም ነው፡፡ ኑሮዋ ውስጥ ደስታም ሆነ የነገ ተስፋ (አላማ) የለም፡፡ በመሆኑም ሴተኛ አዳሪነቷ ከማኀበረሰቡ እስር የምታመልጥበት ሳይሆን መውደቋን ያረጋገጠችበት ነው ማለት ይቻላል፡፡ ገንዘብ እንኳ ኃይል ሆኗት እርካታ አያወጣትም፤

> "ገንዘብማ አገኛለሁ፡፡ በሳምንት አራት ቀን ሰርቼ እንኳ ብዙ አገኛለሁ፡፡ ነገር ግን ከዚህ በኋላ ሁሉም ነገር የሚቃና ስለማይመስለኝ ለሕይወት ግድ የለኝም፡፡ በዚያ ላይ ብሩ በረከት የለውም፡፡ 1ሺህ ብር እጄ ላይ ይገኝ እንዴት እንደሚጠፋ አላውቀውም የብር ችግር እኮ የለብኝም፡፡ ነገር ግን የቡና ቤት ሴት እጅ ላይ የሚወድቅ ብር ሰላቢ ነው፡፡ ብን ብሎ ነው የሚጠፋው፡፡ አግኝቼ ካልተጠቀምኩበት ደግሞ ዋጋ የለውም፡፡" (ገጽ 65-66)

ማኀበረሰቡ አውቆትም ይሁን ሳያውቅ ሴት ልጆች ነጻ ህልውና ፈጥረው በምልዓት እንዳይኖሩ አድርጎ ከሚያሳድግባቸው መንገዶች አንዱ ለቁንጅና የሚሰጠው ግምት ነው፡፡ ይህ ዓይነቱ ግምት ለረጅም ጊዜ የእንስታውያን የተቃውሞ ርእስ ጉዳይ ሆኖ ቆይቷል፡፡ በዚሁ ድርሰት ውስጥ የሚገጥመን "[ቆንጆነሽ] እያሉ ገፋፍተው ነው እዚህ ነገር ውስጥ የከተቱኝ" በሚል ርዕስ የቀረበ ታሪክ ለዚህ ዓይነቱ ግምት አብነት ይሆነናል፡፡ ሴቷን ልጅ በአካላዊ ገጽታዋ ብቻ ማሰብ እና መመዘን አካላዊ ገጽታዋን በማግዘፍ ምክንያት ፍጡርነቷን ዘንግታ ተፈጥሮ የሰጣትን ሴትነት ለወንዶች ፍላጐት ያለ ጥያቄ ተገዥ እንዲሆን ማድረግ አንዱ የአባዊው ሥርዓት የመቆጣጠሪያ መንገድ ነው፡፡ "የኔ አባት ልጄ ስታድግ ማንንም ወንድ የምታንበረከክ ትሆናለች ንግሥት እኮ ነች … ልዕልት እኮ ነች፡፡ እከሌ ደግሞ ልጅ አለኝ

ይላል እንዴ… ቡዳ እንዳይበላብኝ እንጂ የልጄ ቁንጅና የትም ቤት የለም" (ገጽ 381)፡፡ ባለታሪኳ የገንዘብ ችግር አልነበረባትም፣ መማርና ብዙ ነገር መሆን የምትችልበት አቅምና አጋጣሚው ነበራት፡፡ ይሁንና ተደጋግሞ ሲሰበከላት የቆየው ውበቷ ነውና ከዚህ አስተሳሰብ ማምለጥ አልቻለችም፡፡ እናም ሴት ልጅ ከሌላው ማንነቷ በላይ ውበቷ እና ሴትነቱ ይፈለግበታል ብላ ወዳሰበችው ሴተኛ አዳሪነት ትዘልቃለች፡፡ ወደዚህ ዓለም በመዘለቋ ግን አትፈወስም፡፡ "ቆሻሻ" እንደሆነ እያሰበች ደስታ ታጣለች፡፡ ሌላው ቀርቶ ይዛው የገባችው ውበት ኃይል ያጣል፡፡ በመሆኑም ውበቷን ብቻ እንድታስብ ተደርጋ ማደጓ ማኅበረሰቡ ሴትነቷን ለወንዶች ፍላጐት ለማስገዛት የተጠቀመበት መሣሪያ እንደሆነ ከታሪክ መረዳት ይቻላል፡፡

በጥቅሉ ስንመለከተው በዚህ ጐራ የሚመደቡት እነዚህ ሴተኛ አዳሪዎች በእድሜም ይሁን በማስተዋል ደረጃቸው ለውሳኔ ያልበቁ፣ ለምርጫ ቢደርሱም የሚስቱ ናቸው፡፡ የአባዊውን ሥርዓት አሸንፈው የራሳቸውን መንገድ መቀየስ ያልቻሉ፣ ማኅበረሰቡ በቀየሰላቸው እጣ ፈንታ ብቻ የሚጓዙ ተሸናፊ ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ ይህ ነው እንግዲህ የባህል ሰለባነት (*victim*) አጠቃላይ መንፈስ፡፡

### 3.1.2.2. ነጻ ሰዎች

በድርሰቶቹ ውስጥ ከሚገጥሙን ሴተኛ አዳሪዎች መኻል ብዙዎቹ የተጎጂ እና የነጻ ሰው ባሕርይ ቅይጦች በመሆናቸው ቁርጥ ላለ ልዩነት አይመቹም፡፡ ተጎጂ ለሚለው ሐሳብ በምሳሌነት የጠቀስኳቸውም ይሁኑ ያልጠቀስኳቸው ነጻ ሰው የሚሆኑበትን አጋጣሚ አልፎ አልፎም ቢሆን አያጡም፡፡ በተለይ ባገልግሎታቸው ከፍያና በተወሰኑ የሰውነት ከፍሎቻቸው ላይ (በተለይ ከንፈርና ጡት) በነጻነት ሲወስኑ መመልከቱ የተለመደ ነው፡፡ ይህ ደግሞ የጁዲዝ በትለርን የነጻ ሰውነትን ሐሳብ የሚያጠናክሩ ይመስለኛል፡፡ ሞያ ሎይድ (Moya Loyd) በትለርን ጠቅሳ ነጻ ሰውነት (*agency*) ሁሌም በሂደት ላይ/ውስጥ ያለ እንጂ ተሰርቶ የሚያልቅና የሚያበቃ አይደለም ትላለች (2005፣95)፡፡ በድርሰቶቹ ውስጥ ከሚገጥሙን ሴተኛ አዳሪዎች ብዙዎች በተለያየ መጠን በሂደት ውስጥ ያሉ ነጻ ሰዎች ናቸው፡፡

ይህ ነጻነት ግን በአማርኛ የሥነ ጽሑፍ ልማድ ውስጥ መሠረት ያለው እንጂ ዛሬ የተፈጠረ አይመስለኝም፡፡ በአማርኛ ሥነ ጽሑፍ "ተጎጂ" ከሚያሰኙ ባሕርያት በከፊል ተላቀው የተቀረጹ ገጸ ባሕርያት አልፎ አልፎም ቢሆን ይገጥሙናል፡፡ ለዚህ ደግሞ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነን *ሌቱም አይነጋልኝ* ነው፡፡ በ*ሌቱም አይነጋልኝ* ውስጥ ሴቶቹ ሰብዓዊ ተደርገው ነው የተቀረጹት፤ በከፊልም ቢሆን የራሳቸው ህልውና አላቸው፡፡ በቅርብ እየወጡ ያሉ ድርሰቶች፣ ይህንን ልማድ የሚያስቀጥሉ ሆነው ነው የምናገኛቸው፡፡ በእነዚህ ድርሰቶች ውስጥ ሴተኛ አዳሪነት በአመዛኙ አገልግሎት መስጠት እንጂ ሰብዓዊ ክብርንና ነጻነትን አሳልፎ መስጠት አይደለም፡፡ በመሆኑም ሴቶቹ ነጻ ሰውነትን ለማግኘት የሚታገሉ ናቸው ማለት እንችላለን፡፡ የአንዳንዶቹ ነጻ ሰውነት ግን የላቀና የተለየ ነው፡፡ ልዩነታቸው አንድም

የባሕርይ፣ አንድም የአስተሳሰብ፣ አንድም የአመለካከት--ለሥራቸው፣ ለጾታቸው፣ ለራሳቸው ኀሊናና ገላ ያላቸው አመለካከት ነው፡፡ ይህ ዓይነቱ እንግዳነት በተጠቀሱት ድርሰቶች ውስጥ ብቻ አይወሰንም፡፡ ይልቁንም በሴተኛ አዳሪነት ላይ ተመሥርተው የተከየኑ ነባር ድርሰቶችን እና ባህሉን ጭምር በእንግዳ ዓይን እንድንመለከት የሚያስገድድ ይመስለኛል፡፡ እነዚህ ሴቶች ወደ ሴተኛ አዳሪነቱ ሕይወት በግዳጅም ገቡ በፍላጎት ሥራቸውን ከጀመሩ በኋላ በማስተዋልና በምክንያት፣ በዓላማና በምርጫ የሚኖሩ ናቸው፡፡ ሴቶቹ ያላቸው በራስ መተማመን እና መረጋጋት የሴተኛ አዳሪነትን ገጽታ የሚገለብጥና ሌላ መልክ የሚሰጥ ነው፡፡ እንደኔ እምነት እነዚህ ሴቶች በአንድ በኩል በአገራችን እየተከሰተ ያለውን አዲስ የሴተኛ አዳሪነትን እሴትና ገጽታ ጠቋሚ ሲሆኑ፤ በሌላ በኩል በዘመናችን "በምዕራባውያን" ሴቶች እየተቀነቀነ ካለው አዲሱ የእንስታዊነት ሐቲት ጋር በወጉ መናበብ የሚችሉ ናቸው፡፡

ሴተኛ አዳሪነት ከርግማን ሥራነት ወጥቶ ሴት በመሆን፤ በተመራጭነትና በዕድለኝነት የሚገኙበት ሆኗል (ለምሳሌ፣ *በሰአት አላፊ የመጀመሪያ ቅጽ* ገጽ 356 እና *በሰአት አላፊ ቅጽ ሁለት* ገጽ 283 ላይ የሚገጥሙንን ሴቶች ማድመጥ በቂ ነው)፡፡ ማኅበሩ ካገለላቸው ይልቅ ማኅበራቸውን የገፉና የናቁ ሴቶች መናኸሪያ ሆኗል (ለምሳሌ፣ በተለምዷዊው ዓለም ውስጥ ትልልቅ ከሚባሉት ተቋማት መካከል አንዱ እና የሴት ልጅ ብቸኛ ሥፍራ ተደርጎ የሚታሰበው የትዳር ሕይወት በእነዚህ ሴቶች ዘንድ በእጅጉ የሚኮነን ጉዳይ ሆኖ እናገኘዋለን *ሰአት አላፊ የመጀመሪያ ቅጽ* ገጽ 365 እና ሁለተኛው ቅጽ ገጽ 284)፡፡ በድርሰቶች ውስጥ የሚገጥሙን ሴቶች ስሜታቸውን የሚያደምጡ፣ ላደመጡት ስሜታቸው ሲሉ የማኅበራቸውን እሴት በድፍረት የሚጥሱ ባለታሪኮች ሆነው ነው የተቀረጹት፡፡ በክፍያ አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡ ከዚያ ባለፈ በተለመደው መንገድ በከፈለው ገንዘብ ሊገዛቸው ለሚሞክር ወንድ እድል አይሰጡም፡፡ *በሰዓት አላፊ* ተደጋግሞ የሚገጥመን የ"ጡቴን አላስነካም" ፈሊጥ ለዚህ ጥሩ ማሳያ ነው (ለምሳሌ፤ *ሰአት አላፊ የመጀመሪያው ቅጽ*፣ ገጽ 104 እና 381) ፡፡

> አንድ ወንድ ከቡና ቤት ሴት ጋር ሲወጣ ያለው እድል አንድና አንድ ብቻ ነው፡፡ ለአዳር ብር ስለከፈለ ብቻ ከንፈር ለመሳም የሚፈልግ ወንድ አለ፡፡ የቡና ቤት ሴት የደንበኛዋን ከንፈር አትስምም፡፡ 120 ብር ስለከፈለ እንደፈለገው መሳም የሚፈልግ ብዙ ወንድ አለ፡፡ እዚህ ቤት ያለነው ሴቶች አቋም ግን ተመሳሳይ ነው፡፡ እንኳን ከንፈርዋን የምትሳም ጡቷን ለማስነካት የምትፈልግ ማግኘት ይቸግራል፡፡ (*ሰአት አላፊ* ገጽ 104)

የመራቢያ አካላቸውን ሰጥተው ጡታቸውን ለሚነፍጉ ለእነዚህ ሰዎች፣ ጡት አንድም በወንድ የማይደፈር የንጻነታቸው ሰንደቅ ነው፡፡ ይህንን፣ በባህል ጥናት፣ በተለይም በነገረ ጾታ ውስጥ እጅግ ከፍ ላሉ ሙግቶች ምክንያት እየሆነ የመጣን ጉዳይ--የሴት ልጅ ሰውነት--የእኛንም ድርሰቶች ስለሚመለከት ትንሽ ገፋ አድርገን መመልከት የሚገባን ይመስለኛል፡፡

ወንድነት በገነነበት ዓለም ስርከ ወንድ ልጅ ከአእምሮ ልዕልና ጋር ተዛምዶ ሲነሳ፣ ሴት ልጅ ግን፣ *በሰዓት አላፊ የመጀመሪያ ቅጽ* ውስጥ "[ቆንጆ ነሽ] እያሉ ገፋፍተው ነው እዚህ ነገር ውስጥ የከተቱኝ

(376)" ስትል እንደስማኖት ባለታሪከ አካላዊ ተደርጋ ትሳላለች፤ ህልውናዋ እዚያ ላይ ብቻ የተመሠረተ እስኪመስል ድረስ፡፡ የሴት ልጅ ሰውነት (*the female body*) በብዙ የዓለም ታሪኮች እና ባህሎች ውስጥ አስደማሚነት ከአስፈሪነት ተቃይጠው የሚፈጥሩት ዝንቅ ምስል ነው፡፡ ይህ ዓይነቱ ዝንቅ አመሳሰል ጥንታዊ በምንላቸው ኪነቶች--በሚቶች፣ በኤፒኮች፣ በሮማንሶች፣ ወዘተ.--ውስጥም ሆነ በዘመናውያኑ ኪነ ጥበባት--በልብ ወለዱ፣ በቲያትሩ፣ በሲነማው--በቋሚነት የሚገጥመን ትዕምርታዊና ርዕዮተ ዓለማዊ መባያ ነው፡፡

ጄን አሸር ፍሮይድን ጠቅሳ እንደምታስረዳው፣ በልዩ ልዩ የኪነ ጥበብ ሥራዎች ውስጥ የሚገጥመን በጎ ያልሆነ የሴትነት አስተማስሎ በአመዛኙ ከወንዶች ፍርሃትና ስጋት የሚመነጭ ነው (2006፤ 7)፡፡ ፍርሃቱ "ውበት ከእናትነት" ተዋህደው በሚፈጥሩት "ምስጢር" ይቀሰቀሳል፡፡ ይህ ምስጢር ወንድ ልጅ "ዓለምን ሠርቼበታለሁ" እና "ዓለምን አስተዳድርበታለሁ" ብሎ ከሚታበይበት ልምዱም ይባል ገጠመኙ፣ በወንዳዊ አእምሮው አደራሁት ከሚለው ነገረ ዕውቀቱም ውጪ ነው፡፡ ወይም በቀላል ቋንቋ ስጋቱ ማኅበራዊ የበላይነቱን የማጣት ነው፡፡ይሄን የወንዱን እንግዳነት (አለማወቅ) *መኃልየ መኃልየ // ቹቹኒዮ*ላይ ትንሽ በሚመስል መልኩ እንዲህ ተገልጾ እናገኘዋለን፤

> "…ብዙ ጊዜ ወንዶች የሴትን ፍላጎትና ተለዋዋጭ ስሜት አይገነዘቡም፡፡የሴትን ስሜት መቋቋም እንደማይችሉም አያምኑም፡፡ ሴት ደግሞ አሳት ናት! በወር ውስጥ ቢያንስ ሶስት ዓይነት የሴክስ ባህሪ ይኖራታል! ፔሬድ ሊመጣ ሲል ሌላ ናት! ፔሬድ ላይ ስትሆን ሌላ ናት! ፔሬድ ስትጨርስ ደግሞ ሌላ ስንቱ ወንድ ነው ይሄን የተከተለ የተጠና ሴክስ የሚያደርገው? አብዛኛውን ወንድ እናውቀዋለን ሲቆምበት ብቻ ቀዳዳ ፈልጎ መከተት ነው የሚያውቀው" (ገጽ 53)

ወሲብ እንዱ የወንድነት መገለጫና የበላይነቱ ማረጋገጫ ተደርጎ የሚታይ ጉዳይ ነው፡፡ይሁንና የሴት ብቻ በሆነው የወር አበባ ምክንያት ከወንድነት ዕውቀት ውጪ ሆኗል፡፡ ምሳሌው ግልጽ እና ትንሽ ማሳያ ነው፡፡ ይህ ከልምዱም ከዕውቀቱም "ራዳር" ውጪ የሆነ "ምስጢራዊ ህልውና" 'ምን እንዳለው ማን ያውቃል?' ነው እንግዲህ ሥጋቱ፡፡ በመሆኑም "ሳብጀክት" ሆኖ በሚያበጃቸው ኪነ ጥበባቱ አማካይነት ሴትን ልጅ፣ ውበት ከአሳሳችነትና ከአደገኛነት ተባብረው የፈጠሯት "ኦብጀክት" አድርጎ በመሳል የማያውቀውንና የሚፈራውን ሴትነት ለመቆጣጠር ይሞክራል፡፡

አሸር እንደምትለው (ገጽ 11-14)፣ የሴት ልጅ ሰውነት በብዙ ባህሎች እና ሃይማኖቶች ውስጥ ብዙ ጥበቃ የሚደረግለት በርካታ ገደቦች የሚወድቁበት ጉዳይ ነው፡፡ በተለይ ሴትን ከወንድ የሚለዩ አካሎችና ግብራካሎች ጡት፣ ማህፀን፣ ወሊድና የወር አበባ በተለያየ መልኩ ጥብቅ ቁጥጥር ይደረግባቸዋል፡፡ በሃይማኖት አስገዳጅነት የሚፈጸሙ አለባበሶች፣ የሴት ልጅ ግርዛት፣ በተለያዩ ባህሎች ውስጥ የሚታየው በወሊድና በወር አበባ ወቅት ከመኖሪያ ሥፍራ ርቆ የሚከናወን የመጽዳት ሥርዓት (እና የተቀደሱ ሥፍራዎች እንዳትደርስ መታገድ ብለን ማከል እንችላለን) ይህን ኃይል ለመቆጣጠር

የተበጁ ስልቶች ናቸው፡፡ በግርዘት ወሲባዊ ፍላጐቷንና ደስታዋን መገደብ፣ በአልባሳት አካሏን መጋረድና ልዩነቷን (*her uniqueness*) መደምሰስና ኃይሏን መንጠቅ ነው የባህሉ ፍላጎት፡፡ በድንግልና የወለዱ ሴቶችን ታሪክ በመንገርና እናትነትን በማግዘፍ ወሲባዊ ህልውናዋን እንድትዘነጋ ትደረጋለች፡፡ በወር አበባና በወሊድ ወቅት የሚካሄዱ "የመጽዳት" ሥርዓቶችም ከዚሁ የሚገጥም ሚና አላቸው፡፡

*በመኃልየ መኃልየ ዘ ቼቺኒያ*፣ *በሰዓት እላፊ*፣ በየቼቺኒያ ሚስጥራዊ ሴሊቶችእና *በሰዓት እላፊ 2* ይህን ሥርዓት ሰብረው የሚወጡ ሴቶች ይገጥሙናል፡፡ ሴቶቹ የራሳቸውን ህልውና ከማግኘትም ባለፍ የወንዱንም ዓለም የመምራት ኃይል ተሰጥቷቸው ጭምር ነው የሚገጥመን፡፡ የኃይል ምንጫቸው አንድም "የሚሠሩት" ገንዘብ መጠን ሲሆን፣ አንድም ራሳቸውን የመምራት፣ የግል ስሜታቸውን የማድመጥ በዚህም ማኅበራቸውን የመጋፋት አቅማቸው ነው፡፡ ለምሳሌ *በሰዓት እላፊ* ሁለተኛ ቅጽ ከገጽ 132-138 የሚገጥመን ምልልስ ይሄንን እውነታ አፍ አውጥቶ የሚያውጅ ነው የሚመስለው፡፡ በዚህ ምልልስ ውስጥ የምናገኛት ገጸ ባሕርይ በተለምዶ ከምናውቃቸው ሴተኛ አዳሪዎች በሙሉ የተለየች በመሆኗ፣ ቢያንስ በድርሰቱ ውስጥ "ለሴተኛ አዳሪነት" አዲስ ፍቺ አስገኝታለች፤ አዲስ እሴት አክላለች፡፡ በወጉ ከተነበበች በማኅበረሰቡ ውስጥ እያቆጠቆጠ ያለውን አዲስ አዝማሚያ ከመጠቆም አልፋ ባህሉ አዲስ የሴተኛ አዳሪነትን ሐቲት ያስብ ዘንድ የምትቀሰቅስ ይመስለኛል፡፡ ይህቺ ሴት ሥራውን የጀመረችው በችግር ወይም በሌላ ማኅበራዊ ግፊት ሳይሆን በምርጫ ነው፡፡ ተምራለች፡፡ ጥሩ ገቢ ካለው ቤተሰብ የተገኘችና በርካታ የሥራ ምርጫዎች የነበሯት ሴት ነች፡፡ ከዚህ ሁሉ መኃል ሴተኛ አዳሪነትን መረጠች፡፡ ከሥራዋ እጅግ ከፍ ያለ ገንዘብ ብታገኝም፣ ከገንዘቡ በላይ የሴትነቷና የአኗኗር ዘይቤዋ አካል በማድረጓ ሥራዋን በታላቅ ፍቅርና አክብሮት ታከናውናለች፡፡ ለምርጫዋ ተአማኒነት ደግሞ የተረጋጋ ማንነቷ፣ አንባቢነቷና እንዲሁም መማርዋ የሚጨምረው ነገር አለ፡፡

ይህች ሴት ነጻ ሴት/ሰው ናት፡፡ ይህንን ለመረጋገጥ ደግሞ ልዩ ልዩ አስረጂዎችን ማምጣት ይቻላል፡፡ እንደ ግለሰብ በራስዋ የምትቆም፣ የራስ ውክልና ያላት እና በምርጫዋ አከባቢዋን ለራስዋ ፍላጐትና ዓላማ የምታስገዛ ነች፡፡ አስቀድሜ እንዳነሳሁት፣ በተጐጂ ሐሳብ አቀንቃኞች አመለካከት ሴተኛ አዳሪነት ሴት ልጆችን ከሚያዋርድባቸውና ሰብዓዊ ፍጡነታቸውን ከሚነጥቅባቸው መንገዶች አንዱ ከደንበኞቻቸው ጋ ያላቸውን ግንኙነት ኢ-ሰብዓዊ ማድረግ ነው፡፡ በዚህ ታሪክ ውስጥ የምናገኛት ሴት ግን ይህን ሐሳብ ጨርሳ የምታፈራርስ ዓይነት ነች፡፡ አስከትዬ ከመጽሐፉ ወስጄ በማቀርበው ጥቅስ ውስጥ ማየት እንደሚቻለው ለሥራዋ መሳካት ደስተኝነቷ እና የልቡና ዝግጅቷ አስፈላጊ ነው ብላ ታምናለች፡፡ በመሆኑም ከብዙዎቹ ሴተኛ አዳሪዎች በተለየ ከደንበኞቿ ጋ ከሥጋ ትሥሥር እኩል የመንፈስም ትስስር እንዲኖር ታደርጋለች፡፡ በእርግጥ ከእነሱ ደስታ በፊት የሷ ደስታ ይቀድም ዘንድ ትሻለች፡፡ ለአገልሎቷ ከደንበኞቿ ጥሩ ክፍያ ትቀበላለች፡፡ አገልግሎቷና ክፍያዋ ከወሲብ ጋር ብቻ እንዲዛመድ አትፈልግም፤ ማንነቷ (*persoanality*) ጊዜዋ፣ ቅርበቷና አብሮነቷ (*company*) አብሮ እንዲቆጠር ትፈልጋለች፡፡ ይህ

ደግሞ ብዙ የሙያው ተቃዋሚዎች እንደሚያነሱት ሴቷን ከሰውነት ተራ አውርዶ የስሜት ማርኪያ፣ መገልገያ እቃ ከማድረግና ሰብአዊ ፍጡሩነቷን ከማዋረድ ፈፅሞ የሚያርቃት ነው፡፡ ሁኔታውን በወጉ ማየት እንድንችል ሲባል ከድርሰቱ በረጅሙ የተወሰደውን አስረጂ እንመልከት፤

"unbelievable ይሄ የማይመስል ነገር ነው፡፡ እንዴት በ60 ብርና በ200 በር ሴትነታቸውን ይሸጣሉ፡፡ oh. በ60 እና በ100 ብር?"

"መሄድ አልነበረባቸውም?"

"I didn't say that ሴት ክብርት ናት፡፡ ዓለም የሚሰግደው ለሴት ነው፡፡ ሴቶች ከዓለም የተሰጣቸውን ቆንጆ ተፈጥሮ ካልተጠቀሙበት እኮ ይጎዳሉ"

"አልገባኝም!" [---]

"ሴት ክብር ናት፣ ሴት የዓለም አድማቂ ናት፣ ሴት ሕይወት ናት፡፡ ሴት ለወንዶች ደስታን የምትሰጥ ናት and so on አየህ… ሴት ያልገባችበት ነገር አያምርም፡፡ ለዚህ ነው ተቃውሞዬ፡፡ ሴት ሆነው ተፈጥረው እንዴት በ60 ብር ይወጣሉ፡፡ ሴትነት መጫወቻ እኮ አይደለም፣ አዝናለሁ?"

"ምን ማድረግ ነበረባቸው?"

"በ60 ብር ሴትነታቸውን ከሚሸጡ የቤት ሰራተኛ አይሆኑም?"

"እነሱ እኮ እነስን አላሉም"

" I swear ተሳስተዋል!"

"እየኖሩበት እኮ ነው?"

"አውቃለሁ ግን ሴትነትን አጠፉት፡፡ በጣም እኮ ነው የተሳሰቱት፡፡ የሴት ልጅ የሚያህል big… big በዚህ ርካሽ ዋጋ፡፡ I swear ወንጀል ነው፡፡ ኢትዮጵያን እኮ ነው ዓይኗን ያጠፏት፡፡ ፈረንጆች እኮ እየመጡ በ5 ዶላር በ10 ዶላር ከቆንጆ ሴት ጋር አድሬያለሁ ብለው ይነግሩናል፡፡ I swear ወንጀል ነው"

"ምን ማድረግ ነበረባቸው?"

"I swear ተዋርደናል!" [---]

"እናንተ ስንት ታስከፍላላችሁ?"

"አይገናኝም ፣ ምንም አይገናኝም"

"ስንት ታስከፍላላችሁ?"

"five hundred…."

"ዶላር?"

"Sure! እነስ ከተባለ 200 ዶላር ነው ዋጋችን፡፡ ደግሞ ተከብረን ነው እንጂ ተዋርደን አይደለም፡፡ የሚስርቋቸው፣ የሚደበድቧቸው ወንዶች እንዳሉ ነግረውናል፡፡ ሌላው ቀርቶ እንደሚያለቅሱ ነግረውሃል oh my god! በጣም ነው ያዘንኩት እኛ እኮ ተከብረን ነው፡፡ እኛ እኮ Resource ነን፡፡"

"እንዴት?"

"የኢትዮጵያ ሀብትነትን የኢትዮጵያን መልካም ገጽታ ለዓለም የምናስተዋውቀው እኛ ነን፡፡ ፈረንጆች እኮ Axum Lalibelaን ብቻ ለማየት አይመጡም፡፡ እኛን ለመጎብኘትም ይመጣሉ፡፡ ስለ አክሱም ከማሰባቸው በፊት ስለ እኛ ያስባሉ፡፡ የኢትዮጵያን ታሪክ የምናንቀሳቅሰው እኛ ነን፡፡ ኢትዮጵያ የገባ ፈረንጅ እኛን ሳይጎበኘን አይሄድም፡፡ ሁሉም ይጎበኙናል፡፡ በዚህም ደስተኞች ነን፡፡ የኢትዮጵያ ቱሪዝም ማለት እኛ ነን፡፡የሚገጥሙንም ወንዶች ለሴት ልጅ ክብር የሚጨነቁ ናቸው፡፡ ሴቶቹ የጠቀሷቸው ችግሮች እኛ ጋ የሉም፡፡ ፈረንጅ ቤቱ ሲወስደን ራሱ አብስሎ፣ ምግብ አብልቶን፣ በስጦታ አንበሽብሾን ነው፡፡ ሆቴል ስናድርም እንደዚሁ ነው፡፡ እኔ አሁን ያላደርኩባቸው ትላልቅ ሆቴሎች የሉም፡፡ ሸራተን አዲስ፣ ሂልተን… ጊዮን… ጁፒተር… ቤቴ ነው"

"ወርሃዊ ገቢሽን ታውቂዋለሽ?"

"አውቀዋለሁ"

"ስንት ይሆናል?"

"በወር ማለትህ ነው?"

"አዎን! በወር?"

"የተጣራ 30 ሺህ ብር አገኛለሁ"

"ወሩን ሙሉ ስራ ተገቢያለሽ?"

"No በስራ ቀናት ብቻ ነው፡፡ በስራ ቀናት ብቻ ገብቼ በወር የተጣራ 30 ሺህ ብር አገኛለሁ፡፡ ከ30 ሺህ ብር በላይ ገቢ ያላቸውም አሉ"

"እርግጠኛ ነሽ?"

"ማሚ ትሙት የኔ ገቢ 'መካከለኛ' ነው የሚባለው፡፡ ዶላሩን ዝም ብለው የሚመዝርጡ አሉ፡፡ እነርሱን ብታይ እኔን ትንቀኛለህ፡፡ I swear!" [---]

"አንዳንዴ ከገቢያችን በላይ ወጪያችን የሚበልጥበት ጊዜ አለ፡፡ ራሳችንን ማስደሰት አለብን፡፡ ራሳችንን ለማስደሰት ነው መስራት ያለብን፡፡ ሴት ልጅ ወንድ ልጅን ማስደሰት የምትችለው ራስዋ ስትደሰት ነው፡፡ እነዛ ምስኪን ሴቶች ከወንድ ጋር ተኝተው ሌላ ዓለም ወስጥ እንደሚገቡና ፍላጎት እንደሌላቸው ነግረውሀል፡፡ የእኛ ከዚህ ይለያል፡፡ ራሳችንን ሳናስደስት ሌላውን ማስደሰት አይቻልም፡፡ …"

"ደምበኞቻችሁ ምን ዓይነት ወንዶች ናቸው?"

"Are you crazy? ወንዶች ናቸዋ! Just ብር ያለው በሴት መደሰት የሚፈልግ፡፡ ለሴት ክብር የሚሰጥ፡፡ ለምሳሌ before two weeks ከአንድ ፈረንሳዊ ጋር ወጥቼ ነበር፡፡ 250 ዶላር ተሰጥቶኛል፡፡ ግን ወሲብ አልፈፀመም"

"ተመርቀሻል?"

"አዎና!"

"የት ኮሌጅ?"

"… የሚባል private college"

"አስተዳደግሽ እንዴት ነው?"

"አስተዳደጌ?"

"አዎ! ጥሩ ገቢ ካላቸው ወይስ…"

"What are you talking about? አብድ ነህ እንዴ ቤተሰቦቼ ሁብታሞች ናቸው፡፡ ጥሩ ገቢ ያላቸው ናቸው የደሃ ልጅ አይደለሁም"

"ታድያ ለምን ሴተኛ አዳሪ ሆንሽ?"

"ሴተኛ አዳሪ አይደለሁም!"

"እንዴት?"

"እኔ ራሴን እንደ ሸርሙጣ አልመለከትም፡፡ የኢትዮጵያን ኢሜጅ ለማሳደግ የምሰራ ሴት ነኝ፡፡ ዶላር ተከፍሎኝ ብተኛም፣ ከፈረንጆች ጋር ስተኛ የምለዋወጣቸውን ነገሮች ማወቅ አለብህ I swear."

"እነዚያ ምንድ ናቸው?"

"የተለያዩ የዓለም ሰዎች ስለኢትዮጵያ የሚያውቁት በእኛ ነው፡፡ እኔ ስለሁሉም ነገር እነግራቸዋለሁ፡፡ ቱሪዝም ማለት እኛ ነን፡፡ ለምሳሌ ስለኢትዮጵያ constitution ይጠይቁኛል እነግራቸዋለሁ"

"ምን ብለሽ?"

"ስለብሔር ብሔረሰቦች፣ ስለክልሎች፣ ስለሴቶች፣ ስለመንግስት አወቃቀር እነግራቸዋልሁ"

"አትሳሳቺም?"

"አልሳሳትም! ማሚ ትሙት አልሳሳትም! እነርሱ አውቀውት ነው የሚጠይቁት፡፡ እኔም እዘጋጃለሁ፡፡ ስለ አክሱም፣ ስለላሊበላ ይጠይቁናል እነግራቸዋለሁ፡፡ የቱሪዝም መፃሕፍቶችና constitution እቤቴ አለ፡፡ ፈረሳይኛና አረብኛ መማሪያ መፃሕፍትም አሉኝ፡፡ ጋዜጦችን እከታተላለሁ፡፡ ፎርቹን፣ ካፒታል፣ ሄራልድና ሞኒተር የሚባሉ የእንግሊዝኛ ጋዜጦችን አነባለሁ፡፡ ስለኢትዮጵያ ምርጫ ስለቱሪዝም የተፃፉትን አንብቤ ለፈረንጆቹ አስረዳለሁ"…

"ስለዚህ አንቺ ራስሽን የምታይው እንደ ሴተኛ አዳሪ ሳይሆን እንደ ቱሪዝም ባለሙያ ነው ማለት ነው?"

"እንደፈለግከው ብለው! እኔ ግን ሸርሙጣ አይደለሁም"

"የእኛ ክላስ ትልቅ ነው፡፡ ራሳችንንም የምንገልፀው የቱሪስት መስህብ አድርገን ነው፡፡ እኔን ያወቀኝ ፈረንጅ እኔን ለማየት ሲመጣ ለኢትዮጵያ ብዙ የውጭ ምንዛሪ ያስገኛል፡፡ ሆቴል ይጠቀማል፣ ዕቃ ሲገዛም አገር ውስጥ ያለው ነጋዴ ክፍል ይጠቀማል፡፡ ገብቶሃል አይደል ስለዚህ እኛ ቱሪስቶች ወደ ኢትዮጵያ በተደጋጋሚ እንዲመጡ የምናደርግ ነን፡፡ በዚህም አገራችን ታድጋለች፡፡ ኢትዮጵያ ትጠቀማለች…"

"ዓላማሽ ምንድን ነው ያንቺ? መፅሐፉ ላይ ያየሻቸው ሴተኛ አዳሪዎች ተቸግረው፣ አማራጭ ሲያጡ እንጀራችን ብለው ነው የገቡበት አንቺ ደግሞ ሀብት የበዛለት ቤተሰብ ልጅ ነሽ፡፡ በጥሩ አስተዳደግሽ እንዳደግሽ ገልፀሽልኛል፡፡ ጥሩ ኮሌጅ ተምረሻል፣ ተመርቀሻል፣ ግን ሴተኛ አዳሪ ሆነሻል"

"Life ስታይሌ ነው ለኔ፡፡ ያስብኩት ደረጃ እስከደርስ እሰራለሁ"

"የት መድረስ ነው ፍላጎትሽ?"

"በቃ ያሰብኩት ደረጃ አለ"

"የት ለመድረስ ታስቢያለሽ?"

"ሰው እኮ ነኝ የተማርኩ እንደመሆኔ የማስበው አለ"

"ምን ታስቢያለሽ?"

"ወደ ውጪ ሊወስዱኝ የተዘጋጁ ደንበኞች አሉኝ፡፡ ከዚህ አገር እወጣለሁ፡፡ ትምህርቴንም መቀጠል እፈልጋለሁ፡፡"

… "የመኪና ቁልፍ የሰጠሽ የቀየ ደምበኛሽ ነው?"

"በዓመት አራት ጊዜ ይመጣል፡፡ ከኔ ጋር መዝናናት ደስ ይለዋል፡፡ ስለ ኢትዮጵያ ሲያስብ ትዝ የሚለው ኃይሌ ገ/ሥላሴ አይደለም፡፡ ትዝ የሚለው አክሱምና ላሊበላ አይደለም፡፡ ጉረኛ ነሽ እንዳትለኝ I swear ኢትዮጵያ ከተባለ ትዝ የምለው እኔ ነኝ ሶደሬ፣ ኩሪፍቱ ይገፍው እሄዳለሁ፡፡ ጥሩ ከስተመሬ ነው" [---]

"ስራውን ስትጀምሪ መስፈርት ነበረው፣ ወይስ ዝም ብለሽ ገባሽ?"

"ቁመናና ቁንጅና ይታያል፡፡ ቫራይቲ ያለው መልከ ይሉታል፡፡ ከራይቴሪያው ፕሮቶኮል መጠበቅና እንግሊዝኛ፣ አረብኛና ፈረንሳይኛ ቋንቋን አቀላጥፎ መናገር ነው፡፡ ከስተመሮች በራሳቸው ቋንቋ ሲጠይቁ በራሳቸው ቋንቋ መልስ የሚሰጣቸው ይፈልጋሉ፡፡ እኔ እንግሊዝኛና ፈረንሳይኛ እናገራለሁ፡፡…"

"ፈረንጆች 500 ዶላር ሲከፍሉ የሚጠይቋቸው ሕገ -ወጥ የወሲብ ጥያቄዎች አሉ"

"የትኛውም ወንድ ህገ-ወጥ ወሲብ ይፈልጋል፡፡ እንደሴቱ ፍላጎት ነው፡፡ በኔ በኩል ግን አልወድም፡፡ አረቦች ለየት የለ ሴክስ ይጠይቃሉ፡፡ የሚሄድላቸውም፣ የማይሄድላቸውም አለ፡፡ የኔ ከስተመሮች ግን ጨዋዎች ናቸው፡፡ የሚጠይቁ አሉ፡፡ No! ካልኳቸው አያስገድዱኝም፡፡ ከአንድ ከስተመሬ ጋር በዚህ ሕገ-ወጥ ወሲብ አማካኝነት ተጣልቼዋለሁ፡፡ ደንበኛዬ አረብ ነው፡፡ ሶስት ጊዜ ዱባይን አስጎብኝቶኛል፡፡"

የዓለም ትልቁን ህንፃ አይቼዋለሁ፡፡ አቡዳቢ፣ ሪያድና ሻርጃህን ጎብኝቻለሁ፡፡ ብዙ ብር ይሰጠኛል፡፡ ግን ሕገ-ወጥ ወሲብ ይወዳል፡፡ በዚህ ተጣላን (*ሰዓት እላፊ 2 ገጽ* 132-138)፡፡

በሴተኛ አዳሪነቱ ውስጥ ንቃተ ኅሊናው እዚህ ደርሷል፡፡ ሰው የተሟላ የኅሊና ነጻነትና የራስ ላይ እምነት ሲኖረው ነው፣ ልጅቷ ባደረገችው ልክ ከራሱ አልፎ ለወገንና ለአገር ማሰብ የሚችለው፡፡ ይህቺ ሴት ራሷን የሚመለከቱ፣ ሴትነትን የሚመለከቱ፣ አገርን የሚመለከቱ በርካታ ኃላፊነቶችን ተቀብላለች፡፡ ትልቁ ነጥብ፣ አንደኛ የትኛውም ኃላፊነት በፈቃድና በፍቅር ራሷ አስባ ራሷ የሠራችው እንጂ ከየትኛውም ወገን በግዳጅ የተቀበለችው አለመሆኑ ነው፡፡ ሁለተኛ፣ ኃላፊነቷን ለመወጣት ያላት የስሜት፣ የምግባርና የዕውቀት ዝግጁነት ደግሞ ደረጃዋን እጅግ ያልቀዋል፡፡ እንዲህ ያሉት ሴቶች የራሳቸውን ሙሉ ህልውና (*agency*) ከማግኘትም ባለፈ የወንዱንም ዓለም የመምራት ኃይል የተቀዳጁ ናቸው፡፡

ባለታሪኳ፣ በምልልሱ መጀመሪያ አካባቢ "አለም ለሴት ልጅ እየሰገደ ነው!" የሚል ሐሳብ ስታቀነቅን ይደመጣል፡፡ በምልልሱ ማብቂያ አካባቢ ደግሞ ከዚሁ ሐሳብ ጋር የሚናበብ ገለጻ ይገጥመናል፡፡ "ስለ ኢትዮጵያ ሲያስብ ትዝ የሚለው ኃይሌ ገብረ ሥላሴ አይደለም፡፡ ትዝ የሚለው አክሱምና ላሊበላ አይደለም፡፡… ኢትዮጵያ ከተባለ ትዝ የምለው እኔ ነኝ!" በዚህ ገለጻ ውስጥ የተካተቱትን ሦስት ነገሮች ማስተዋል ጠቃሚ ነው፡፡ ምክንያቱም በዘፈቀደ የተጠቀሱ ሳይሆኑ ከራሳቸው አልፈው የሚሄዱ እሴቶችን የተጫኑ ናቸውና፡፡ አክሱም፣ የጥንታዊው ሥልጣኔ ምልከት፣ የታሪካችንም ማረጋገጫ ነው (በቅርፁ ጭምር ወንድነት የሚወክል መሆኑን ልብ ይሏል)፡፡ ላሊበላ የጥበብና የሃይማኖት ወኪል ነው (ይሄም በወንድ ጥንካሬና ሃይማኖታዊ ጽናት የቆመነው)፡፡ እንዲሁም ደግሞ

ኃይሌ ገብረ ሥላሴ የዚህ ዘመን ጽናትና ጥንካሬ መከሰቻ ነው (ብዙ ሴት አትሌቶች ባሉባት አገር ውስጥ ኃይሌ ተነጥሎ መነሳቱ የጥንካሬውን መጠን ብቻ ሳይሆን ወንድነቱንም ከግምት የሚያስገባ ይመስለኛል) ። ይሁንና በዚህ ታሪክ ሴተኛ አዳሪነት ከነዚህ ሁሉ ቀድሞ ለአገር መታወሻነት፣ መገለጫነት ሲውል እናየዋለን። በመሆኑም በእነዚህ ትልልቅ የወንድነት መገለጫዎች አማካይነት የትላንት ታሪክ፣ የዛሬው ምስል እንዲሁም የአገር ስም "በሴተኛ አዳሪዋ" አማካይነት ለሴትነት ይሰጣል።

የሴት ልጅ ገላ በእነዚህ ድርሰቶች ውስጥ ያለፈቃዳቸው በወንድ የማይደፈር የነጻነታቸው ሰንደቅ ነው። በዚህ ምክንያት ሚናና የኃይል አሰላለፉ (*power relation*) ይለወጣል፤ አድራጊ-ፈጣሪ (*the subject*) ሴቷ ትሆናለች። ወንዱ ወደሌሎች ፈቃድ፣ ፍላጎትና ድርጊት ማደሪያነት (*object*ነት) ይቀየራል። ይህንን ሐሳብ ከ*መኃልየ መኃልየ ዘ ቺቺኒያ* በወሰድኩት ጥቅስ ተጨባጭ ላድርግ። በጥቅሱ ውስጥ የምንመለከታ ሴት በሂሳብ ትምህርት በመጀመሪያ ዲግሪ የተመረቀች ናት። በእርግጥ ወደ ሴተኛ አዳሪነት የገባችው ያስከፋት ባልዋን ለመበቀል ነበር። ነገር ግን ሕይወቱን ከጀመረች በኋላ በነጻነት እና በምርጫ ወደምትኖር ሴትነት ትለወጣለች። ወንዶች ይገኑበታል፤ በምላሹም ሴቶች የበታችነታቸውን ያረገግጡበታል በሚባለው ሴተኛ አዳሪነት በባላይነት ትንቀሳቀሳለች።

> "አንቺኮ ሽርሙጥናን እየኖርሽበት አይደለም!? ብቀላ ነው የያዝሽው"
>
> "አይምስልህ አንዴ ከገባሁበት በኋላ ተመችቶኛል ያጣሁትን ነገር ሁሉ በራሴ ፍላጎት መስራት ማግኘት የቻልኩበት ሕይወት ነው! አለች ፈርጠም ባለ አቋም (ገጽ 137)
>
> ሴተኛ አዳሪነት እንደብዙዎች እምነትና ተግባር ሴት ስለተሆነ ብቻ የሚሰራ ስራ ከመሆን ከፍ ብሎ "ሳይንስ" ይሆናል።
>
> … "ሽርሙጥና ለኔ ሳይንስ ነው ብለሽኝ ነበር"
>
> "አሁንም እልሃለሁ! አዎ ሳይንስ ነው! ሂሳብም ነው! ሳይንስ የሚሆነው አንተ ራስህንም ሆነ ሌላውን በደንብ መረዳት ከቻልክ ነው እዚህ ሰፈር የሚሰሩ ሴቶች ምን ሲሉ እንደሰማሁ ታውቃለህ "የሰሞኑ አኪር የከሊት ነው" "በዚህ ወር እከሊት ዛር ቆሞላታል" ምናምን ይላሉ። እኔ እንዲህ ዓይነት ነገር አይገባኝም እኔ እስከፈለግኩ ድረስ የፈለግኩትን የማድረግ ብቃት እስካለኝ ድረስ ወንድ ሁሉ በዘመቻ ታፍሶ አገሩ ጭር እስካላለ ድረስ የምፈልገውን ያህል ወንድ ሰርቼ የማልገባበት ምክንያት አይታየኝም ያገኘሁትን ማግበስበስ ግን አልፈልግም"
>
> "ቢዝነሱን የሚመራው የደንበኛሽ ፍላጎት አይደለም?"
>
> "ልክነህ! ፍላጎቱ የወንዱ ነው ቢዝነሴን የምመራው ግን እኔም ጭምር ነኝ በሌላ አባባል እኔም በራሴ ዘዴ እመራዋለሁ ማለት ነው"
>
> "እንዴት አድርገሽ?"
>
> …"በኔ እምነት ውስጥ ቻንስ ብሎ ነገር የለም ቻንስ ሊፈጠር የሚችለው ወይ እብድ ወይ ሰካራም ሲኖር ነው እኔ ደግሞ ሁለቱንም አልጠጋም"
>
> "ቻንስ አይሰራም እያልሽኝ ነው?"

"ስለሌላው አያገባኝም እኔ ግን ተብለጭልጩ ተቁለጭልጩ፤ ባንኮኒ ላይ እንደ ድንጋይ ተጎልቼ እሱ የከፈተውን እምስ እሱ ሳይዘጋው አያድርም እያልኩ በማንጋጠጥ አላምንም ዛሬ እበዳለሁ ይህን ያህል ብር እሰራለሁ ካልኩ አልኩ ነው በቃ ዛሬ ማንም ምንም ዓይነት ብር ይዞ ቢመጣ አልሄድም አልሰራም አልጠጣም ትንሽ ተጫውቼ በዚህ ሰአት ወደቤቴ እገባለሁ ካልኩም አልኩ ነው ከዚያኛው ወንድ በቀር ሌላ ወንድ ወርቅ ቢያንጥፍልኝ አልሄድም ካልኩም የመረጥኩት ላይ የምሰራውን ሰርቼ እርፈበታለሁ ካልሆን ይቀራል ማለት ነው፡፡

"ወንድ የሚፈልጋትን ሴት እንደሚወስድ ነበር የማውቀው" አልኩ በግርምት

"አንድ ነገር ልንገርህ የትም ቦታ ሊዝናና የሚመጣ ወንድ በመልከ፣ በገንዘብ በመኪና ወይም በሌላ ነገር እንጂ በሴት ውበትና ጥበብ በመጠመድ በኩል ሁሉም አንድነው ገና ወደዚህ ሰፈር ሲመጣ ማወቅ ትችላለህ መጠጥ ብቻ ቢፈልግ ሌሎች ቦታዎች ላይ ያገኘው ነበር ሴት ብቻ ቢፈልግ ፍቅረኛና ሚስት ትበቃው ነበር ሁለቱንም አንድ ቦታ ፈልጎ ከመጣ ደግሞ እኔም ያለጥርጥር መፈለጌን አውቃለሁ፡፡"

"እሺ ወንዱ መጣ ያንቺ ድርሻ ምንድን ነው ስትጠሪ መሄድ አይደለም?"

"ማን አለና? እየት አድርጌ መስሎ የታየኝን ማጥመድ ስችል!""

"እጥምደሽስ?"

"ዓይኑን በልጥጨ ዘው ነዋ!"

"ጉድ ፈላ አይኖቼን በሃይል አፈጠጥኩባት መስል በነገር ቀደመችኝ"

"የወንድ አይን በሽፍደት እንዴት እንደሚበለጠጥ መቼም ታውቀዋለህ?"

"አንቺ ካልነገርሽኝ በምን አውቃለሁ? አልኳት ኮስተር ብዬ…

"እንደ አለባበሴ ነዋ ዋናው ማጥመጃዬ የሰውነቴ ቅርጽ ነው አይኔ፣ የእጆቼና የእግሬ ጣቶች ከንፈሬ፣ ፀጉሬ፣ አምብርቴ ጭምር ያጠምዳል፣ ወንዶች የሴት ልጅ አምብርት ማራኪ ቅርፅ ይዞ ካዩ አቅላቸውን ይስታሉ" በተመስጦ ማድመጥ ቀጠልኩ፣ የወሲብን ፍልስፍና የምታስተምር እንጂ ስለሽርሙጥና የምታወራ አልመሰል አለኝ!

"ሱሪ ካደረግኩ ጃርባዬን ሰጥቼው የፒኪኒዬን ገመድ አልፎ አልፎ ሳብ እያደርግኩ በቂጤ ቦይ ላይ አጫውታለሁ አቀማመጤን የማስተካከል እየመሰልኩ ወደፊት፣ ወደኋላ ወደግራ፣ ወደቀኝ እያጋደልኩ ከተቀመጥኩበት ወንበር ጋር እፋተጋለሁ አጭር ሚኒ ከለበስኩ ደግሞ አቀማመጤ ቀሚሴን የሰበሰበው እያስመሰልኩ እግሮቼን ከፈት እያደረግኩ የጭኔን መገጣጠሚያ አልፎ የፓንቴን ጠርዝ እስኪያይ ድረስ አጋብዘዋለሁ!"

"ከሙዚቃው ምት ጋር የእጆቼን ጣቶች ወደ ጡቴና ወደ ዳሌዬ በመላክ ፒያኖ እንደሚጫወት እጠበጥባለሁ፡፡ አልፎ አልፎ የአምብርቴን ዙሪያ በጣቶቼ እያካለልኩ ከራሴ ጋር እጫወታለሁ! አንዳንዴ ሎሊፖፕና ከረሜላ ከንፈሬ ላይ እያንከባለልኩ የምጠጣበትን ብርጭቆ አፍ በከንፈሬ እየዳበስኩ ማንንም እንደማላይ አስመስዬ የጐሪጥ እያየሁት ነፍስና ስጋው እስኪለይ ድረስ አብጦ እንዲፈራገጥ አደርገዋለሁ!"

"እጆቼን ጭኖቼ መሃከል መሽጎጥም እችላለሁ፣ የእግሮቼን ጣቶች በባለጌ ወንበር ብረቶች ዙሪያ እያጠላለፍኩ ማሻሸትም አያቅተኝም፡፡ ታዲያ ይሄ ሁሉ ምን ይመስልሃል? የወንዱን ዓይን መብዳት ነው! እንደዚህ አድርጌ የበዳሁት ወንድ የሚምረኝ ይመስልሃል? ሁለመናው እሳት ነዶበታላ! ያየው ቀዳዳና ስንጥቅ ሁሉ የእኔ እንትን እየመሰለው ይጎመጇል ለተበዳ የወንድ ዓይን የጠርሙስ አፍ ሳይቀር እንትን ይመስለዋል፡፡ ምላሱን ሲወትፍበት ልታይ ትችላለህ አሷን ቢያጣ ሌላ፣ የሰው ቢያጣ የኩብት፣ ፍጡር እንኳን ቢያጣ ግድግዳ ፈርፍሮ ከማድረግ የማይመለስበት ደረጃ ላይ ካደረስኩት ምን እፈልጋለሁ! ቀብረር ነዋ! ከዛ በኋላ ደግሞ" ብላ በእንጥልጥል አስቀረችውና ሳቀች፡፡… (*መንልየ መንልየ ዘ ቺቺኒያ*፣ ገጽ 126-128)

በሴተኛ አዳሪነት ሕይወት የወንዶች የበላይነት ይረጋገጥባቸዋል ተብለው ከሚነሱት ጉዳዮች ዋነኛው ገንዘብ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ወንዱ ገንዘብ እስከያዘ ድረስ የሚፈልጋትን ሴት መርጦ፣ እንደፈለገ አድርጐ ለብቻው ወሲባዊ እርካታውን ለማግኘት በመቻሉ ነው፡፡ ይሁንና በዚህ ታሪክ ውስጥ ያለችው ሴት ይህ እውነታ ሌላ ገጽታ እንዳለው ታሳያለች፡፡ ከምርጫው ሲጀምር የሚገለጠው በወንዱ ድምፅ ሊሆን ይችል ይሆናል እንጂ ምርጫውን የሚፈፅመው ተገዶ ነው፤ በተለያዩ ድምፅ አልባ ድርጊቶች በሲቷ ከተመረጠ በኋላ ነው፡፡ ያንን አስገዳጅ ሁኔታ የሚሰራው ደግሞ የሴት ልጅ አካል በወንዱ ልጅ ወሲባዊ ተፈጥሮ ላይ ባለው የበላይነት በመጠቀም ነው፡፡ መርጣው ነውና የሄደችው ወሲባዊ እርካታው አብሮ ይመጣል፡፡ ይህ ብቻ አይደለም፡፡ የሴት ገላዋ በዚህ ዓውድ ውስጥ፣ የጥንካሬዋ፣ የብርታቷና የኃያልነቷ ማሳያ ሆኖ ነው የቀረበው፡፡ በዚህ ትዕይንት ውስጥ የሚና ለውጥን--የወንድነትንና የሴትነትን ሚና--ጭምር ማጤን እንችላለን፡፡ የቋንቋዋ ሁኔታ በተለይ የቃል ምርጫዋ ይህንን ለውጥ እንዲያሳይ ተደርጎ ነው የተቀረጸው፡፡ በተለይ የወንዱ ዓይን የሴትነትን ሚና ወስዷል--"ዓይኑን በልጥጨ ዘው ነዋ!" “የወንዱ ዓይን ሙብዳት ነው”--፤ በምላሹ የእርሷ ገላ (መላ ሰውነት) ወንድነትን ነጥቋል፡፡ የሚና ለውጡ፣ ወንዱ የሚዘለቅ፣ ሴቷ ደግሞ የምትዘልቅ መሆናቸው ነው፡፡

ነገረ ወሲብ በመሠረቱ ከሌሎች ጋር በሚኖረን መስተጋብር የሚፈጠር ማኅበራዊ ክስተት መሆኑን፣ መስተጋብሩ በባህሉ ውስጥ ባለ የኃይል አሰላለፍና ሐቲት እንደሚወሰን ንድፈ ሐሳባዊ ዳራ በሰጠሁበት ምዕራፍ ለማመልከት ሞክሬያለሁ፡፡ በማኅበራዊ ግንባታውያን እምነት ደግሞ የነገረ ወሲብ ጣጣዎች በዚህ ዓይነቱ ሐቲት ላይ የሚመሠረቱ ሲሆኑ ቋንቋ ይህንን ሁሉ ለማከናወን እጅግ የላቀ ሥፍራ አለው፡፡ ድርሰቶቹ እንዲህ ባለው ቅኝት የተጠመቁ የሚመስሉ ገጸ ባሕርያትንም የያዙ ናቸው፡፡ የቋንቋ ኃይል የገባቸው የሚመስሉት እነዚህ ገጸ ባሕርያት፣ በቋንቋ መሣሪያነት የሴተኛ አዳሪነት ሕይወታቸውን በሚመለከት ራሳቸውን ያሳምናሉ፤ ከማኅበሩ ትችት ራሳቸውን ይከላከላሉ፤ አዲስ ምንትነት ለመገንባትና እሱኑ በወጉ ለማስረዳት፣ ለዚህ ምንትነታቸው አዲስ ፍቺ ለማርቀቅ፤ በጥቅሉ አዲስ ሐቲት ለመመሥረት ይታገላሉ፡፡ በዚህ ሁሉ ሂደት ውስጥ እያነወረ፣ እየወነጀለ “ሌላ” የሚያደርጋቸውን ማኅበር በገዛ ራሱ ሐቲት አነውረውና ወንጅለው ወደ “ሌላነት”--ለዚያውም እጅግ ወደ ከፉ “ሌላነት”--ይቀይሩታል፡፡ ስለዚህ ሴተኛ አዳሪነት አንድም፣ ማኅበሩ ካገለላቸው ይልቅ ማኅበራቸውን የገፉና የናቁ ሴቶች መገኛ ሆኗል ማለት ይቻላል፡፡ ይህንን ዓይነቱን ማጠቃለያ ተጨባጭ ለማረድግ እንድንችል ተከታዩን፣ ከሰዓት ኋላፊ የመጀመሪያ ቅጽ የተወሰደውን አስረጅ መመልከቱ ይበቃል፤

"አሁን ስንት ደርሷል ዕድሜሽ?"

"27 ሞልቶኛል መዝናናት እወዳለሁ፡፡ ሁሉም ሰው ተደስቶ ተዝናንቶ መኖር ነው ያለበት"

"አሁን አንቺ ደስተኛ ነሽ ማለት ነው?"

"ምነው ደስተኛ አልመሰልም?"

“ሴትነትሽን ቸርችረሽ ፣ ስጋሽን ሸጠሽ እየኖርሽ እንዴት ደስተኛ ልትሆኚ ትችያለሽ?"

"አትሳሳት!! ወደዚህ ነገር ውስጥ የከተተኝ ነገር ነው እንጂ መጥፎ እዚህ ነገር ውስጥ ከገባሁ በኋላ ያለው ነገር አይደለም፡፡ በእርግጥ ስጋዬን እንድሸጥ ያደረገኝ ነገር ችግር ነው፡፡ ስጋዬን ሽጬ መኖር ከጀመርኩ በኋላ ግን 'ችግር ደህና ሁኚ' ብያለሁ ስለዚህ 'ደስተኛ አይደለችም' ብለህ ልትደመድም አትችልም"

"እና ስጋሽን ሸጠሽ በመኖርሽ ደስተኛ ነሽ ማለት ነው?"

"ስጋዬን ሽጬ ስለመኖሬ እርግጠኛ ነህ?"

"እንዴ....! ምን እያልሽ ነው?"

"ሁላችሁም ሰይጥኖች ናችሁ የምለው ለዚህ ነው የማታውቀውን ነገር ልነግርህ እችላለሁ፡፡ የትኛውም ወንድ ገንዘብ ከፍሎ ሲወስደኝ እኔ ሙት ገላ ያለኝ በድን ነኝ ከየትኛውም ወንድ ጋር ስተኛ ሕይወት አለኝ ብዬ አስቤ አላውቅም፡፡ ስለዚህ እኔ ስጋዬን ሽጬ እየኖርኩ ነው ለማለት አልችልም፡፡ እነርሱ አሻንጉሊት አቅፈው እንደተኙ ነው የሚቆጠረው፡፡ በድንና ሙት ገላ በገንዘባቸው የገዙት ሰዎች ናቸው ሞኞቹ"

"ተፈላሰፊ ነሽ ልበል?"

"ፍልስፍና አይደለም! እውነት ነው! ገንዘብ ከፍለው ይዘውኝ የሚሄዱ ወንዶች ከሴት ጋር የተኙ ይመስላቸዋል እንጂ አይደለም፡፡ እኔም ሆንኩ ሌሎች ሴቶች ከወንዶች ጋር ስንተኛ በድኖች ነን፡፡ ሕይወት ከሌለው ሰው ጋር የምትፈፅመው ወሲብ ምን ስሜት ይሰጥሃል? ወሲብ እንደዚህ ነው? ወሲብ እኮ በሁሉም የተፈቃቀዱ ጥንዶች መሐከል የሚፈፀም ጤነኛ ግንኙነት ነው እንጂ ሙት ገላ አቅፈህ የምትፈፅመው ነገር አይደለም፡፡ ወንዶች ግን ቂል ሰይጣኖች ስለሆኑ ይህን እንኳን ለመረዳት አልቻሉም፡፡" (ገጽ 324-325፤ አጽንኦቱ የእኔ ነው)

ደጋግሜ እንዳነሳሁት በብዙዎች እምነት ሴተኛ አዳሪነት ሴት ልጅ የሰውነት ክብሯን የምትገፈፍበትና የምትዘቅጥበት ተግባር ነው፡፡ ሴት ልጅ በዚህ ተግባርና ሁኔታ ውስጥ ስሜት አልባ ወሲብን በመነገድ ወደ ሕይወት አልባ ዕቃነት ትቀየራለች፡፡ ይሄ ዓይነቱ አመለካከት አንድም የብዙ ሙግቶች ምንጭ ነው፤ አንድም ሴተኛ አዳሪነት “ወሲባዊ ፍንገጣ ነው” ለመባሉም ሆነ ሴተኛ አዳሪዎች በ“ሌላነት”ለመፈረጃቸው መሠረታዊ ምክንያት ነው፡፡ በዚህ ምልልስ ውስጥ የምናስተውለው እውነታ ግን የዚህ ግልባጭ ነው፡፡ ‘ሴተኛ አዳሪነት ሥጋ መቸርቸር አይደለም’ የሚል እንግዳ፣ ነገር ግን እጅግ ጠንካራ ሙግት ይገጥመናል፡፡ ሙግቱ፣ ሴተኛ አዳሪነትን “ከበድንነት፣ ከሙት ገላነት” የሚያመሳስለውን የባህሉን ነባር ዘይቤ “ተቀብሎ”[11]፣ የማኅበሩን የ“ሌላነት” ሐቲት ፉርሽ ያደርጋል፡፡ ክርክሩ፣ ከስሜታችን ውጪ “እኔም ሆንኩ ሌሎች ሴቶች ከወንዶች ጋር ስንተኛ በድኖች ነን፡፡ ሕይወት ከሌለው ሰው ጋር የምትፈፅመው ወሲብ ምን ስሜት ይሰጥሃል?” በሚል እንግዳ አመክንዮ ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ ይህ አመክንዮ በቀላሉ አይገፋም፤ ከነጭራሹ አይነቀነቅም፡፡ ይልቁንስ በራሱ፣ በባህሉ ዘይቤ ሴተኛ አዳሪነትን ነጻ አውጥቶ ማኅበሩን “ሌላ” ያደርጋል፡፡ በዚህ፣ ለማኅበሩ በተሰጠው አዲስ

---

[11] ቲሞቲ ጊልፎይል (Timothy Gilfoyle) “በድንነት”ና ከዚሁ ጋር የተዛመዱ ቅጥያዎች (*“rotting flesh, corpses, and filth”*) በብዙ ባህሎች ውስጥ ለረጅም ዘመን ለሴተኛ አዳሪዎች መግለጫነት ጥቅም ላይ ሲውሉ የኖሩ ዘይቤዎች መሆናቸውን ይጠቁማል (1999፡ 118)፡፡

"ሌላነት" ውስጥ የምናስተውለው "ነውር"፣ "ኃጢአት"፣ "ወንጀል"፣ ወዘተ. ከሴተኛ አዳሪነቱ "ሌላነት" በብዙ ያጥፋል፡፡ ይህንን ዓይነቱን የሚና ለውጥ ነው የባህል አጥኚዎች፣ በተለይም የነገረ ወሲብ ተመራማሪዎች "*reverse discourse*" ሲሉ የሚገጥመን ("ግልብጥ ሐቲት" እንበለው ይሆን?) ፡፡

ይሁንና ይህ ሙግት የማኅበሩን "ክብር" የሚገፋ እንጂ ለብቻው ሴተኛ አዳሪነትን ነጻ የሚያወጣ ላይሆን ይችላል፡፡ እዚህ ላይ ልብ ሊባል የሚገባው ጉዳይ ሴቷ ስሜቷን መከልከሏ እና በድን መሆኗ የምርጫ ጉዳይ መሆኑን ነው፡፡ በድንነትን የመረጠች ሴት የመራቢያ አካሏን ነው እንጂ፣ በተለይ ከንፈርና ጡቷን አትሰጥም፡፡ ከንፈርና ጡት በእኛ አገር ሴተኛ አዳሪዎች ዘንድ ብቻ ሳይሆን በብዙ ቦታዎች ለድርድር የማይቀርቡ ለወሲባዊ ተግባሩ የተከለከሉ ክፍሎች ናቸው፡፡ በእነዚህ ገደቦች አማካይነት ነጻ ሰውነቷን ማረጋገጥ ትችላለች፡፡ ጡትና ከንፈር የሴትነት ብዙ መገለጫ ናቸው፡፡ ትእምርታዊ ፍቺውን ትተን እንዲሁ ከወሲባዊ ተራክቦ አንጻር ብቻ እንኳን ብናያቸው የፍቅር፣ የጠበቀ ስሜት መግለጫና መቀስቀሻ ናቸው፡፡ በመሆኑም በዚህ ታሪክ ውስጥ የሴትነት ገላ በጥቅሉ ስሜት አልባነቱ ተገልጦ "በድን" ተባለ እንጂ፤ የከንፈርና ጡት አለመደፈር የሴቶቹን የመምረጥና የመወሰን አቅም፣ እንዲሁም የራስ ባለቤትነታቸውን ያመለክታል፡፡

## 3.2. በተመሳሳይ ጾታ መኃል የሚፈጠር ፍትወት

በተመሳሳይ ጾታዎች መኃል የሚፈጸም ግንኙነት ለአማርኛ ሥነ ጽሑፍ እንግዳ አይደለም፡፡ ቴዎድሮስ ገብሬ፣ በሌላ ለሕትመት በተዘጋጀ መጣጥፉ፣ "የስብሐት መጫወቻ ካርዶች፤ ፍትወት፣ ልቡናና ታሪክ"፣ የአማርኛ ሥነ ጽሑፍ ቢያንስ ቢያንስ ታደሠ ሊበንን መነሻ ያደረገ መሠረት እንዳለው ያስረዳል (ገጽ 39)፡፡ ይህን ልማድ በማስቀጠል ረገድ ስብሐት ብዙም አቻ የሚገኝለት አይመስልም፡፡ የስብሐት ረጃጅም ልብ ወለዶችና ኖቬላዎች "በሆሞኤሮቲክ ጭብጦች የተሞሉ ናቸው" የሚለው ቴዎድሮስ በየድርሰቶቹ ውስጥ ግን እነዚህ ለባህሉ እንግዳ የሚመስሉ ጭብጦቹ በተመሳሳይ መንገድና በአንድ ዓይነት ደረጃ እንደማይገኙ ሲያስረዳ፣ "በሌቱም አይነጋልኝ ይህንን ዓይነቱን መሳሳብ [በተመሳሳይ ጾታ መኃል የሚፈጠር ፍትወታዊ መሳሳብ] እጅግ በተራቀቁ ቴክኒኮችና ትእምርቶች በስውር የሚነድፈው ስብሐት በሰባተኛው መልአክ ውስጥ በገሃድ፣ በምልልስም ይባል በድርጊት ገልጦ ያሳያል" ይላል (ገጽ 41-42)፡፡ በእኔ የንባብ ልምድ ከስብሐት በኋላ ይህንን ጉዳይ የታሪኮቻቸው አካል አድርገው የቀረቡ ድርሰቶች የገጠሙኝ በ1990ዎቹ፣ በተለይ በተድባበ ጥላሁን፣ *መኃልየ መኃልየ ዘካዛንችዝ* (1992) እና በሰለሞን ሹምዬ *ገመና* (1999) ውስጥ ነው፡፡ ይህ ጭብጥ ከ20ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ በኋላ ባለው ጊዜ እንዲህ ሲንደረደር ከርሞ ነው ለጥናት እመረጥናቸው የ21ኛው ክፍለ ዘመን መባቻ ድርሰቶች ላይ የሚያደርሰን፡፡

በ21ኛው ክፍለ ዘመን መባቻ ድርሰቶች ውስጥ "ግብረ ሰዶማዊነት" በተለይ ከሴተኛ አዳሪነት ጋር ተቆራኝቶ የሚገኝ ሲሆን በአንደኛው ድርሰት ደግሞ በተጨማሪ "ሳዶማሶቺዝም" (*sadomasochism*) ከሚባለው ጉዳይ ጋር የደምና የሥጋ የሚመስል ዝምድና አለው፡፡ በድርሰቶቹ ውስጥ የሚገጥመን "ግብረ ሰዶማዊነት" በመጠንም በዓይነትም ይለያያል፡፡ በ*መኃልየ መኃልየ ዘ ቺቺኒያ* "ሴት ነኝ ሴትነቷን አሳምሬ አውቀዋለሁ፤ እንደሙዚቃ ነው የማደምጣት፤ ዝግ ያለችውን ዝግ ባለ ሪትም እየዘለለች መፍረጥ ያማራትንም እንዳማራት ሆኜ አስደስታታለሁ" (2001፣ 53) የምትል፣ "ጣእቷ" በሚል ቅጽል የምትታወቅ ሴት "ግብረ ሰዶማዊት" ገጸ ባሕርይ ትገጥመናለች፡፡ በበባሕል ተጋፊነቱ የሚስተካከለው ያለ የማይመስለኝ ድርሰት፣ *የሰዶም ነፍሳት* ሙሉ በሙሉ በተመሳሳይ ጾታ መሳሳብ ላይ አተኩሮ ከመጻፉና ሴተኛ አዳሪነትን ጎን ለጎን ከመያዙ ባሻገር፣ ከኃይልና ከጸብ ጋር የተቀየጠ ወሲብ የገነነበት ነው ማለት ይቻላል፡፡ በመሆኑም ሌሎቹን አስተሳስሮ ለመመልከት እንዲያስችለኝ ትንታኔዬን በዚህ ድርሰት ላይ እመሠርታለሁ፡፡

"ግብረ ሰዶም" የሚለውን ቃል መቼና በማን አማካኝነት ግልጋሎት ላይ ማዋል እንደጀመርን ለማወቅ ቢከብድም ቃሉ ግን ከመጽሐፍ ቅዱሱ "የሰዶምና ጎመራ" ታሪክ ስለመወሰዱ መገመት ይቻላል፡፡ የቃሉን ፍቺ *የአማርኛ መዝገበ ቃላት* ሲፈታው "በወንድና በወንድ መካከል የሚደረግ የግብረ ሥጋ ግንኙነት" በማለት ነው (1993፣ 499)፡፡ በተመሳሳይ የምዕራቡ ዓለም "*sodomy*" ቀደምት የሚባለው ስያሜ ሲሆን መጠሪያው በተመሳሳይ ጾታ (በተለይም በወንዶች) መካከል የሚኖርን ወሲባዊ ግንኙነት ከመግለፅ ባሻገር፣ በመቀመጫ የሚፈፀሙ የትኞቹንም ወሲባዊ ተግባራት ለመግለፅ አገልግሎት ላይ ይውል ነበር፡፡ ምዕራቡ ዓለም በ19ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ እርግማን፣ መቅሰፍት፣ ቁጣ፣ የመሳሰሉ እሴቶች የተጫኑበትን "ግብረ ሰዶም" (*sodomy*) የሚለውን መጠሪያ ትቶ ከእሴቶቹ በጸዳው ቃል፣ "*homosexuality*" መገልገል ጀምሯል፡፡ "*homosexuality*" በዘመናዊ አጠቃቀሙ በተመሳሳይ ጾታ መኃል የሚፈጠርን ፍትወታዊ መሳሳብ የሚያመለክት ቃል ነው፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ስሜት የሚስማቸው ወንዶችም ይሁኑ ሴቶች በወል "*homosexual*" ተብለው የሚጠሩ ሲሆን ሴቶቹ "*lesbian*" የሚል አማራጭ መጠሪያም አላቸው፡፡ ሃውክስና ስኮት (Hawkes and Scott) እንደሚሉት (2005፣ 19) ከቅርብ ጊዜያ ወዲህ የተመሳሳይ ጾታ መፈቃቀድ ከ"ኩነኔ"ና ከ"በሽታ" ጋ ተዛምዶ መታሰቡ እያበቃ እንደ የአኗኗር ዘይቤ መቆጠር ስለጀመረ "*queer*" እና "*gay*" የሚሉ መጠሪያዎች የተሻለ ተቀባይነት እያገኙ መጥተዋል፡፡

የአገራችን የሥነ ጽሑፍ ሥራ በሆነው *የሰዶም ነፍሳት* ውስጥ የስያሜ ጣጣ ትኩረት አግኝቷል፡፡ ዋናው ገጸ ባሕርይ አብይ እራሱንም ይሁን በተመሳሳይ ተግባርና ሕይወት ውስጥ አሉ የሚላቸውን ሰዎች ሁሉ "ግብረ ሰዶማዊ" እያለ ይጠራል፡፡ ሆኖም ቃሉ አዎንታዊ አንድምታ እንደሌለው ደግሞ ይገልፃል፡፡

በድርሰቱ ውስጥ "ግብረ ሰዶማዊ" ከሚለው መጠሪያ ይልቅ "ዜጋ" የሚለው ቃል ሲመረጥ እናስተውላለን፡፡ "ዜጋ" ከድርጊቱ ይልቅ የግለሰቦቹን ማኅበራዊ ህልውና መጠቆም የሚችል መጠሪያ ነው፡፡ ይህም በድርሰቱ ውስጥ ተደጋግሞ ተገልጾ ይገኛል፡፡

> የሌላ አለም ሰዎች የሆንን ያህል ቢሰማንም እኛ ዜጎች የራሳችን አለም ያለን ነን፡፡ እውቅና የተሰጠው አድርና እቁብ ባይኖረንም ዜጋችን ሲሞት ጡሩንባ ሳናስነፋ፣ ማንነቱንና ምንነቱን ሳንገልፅም ቢሆን እንቀብረዋለን፡፡ ታሞ ቢተኛም እርስበርሳችን ስለምንረዳዳ እንጠይቀዋለን፡፡ ቢቸገረው እንደርስለታለን፡፡ አንድ ዜጋ በብቸኝነት አለም ውስጥ ብዙ ከቆየ በጭንቀት ምክንያት እንደሚታመም፣ እንደሚያብድ አልፎ ተርፎም ራሱን እንደሚያጠፋ እናውቃለን፡፡ ራሳቸውን ከማኅበረሰቡ ጋር አዋህደው በስልት የሚኖሩት አውጪዎች ናቸው፡፡ እነሱ ለሴትም (ዐይነ ጥላ) ሆነ ለወንዱ እንትናቸው ዝግጁ ነው፡፡ ወጪዎች ግን ከማኅበረሰብ ጋር ለመመሳሰልም ሆነ ትዳር መስርቶ ለመኖር ያዳግተናል፡፡ በጣም ጥቂቶች ናቸው በዚህ ረገድ ስኬታማ የሆኑት፡፡ በራሳችን አለም ግን ባንዋለድና ባንባዛም ትዳር እንመሰርታለን፡፡ ፓርቲ እናዘጋጀለን፣ እንደ ሴትም ለብሰን በነፃነት ሴት እንሆናለን፡፡ (ገጽ 213)

"ዜጋ" የሚለው መጠሪያ በየሰዶም ነፍሳት የተለያዩ ተግባራትንና ሁኔታዎችን ለመግለፅ ግልጋሎት ላይ ውሏል፡፡ ለምሳሌ እራስን ከሌሎች ("ግብረ ሰዶማዊነት"ን ከሚቃወሙ፣ ከሚጠየፉ፣ ከሚፈሩና በነዚህ ምክንያቶች አደጋ ሊጥሉ ከሚችሉ) ለመሠወር ወይም ጭምብል ለማበጀት፣ ምንትነትን (ማኅበራዊ፣ ነገረ ወሲባዊ፣ ሥርዓተ ጾታዊ) ለመለወጥ፤ "አሮጌ" የአኗኗር ዘይቤን (*life style*) ትቶ "አዲስ" ማኅበራዊና ተቋማዊ ህልውና ለማግኘት፤ ወዘተ.፡፡

> ሁላችንም በዜግነት አለም ሁለተኛ ስም፣ ሁለተኛ ድርጊት አለን፡፡ የራሳችን የሆነ ማህበራዊ ኑሮ አለን፡፡ ከመውለድ በቀር ህጋዊም እንኳን ባይሆን እንጋባለን፡፡ በህግም በኩል እንኳን ባይሆን እንካሰሳለን፣ ሚስጥራችን አደባባይ እንዳይወጣብን ስንል በዜጎች ጓደኞቻችን የሚሰጠንን ፍርድ እንቀበላለን፡፡ (ገጽ 132)

ማኅበረሰብ፣ ድርጊቶችንና ኔታዎችን ልክ እና ስህተት፣ ተቀባይነት ያለውና የሌለው ወዘተ እያለ ይፈርጃል፡፡ በመሆኑም እንደ ባህሉና እንደ ዘመኑ የየራሱን ሚዛን ይዞ እንደሚገኝ ቀደም ባለው ምዕራፍ ገልጫለሁ፡፡ በዚህ ሚዛን ውስጥ ገብቶ ሚዛን ያልደፋው ጉዳይና የጉዳዩ ባለቤት ፍንገጣ እና አፈንጋጭ ተብለው ይገፋሉ፤ ከፍ ሲልም ቅጣት ይወድቅባቸዋል፡፡ ይህ ማኅበሩ ከብርና ሥፍራ የነፈገው ወገን በትልቁ የሚዋጥበት አጋጣሚ ቢበዛም (ምክንያቱም አፈንግጦም ቢሆን ራሱን የሚመዝነው በዚያው ማኅበረሰቡ በሰጠው ዐይን ስለሆነ) አንዳንዴ ግን ሌላ መንገድን ይመርጣል፡፡ መዝኖ ያቀለለውን፣ ስህተት ብሎ የጣላውን፣ ጥፋት ብሎ የቀጣውን እና "ሌላ" ብሎ የገፋውን አካል የሚቋቋምበት ከፍ ሲልም "ሌላ" ብሎ እራሱን "ትክክል"፤ "ትክክል" ነኝ ያለውን "ስህተት" የሚያደርግበት የራሱን መመዘኛ ያዘጋጃል፡፡ ይህ ዓይነቱን እውነታ ጭምር ነው በድርሰቱ ውስጥ የምንመለከተው፡፡

ከድርሰቱ ከተወሰዱ አስረጂዎች መመልከት እንደምንችለው፣ "አፈንጋጭ" ተብለው ከማኅበረሰቡ የተለዩት እነዚህ "ዜጎች" የራሳቸው ዓለም አላቸው፡፡ ልክ እንደማንኛውም ተቋም በአባላቱ ፈቃድና ፍላጎት ላይ የተመሠረተ ሲሆን የራሱ ህግና ደንብ፣ የሚታወቁ አባላት፣ የተለያዩ ንኡሳን ተቋማት

(የጋብቻ፣ የእቁብ፣ የእድር ወዘተ) እና ተግባራት አሉት፡፡ የትኛውም አባል ደግሞ ለሕገ ደንቦቹ እና ለአኗኗር ሥርዓቱ ተገዢ ይሆናል፡፡ ምክንያቱም ተቋማቱ በችግር ጊዜ ከመድረስና ጥላ ከመስጠት ባሻገር የማኅበሩን አባላት ከራሳቸው ጭምር ይታደጋሉ፡፡

ይህ ማኅበራዊ ተቋም ደግሞ "የግብረ ሰዶማዊነት" ብቻ ሳይሆን የሴተኛ አዳሪነትም ጭምር ነው፡፡ "የግብረ ሰዶማውያን" ሴተኛ አዳሪነት ከተለመደው ሴተኛ አዳሪነት (ከሴቶቹ) ይለያል፡፡ ምክንያቱም በድርሰቱ ውስጥ በገሃድ እንደምንመለከተው ለብዙዎቹ ከገንዘብ ይልቅ ወሲባዊ ደስታው ይቀድማል፡፡ ልክ እንደ ሴቶቹ ሴተኛ አዳሪነት "የሴትነት ባሕርይ" ያላቸው ግብረ ሰዶማውያን የሴቷን ቦታ ይዘው ለሥራው ይውጡ እንጂ ወንዶቹ (አውጪ "ግብረ ሰዶማውያኑ") ገንዘብ ስለያዙ ብቻ ፍላጎታቸውን ማሟላት አይችሉም፡፡ ሴተኛ አዳሪዎቹ (ወጪዎቹ)፣ ግብረ ሰዶማዊነታቸውን ለደንበኞቻቸው ከማስተዋወቅ አንስቶ የፈለጉትን ወንድ ከፍለው እስከመውሰድ የሚደርስ ነጻነት አላቸው (ገጽ153-54)፡፡

በተመሳሳይ ጾታ መፈቃቀድ ላይ በተመሠረቱ ጥናቶች ውስጥ ተደጋግመው ከሚገጥሙን ጉዳዮች መኃል አንዱ የ"ንቁነት" (*active*) እና የ"ፍዝነት" (*passive*) ሚና ነው፡፡ "ንቁነት"ና "ፍዝነት" የተለያየ ፍቺዎች ሊሰጧቸው የሚቻል ቢሆንም አንደኛው ፍቺ በወሲባዊ ተግባር ወቅት የሚኖርን ሚና የሚያሳይ ነው፡፡ በዚህ ትርጓሜው ስናነሳው በግብረ ሥጋ ግንኙነት ወቅት የወንድ ብልቱን የሚጠቀመው ተዳኝ "*active*" ሲባል የወንድ ብልቱን የሚቀበለው ደግሞ "*passive*" በመባል ይታወቃል፡፡ ዶናልድ ዌስት (Donald West) እንደሚያስረዳው፣ እነዚህ ሁለት ሚናዎች ብዙውን ጊዜ ተለዋዋጭ ቢሆኑም በተደጋጋሚ የ "*passive*" ነት ሥፍራን የሚይዙት "ግብረ ሰዶማውያን" በተለየ መልኩ "ግብረ ሰዶማዊነታቸው" ሊለይ የሚችልና እራሳቸውን እንደ ሴት የሚቆጥሩ ናቸው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በአብዛኛው የ"*active*"ነት ሚናን የሚመርጡት ተዳኞች ያንን ሥፍራ ባለመልቀቅ ተባእትነታቸውን ወይም ወንዳወንድነታቸውን ለማስጠበቅ ወይም ከሌላው ከተለምዷዊው ወንድነት "*heterosexual masculinity*" የተለዩ እንዳልሆኑ ለማሳየት የሚሞክሩ ናቸው፡፡ ለዚህም እንደ ሽፋን ይሆናቸው ዘንድ ደጋግመው የሚያነሱት ምክንያት "*passive*" የሆኑት ተዳኞቻቸው የሴት ተለዋጭ አድርገው ስለሚወስዷቸው እንጂ ወንድነታቸው ጉዳያቸው እንዳልሆነ በማሰብና በማሳየት ነው (2008፣ 14)፡፡

ቀደም አድርጌ ከሰዶም ነፍሳት ጠቅሼ ባስቀመጥኳቸው አስረጂዎች ውስጥ በደብዛዛውም ቢሆን "የወጪነት" እና "የአውጪነት" ጉዳይ ተነካክቷል፡፡ በዚህ ድርሰት ውስጥ ባለታሪኩ፣ የተመሳሳይ ጾታ መሳሳብን አስመልክቶ በሚደረጉ ምርምሮች የማይቀሩ ጽንሰ ሐሳቦችን ለይቶና ጎራ አሲዞ፣ አንዳንዴ ብያኔ እየሰጠ ጭምር ሲተነትን ይገጥማል፡፡ ይህ የሚሆነው በተለይ ባለታሪኩ "ዜግነት"ን (ተቋማዊ ሴተኛ አዳሪነትን) ከጀመረ በኋላ ነው፡፡ ወደ ተቋሙ የሚቀላቅለውን መንገድ ሲጀምር አንስቶ ለነገሮች ስያሜ

ማውጣት፣ ዓይነቶችን መግለፅና ብያኔ መስጠት አብረው ይጠነሰሳሉ፡፡ ይህንን፣ በተለይ ደግሞ ቄስትን በመጥቀስ ለማንሳት የሞከርኩትን የ"አውጪ" (*active*) እና የ"ወጪ" (*passive*) "ግብረ ሰዶማዊነት" ምንነትን በመበየን ይጀምራል፡፡

> … አውጪ የሚባለው እንደ እኔ፣ አጠለልና ሃብሏ ያለነውን የወንድ ሴት የሚገናኘን ወንዱ ማለት ሲሆን የማይደረግ ነው፡፡ ወጪ የሚባሉት መደረግ እንጂ ማድረግ የማይፈልጉ ናቸው፡፡ በአጭሩ ወጪ ማለት ሴት፣ አውጪ ማለት ወንዱ ነው፡፡ በትክክለኛው አለም ወንድ ሴት መሆን አይችልም፣ ሴቷም እንደ ወንድ አታደርገውም፡፡ በዜግነት አለም ግን ሁለቱም ይቻላል፡፡ ሴቷ አሁን ሴት ሆና ከሆነ በሰከንድ ወንድም መሆን ትችላለች፡፡ ጾታ እንደፈለገ ሊቀያየር ይችላል፡፡ ብዙዎች ግን ወይ ወጪ ወይ አውጪ ብቻ መሆን ነው የሚመቻቸው፡፡
>
> … ኮርማ አውጪ ማለት ነው፡፡ ቆንጆና ወንዳ ወንድ የሆነ፣ ግን በዜግነት ህይወት ውስጥ የሌለም ኮርማ ተብሎ ሊጠራ ይችላል…" (ገጽ 125 እና 129)

በጥቅሡ እንደተገለፀው "አውጪ/ኮርማ" የሚባለው ተዳኛኝ "*active homosexual*" ብሎ Donald ካስቀመጠው ጋር አንድ ዓይነት ሲሆን ወጪ የሚባለው ደግሞ ከ "*passive homosexual*" ጋር ይገጥማል፡፡ እነዚህ ሁለት ጉዳዮች በድርሰቱ ውስጥ በተለያየ መልኩ ይገለጻሉ፤ ይብራራሉ፡፡ ሲጀመር "ዜግነት" ብለው የሚገልጹት ማኅበራዊ ሕይወት የሚመለከተው ወጪዎቹን ሲሆን እነዚህ "ግብረ ሰዶማውያን" በአብዛኛው እራሳቸውን እንደ ሴት የሚቆጥሩና ሌሎችንም ለማሳመን የሚሞክሩ ናቸው፡፡ የሚወጣላቸው ተቋማዊ፣ አዲስና የጭንብል ስም የሴት ከመሆኑ በተጨማሪ አንዱ ሌላውን የሚጠቅሰው በእንስታዊ ጾታ ነው፡፡ አጠቃላይ በሆነው አካላዊ እንቅስቃሴ እንስታዊ ባሕርይ የሚስተዋልባቸው እንደ አመቺነቱም በሴት መዋቢያዎች እንዲሁም አልባሳት የሚያጌጡ ናቸው፡፡ በአብዛኛው በ"ዜግነት" ማኅበር ውስጥ ያሉ "ወጪ" ገጸ ባሕርያት በልጅነታቸው የሴት ባሕርይ እንደነበራቸው፣ እራሳቸውንም እንደ ሴት እንደሚቆጥሩ፣ አንዳንዶቹም የሴት አልባሳትን ይለብሱ፣ ወይንም በልዩ ልዩ ምክንያቶች ያንን ማድረግ ባይችሉም መልበሱን ይፈልጉት እደነበር ተደጋግሞ ይነገራል፡፡

> …አውጪ ሆነው እንደሴት የሚለባብሱ እንደ ሴት የሚሆኑ እጅግ በጣም ጥቂት ናቸው - ያውም ወጪና አውጪ (አውቶ ሪቨርስ ሁለቱንም የሚሰራ) ከሆነ ነው፡፡ አውጪዎችን ለመበየን ይከብዳል፡፡ ያው ወንድ ናቸው፡፡ በግራ ጆሯቸው ሎቲ ላያንጠለጥሉ ወይ ሊያንጠለጥሉ… ሱፍ ሊለብሱ ወይ ላይለብሱ… ቻፒስቲክ ሊቀቡ ወይም ላይቀቡ ይችላሉ፡፡ ትዳር ሊኖራቸው ወይም ላይኖራቸው ይችላል፡፡ ታቱ (ንቅሳት) ሊኖራቸው ወይም ላይኖራቸው ይችላል፡፡ ወጪዎች ግን ድምፃቸው እንደ ሴት ስለሚቀጥን ይለያሉ፡፡ እንደ ሴት የተኳኳሉ ስለሆኑ ይለያሉ፡፡ ሰለሚቅለሰለሱ ይታወቃሉ፡፡ እምብርት የሚያሳይ ቡዲ ሊለብሱ ይችላሉ፡፡ ሹል ጫማ ሊጫሙ ይችላሉ… ሎቲ ሊደረድሩ ይችላሉ… ፀጉራቸውን ሊሰሩ ወይም ሊፈርዙ ይችላሉ፡፡ ከሩቅ የሚጣራ ለየት ያለ ሽቶ ይቀባሉ (ገጽ 151)፡፡

በጥቅሱ እንደምንመለከተው "አውጪዎች" ላይ አካላዊ ልዩነት የሚታየው በተወሰነ ደረጃ ወይም አልፎ አልፎ ነው፡፡ በአንጻሩ ወጪዎች በጥቅሉ ማለት ይቻላል፣ በሴታዊ ባሕርይ የሚገለፁ ናቸው፡፡ በአብዛኛው "ልቡናዊ ፍናፍንትነት"ን (*psychical hermaphroditism*) ለማጥናት የሚቀርቡ ንድፈ

ሐሳቦች እንደሚገልፁት “ወጪ ግብረ ሰዶም” ራሱን እንደ ሴት በመቁጠር (በአእምሮም ይሁን በአካላዊ ገጽታ) ወንድ ተጓዳኝን ይፈልጋል፡፡ በመሆኑም ከወንዳወንድነት በሚገኝ ውበት ይማረካል፡፡ እንደ ፍሮይድ አመለካከት ይህ ሁኔታ ሁሉንም ወጪ ግብረ ሰዶማውያንን የሚመለከት አይደለም፡፡ ይህ ባሕርይ እንዲያውም በሴት “የወንድ” ሚና ባላቸው ሴት ግብረ ሰዶማውያን ላይ ገንኖ የሚታይ ነው፡፡ “ተንቀሳቃሽ” (*active*) የሆኑት ሴቶች ወንዳወንዳዊ ባሕርይን በአካላዊም በአእምሯዊም መንገድ የሚያሳዩ ሲሆን ከተጓዳኞቻቸው በአመዛኙ ሴታሴትነትን ይፈልጋሉ (ዝኒ ከማሁ፣ 1473)፡፡ በዊክስ እምነት ደግሞ፣ በብዙ “ወጪ ወንዶች” ላይ እንስታዊ ባሕርይን መመልከት የተለመደ ነው፡፡ እንዲያውም በብዙ ባህሎች ውስጥ "ግብረ ሰዶማዊነት" ተቀባይነት እንዲያጣ የሚያደርገው ድርጊቱ ራሱ ሳይሆን የሴት ሚናን የሚወስዱ የድርጊቱ ፈጻሚዎች በሚያሳዩት የ“ሴታሴትነት” ባሕርይ ነው፡፡ ይህ ባሕርይ አባዊ ለሆነ ማኅበር ጥቅሉን ወንድነት (*the very idea of masculinity*) እንደማዋረድ ይቆጠራል፡፡ ዊክስ ለዚህ ክርክሩ በማረጋገጫነት የሚያመጣው ብዙ ባህሎች “ወንድነታቸውን” ጠብቀው ተግባሩን የሚፈፅሙትን (*active homosexuals*) ማኅበሩ ታግሶ አብረውት እንዲኖሩ መፍቀዱን ነው (2004፣ 29)፡፡

ቀደም አድርጌ ከድርሰቱ ወስጄ ባሰፈርኳቸው ጥቅሶች የመጡ ጉዳዮችን ስናጤን የዊክስን ሐሳብ የሚደግፉ ዓይነት ሆነው እናገኛቸዋልን፡፡ ተለምዷዊ ተብሎ የሚገለጸው ማኅበር "ልክ ያልሆነ" ተግባር አትፈፅሙ ሳይሆን ተግባሩን ስትፈፅሙት በአደባባይ አይሁን ብሎ የተቀመጠ ይመስላል፡፡ “ወንድነታቸውን” ጠብቀው ተግባሩን በ"ሽሽግ" የሚፈፅሙትን ባህሉ ችላ ይላል (ባህሉ በወንድነት የቆመ የወንዶች ዓለም መሆኑን ማስታወስ ያስፈልጋል)፡፡ በግልፅም ቢሆን "ወንድነታቸውን ያላንኳሰሱትን" (የወንድነት መገለጫ፣ የኃይል ማሄጃ ትዕምርት (*phallic symbol*) የሆነውን “ወንድነታቸውን” መጠቀም ትተው በሌሎች አካላዊ ክፍሎች ወሲብ የማይፈፅሙትን) "አውጪ ግብረሰዶማውያን" በሁለቱም ዓለማት እንዲኖሩ ይፈቅዳል፡፡ እናት ወንድ ልጇ ሌላ ወንድ ይዞ መጥቶ "ሰዶማዊ" ወሲብ ሲፈፅም እያየች አትገረምም (ገጽ 164)፣ ሚስት ባሏ ከወንድ ጋር “ግብረ ሰዶማዊ” ግንኙነት እንዳለው በወሬ ወይም በግምት ሳይሆን በዐይኗ እያየች ዝም ብላ ትቀመጣለች (ገጽ 189-193)፡፡ ይህን አቋም የሚያጠናክሩ በርካታ ሁነቶች ከድርሰቱ መልቀም ቢቻልም፣ ሐሳቤን ለመቋጨት አንድ አስረጂ ብቻ ጠቅሼ ወደ ሌላ ጉዳይ ልለፍ፡-

> ብዙ ጊዜ ኅብረተሰቡ ግብረ ሰዶማዊ ሥራዎችን እያየ፣ እንዳላየ ይሆናል፡፡ እየሰማ እንዳልሰማ ይሆናል፡፡ አልፎ አልፎ ከሚገጥመን ስድብና ዱላ በስተቀር ዜጋ በመሆኑ እንዲህ ደረሰበት ሲባል የሰማሁት ሰው የለም፡፡ <u>በአነጋገራችን፤ በአለባበሳችንና በአኳኋናችን ሰዎች ከለዩን "ቡሽቲ" እያሉ ይሰድቡናል፡፡ አጉል ታማኝ ነን የሚሉ ቀጦች [streets] ደግሞ ሊመቱ ያሳድዱናል</u> (ገጽ 206፤ አጽንኦቱ የእኔ ነው)

የ"ግብረ ሰዶማዊነት"ን መነሻ ምክንያት ለመፈለግ ብዙዎች ሞክረዋል፡፡ ብዙዎቹም የየራሳቸውን ምላሾች ከሞላ ጐደል አግኝተዋል፡፡ በርካቶች የተለያዩ ተፈጥሯዊ፣ ሥነ ልቡናዊና ማኅበራዊ ማብራሪያዎች፣ ማስረጃዎች አቅርበዋል፡፡ ማናቸውም ግን ሁሉንም የሚያስማማ ወጥ የሆነ ምላሽ መስጠት አልቻሉም፡፡ በተለይ ቀደም ባለው ጊዜ በአውሮፓና በአሜሪካ የተነሱት ተመራማሪዎች ግብረ ሰዶማዊነትን እንደ ፍንገጣ እና እንደ በሽታ ይቆጥሩት ስለበር ምክንያቱን ማግኘት ወደ መፍትሄው የሚያደርስ መንገድ ነው ብለው ያምኑ ነበር፡፡

በፍሮይድ አስተሳሰብ በተመሳሳይ ጾታ ላይ የተመሠረተ የፍትወት ምርጫ (*sexual-object-choice*) ሁለንተናዊ የሆነ ስብዓዊ ክስተት ነው፡፡ በተግባር የሚያከናውኑት በገሃድ ስለታወቁ ነው እንጂ ሁሉም ሰው ኢ-ንቁ በሆነ መልኩ የጾታ ተጓዳኙን ይፈልጋል፤ መርጦም ጥልቅ በሆነው አእምሮው ቆልፎ ያስቀምጣል (ዝኒ ከማሁ፣ 1473)። ይህ ዓይነቱ ዝንባሌ በልጅነት ይከሰታል፡፡ ከዚያ ውጪም በጉርምስና እድሜ ወይም ከጉርምስና እድሜ ጥቂት ጊዜያት ቀደም ብሎ ሊታይ ይችላል። አዝማሚያው ከታወቀ በኋላ እስከ ሕይወት ፍፃሜ ሊዘልቅ፣ ሄድ ብሎ ሊመለስ አልያም ጠፍቶ ሊቀር ይችላል። በሌላ ጊዜ ደግሞ በተለምዷዊ የእድገት ሂደት ውስጥ እንደ አንድ ምዕራፍ ሊከሰት፣ ወይም ከረዥም ዘመን ተለምዷዊው የወሲብ ሕይወት በኋላ ሊፈጠር ይችላል። አልፎ አልፎም ተለምዷዊና "አፈንጋጭ" (*invert*) ወሲባዊ ተጓዳኞች (*objects*) በመፈራረቅ የሚመጡበት አጋጣሚም ይታያል። እንዲህ ዓይነት አጋጣሚ የሚከሰተው ተለምዷዊ ከሆነው ተጓዳኝ ጋር ጥሩ ያልሆነ ሁኔታ ከተፈጠረ በኋላ ነው (ዝኒ ከማሁ፣1466)

በሰዶም ነፍሳት ዋናው ገጸ ባሕርይ፣ አብይ "ለግብረ ሰዶማዊነቱ" ምክንያት ብሎ የሚጠቅሰው አጋጣሚ በስድስት ዓመቱ፣ የአሥራ አራት ዓመት እድሜ ባለው የወንድሙ ክርስትና አባት ልጅ በኃይል መደፈሩን ነው፡፡ ከዚህ አጋጣሚ በኋላ አጠቃላይ ስብዕናው እንደተቀየረ ይገልፃል (ገጽ 18-19)፡፡ አጋጣሚው ምንም አስተዋፅኦ አልነበረውም ለማለት ቢከብድም ይህ ሁኔታ ብቻ "ግብረ ሰዶማዊነቱን" ፈጥሮታል ማለት ግን አይቻልም፡፡ ከዚህ አጋጣሚ በኋላ ገጸ ባሕርይው ከሁለቱም ጾታዎች ጋር ተመሳሳይ ሊባል የሚችል ወሲባዊ ግንኙነት ነበረው፡፡ በገጽ 20-21 በቀረበው ታሪክ አብይ፣ ከታናሽ ወንድሙና ከሦስት የሠፈሩ ወንድ ሕፃናት ጋር እርስ በርስ ወሲብ ሲፈፅሙ አዋቂ ሰው ይደርስባቸዋል፡፡ በመሆኑም እናቱ ትቆጣዋለች፡፡ ቁጣው የተቀሰቀሰው "የአባቱ ብጤ ቅንዝራም" በመሆኑ ነው እንጂ በፈፀመው ያልተለመደ ወሲባዊ ተግባር አይደለም፡፡ እንዲያውም ይሄው ተግባር እናቱን ሲያስቃት ይታያል፡፡ ዋናው ጉዳዩ ከዚህ በኋላ ከወንድና ከሴት ጋር በየተራ የፈፀማቸው ወሲቦች ስለሆኑ ወደዚያው ልለፍ፡-

> ልጅቱ አስር አመት ቢሆናት ነው፡፡ ቆንጅዬ ነበረች፡፡ ባለማንገቻ ሱሪና ከኔትራ ነበር የለበሰችው፡፡ ገና የሱሪዋን ማንገቻ ዝቅ ስታደረገውና ሱሪዋ ሲወድቅ እንደ እኔ ወጥቶ የሚታይ ነገር እንደሌላት ተረዳሁ፡፡ ከዛን ቀን በፊት ሳላየው ቀርቼ አልነበረም፡፡ በትኩረት የተመለከትኩት ግን ያን ዕለት ነበር፡፡ <u>እንትኗ በጣም የሚያምር ነበር፡፡ ገና</u>

ሳየው እንትኔ በስሜት ተነሳ:: የእኔና የእሷ እንትን እንዴት እንደሚገጥም ማሰብ ጀመርኩ:: (ገጽ 40፡ አጽንኦት የራሴ)

ይህ አጋጣሚ የአብይን በተቃራኒ ጾታ ላይ የተመሠረተ ፍትወት (*heterosexual desire*) የተመለከትንበት ነው:: ሁኔታው የተፈጠረው ከተደፈረ እና "ሕይወቴ ተለወጠ" ካለ በኋላ ይሁን እንጂ ለሴት ልጅ የነበረው አመለካከት ቢያንስ እንዳልተለወጠና ወሲባዊ መነሳሳቱም፣ ፍትወቱም እንደዘለቀ ማየት ይቻላል:: ምክንያቱም ከመደፈሩ ጥቂት አስቀድሞ በደፋሪው፣ በመስፍን እህት በሴትነቷ እንደተማረከ ይጠቁመናል (ገጽ 17):: ብዙም ሳይቆይ ከሴት ልጅ ጋር ወሲባዊ ተግባር የሚፈፅምበት ሁለተኛው አጋጣሚ ይፈጠራል፡፤

ከዚያች እለት ጀምሮ የሴትና የወንድ ብልቶች ሲገጥሙ መስፍን እኔ ላይ አልገባ ብሎት እንዳስቸገረው ያስቸግር እንደሆንና እንዳልሆነ፣ መስፍን የተደሰተውን ያህል እኔንም ያስደስተኛል አያስደስተኝም፣ እሷንም ምን ያደርጋት ወይም ምን ይሰማት እንደሆነ ለማወቅ ጓጓሁ:: አጋጣሚ የምንማርበት ትምህርት ቤት የነበረች አንዷት ጓደኛዬ ቤት ሄደን ሳለ እናቷ ቂጣ ጋግረውና በቅቤ ለቅልቀው ሰጡንና "ወተት ይገፍ ልምጣ" ብለው ራቅ ያለ ቦታ ሄዱ:: አጋጣሚውን ለመጠቀምም ፈልጌ "እናድርግ?" ብዬ ስላት "እሺ" አለችኝ:: እንደ ባለስልጣኑ ልጅ ቆንጆ አልነበረችም:: እድሜዋም ትልቅ ነበር:: የሆነው ሆኖ እሺ እንዳለችኝ እሷም የለበሰችውን ቀሚስ ከፍ አድርጋ፣ እኔም ሱሪዬን ዝቅ አድርጌ ገጠምነው:: ወሲብ መፈፀማችን ትዝ ይለኛል:: ልርካ አልርካ ግን አላስታውስም:: የማስታውሰው እንትኔ እንናትኗ ውስጥ ያለ ብዙ ትግል መግባቱንና እንትኗ መጥፎ ጠረን እንደነበረው ነው:: "ይሸታል!" አልኳት:: ስትናደድ ይታወቀኛል:: እኔም ተናድጄ ነበር:: የተናደድኩት እንደዚያ የሚያስጠላ ነገር ይሆናል ብዬ ስላልጠበቅኩ ነው:: ሁለተኛ ይሄን ነገር አልሞክረውም! አልኩ በልቤ:: ወዲያው አባቴ በሥራ አማካይነት ወደ አጋሮ ተቀየረና ኩሎ ኮንታን ለቀን ስንሄድ እኔ ሴት ነኝ መስፍን እንዳደረገኝ መደረግ ብቻ ነው ያለብኝ ስል አሰብኩ:: (ገጽ 41፤ አጽንኦቱ የእኔ ነው)

ልክ እንደ መጀመሪያው አጋጣሚ ሁሉ በዚህ በሁለተኛው አጋጣሚም የሚታየው በተቃራኒ ጾታ ላይ የተመሠረተ ፍትወት ነው:: ፍትወቱንም ወደ ተግባር ለመለወጥ ችግር ሲገጥመው አልተመለከትንም:: ችግሩ የልጅቷ አካል መጥፎ ጠረን መፍጠሩ፣ በጠረኑ ምክንያት በገጸ ባሕርይው ስሜት ውስጥ ጠየፌታ ማስከተሉ ነው:: ፍሮይድ የመጠየፍ ስሜት (*disgust*) ወሲባዊ ዓላማን ከሚያሰናክሉ ጉዳዮች አንዱ መሆኑን ደጋግሞ ይጠቁማል:: በመሆኑም በዚህ ስሜት አማካይነት ገጸ ባሕርይው ወሲባዊ ዝንባሌውን ለመለወጥ የሚያደርገውን ሙከራ እናስተውላለን:: ሆኖም መሠል ሁኔታ ከወንድ ጋር በፈፀመው ሩካቤ ሥጋ ውስጥም ስለሚከሰት ይህ ሙከራ ተጨናግፏል ማለት ይቻላል::

እንትኑን በምራቁ ቀባና ጭንና ጭኔ መሀል አስገባው:: ያለ ምንም ችግር ገባ፣ ወጣ ስላለለት የልቡን አደረሰ:: አባላዘሩ ጭኖቼ መሀል ሲፈስ ከበደኝ:: ቅጠል በጥሼ ጭኔን ስጠራርግ የአባላዘሩ ሽታ ሊያስመልሰኝ ሲደርስ በአንድ ነገር እርግጠኛ ሆንኩ ዳግመኛ እንዲህ ያለውን አስቀያሚ ነገር ላለማድረግ:: (ገጽ 48፤ አጽንኦቱ የኔ ነው)::

ከላይ ለመግለፅ እንደሞከርኩት እነዚህ ሁለት ተከታታይ ገጠመኞች የተመሳሰሉ እና ሚዛናዊ በሆነ መልኩ በግራና በቀኝ ቆመው ወሲባዊ ዝንባሌው ወደ አንድ እንዳያደላ ማድረግ የሚችሉ ናቸው፡፡ ምናልባትም ስለአጠቃላይ ወሲባዊ ግንኙነት ያለውን አመለካከት ጥያቄ እንዲፈጠርበት ያደርጉ እንደሆን ነው እንጂ ወሲባዊ ዝንባሌውንና አጠቃላይ ሰብእናውን ወደ "ግብረ ሰዶማዊነት" ለመምራት የሚቻላቸው አልነበሩም፡፡ ሆኖም ከሴቷ ጋር ወሲብ ከፈፀመ በኋላ ያለምንም በቂ ምክንያት እራሱን "እኔ ሴት ነኝ" ሲል ይደመድማል፡፡ ከወንዱ ጋር ተመሳሳይ ሁኔታ ተፈጥሮና ተመሳሳይ ተጽእኖ ኖሮት እኔ "ወንድ ነኝ" ሲል አንሰማውም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ብዙ ጥቃቅንና ጥልቅ ታሪኮችን ከሙሉ ስሜቱ ጋ ሲተርክልን ቆይቶ ከሴቷ ጋር ወሲብ ከፈፀመ በኋላ እርካታ ይሰማው አይሰማው እንደማያስታውስ ይነግረናል፡፡ እንዲህ ዓይነቱ "የመርሳት" ሁኔታ ከዚህ ሁነት ውጪ ባሉ ሁነቶች ወይንም በትረካው ሂደት ውስጥ ዳግመኛ አይገጥመንም፡፡ ገጸ ባሕርይው ይህን ሁኔታ እና ስሜት አላስታውስም በማለት ከዋናው ምክንያት ኢ-ንቁ በሆነ መንገድ ለማምለጥ የፈለገ ይመስለኛል፡፡ ይህ ዓይነቱ ሽሽት፣ ወይም እንዲህ ያለው የልቡና መፈርቀቅ (*psychic disintegration*) ከራስ ጋር እርቅ ለማውረድ ካለመድፈር የመነጨ ነው የሚል ግምት አለኝ፡፡ ምክንያቱም "ለግብረ ሰዶማዊነቱ" ምክንያት ብሎ ከጠቀሰው የመደፈር አጋጣሚ በኋላ ከተቃራኒ ጾታ ጋር በፈጸመው ወሲብ ተደሰትኩ ካለ ያቀረበው ምክንያት ጥያቄ ውስጥ መግባቱ አይቀርም፡፡ ከዚህ ጋር አብረን የድርሰቱን ዓላማ፣ ይህንን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የመረጠውን የአቀራረብ ቅጥ እና ቅጡ የተመሠረተበትን ዘውግ ማሰብ እንችላለን፡፡ ተራኪው በገሃድ የሚያውጀው ዓላማ "ጥፋቱን" ማመን፣ "ኃጢአቱን" መናዘዝና፣ "መለወጡን" ማወጅ ነውና፡፡ የሰዶም ነፍሳት ዘውጉ "የንስሐ/የመለወጥ ተረክ" (*confessional/conversion narrative*) የሚባለው ነው ማለት ይቻላል፡፡

በእርግጥ ከላይ በምክንያትነት የተጠቀሱ ሁነቶችና አጋጣሚዎቹ ለገጸ ባሕርይው የዛሬ ነገረ ወሲባዊ ምንትነት የየራሳቸው አስተዋፅኦ ሊኖራቸው ይችላል፡፡ የእኔ ሙግት ግን ዓቢዩና መሠረታዊው ምክንያት የአስተዳደግ ሁኔታው ነው የሚል ነው፡፡ በልጅነት ዘመኑ ከገጠሙት ጥቂት ወሲባዊ ገጠመኞች በላይ የአስተዳደግ ሁኔታው እጅግ ከፍተኛውን ሚና የተጫወተ ይመስለኛል፡፡ ገጸ ባሕርይው አስገድደው ከደፈሩት ወንዶች ይልቅ ለአባቱ ያለውን ጥላቻ ደጋግሞ ይነግረናል፡፡ "ለእናቴም ሆነ ለአባቴ የጥላቻ ስሜት ሊፈጠርብኝ የቻለው ለእኔ ህይወት መበላሸት የእነርሱም አስተዋፅኦ ስላለበት ነው፡፡ ሁለቱም እያቀባበሉ ይተኩሱብኝ የነበሩት ቃላት ናቸው መርዝ ሆነው በቁሜ የገደሉኝ" (ገጽ 33) ሲል የእናትና አባቱ ስድብ እና ማንኳሰስ እንዲሁም የከፋ ድብደባ ሕይወቱን እንዳበላሸው ይገልፃል፡፡ ከጥቃት በኋላ እንኳን በአብዛኛው የተደፈሩ ሰዎች ላይ የሚታየው ብቸኝነትን የመምረጥ የድብርትና

የመሳሰሉት ሁኔታዎች የሚታዩበት ቢመስልም ይህንንም ሁኔታ ከቤተሰቡ ጋር ሊያስተሳስር ሲሞክር ነው የምናየው፡፡

> እያደር ብቸኝነት ነገሰብኝ፡፡
>
> አብዛኛውን ጊዜዬን ጫካ፣ ለጫካ ስሮጥ ወይም በብቸኝነት ስቆዝም ነበር የማሳልፈው፡፡ ለትምህርት ያለኝ ፍላጎት ይብስ መጥፎ እየሆነ ቢሄድም ሁለተኛና ሶስተኛን ክፍል ተንጠልጥዬ ለማለፍ አልተቸገርኩም ነበር፡፡ ችግሩ የትምህርቴ ጉዳይ አልነበረም፡፡ ችግሩ ለምን እንደምኖር አላማወቄ ነበር፡፡ የተጠላሁና የተተፋሁ ሆኜ ለምን እንድኖር ተፈቀደ? ሊገባኝና ሊመለስልኝ ያልቻለ ጥያቄ ነው፡፡ ብቻዬን ሆኜ እወጣና አወርዳለሁ፡፡ መፍትሄ ባላገኝም ብቸኝነቴ ተስማምቶኝ ነበር፡፡ ከእናትና አባቴ ማሸሚጠጥ፣ ጥላቻና እብሪተኝነት የምሸሸው በጫካ ውስጥ ወይም በገደልና ተራራው ስር በመደበቅ ነው (ገጽ 39) ፡፡

እዚህ ጋ የፍካሬ ልቡናን መላ ምት ማንሳት ተገቢ ይመስለኛል፡፡ ለሕጻናት ወሲባዊ ሕይወት ወሳኝ ጉዳይ ከወላጆቹ ጋር የሚኖረው ግንኙነት እንደሆነ ፍሮይድ ያስረዳል፡፡ በዚህ ውስጥ "*Oedipus complex*" የሚባለው ስብዓዊ ባሕርይ ለሕጻናቱ ሁለት ምርጫዎችን ያቀርባል፤ "*active*" እና "*passive*"፡፡ አንድም እራሱን ተባእታዊ በሆነው በአባቱ ቦታ አስቀምጦ ልክ አባቱ እንደሚያደርገው ከእናቱ ጋር ወሲብ መፈፀም፤ አንድም ደግሞ በእናቱ ሥፍራ እራሱን አኑሮ በአባቱ ልክ እንደ እናቱ መወደድ/ወሲብን መፈፀም፡፡ ከእናታቸው ወይም ቅርብ ካለች ሴት አሣዳጊያቸው ጋር ቅርበትና ጥሩ ፍቅር የነበራቸው ወንድ ሕጻናት በእናታቸው ምስል የምትመጣ ወይም የምትተካ ሴት ወሲባዊ ተጓዳኝ ለመፈለግ ይገደዳሉ፡፡ አለበለዚያ ግን ከመጠን ያለፈ ፍቅር እና ቅርበት እንዲሁም እርቀትና ጥላቻ ወደ ተመሳሳይ ጾታ የፍቅር /የወሲብ ተጓዳኝ ምርጫ ሊመራ ይችላል (1905፣ 1541)፡፡

ገጸ ባሕርይው ከእናትና አባቱ የሚገባውን ፍቅር ያገኘ ሰው አይደለም፡፡ ያንን ደግሞ በድርሰቱ የመግቢያ ምዕራፍ ላይ በሰፊው ለማሳየት ሞክሯል፡፡ በስድስት ዓመቱ የሚያስታውሰው ብቸኛ የእናትንት ቅርበት ሲያመው የምታሳየው እንክብካቤ መሠል ድርጊት ብቻ ነበር፡፡ ያንን ደግሞ የሚያስታውሰው እየተደፈረ በነበረበት ቅፅበት ነበር፤ "በድንገት እጆቹ ሰውነቴን ያሻሹት ጀመር፡፡ እቤት ምን አይነት ልጅ ነው? አልኩኝ እናቴ ሲያመኝ ሰውነቴን አሻሽታ እንዲሞቀኝ በማድረግ ሳላስበው እንቅልፍ የምታስወስደኝ ትዝ ብሎኝ፡፡ እያሻሻኝ ከእኔ ሙቀት ይበልጥ እሡ አተኮሰ" (ገጽ 18) ፡፡ ተለምዷዊ በሆነው መንገድ ከላይ እንገደለፅኩት የእናቱን ምስል የምትተካው ሴት መሆን ሲኖርበት በዚህ ከላይ በተገለፀው ሁኔታ ውስጥ በእናቱ ቦታና በእናቱ ትዝታ ወንድ መተካቱ መፃኢ የወሲባዊ ተጓዳኝ ምርጫውን የሚያመላክት ይመስለኛል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ የማይዘነጋው ለአባቱ የነበረው ጥላቻና በአባቱ የሚደርስበት ስድብ፣ ማስፈራሪያ እና ድብደባ ነው፡፡

## 3.3. በጭካኔና በጥላቻ የተቃኙ ወሲባዊ ባሕርያት

በጭካኔ የተቀየጠ፣ በስቃይ የተሸለመ፣ ከሞት ጋር የተጠራራ ፍትወትና ሩካቤ ሥጋ ከወሲባዊ ፍንገጣዎች መኃል አንዱ ነው፡፡ ስቃይን መሻት፣ በራስና በሌሎች ስቃይ መርካት፣ ሌሎች ላይ ጭካኔን መፈጸም፣ በሌሎች አማካይነት ራስ ላይ የሚፈጸም ጭካኔን መናፈቅ፣ ወዘተ. "*sadism*"፣ "*masochism*"፣ "*sadomasochisim*" የሚሉ ቴክኒካዊ መጠሪያዎች ተሰጥቷቸው በነገረ ወሲብ ሥር የሚመረመሩ ስብዓዊ ጉዳዮች ናቸው፡፡ እነዚህ በወሲባዊ ፍንገጣ ሲፈረጁ የሚገጥሙን ጉዳዮች ለጥናት በመረጥናቸው ድርሰቶች ውስጥ በተለያየ መጠንና ቅጥ የተስተማሰሉ ስብዓዊ ጉዳዮች ሲሆኑ በአመዛኙ ከወንድነት ጋር ተዛምደው ይመጣሉ፡፡ ድርሰቶቹን ከእነዚህ ነጥቦች አንጻር ከመተንተኔ በፊት ጽንሰ ሐሳቦቹን በአጫጭሩ ለማስተዋወቅ እሞክራለሁ፡፡

"*sadomasochisim*" በአውሮፓ በ1890ዎቹ በክራፍት ኤቢንግ (Krafft-Ebing) አማካይነት ለመጀመሪያ ጊዜ እንደ አንድ ሥነ ወሲብ ጉዳይ (*sexological issue*) ሆኖ መጠናት ጀመረ፡፡ ቀድሞ በብዙዎች የተለመደው የጽንሰ ሐሳቡ መጠሪያ "*algolagrnia*" ሲሆን ቃሉ የሚገልፀው በስቃይና በጭካኔ የሚገኝ ደስታን ነበር፡፡ kraft *'sadism'* እና *'masochism'* ከሚሉ ሁለት ቃላት ጥምረት የፈጠረው *'sadomasochisim'* ከቀዳሚው "*algolagrnia*" ሰፋ ያለ ትርጓሜን ይይዛል፡፡ በየትኛውም ቅርፅ በሚመጡ ውርደቶች እና ስቃዮች እንዲሁም በነሱ አማካይነት የሚገኙ ደስታና እርካታዎች በዚህ ወሲባዊ ፍንገጣ ውስጥ ይጠቃለላሉ፡፡ የመጀመሪያው "*sadism*" ተንቀሳቃሽ (*active*) ቅርጽ ሲኖረው ሁለተኛው ደግሞ ለዘብተኛ (*passive*) በሆነ ቅርጽ ይገለፃል (ፍሮይድ፣ 1484)፡፡

ክራፍት፣ "*sadism*" ተቃራኒ ጾታን ጠብ እና ጭካኔ በተሞላበት መልኩ በማሰቃየት ተግባራቱን ከወሲባዊ ፍትወት ጋር ቀይጦ የመደሰትን ባሕርይ እንደሚገልጽ ያስረዳል (ጆን ክራዚየር/Juan Crazier 2004፣ 277)፡፡ "*masochism*" ደግሞ ሙሉ በሙሉ በየትኛውም ጊዜና ሁኔታ ተቃራኒ ጾታ ላይ ፍላጐት በማሳደር፣ እነዚህ ሰዎች በሚፈፀምባቸው ውርደትና ስቃይ መደሠት ነው፡፡ ይህም ተግባር ለብቻው የሚመጣ ሳይሆን ከወሲባዊ ፍላጎት እና እርካታ ጋር የሚቀየጥ ነው፡፡ "*masochist*" የሆነ ሰው በነዚህ ሁኔታዎች ስለሚደሠት አጋጣሚዎቹን እራሱ ይፈጥራል፡፡ ሆኖም ይህን ባሕርይውን የሚረዳው እጅግ በጣም አልፎ አልፎ ነው፡፡

ለፍሮይድ እነዚህ ሁለት ጉዳዮች ከክራፍት ሐሳብ ጋር ተቀራራቢ ግን በመጠኑ ለየት ያለ ትርጉም አላቸው፡፡ በብዙ የወንዶች ነገረ ወሲብ ውስጥ የጠበኝነት ፍላጐት አይጠፋም፡፡ "*sadism*" በአንድ በኩል ለተጓዳኝ በሚኖር የጥላቻ ስሜትን፣ በሌላ በኩል ደግሞ ተጓዳኝን በማዋረድና አስጨናቂ ሁኔታ ውስጥ በመክተት ላይ የተመሠረተ እርካታን ያመለክታል፡፡ ከዚህ ሁኔታ ውስጥ እንደ ወሲባዊ ፍንገጣ

(*perversion*) ሊቆጠር የሚገባው ይህ ሁለተኛው የደስታ ስሜት እንደሆነ ፍሮይድ ያስረዳል (1484)። በሌላ በኩል ደግሞ "*masochism*" የሚለው ቃል የሚገልፀው ለወሲባዊ ተጓዳኝም ይሁን ለአጠቃላይ ወሲባዊ ሕይወት የሚኖር ቀዝቃዛ ስሜትንና ወይም ለዘብተኛ አመለካከትን ነው። ይህ ተግባር ጠንከር ባለ ሁኔታው ሲገለጥ ደግሞ በወሲባዊ ተጓዳኝ አማካይነት ራስ ላይ በሚፈጠር አካላዊም ይሁን ሥነ ልቡናዊ ስቃይ መደሠትን ያመለክታል። አብዛኛውን ጊዜ ለዘብተኛ የሆነው "*masochism*" ተንቀሳቃሽ የሆነው "*sadism*" ተቀጥላ ተደርጐ ይታያል። ሆኖም ከሊኒካዊ በሆኑ ጥናቶች አማካይነት እንደሚታየው ለ"*masochism*" ብዙ ዓይነት የመነሻ ምክንያቶች አሉ (ዝኒ ከማሁ)።

እላይ በተነሱት ጉዳዮች ላይ እጅግ ከፍ ያለ ምርምር በማከናወን ስማቸው የሚነሳው ሁለቱ ምሁራን፣ ክራፍትና ፍሮይድ በጉዳዩ ላይ ባላቸው አመለካከት የሚለያዩበት አጋጣሚ ባይጠፋም የሚመሳሰሉባቸው ጉዳዮች በርካታ ናቸው። ቀዳሚው ስምምነት፣ "*sadomasochism*" በአፈንጋጮች ብቻ ሳይሆን በተለመደው ወይም ጤነኛ ተብሎ በሚታሰበው ሰው ውስጥም ይገኛል የሚል ነው። በተለይ ለፍሮይድ የጭካኔ ስሜት ሁለንተናዊ በሆነ ሁኔታ ሁሉም ሰው ከሕጻንነቱ ጀምሮ አብሮት የሚኖር ጉዳይ ነው። በሌላው ሰው ስቃይ የመደሠትን ደመ ነፍሳዊ ስሜት የሚያግዱ መከላከያዎቹ ገና ስላልጐለበቱ፣ ወይም ቀለል ባለ ቋንቋ የርህራሄ ወይም የማዘን ችሎታው ገና ስላልሠለጠ የሰው ልጅ በሕጻንነት ዕድሜው ለጭካኔ ቅርብ ነው። ይህ ሁኔታ ደግሞ በጭካኔና በወሲብ ደመ ነፍስ መካከል ቁርኝት የሚፈጠርበትን ዕድል ያሰፋል (ዝኒ ከማሁ፣ 1517)። የወሲባዊ ፍንገጣ አንድ መገለጫ በሕጻንነት ወቅት የነበሩ ስሜቶችና ተግባራት በአዋቂነት ዘመንም በተለያዩ ገደቦች ሳይታረቁ፣ ተለምዷዊውን ሳይመስሉ መገኘታቸው እንደመሆኑ በ"*sadomasochism*" ውስጥ ተለያይተው ማደግ የነበረባቸው የጭካኔ እና የወሲብ ስሜቶች ተቆራኝተው በአንድነት ይመጣሉ። ይህን ሐሳብ ክራፍት ሲያጠናክረው እንዲህ ይላል፡-

> *... phenomena's such as pain were related to so-called normal sexual desires, there by implying that society's definition of 'normal' sexualities should be altered so as include algaphilias rather than stigmatizing these individuals as "perverse"* (በክራዚየር የተጠቀሰ፣ 2004፣ 276).

በጥቅሡ ክራፍት ለማሳየት እንደፈለገው "*sadomasochism*" የሆነው ባሕርይም ሆነ ባለ ባሕርይዎቹ የሚገፉ ሳይሆኑ ከተለምዷዊው ተርታ ሊሰለፉ የሚገባቸው ናቸው። ምክንያቱም ስቃይም ይሁን ከሱ የሚገኘው ደስታ በተለምዷዊው ሰው ውስጥም እጅግ የሚዘወተር ነውና።

ሁለተኛው ተመሳስሏቸው ንቁ /*active*/ እና ፍዝ /*passive*/ ወሲባዊ ባሕርያት በአንድ ጊዜ በአንድ ሰው ላይ ይገኛሉ ብለው ማመናቸው ነው። "*sadomasochism*" ከሌሎች ፍንገጣዎች ልዩ ሆኖ

የመታየቱ አንዱ ምክንያት ይሄው የጋራ ህልውና ነው። በወሲባዊ ግንኙነት ውስጥ አንድ ሰው በተጓዳኙ ላይ ስቃይን በመፍጠር የሚደሠት ከሆነ እሱም በተጓዳኙ አማካይነት ሊፈፀምበት በሚችለው ስቃይ የመደሠት ዝግጁነት ይኖረዋል። በመሆኑም "*sadist*" የሆነ ሰው ወዲያውም "*masochist*" ነው ማለት ይሆናል። ምንም እንኳን ከሁለቱ አንዱ ገንኖ በይበልጥ የሚታይ ባሕርይም ቢሆን ሌላኛው እድፍጦ አብሮ መኖሩ አይቀርም። ፍሮይድም ይሁን ክራፍት "*sadomasochism*"ን ለማጥናት ወይም ለመመልከት የሚሞክሩት ከወንድ /*active*/ እና ከሴት /*passive*/ አቅጣጫ ወይም ከተቃራኒ ጾታ መፈቃቀድ አንፃር ነው ማለት ይቻላል። ሆኖም በተመሳሳይ ጾታ ግንኙነቶች ውስጥም ይሄው ተግባር ይዘወተራል። በመሆኑም ይህ አመለካከታቸው ሦስተኛው የጋራ ነጥብ ተደርጐ ሊወሰድ የሚችል ይመስለኛል። ከእነዚህ አጥኚዎች በኋላ የተነሱ አንዳንድ ተመራማሪዎች የተለዩ አመለካከቶችን ማራመድ ጀምረዋል። ለምሳሌ ደ ማሲ (de Masi) በጥቅሉ ወሲባዊ ፍንገጣ፣ በጠባቡ ደግሞ "*sadomasochism*" በሁሉም ሰው ውስጥ ከሕጻንነት አንስቶ አብሮ የሚኖር ሁለንተናዊ ጉዳይ ነው የሚለውን የፍሮይድ ሐሳብ ይተቻል። ይልቁንም በነገረ ወሲብ እድገት መዛነፍ ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ ሰብእና እና አእምሯዊ መዋቅር መዛባት የሚፈጠር ችግር ነው የሚል አቋም አለው። በዚህ ጎራ ውስጥ የሚገኙ ሰዎች በአብዛኛው በሕጻንነት ወቅት በአስከፊ ችግር ውስጥ ያለፉ ናቸው። ምንም እንኳን ሁለቱ ጉዳዮች ተነጣጥለው የሚታሰቡም ባይሆን በተለይ "*masochism*" በሴቶች ላይ ሲታይ፣ የሚፈጠረው የስሜት መቀዛቀዝና በወሲብ ደስታን ማጣት በተደጋጋሚ ከደረሰ ጉዳት የሚመነጭ ነው (1999፣ viii)።

ጠቅለል ባለ መልኩ እነዚህ ስሜቶችና ምንትነቶች በአንድ መንገድ ብቻ የሚገለጡ አይደሉም። ለምሳሌ ክራፍት እንደሚለው፣ እነዚህን ሁኔታዎች ለመለየት የዐይንና የጆሮ ምስክርነት ብቻ በቂ አይደለም። በተለየ መንገድ የማስተዋልን፣ የመተርጎምን ሙከራ ይጠይቃል፤ "*... the infliction of pain could be real, symbolic, observed, or experienced in a sadistic act. It did not have to be one person beating another for sexual pleasure*" (በክራዜየር የተጠቀሰ፣ 278)።

ስቃይን መሻትና በራስ ስቃይ መርካት፣ ጥቂት በማይባሉ ድርሰቶች ውስጥ በተለያየ መጠንና የአመሳሰል ቅጥ በመባያነት ይመጣል። መቼታቸውን የሴተኛ አዳሪዎችን ሰፈር ባደረጉ ድርሰቶች ውስጥ ባለመታጠቡ ጠረኑን የለወጠ የሴት ብልት የሚያሳድዱ ጥቂት የማይባሉ ወንዶች ይገጥሙናል። አውጥተው ባይናገሩትም ኃይል የተቀላቀለበት የግዳጅ ወሲብ የሚያስደስታቸው ወንዶችና ሴቶችም አሉ። እነዚህ ዓይነቶቹ ፍላጎቶች የጭካኔውም ይሁን የስቃዩ መጠን ብዙም የማይከብድባቸው ናቸው። ጭካኔና ስቃዩ ሲያይል ወሲባዊ ፍንገጣው አዲስ መልክ ይይዛል። ለምሳሌ፣ *የቺቺኒያ ሚስጥራዊ ሌሊቶች* ገናን ገጸ ባሕርይ፣ አባባ በግዱ እቤቱ የሚወስዳቸው ሴተኛ አዳሪዎች እንዲገርፉት ያዛል። ሴቶቹ መጨከኑን ባይፈቅዱም እንዲፈጽሙ ስለሚገደዱ ያደርጉታል፤ "እየሰሰተች ይዛው የነበረውን

የተገመደ ሽቦ ጀርባቸው ላይ አሳረፈች" (ገጽ 162)፡፡ በ*የሰዶም ነፍሳት* ኃይልና ጭካኔ የተደባለቀበትን የግዳጅ ወሲብ የሚመርጡ፣ ሚናቸው እንስታዊ የሆነ ወንድ "ግብረ ሰዶማውያን" በርካታ ናቸው፡፡ ይህ ድርሰት ከሌሎቹ ድርሰቶች በተለየ በእንዲህ ያለው በገሃድ በሚታይ ወሲባዊ ፍንገጣ የተሞላ ስለሆነ እሱኑ ይዤ ትንተናዬን እቀጥላለሁ፡፡

ብዙውን ጊዜ በጥላቻና በድብደባ ያደጉ ልጆች ሲያድጉ ሳዶማሶቺስት የሚሆኑበት አጋጣሚ ብዙ ነው፡፡ በ*የሰዶም ነፍሳት* ውስጥ "ግብረ ሰዶማዊነት" ከዚህ ወሲባዊ "ፍንገጣ" ጋር ተቃልጦ (*fused* ሆኖ) የተሳለ ይመስለኛል፡፡ ዋናው ገጸ ባሕርይ አብይ በተለይ ማሶቺስት ነው ማለት ይቻላል፡፡ እንዲያውም በገሃድ በሚፈጸም ወሲብም ይሁን በልቡናው ብቻ በሚመላለሱ ወሲባዊ "ፋንታሲዎች" ውስጥ እንደምናስተውለው፣ የሚያሳድደው ከሩካቤ *ሥጋ* የሚገኝ ደስታና እርካታን አይደለም፤ ስቃይንና ህማምን እንጂ፡፡ ከፍ አድርጌ እንዳሳየሁት ከሴት ጋር በፈጸመው ወሲብ ወቅት የነበረውን ስሜት ያለማስታወሱም ምክንያት፣ ይህ ዓይነቱ ወሲባዊ ተራክቦ በመቀመጫ እንደሚፈፀሙ ወሲቦች በስቃይ የተሞላ ስላልነበረ ይመስለኛል፡፡ እንዲያውም አጠቃላይ "የግብረ ሰዶማዊነት" ምስሉ በስቃይ እንደመሞላቱ "ግብረ ሰዶማዊ" የሆነበት ምክንያት ስቃይን አብልጦ በመፈለጉ ነው እስከ ማለት የሚያስደፍር ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ በዝርዝር የተገለጹ ከተለያዩ ወንዶች ጋር የተፈጸሙ "ግብረ ሰዶማዊ" ግንኙነቶቹን ከድርሰቱ መዝዞ ማሳየት ይቻላል፡፡ ከዚያ ይልቅ ግን እነዚህ ሁለት ጉዳዮች--ወሲብ እና በስቃይ መደሰት (*masochism*)--ለቅፅበት ብቻ ተላቀው መልሰው የሚገጥሙበትን ትዕይንት ላሳይ፡-

> … እሱም ፈልጎ ያገኘኛል፣ ያኔም "አለሽ?" ይለኛል እኔም ዝም እላለሁ፡፡ ሁለት ጊዜ በጥፊ ሲያልሰኝ ቀጥ ብዬ ወደሚፈልግበት አመራለሁ፤ እሱም የልቡ እስኪደርስ ኃይል በተቀላቀለበት ሁኔታ ይገናኘኛል፡፡ ከእሱ ጋር በሚኖረኝ ግንኙነት ስለማልረካ ከተለየሁት በኋላ ሀይሉን፣ ወንዳወንድነቱን እያሰብኩ ተደብቄ ራሴን እረካለሁ፡፡ ይሄ የሕይወት ግዴታ ያህል የሚደጋገም ቋሚ ተግባር ሆነ (ገጽ 80፤ አጽንኦቱ የእኔ ነው)

ብዙ ጊዜ በ"*sadomasochism*" ውስጥ ወሲባዊ እርካታ የሚገኝ ሲሆን፣ ይሄ ለገጸ ባሕርይው ብዙም የሠራ አይመስልም፡፡ ገጸ ባሕርይው እርካታ ላይ የሚደርሰው ቀድሞ የደረሰበትን ስቃይ በሐሳቡ እያመላለሰ በሚፈጽመው ሌላ ዘዴ ነው፡፡

> … ሴት ሊያደርገኝ የፈለገ አንድ ሃይል አለ፡፡ የሴት ብልት የለኝም ይሁንና መቀመጫዬን ወደ ሴት ብልትነት ልቀይረው እየሞከርኩ ነው ያለሁት፡፡ የእኔን ብልት ምን ላደርገው እንደምችል አልገባኝም፡፡ ደርሶ ፍቅር ለመስራት ሲሞክር የእኔም ብልት በስሜት ተወጥሮ በተጠንቀቅ ቆሟል… ይሄ ማለት ስሜት አለው ማለት ነው፡፡ ታዲያ ምን ላደርገው ነው?… (ገጽ 48)

በዚህ ጥቅስ ውስጥ የሚነሳው ጥያቄና ግራ መጋባት በላይኛው ጥቅስ የሚመለስ ይመስለኛል፡፡ ከወንዶቹ የሚፈለገው ስቃይንና የስቃዩ ሐሳብ ነው፡፡ ይህ ሲባል ግን በገሃድ በተከናወነው ወሲብና ያንን እያሰበ፣

በፋንታሲ በሚያገኘው ወሲባዊ እርካታ መካከል የተቆረጠ ልዩነት አለ ማለት አይደለም፡፡ ምክንያቱም የጊዜ መዘግየት እንጂ ወሲባዊ እርካታው የሚገኘው ከስቃዩ ስለሆነ፡፡

አስቀድሜ ለመጠቆም እንደሞከርኩት በዚህ ድርሰት ውስጥ ሳዶማሳቺዝም " እና "ግብረ ሰዶማዊነት" የአንድ ጉዳይ ሁለት መጠሪያዎች የሆኑ ያህል እጅግ ተቆራኝተዋል፡፡ በርከት ያሉ የዘርፉ ምሁራን--በዋናነት ፍሮይድንና ክራፍትን መጥቀስ ይቻላል--እንደሚያስረዱት ሳዶማሳቺዝም የብዙ ወሲባዊ ፍንገጣዎች (*pervertions*) መገለጫ ነው፡፡ በዚህ ድርሰት ውስጥ ደግሞ ከግብረ ሰዶማዊነት ጋር ተቀይጦ፤ አንዱ በአንዱ ስምና ጥላ ውስጥ ተከልሎ ይኖራል፡፡ ቀደም ባለው ክፍል እንደጠቆምኩት፣ ለአብይ "ግብረ ሰዶማዊ" መሆን ምክንያቱ የተበላሸ ቤተሰባዊ ግንኙነት ነው፡፡ ይህም በስድብ፣ በማንኳሰስ እና በድብደባ በሌላ አነጋገር "ሳዲስታዊ በሆነ መልኩ ይገለፃል፡፡ ይህንን እውነታ በድርሰቱ ከገጽ 36-39 በተነደፈው ትዕይንት አማካይነት በወጉ ማጤን እንችላለን፡፡ አስር ዓመት የማይሞላው ሕጻን መሳሳትና ማስተካከል በሚችልበት እድሜው በስድብ፣ በዘለፋና በዱላ ተስፋ እንዲቆርጥ ይገደዳል፡፡ ከለላ ይሆኑት ዘንድ የሚያልማቸው እናትና አባቱ ጥፋቱ ምን እንደሆነ ባልገባው ታዳጊ ላይ በቅብብል ይሳለቃሉ፡፡

> "ግዴለህም… በትርፍ ጊዜያቸው የመዋለ ሕጻናት ልጆች ሳይሆን አይቀሩም የሚፅፉለት" [ትላለች እናቴ]፡፡
> "ደደብ ስለሆነ እንጂ ምን እነሱ ይጽፉለታል፡፡"
> "ደደብ" የሚለውን ቃል ቋቅ እስኪለኝ ከመስማቴ የተነሳ ትርጉም የሌለው ባዶ… ኳኳታ የበዛበት ተራ ቃል ሆኖብኝ ነበር፡፡ አባቴ እየተሳደበ እናቴ ወደ ሌላ ገጽ ታልፋለች፡፡ … ለምን ጽሑፌ እንዳማይነበብልኝ በማማረርና የፈጠረኝን አምላክ ለምን ፈጠርከኝ በማለት አለቅሳለሁ፡፡ እያለቀስኩ በድካም እንቀላፋለሁ፡፡ (ገጽ 39)

“እዚህ ላይ የእናትና አባቱን ሳዲስታዊነት በቀላሉ ማየት የሚቻል ይመስለኛል፡፡ አባቱ ከእናቱም በባሰ በጭካኔው ውስጥ፣ በልጁ ስቃይ ውስጥ  እርካታን ሲያሳድድ ነው የሚገጥመን፡፡ ይህንን በወጉ የሚያሳይልኝን ሌላ አስረጂ ላምጣ፤

> … አንድም ቀን አስሩን ሲጥል ገጥሞኝ አያውቅም፤ እንደውም የአባቴ ጆብደኝነት ከሴት ጋር በተያያዘና በእኔ ላይ ተፈፃሚ ሲሆን ነው የማየው፡፡ ልጅ እያለሁ እግሬን ይዞ ዘቅዝቆ በማንጠልጠል ይደሰት ነበር፡፡ እኔ ነብሴ ተጨንቃ ልትወጣ ደርሳ እጮህ ነበር፡፡
> "ወይኔ… እማዬ ድረሽ!" እላለሁ ሲያንጠለጥለኝ፡፡
> "ወንድ አሳደቢ እስቲ ምን ትሆን?" ይለኛል እየሳቀ፡፡
> "ወይኔ ጉዴ ኡኡኡኡ!" ከት ብሎ ይስቃል፡፡ ከፍርሃት ወጥቼ እንዴት ጆብደኛ መሆን እንዳለብኝ አይነግረኝም፡፡ ወይም አይመክረኝም፡፡ ጆብድ አልባ በመሆኔ ግን ይዝናናል፡፡ "ወኔ ቢስ የሴት ልጅ!" ይለኛል፡፡ በተለይም ብስክሌት ሲጋልብ በአንድ እጅ መሪውን፣ በሌላኛው እጅ የእኔን የልጅ እግሮች ይዞ ዘቅዝቆ ነብስ ግቢ፣ ነብሴ

> ውጪ በማስባል የሚደሰተው ደስታ ወደር አልነበረውም፡፡ የእኔን ፍርሃት የጀብደኝነቱ ማድመቂያ ያደርገዋል፡፡ (ገጽ 32)፡፡

በሰው ስቃይ የሚደሰተው "ጀብደኛ" አባቱ በሕጻን ልጁ ጭንቀት ከመሳለቁ በላይ ስድቡ "ወንድ አሰዳቢ"፣ "ወኔ ቢስ የሴት ልጅ!" የሚል ነው፡፡ "ወንድ" አባቱ የእሱና የ"ሴቷ" እናቱ ቦታ አንድ እንደሆነ ያሳየዋል፡፡ ከሌሎች "ወንድ" ወንድሞቹ ነጥሎ "ሴት" እንደሆንና ፍርሃቱ የወንድ ባሕርይ እንዳልሆነ ይነግረዋል፡፡ (ስለአባቱ ወሲባዊ ምንትነትስ የሚነግረን እውነታ አይኖረውም ይሆን? ከሌሎቹ ልጆቹ ለይቶ ይህንን "ሴታ ሴት ልጅ" እየተከታተለ በማሰቃየት የሚያገኘው እርካታስ በተመሳሳይ ጾታ መሳሳብ ከሚፈጠር ፍትወት ጋር ዝምድና ቢኖረውስ? ብሎ መገመት የሚቻል ይመስለኛል፡፡) ይሄን ደግሞ እንዳለ ተቀብሎ "የናቱ ልጅ" እንደሆነ ሲናገር፣ እንደ ሴት ለመሆን ሲሞከር እናየዋለን፡፡ "እኔ ሴት ነኝ" የሚለው ደጋግሞ ነው፡፡ ሌላው ቀርቶ በ"ግብረ ሰዶማዊ" ሕይወቱ "የሴት" ባሕርይ አላቸው ተብሎ ከሚታመኑት "ወጪ" "ግብረ ሰዶማውያንን" ጐራ ነው፡፡ ይህን ሐሳብ ከግብረ ሰዶማዊነቱ ውጪ በመጀመሪያ ሲቀበለው ያለውን ገጽታ የሚያሳይ ምሳሌ ልጥቀስ፡-

> ታላቅ ወንድሜ የሴት የሆነ ሙያ አይሆንለትም፡፡ ሽሎ (ሙልሙል ዳቦ) ጋግር የተባለ እንደሆነ ምጣዱን ይፈቀፍቀውና የብይ መጫወቻ ጉድጓድ ያደርገዋል፡፡ እኔ የጋገርኩ እንደሆነ ምጣዷን አቅበጠብጣታለሁ፡፡ እናቴ ቆንጆ ወጥ ሲቀርብላት ገና "ዛሬ ልጄ ነው የሠራው ማለት ነው" ትልና ትታረቀኛለኛች፡፡ እኔ በእናቴ ነው የወጣሁት ከአባቴ ከወረስኩት አመንዝራነት ውጪ (ገጽ 70)፡፡

ልክ ሴትነቱን እንደተቀበለ ሁሉ ሌሎቹንም ከወላጆቹ ይሰነዘሩ የነበሩ ስድብና ውርደቶችን አሜን፣ ልክ ብሎ ይቀበላል ("አመንዝራነትን ከአባቴ ወረስኩ" ሲልም በእናቱ የተነገረውን ተቀብሎ መሆኑን ከገፅ 21 ላይ ማየት ይቻላል)፡፡ በስድብና በዱላ የራስ መተማመኑን የተነጠቀው አብይ በህይወቱ የሚደርሱ ክፉ ገጠመኞችና ጉዳዮች ለርሱ የተገቡ እንደሆኑ ያምናል፡፡ ከሕጻንነት ጊዜው አንስቶ እስከ ታሪኩ ማብቂያ ባሉ የሕይወት ዘመናቱ ሁሉ ለሕይወት ያልተገባ መሆኑን በማመን ሞቱን ሲናፍቅ ይስተዋላል (የከሸፈ የራስ ማጥፋት ሙከራው ለዚህ ጥሩ አስረጂ ሊሆነን ይችላል)፡፡ ይህም ሲባል ራሱንም ይሁን ሕይወትን የሚመለከትበት መነፅር ከቤተሰቦቹ የተዋሰው ነው፡፡ በመሆኑም ሲጀምር የሚነሳው በትንንሽ ጉዳዮች ነው፡፡ በእናትና በአባቱ ይነገሩ የነበሩትን ስድቦች እና ማንኳሸሻዎች ልክ መሆናቸውን በማመን እና በማረጋገጥ፡፡ ገጽ 16 ላይ እንዲህ ይላል፡- "እርግጥ እናቴ እንደምትለው የእንግዴ ልጅ ነኝ አባቴም እንደሚለው 'ደደብ' ነኝ"፡፡ በማስከተል በገጽ 56 ላይ የቤተሰቦቹ ሐሳብ ልክ መሆኑን ሌሎች ሰዎችም እንደሚስማሙበት በማሳየት ራሱን ለማሳመን ሲታገል እናየዋለን፡፡

በሕጻናት ምንትነት ምሥረታና ቀረጻ ላይ ከፍ ያለ ሚና ያላቸው መምህራን እንደ ሰው ቁጭ ብሎ ከመማር ይልቅ እንደ እንስሳ ዛፍ ላይ እንዲውል ሲጋብዙት፣ የራሱ የሆነውን ነገር ወስደው ሲገፉት

ልክ ነው ይላል፡፡ በማይደመጥ ድምጽ በልቡናው እንዲ ሲቃወም፣ ተገቢ አይደለም ብሎ ሲያምፅ አንሰማውም፡፡ ምክንያቱም ለመምህራኑ ድርጊት ተገቢነት የቤተሰቦቹ የስድብና የዱላ ማረጋገጫ በኅሊናው ስለሚቀርብ፡፡ ከፍ እያለ ሲሄድ የሚደርሱበትን ጉዳቶች መጋፈጥ ባይችልም ለመሸሽ ይሞክራል፡፡ በአካል ጭምር ከአገር አገር ይሰደዳል፡፡ ከጅማ አዲስ አበባ፣ ከአዲስ አበባ ሸንኮራ ዮሀንስ፣ ከሸንኮራ ሐረር፣ ከሐረር አዲስ አበባ፣ በስተመጨረሻም ከአዲስ አበባ ሣዑዲ አረቢያ ድረስ፡፡ ሆኖም ትንሽነቱን እየነገሩ፣ ለጥሩ ነገር ያልታጨ ዕድለ ቢስነቱን እያሳዩ ያሣደጉት የቤተሰቦቹ ጥላ እየተከተለ ገጽና ሥፍራ እየቀየረ ይጥለዋል፡፡ ሐሳቡ ሁሌም መንታ ነው፡፡ ውሳኔዎቹ በግጭት የተሞሉና እርጋታ የተለያቸው ናቸው፡፡ እነዚህን ግጭቶች ለማርገብ፣ ፍርቅነቱን አሸንፎ አንድ ለመሆን በሞከረበት ሜዳ ሁሉ ተማርኳል (ገጽ 104)፡፡

ፊት ለፊት አብሮ በመኖር ሊቀይረው ያልቻለውን ምንትነት ሸሽት ሲጀምር የሚነሳው ጫካ ከመዋል ነው (ገጽ 39)፡፡ ያም አላዋጣ ሲለው ቤተሰቦቹ የሚኖሩበትን ጅማን ለቆ አዲስ አበባ ይገባል፡፡ የሚሸሸው "ግብረ ሰዶማዊነት" አዲስ አበባ ውስጥም ከችግር ጋር ተስፋፍቶ ይጠብቀዋል፡፡ በየአብያተ ክርስትያናት ውስጥ ለመሸሸግ፣ በሃይማኖት ጥላ ውስጥ ለማምለጥ ይሞክራል (ገጽ 93-98)፡፡ የሸሸው ነገር እየተከታተለ፣ ቀድሞ እየጠበቀ መሸሸጊያውን ያፈርሰዋል፡፡ ጸድቻለሁ፣ ታድሻለሁ ሲል ቆይቶ "እርኩስ" የሚለው ሐሳብና ተግባር ከደጃፍ ድረስ መጠቶ ያሸንፈዋል (ገጽ 96 እና 97)፡፡

መንገዶች "በትክክለኛው" ይሁን "በተሳሳተ" ገጻቸው እሱን ካሰበበት ለማድረስ አቅም የላቸውም፡፡ "ትክክለኛ" ብሎ ያመነበትን ጐዳና ተከትሎ ለመጓዝ አቅም አንሶት "በተሳሳተው" መንገድ እየተጓዘ ለመረጋጋት ሲሞክር እንኳን ደርሶ መንገዱ መናወጥ ይጀምራል፡፡ የያዘው መንገድ "ስህተት" ነውና በሌላኛው "በትክክለኛ" መንገድ ለመጓዝ ደግሞ የግዳጁ ወኔ ደርቦ ከወደቀበት ለመነሳት ይንደፋደፋል፡፡ ለምሳሌ ከገጽ 104-105 ባለው ታሪክ እንደተገለፀው ከአዲስ አበባ ሸንኮራ ዮሀንስ ሄዶ ከድህነትና "ከግብረ ሰዶማዊነት" ለማምለጥ ሞክሮ አልሳካ ሲለው የሚሸሸው ወደ ሐረር ነው፡፡ እዛም ገብቶ ስለመለወጡ ስለመታደሱ ደግሞ ይናገራል፡፡ ሆኖም እዚህም ሽንፈት አይቀርለትም፡፡ እናም "በስህተት" መንገድ ገብቶ "ግብረ ሰዶማዊ" ወሲብ እንደወትሮ ፈፅሞ ዞር ከማለት ይልቅ "ግብረ ሰዶማዊ" ትዳር መሥርቶ በመኖር በዚህ መንገድ የራሱን መድረሻ ለመሥራት ይሞክራል፡፡ ሆኖም ብዙም ሳይቆይ ማረፊያዬ ያለው "ስህተትም" ቢሆን የተቀበለው ትዳር ወረትና አለመግባባት ወርሶት ሲፈርስ እንዲህ ይላል፡-

> አዲስ አበባ እንደገባሁ አንገት ማስገቢያ የሆነች አንዲት ዛኒጋባ የመሰለች ቤት ተከራየሁ፡፡ ወደ ቤተሰቦቼ የምመለስበት ምንም ምክንያት አልነበረኝም፡፡ ኑሮዬን ራሴ ልኖረው ወስኜ ነው ከጅማ የመጣሁት፡፡

በአረማመዴና በአናናሬ ሁሉ በሕይወቴ ላይ ቀልድ የያዝኩ መሆኑ ታወቀኝል። ለዛም ነው አዲስ አበባ እንደተመለስኩ ቤት የተከራየሁት። ሥራ ፈልጌ ቀን ቀን እየሰራሁ ማታ መማር እንዳለብኝ አስቢአለሁ። እናቴ፣ አባቴና የሚያውቁኝ ሁሉ ከ"ደደብ" ተማሪነት ወደ ጎበዝ ተማሪነት መቀየሬን ማወቅ አለባቸው። የእኔን ዕጣ ፈንታ የምሰራው እኔ ራሴ ነኝ። ስለዚህም የከበረ ሀብቴ ትጋቴ ይሆን ዘንድ ሥራ ፍለጋ ተነሳሳሁ (ገጽ 105-106)።

ይህንንም ሥራ ካገኘ በኋላ ያለበትን ሁኔታ ትእምርታዊ በሆነ መልኩ እንዲህ ሲል ይገልፀዋል፡- "የመጀመሪያ ብርጭቆ ሣጥብም ሕይወቴ ልክ እንደ ቤልጅግ ብርጭቆ ታጥቦና ተወልውሎ የፀዳ ያህል አዲስነት ተሰማኝ" (ገጽ 107)። ይህ አቋም እና ውሳኔ ለተወሰነ አጭር ጊዜ እውነት የሆነ ይመስላል። ድንገት ግን የዕጣ ፈንታው ዘዋሪ ደርሶ አቅጣጫውን ይለውጠዋል። ለሁሉም የሕይወቱ መንገድ መስመር ያስይዝልኛል ካለው ሥራው "አጥቦ ከደረደራቸው ሲኒዎች አንዱ ወድቆ ስለተሰበረ" ይባረራል። ከዛ ወጥቶ ግን ሊሸሽግ የሚሞክረው አሸንፍኩት ሲል ወደ ቆየው "ግብረ ሰዶማዊ" ሕይወት በመመለስ ነው።

"ሂሳቤን ስጠኝና ሥራህን እለቅልሃለሁ አልኩት። በንዴት ቱግ ብሎ ወጣ።" የተሰበረና ያልተሰበረውን፣ ያልተፈጠረና የተፈጠረውን ቆርጦ ደሞዜን ሰጠኝና አይንህን ማየት አልፈልግም ብሎኝ ወጣ። እኔም ልብሶቼን ሰብስቤ ልወጣ ስል ምንም መሄጃ እንደሌለኝ አስቤ አለቀስኩ። የእኔ የምለው ሰው ቢኖር፣ አይዞህ ብሎ ቢያቅፈኝ፣ ቢያባብለኝና ትከሻውን አንተርሶኝ ቢተኛ ፈለግኩ።

"ኤፍሬም.."

"አቤት"

"አንድ ጥያቄ ብጠይቅህ ቅር ይልሃል?"

"አይለኝም" ዝምታ ዋጠኝ። "ጠይቀኝ"

"ጌዮች- አዲስ አበባ ውስጥ ግብረሰዶማውያን የት ነው ያሉት?"

"አንተ?" ጮኸ። ሳፈጥበት ደንግጦ አቀረቀረና መልስ ሰጠኝ። "ፒያሳ… ሲኒማ ኢትዮጵያ ፊትለፊት ያለው ሽንት ቤት ሲመላለሱ የሚውሉት እነሱ ናቸው ሲባል ስምቻለሁ።"

ገጸ ባሕርይው በአዋቂነት ዘመኑም በሕጻንነቱ ያጣውን ፍቅርና ተፈላጊነት፣ ከአባቱ የተነፈገውን የወንድነት ሥፍራና አለሁ ባይነት፣ ከእናቱ የናፈቀውን እንክብካቤና ቅርበት ሲፈልግ የሚኖር "ሕጻን ልጅ" ነው። ያንን ደግሞ በብልጭታም ቢሆን ሲገለጽ ያየነው "ግብረ ሰዶማዊነቱን" አስተዋወቀኝ ከሚለው ከደፋሪው ከመስፍን ጋር በነበረው ወሲባዊ ተግባር ነበር። እዚህ ጋርም ከላይ በተጠቀሰው ጥቅስ እንደሚታየው እንክብካቤና ቅርበትን ፍለጋ የሚሄደው "ግብረ ሰዶማዊነት" እና "ግብረ ሰዶማውያን" ጋር ነው። ይህ ሕይወቱ ከቤተሰቦቹ ጋር የነበረውን ሕይወት በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ

አስታዋሽ ነው፡፡ በዛ ሕይወት የሚያገኛቸው ወሲባዊ ተጓደኞች ደግሞ የቤተሰቦቹ በተለይም ደግሞ ጨካኝ (ሳዲስት) የሆነው አባቱ ምትክ ናቸው ማለት ይቻላል፡፡

በእነዚህ ከላይ በቀረቡት ታሪኮች ውስጥ የሚታዩት የአቋም ልዩነቶች ፍፁም የተቃረኑ ናቸው፡፡ ሁሉንም ዓይነት ውሳኔ ሲወስን ግን አቋም እንዳለው ሰው በምርጫ ሳይሆን ከውጪና ከውስጥ በሚነሱ አስገዳጅ ምክንያቶችና አጋጣሚዎች ነው፡፡ በየደረሰበት በሚነሱ የሕይወት ማእበሎች፣ የስሜት ግንፍልታዎች ነው ሕይወቱ የሚዘወረው፡፡ በብዙዎቹ አላይ ባሰፈርኳቸው ጥቅሶች ውስጥ እንደሚታየው ዞሮ ዞሮ የሚወድቀው ወደ ቤተሰቦቹ፣ ወደ ልጅነቱ አዙሪት ነው፡፡ "የአሸናፊነት" ጉዳናውን ቢይዝ የቤተሰቦቹን ተቀባይነት እንዲያገኝ፤ "ተሸንፎ ቢወድቅ" የነሱን ቃል እና ተግባር እውነትነት ሊያረጋግጥ፡፡ ይሄ ሁሉ ግራ መጋባትና መውደቅ መነሳት በአንድ ሐሳብ ይጠቀለላል፤ በሞት፡፡ ሕይወቱ እንዲያበቃ የሚማጸንባቸውን፣ ሞትን የሚመኝባቸውን ቦታዎች መዘርዘር ብዙም አስፈላጊ አይመስለኝም፡፡ ምክንያቱም በየውድቀቱ መኃል ትዝ የሚለው ማምለጫ፣ የቅጣቱ ሁሉ ማሣረጊያ ሞት ነው፡፡ እራሱን በተለያየ መልኩ ወደ ስቃይና መከራ ሲመራ፣ "ለሕይወት ያልተገባ ኃጢአተኛ" መሆኑን ሲያውጅ ኖሮ ታሪኩን ሩጫና ሽሽቱን የሚዘጋው "ሞቻለሁ" ብሎ ሲያረጋግጥ ወይም ሲያምን ነው፡፡

> "አብይ... ኤች አይ ቪ. በደምህ ውስጥ ተገኘ ማለት አሁን ትሞታለህ ማለት አይደለም..." ራሴ ሲዞርብኝ፣ ሁሉም ነገር ድብልቅልቅ ሲልብኝ... የሆነ የማጥወልወል ስሜት ሲሰማኝ ይታወቀኛል፡፡
>
> ... አንተ የስራህን ነው የተቀበልከው፤ ደሞዝህ ነው የተከፈለህ አለኝ የሆነ ድምፅ የኃጢአት ደሞዙ ሞት ነው! የሚል የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ትዝ አለኝ፡፡ ያ-የሚ-ያጥወለውለኝ ስሜት፣ ያ- የሚያዞረኝ ነገር ሁሉ ጠፋ፡፡ ደሞዜን እንደተቀበልኩ ሳውቅ እከስና እወቅሰው ዘንድ ማንም እንደሌለ ገባኝ፡፡ እኔ ነኝ የራሴን እጣ ፈንታ የቀረፅኩት፡፡
>
> ከተቀመጥኩበት ስነሳ ያዞረኛል ብዬ ብጠብቅም ምንም አልሆንኩ፡፡ እኔ የኤች አይ ቪ /ኤድስ ቫይረስ በደሜ ውስጥ መኖሩን ያወቅኩና ምንም ያልመሰለኝ ሰው ነኝ፡፡ ኧረ ኃጢአቴን አወራርጄም መሄድ ከቻልኩ እድል ነው!

ታሪኩን ከዚህ በኋላ በተስፋ፣ በለውጥ ሊሞላው፣ አርአያ ሊሆን ይሞክራል፡፡ ግን ይሄም የተጨናገፈ ሙከራ ነው፡፡ ምክንያቱም ኤች አይ ቪ. እንዳለበት አውቆ እራሱን ተንከባክቦ ለመኖር የሚረዳውን የመጨረሻ ትግል ታግሎ እንኳን ወድቋል፡፡ ሳዑዲ ለመድረስ ብዙ ወድቋል ተነስቷል በስተመጨረሻ ግን ከደረሰ በኋላ ብዙም ሳይቆይ ተይዞ ወደ አገሩ ይመለሳል፡፡ "ተስፋ አለኝ አሁን መኖር እጀምራለሁ" ሲል ቆይቶ (ምንም እንኳን ከላይ በጥቅሱ እንዳስቀመጥኩት ተስፋውን የገነባው "በቅጣቱ" ወይም "በሞቱ" ላይ ቢሆንም) ከዛ በኋላም ደግሞ ሞቱን ሲመኝ እናገኘዋለን፡፡ ፖሊሶች ሲያሳድዱት እንደሚገድሉት ሲያስፈራሩት እሩጫውን ይቀጥላል፡፡ በዚህ እሩጫው ውስጥ ዓላማውን ለማሳካት

ያለውን ቁርጠኝነት ለማሳየት ያደረገውን ትግል ከሆነ የምናየው ተሳስተናል፤ ምክንያቱም አንዱ የመሞት--የሳዶማሶቺዝም--ፍላጐቱ መገለጫ ስለሆነ፡፡

"ቁም!"

ከሚያባርሩኝ ፖሊሶች አንዱ ሽጉጡን ሊተኩስብኝ ካቀባበለ በኋላ ነበር ከመተኮሱ በፊት የመጨረሻ እድል የሰጠኝ፡፡ እኔ ግን ቢተኩስ እና መትቶ ቢጥለኝ ግድ አልነበረኝም፡፡ ሞት ለእኔ እረፍት ብቻ አይደለም፡፡ ዘለአለማዊ ደስታ ነው፡፡ መገላገል ነው፡፡ የሳውዲው ፖሊስ እንደ እናትና አባቴ በቁም የሚገል ቃል አይደለም የሚተኩስብኝ፡፡

ጥይት ነው!

ፍንዳታው ሲሰማ ጥይቱ ማጅራቴን ቦድሶት ይወጣና ተፍገምግሜ ከመሬት እደፋለሁ፡፡ ጌታ ሆይ ነብሴን ተቀበላት ብዬ አጉተመትምና እውነተኛውን ሞት እሞታለሁ፡፡ እዛ ግብረ ሰዶማዊነት እንደማይኖር፣ ፍርሃት እንደማይኖር... ሰላምና እረፍት ብቻ እንደሚኖሩ ይሰማኛል፡፡

ከዚህ በኋላ ታሪኩን የደመደመበት "የአዲስ መንገድ" ገለፃ፣ አዲስ ነገር ይዞ የሚመጣ ነው ለማለት ይከብዳል፡፡ ምክንያቱም መሠረቱን የጣለው እነዚህ ሁለት ጥቅሶች ላይ የሚታየው መንፈስ ላይ ስለሆነ፡፡

እነዚህ በተለያዩ መንገዶች የተገለጡትን የሳዶማሶቺዝም ሐሳቦች ከወሲብ ጋር ያላቸውን ጥምረታዊ አቀራረብ ደግሞ ልቃኝ፡፡ ሳዶማሶቺዝም፣ እስካሁን እንዳነሳሁት በመጠኑም ቢሆን ሸሸግ ብሎ ብቻ አይደለም በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኘው፡፡ በወሲባዊ ሕይወት ለመለየት በማያስቸግር መልኩ ደምቆ እና ጎልቶ ይታያል፡፡ አስቀድሜ እንዳነሳሁት "ግብረ ሰዶማዊነት" እና ሳዶማሶቺዝም ያላቸው ቁርኝት በወጉ ተነድፏል፡፡ ያውም ግልፅ በሆነ መልኩ የትኛው ክፍል ማሶቺዝም ነው? የትኛውስ ሳዲዝም ነው? ብለን በቀላሉ ለማየት እስኪያስችለን ድረስ፡፡ በዚህ ድርሰት ውስጥ ልዩ ትኩረት የተሰጣቸው "ወጪ ግብረ ሰዶማውያን" ከአብይ በቀር፣ በአመዛኙ ማሶቺስት ናቸው፡፡ የአብይንም ሳዲስታዊ ባሕርይ የምናየው ከወሲባዊ ሕይወቱ ውጪ ነው፡፡ አንዳንድ እነስ ያሉ ይህን ባሕርይውን የሚያሳዩ አጋጣሚዎች በታሪኩ ቢኖሩም ግልጥ አድርገው የሚያሳዩት በገጽ 40፣ ከ43 እስከ 44 ያሉት ሁነቶች ናቸው፡፡

አብይ በቀላሉ እንደመዝናኛ የወሰደው የሰዎችን ድንጋጤ እና ጉዳትን ሲሆን የሚሠራው ነገር ለሌሎች ያለውን ጉዳት አስታውሶ፣ ተው የሚል ንቃተ ኅሊና አይደመጥም፡፡ ይህ ጉዳይ ስለ ሳዲዝም ባነሳሁበት ክፍል እንዳስረዳሁት፣ በየትኛውም ሕጻን ላይ የሚስተዋል ይሁን እንጂ በዚህ ገጸ ባሕርይ ስሜት ላይ ግን የሚጨመሩ ምክንያቶች ያሉ ይመስለኛል፡፡ በወላጆቹ የሚደርስበት ጉዳት ቢሰማውም ፊት ለፊት የሚጋፈጥበትና ምላሽ የሚሰጥበት አቅም አልነበረውም፡፡ ይሄው አጋጣሚ ከመፈጠሩ በፊት በሚደርስበት ጉዳት የተነሳ የብቸኝነት እና የተፈላጊነት እጦት ይሰማው እንደነበር ይናገራል፡፡ ከዛም

ደግሞ ብቸኛው መዝናኛው የነበረው፣ ጫካ ውስጥ ለብቻው መቀመጥ እንደነበር ይገልፃል፡፡ ጫካው ግን መዝናኛው ብቻ ሳይሆን መሸሸጊያው፣ የታፈነ ብሶቱን ማውጫው ጭምር ነበር፡፡

> እንደፈለኩ ለመጮህ፣ ብሶት ሲያናውዘኝ ለማልቀስ፣ እልህ ሊውጠኝ ሲደርስ የፈለግኩትን ለመሳደብ ተራራና ሸለቆ፣ ጫካና ጉድባው ተመቸኝ፡፡ በነፃነት ስሜቴን ለአየሩ በመግለጼ ምንኛ እድለኛ ነበርኩ?! (ገጽ 40)

ይህ ሥፍራ ብሶቱን ብቻ ሳይሆን ሳዲስታዊ ፍላጎቱን የሚወጣበትም ነው፡፡ "የእኔ ፍላጎት ግማሽ ሳይሆን ሙሉ ያውም የማያጠራጥር ሰይጣን መምሰል ነው" የሚለን አብይ በልጅነቱ ከሰል አድቅቆ ከሬንጅ ጋር በመደባለቅ ፊቱን እየተቀባ፣ ቅንድቡን ለብቻው ለይቶ ሊጥ እየነከረ የፍየል ቀንድ በጆሮ ግንዱ በኩል አስሮ ሰው ሲያስደነግጥ፣ ሲያሳቅቅና ሲያሰቃያ በዚህም ደስታ ሲያገኝ እርካታን ሲጎናጸፍ ነው የኖረው (ገጽ 43-44)፡፡ ተመልካች የተነፈገው ሕጻን ደስታና እርካታውን የሚያገኝባቸው መንገዶች እንደዚህ እንግዳ ናቸው፡፡ ብዙዎቹ የደስታና የእርካታ ምንጮቹ ራሱ ላይ በሚፈጸሙ ጭካኔዎች የሚቀሰቀሱ ሲሆኑ አልፎ አልፎ ግን ከፍ ብዬ እንደጠቆምኩት ያሉ ሌሎች ላይ በሚፈጸሙ ጉዳቶች አማካይነት ደስታን የማትረፍ ሙከራ ይገጥመናል፡፡ እነዚህ ሙከራዎች አንዳንዴ ረቀቅ ያሉ፣ የጎዱትን፣ በተለይም ቤተሰቡን ዋጋ የሚያስከፍሉ ዓይነት ናቸው፡፡ ተከታዩን ምሳሌ እንመልከት፤

> እርግጠኛ ነኝ እናቴ ወኔ አግኝቼ እንደማልጠፋ እያሰበች እንደነበር ገና እግሯ የበሩን ደፍ እንደረገጠ ተወርውሬ ወደ መኝታ ቤት ገባሁና ቁምሳጠኑን ሰበርኩት፡፡ የትምክህተኛው አባቴ ሱፎች በመልክ፣ በመልክ ተሰቅለዋል፡፡ ይሁዳ ኢየሱስን ለፈሪሳውያን አሳልፎ እንደሰጠው እኔም አባቴን አሳልፌ የሰጠሁት ያህል ተስምቶኝ ተደሰትኩ፡፡ ልብሶቹን ይገዥ፣ ቶሎ አውርጄ በፌስታል በማድረግ ሰልባጅ ተራ ይገዡው ሄድኩ (ገጽ 82)

አብይ ደጋግሜ እንዳሳየሁት የሚደርስበትን እንግልትና ስቃይ 'ይገባኛል' ብሎ በጸጋ የሚቀበል ሰው ነው፡፡ ይሁንና የዝምታው፣ የተቀባይነቱ የማይታይ መነሻው አንዳንዴ ይሄው ሳዲስታዊ ፍላጎቱ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ከላይ ባሰፈርኳቸው ጥቅሶች ቀለል ብለው የተገለፁት የዚህ ስሜት ፍንጥቅታዎች እዚህ ጥቅስ ውስጥ በገሃድ የተገለጡ ይመስለኛል፡፡ በጥቅሱ የምናየው አባቱን በክርስቶስ መስሎ እራሱን ደግሞ በይሁዳ ሥፍራ አስቀምጦ አባቱን ለሞት አሳልፎ በመስጠት የሚሰማውን ደስታ ነው፡፡ የአባቱን ሙሉ ልብስ የክብሩ መገለጫ አድርገን ልንወስደው እንችላለን ልብሶቹን በመሸጥ አባቱ በእርሱ ላይ የነበረውን ኃያልነት ለቅፅበትም ቢሆን ያሸንፋል፡፡

ከእነዚህ በትእምርት ከተገለጡ ሳዲስታዊ ፍላጎቶች ውጪ በአብይ ወሲባዊ ሕይወት ውስጥ የሚታየው ማሶቺስት የሆነው ባሕርይ ብቻ ነው ነው፡፡ በገጽ 97 እና 116 ከሚፈጽማቸው "ሰላማዊ" ወሲቦች ውጪ ሁሉም ማለት ይቻላል ማሶቺዝም በገናኑ የሚታይባቸው ናቸው፡፡ እነዚህን ሁሉ ጠቅልሎ ያሳያል ብዬ ያሰብኩትን ትዕይንት ልጥቀስ፡-

"ከእኔ ጋር ጫካ ትሄዳለህ አትሄድም?" በቁጣ፡፡

"አልሄድም!" በሰለለ የፍራቻ ድምፅ፡፡

ትኩር ብሎ ተመለከተኝና ፈገግ አለ፡፡ ወዲያው ያለምንም ቃል ሁለት ጊዜ ኃይለኛ ጥፊ ሲያቀምሰኝ ከየት መጣ ያላልኩት የወሲብ ስሜት እንደፈላ ወተት ግንፍል ብሎ አቅበጠበጠኝ፡፡ ሴም ለቀቀኝና ባሳየኝ መንገድ እንድሄድ ቆሞ ጠበቀኝ፡፡ ሮጬ ለማምለጥ አልሞከርኩም፡፡ ለማጉረምረምም አልሞከርኩም፡፡ ዝም ብዬ በሚያሳየኝ መንገድ አመራሁ፡፡

ጫካ ውስጥ ቦታ ከመረጠ በኋላ ከኪሱ ሲባጎ ገመድ አውጥቶ እጄን በጀርባዬ በማዞር አንድ እግሬን ከብርቱካን ዛፍ ላይ ጥፍንግ አድርጎ አሰረና አመቻቸኝ፡፡ ከላይ የለበስኩትን ከኔትራ አስወልቆ በአፌ ጠቀጠቀው፡፡ ይሄን ሁሉ ሲያደርግ በኃይል ስለነበረ የሚያደርገው ደስ ብሎኝ ያለተቃውሞ እንደሚፈልገው ሆንኩለት፡፡ ለምንና እንዴት በኃይል ለሚደረግ ወሲብ ከፍተኛ ፍላጎት እንዳደረብኝ ላውቀው አልቻልኩም፡፡ ሴም ልብሱን አወላለቀና ከኪሱ በላስቲክ የያዘውን ቫዝሊን አወጣ፡፡ የእኔንም ሱሪ አውልቆ እርቃኔን አስቀረኝ፡፡

በቫዝሊኑ ብልቱን ቀባው፡፡

ብልቱን እየቀባው የሰውነቱ ትኩሳት መቀመጫዬን እየገረፈኝ ነበር፡፡ ቀስ ብሎ ይገናኛል ብዬ እየጠበኩት ሳለሁ በድንገት በመቀመጫዬ ሲያደርገው አይኖቼ ግልብጥ፣ ግልብጥ ብለው ሲወጡ ታወቀኝ፡፡ እንዳልጮህ ታፍኛለሁ፡፡ ሰውነቴ እንደሆነ ነገር ተቃጠለ፡፡ መቀመጫዬ ውስጥ ጩቤ ገብቶ ተቀርቅሮ የቀረ መሰለኝ፡፡ ሴም ቅንጥና ቅንጤን በእጁ ይዞ ብልቱን ወጣ፣ ገባ ሲያደርገው አጓራሁ፡፡ ተንሰፈሰፍኩ፣ ተቃጠልኩ፡፡ እሳት ሰውነቴ ላይ ነደደ፡፡ ጩቤው መቀመጫዬን ገዘገዘው፡፡ በታፈነው አፌ "ሞትኩ… ቀደድከኝ" ብለውም አልተሰማውም፡፡ ሶሶተኛ እግር የሆነው እንትኑ ወጣ ገባ፣ ወጣ ገባ ብሎ ከተለማመደ በኋላ በኃይል ሲገፋው መቀመጫዬ ብጥስጥስ ሲል ታወቀኝ፡፡ ሙቅ ፈሳሽ ከመቀመጫዬ እየረሰረሰ ወደ ጭኔ ወረደ፡፡

በአስራ ስድስተኛ አመቴ ላይ ድንግልናዬ ተወሰደ፡፡

ሴም በስቃይ መቃጠሌ፣ የእንባ በጆሮ ግንዴ መውረድና በደም መታጠቤ ግድ ሳይሰጠው ወሰበኝ፡፡ በኃይል… በጉልበት፣ በትግል እየተገናኘና በቦክስ፣ በጥፊ፣ በእግር ጉሽም ደብድቦኝ እንደ አውሬ አጓርቶ፣ አጓርቶ ጨረሰ፡፡ ቁናቁና ተንፍሶ ብልቱን ከመቀመጫዬ ሲያወጣው ሰውነቴ ላይ የተሰነቀረ ጩቤ የተነቀለ ያህል ነፍሴም ምንጥቅ ብላ ወጣች፡፡…

… ወደ ሁለት ወር ያህል በቁስሉ ስሰቃይ ከርሜ አገገምኩ፡፡ ህመሜን ሳስታምም በነበረበት ጊዜ ሁሉ አስብ የነበረው ስለ ሴም ነበር፡፡ እኔ በሴም ተገድጄ አልተደፈርኩም- ሴም ኃይል ቅልቅል ወሲብ ነበር እንጂ የፈፀመብኝ፡፡ ከማሳመሙ በስተቀር የሆነው ሁሉ ተመችቶኝ ነበር፡፡ (2005፣ 17-79)

በድርሰቱ ውስጥ ይህንን የሚመስሉ ትዕይንቶች በርካታ ናቸው፡፡ ገጸ ባሕርይው፣ በሁሉም ውስጥ ማለት ይቻላል፣ ኃይል የተቀላቀለበት ወሲብ እንደሚያስደስተው ደጋግሞ ይናገራል፡፡ "በሰላም"፣ ኃይል ያልተቀላቀለባቸውን ሁለት ወሲቦችን ሲፈፅም ተድበስብሶ ያልፋል እንጂ እንደሌሎቹ ትዕይንቶች ዝርዝር ያለ የስሜትም ይባል የክንዋኔ መረጃ አይሰጠንም፡፡

በዚህ ድርሰት ውስጥ በማሶቺዝም የሚገለፀው አብይ ብቻ አለመሆኑን ቀደም አድርጌ ጠቁሜያለሁ፡፡ "ወጪ ግብረ ሰዶማውያኑ" ሙሉ በሙሉ የዚህ ስብዓዊ ጉዳይ መከሰቻዎች ናቸው፡፡ ይህን ሁኔታ ባለ ታሪኮቹ ራሳቸው ልብ ያሉት ይመስላል፡፡ ከገጽ 179-181 ባለው የታሪኩ ክፍል ውስጥ

ሁሉም "ወጪ ግብረ ሰዶማውያን" ተሰብስበው በኃይልና በጋራ (የሻማ በሚሉት) ስለመደፈር አስደሳችነት ሲያወሩ፣ የወል ፋንታሲያቸው ሲጋሩ ይገጥመናል።

## 3.4. መልክአ ተባእት በሴተኛ አዳሪዎች መንደር

*የመኃልየ መኃልየ ዘ ቺቺኒዮ፣ የሰአት አላፊ፣ የቺቺኒያ ሚስጥራዊ ለሊቶች* እና *የሰአት አላፊ 2* ዓቢይ ትኩረት ሴተኛ አዳሪነትና ሴተኛ አዳሪዎች ናቸው። ይህ ማለት ግን ድርሰቶቹ በእነዚህ ጉዳዮች ብቻ ታጥረው የተቀመጡ ናቸው ማለት አይደለም። የድርሰቶቹ ዋነኛ ትኩረቶች ሴቶቹ (ሴተኛ አዳሪዎቹ) ይሁኑ እንጂ ከእነርሱ ባሻገር ወደ ተለያዩ ማኅበራዊ ጉዳዮችና ክፍሎች የሚዘምቱ ናቸው። ሁሉም ድርሰቶች ማለት ይቻላል የሴተኛ አዳሪነትን ሕይወት "እስከፊ ገጽታ" ለማሳየት የሚሞክሩ ይሁን እንጂ ከዚያ ይልቅ "ትክክለኛ" የሚባለውን ዓለም (ዓለሙ በወንዶች የሚወከል መሆኑን ማስታወስ ይገባል) "እንከን" በማጉላት የተሳካላቸው ይመስለኛል።

በድርሰቶቹ ውስጥ ሴቶቹ በአመዛኙ በጊዜና በሥፍራ ተገድበው እንዲንቀሳቀሱ የተገደዱ ናቸው። የሥራቸው ባሕርይ ከሞላ ጎደል ሥራው ከመሸ በኋላ እንዲሰራ የሚፈቅድ ነው። ይህን የሚያከናውኑት ደግሞ በተወሰኑ በታወቁ መንደሮች፣ ቡና ቤቶች አልያም ጎዳናዎች ነው። "ለትክክለኛው" ዓለም ሲመሽ ለአፈንጋጮቹ ይነጋል። ካንቀላፋው ዓለም ጋር ሕግና ሥርዓቶቹም ያንቀላፉ ይመስል እነዚህን ሕጎች እና ሥርዓቶች በማፍረስ የሚተዳደሩት "ሌሎቹ" ዓለማት መንቀሳቀስ ይጀምራሉ። በሁለቱ ዓለማት የሚኖሩ የሴቶቹ ደንበኞች አንዷን ፀሐይ ሸኝተው ሌላኛዋን ይቀበላሉ። በንድፈ ሐሳብ ዳራ ውስጥ እንደጠቆምኩት ነገረ ወሲብ የየዘመኑና የየባህሉ ውጤት ነው። ባህል እና ዘመን ደግሞ መለያቸው፣ መገለጫቸው ብዙ ነው። ከነዚህ መካከል በማሳያነት የሚቀመጡት "አርአያዎች"፣ በተለይም ዊልተን "*significant others*" የምትላቸው "የሩቅ አርአያዎች" ናቸው። እነዚህ ወገኖች ብዙውን ጊዜ የፍንገጣው አካሎች ይሆናሉ። ከ"ትክክለኛው" ዓለም የሚመጡ ወንድ ደንበኞች በአመዛኙ በማኅበራቸው ውስጥ ከፍ ያለ ሥፍራና ሚና የሚሰጣቸው ግለሰቦች--የመንግሥት ባለሥልጣናት፣ የሃይማኖት አባቶች፣ ምሁራን፣ ትልቅ ስም ያላቸው ነጋዴዎች፣ የመሳሰሉ "ዕንቁ ዜጎች" ናቸው (እርግጥ ነው መንደሮቹ ስም በሌላቸው ተርታ ወንዶችም ሲጨናነቁ ይታያል)። ትልቁ ነጥብ በዚህኛው ዓለም ውስጥ ከሴትነት ይልቅ የወንድነት መልክ የተበላሸ መሆኑ ነው። በዚህ ዓለም ሴተኛ አዳሪዎቹ ተለይተው ከሚታወቁበት ወሲባዊ ፍንገጣ በላይ የ"ትክክለኛው" ዓለም ሠሪና ፈጣሪ የሆኑ "ዕንቁ ዜጎች" ፍንገጣ በዓይነትም በመጠንም ይገዝፋል፣ ይሰፋል። ወንዶቹ በድርሰቶቹ ውስጥ በአመዛኙ ብስለት የራቃቸው፣ ንቃት የጎደላቸው፣ ጨካኝ፣ ሞኛ ሞኝና ለሴቶቹ መጫወቻነት የቀረቡ

ሆነው ነው የሚገጥሙን፡፡ ይህንን ሐሳብ የሚያጠናክሩ፤ በሴተኛ አዳሪዎቹ መንደር የተከሰቱ የተባእነት መልኮችን የሚነድፉ ጥቂት ምሳሌዎችን ከየድርሰቶቹ በየተራ እንመልከት፡-

**ምሳሌ አንድ፤** *መኃልየ መኃልየ ዘ ቼቼኒያ*

"አንድ ዘናጭ ሼባ ነበሩ፤ ቅዳሜ ቅዳሜ ቼቼኒያ ሊሳለሙ ይመጣሉ፤ እላይ ግሮሰሪ አካባቢ ሲጠጡ ያመሹና ወደ አምስት ሰአት ላይ ከመንገድ ላይ አንድ ሴት ይዘው መኪናቸውን እየነዱ ጨለም ወዳለበት ሰፈር ይገባሉ ብዙ አይቆዩም ጣጣቸውን ጨርሰው ይወጡና ልጅቷን ያገኙበት ቦታ መልሰዋት ይሄዳሉ ብዙ ሴቶች "እጉል ነገር ላርግ ይላሉ እንጂ ደህና ይከፍላሉ" ይሏቸዋል አንድ ቀን እኔ ሾርት ሄጄ እስከመለሰ ስስቴ ተመላልሰው ትንሿን ልጅ ካልሆነ ማንንም አልፈልግም ብለው ሄዱ ብለው ሴቶቹ ሲነግሩኝ አላመንኩም ምክንያቱም ብዙ ጊዜ መኪናቸውን አጠገቤ አቁመው በደንብ ካዩኝ በኋላ ሰፍ ስል አልፈው ሌላ ሴት እየወሰዱ ያናድዱኝ ነበርና አይፈልጉኝም ብዬ አስብ ነበር፡፡ ያን ቀን ግን ስድስት ሰአት ላይ ተመልሰው መጡና ይዘውኝ ወደ ሌላ ቦታ መሄድ ጀመርን ለምን ከዚያ ሰፈር እንዳራቁኝ ያወቅኩት ፍል ውሃ በር ላይ መኪናቸውን ሲያቆሙ ነው፡፡ አስቀድመው ወረፋ ስላስያዙ በቀጥታ ወደ አንደኛው ማእረግ መታጠቢያ ገባን ቶሎ ታጠቢና ነይ ብለው ገንዳ ውስጥ ገቡ ታጥቤ ስመለስ ራቁታቸውን ባዶ ገንዳ ውስጥ ተንጋለው ነበር ፎጣውን ጥዬ ራቁቴን ደረታቸው ላይ እንድቀመጥ አዘዙኝ፤ ደረታቸው ላይ ስቀመጥ እግሮቼን ወደ ትከሻቸው በመስቀል በሁለት እጃቸው ከቂጤ ብድግ ሲያደርጉኝ ፍላጎታቸው ስለገባኝ እንዳልወድቅ ጭንቅላታቸውን ያዝኩት ትንፋሻቸው ይፋጇል ምላሳቸው ይሞቃል፡፡ የውጭውን አንድ ባንድ ካዳረሱ በኋላ ምላሳቸውን ብልቴ ውስጥ እያስገቡ እያወጡ ሲያደርጉኝ ሰውነቴን መቆጣጠር አቃተኝ እውነቱን ለመናገር እንደዛ ተደርጌ አላውቅም ነበር የያዝኩትን ለቅቄ ወደ ኋላ ተንሳፈፍኩ ባንድ እጃቸው ወገቤን ወጥረው ይዘው በሌላ እጃቸው ጡቶቼን እያፈራረቁ እያሹ ደግሞ ታች ወርደው በምላሳቸው ላይ ጣቶቻቸውን እያፈራረቁ በቃ ምን ውስጥ እንዳለሁ እንኪጠፋኝ ድረስ አይቼው የማላውቀው ስሜት ውስጥ ከተቱኝ ስጨርስ የሳቸውን አስጀመሩኝ፡፡ በጣም ደስ ብሎኝ ነበር፤ እኔም በአፌ በደንብ አስደሰትኳቸው"

"ስንወጣ የሰው ዓይን የሚያሟሟኝ መስሎኝ ፈርቼ ነበር እሳቸው ግን ደንታ አልሰጣቸውም፤ አቅፈውኝ ነበር"

[---]

… "መጠጥ ሲጀምሩ እኔ አልጠጣም ብዬ እምቢ አልኩ እሺ ታጠቢ ብለው ሻወር አስገቡኝ ታጥቤ ስመለስ ኮካ በብርጭቆ ቀርቦልኛል ጠምቶኝ ስለነበር ባንድ ትንፋሽ ጠጥቼ ቁጭ አልኩ ሳሎን ነበርን ብዙ ሳይቆይ የመደንዘዝ ስሜት ተሰማኝ ልብሴን በየተራ ሲያወልቁልኝ እስቅ ነበር፡፡ በየተራ እየተቀባበሉ ያቅፉኛል፡፡ በየተራ ሱሪያቸውን እያወለቁ በተየራ እያወጣሁ ማንም ሳያዘኝ በእጄ በአፌ ማስደሰት ስጀምር ያጨበጭቡልኝ ነበር ከዛ በኋላ ኮንዶም ወጣ፡፡ ይዘውኝ የሄዱት ሰውዬ ምንጣፍ ላይ አስተኝተው በሃይል ካደረጉኝ በኋላ ያኛውም በተራው እግሮቼን ወደ ትከሻዬ አጣብቆ በተለይ የሁለተኛው ሰውዬ በጣም ያሰቃዩኝ ነበር፡፡ ግን አልጮህም የሆነ ነገር ይዞኛል ጥርሴን ነክሼ እያቃሰትኩ እያማጥኩ እስቅ ነበር ሲጨርስ ደግሞ የመጀመሪያው ሰውዬ በጀርባቸው ተኝተው ተሸከመው ከላይ አደረጉኝና ወገቤን አጥብቀው ይዘው ወደ ላይ በፍጥነት ያጣድፉኝ ጀመር፤ ያን ጊዜ ነው አእምሮዬ ወደ ትክክለኛ መንገድ መመለስ የጀመረው ግን ምንም እድል አልነበረኝም፤ ድንገት ያኛው ሰውዬ ኮንዶም ሲያጠልቅ ከኋላዬ ተሰማኝ ዘወር ስል የሆነ ቅባት ይዞ ቂጤን ወደታችና ወደጎን ጫን አድርጎ ያዘና ቀዳዳው ላይ ቅባቱን ለጠፈበኝ መጮህ ፈልጌ አፌን ከፈትኩ ግን ድምፄ ተዘግቷል ለማምለጥ ሞከርኩ፤ ሰውዬው ከታች ዳደኛው ከላይ ወጥረውኛል፤ በዚያው ቅጽበት ነው ብልቱን ቂጤ ውስጥ ማስገባት የጀመረው በዚያ ሰአት የተሰማኝን ህመም መግለጽ አልችልም ከታችም ከላይም ተተከለውብኛል ትንፋሽ አጥሮኛል ሰውነቴ መዛል ጀምሯል፤ አቃስታለሁ መፈጠሬን እስከጠላ ድረስ በሀይል በጭካኔ ተጫወቱብኝ"

"አጣጥበው ሲያስተኙኝ በከፊል ራሴን ስቼ ነበር በማግስቱ ጠዋት ሰውነቴ ሁሉ ቁስል የሆን ያህል መንቀሳቀስ አቃተኝ የወሰዱኝ ሰውዬ ጋቢ ለብሰው ዳዊት ይደግሙ ነበር ሲጨርሱ ከማታው ጋር በአጠቃላይ ዘጠኝ መቶ ብር አስይዘው በኮንትራት ታክሲ ሸኙኝ ለሶስት ቀን ያህል ሽንት ቤት መቀመጥ አቅቶኝ ነበር፡፡…ለሶስት ቀናት

አልወጣም ቢያንስ ለአራት ወር ያህል ሰርቼዋለሁ! በመጨረሻ ግን ጠቆብኝ አንዱን ግን በቅርብ በቲቪ አይቼዋለሁ ባለስልጣን ነው መሰለኝ… (ገጽ 81-85)

በዚህ እረኛም ወሲባዊ ትዕይንት ውስጥ የተለያዩ ወሲባዊ ፍንገጣዎችን በአንድነት ማየት ይቻላል፡፡ ሲጀመር ጀምሮ እስኪያልቅ ወሲቡ የሚፈፀመው ተለምዷዊ በሆነው "ትክክለኛ" የወሲብ ሥርዓት አይደለም፡፡ ቀድሞ የሚመጣው ፍንገጣ ለወሲብ ያልተፈቀደ የአፍንና የመቀመጫን አካላትን ለወሲብ መጠቀም ነው፡፡ በእነዚህ ሁለት አካላት የሚፈፀም ወሲብ በድርሰቶቹ ውስጥ እጅግ የተለመደ ሲሆን በተለይ በአፍ የሚፈፀም ወሲብ የጋራ ሊባል የሚችል ነው፡፡ ስለ ወሲብ ፍንገጣ (*perverstion*) ባነሳሁበት ክፍል የፍሮይድን ሐሳብ ይዤ ለመግለፅ እንደሞከርኩት የአፍና የመቀመጫ አካባቢዎች በሕጻንነት የወሲብ ዕድገት ውስጥ በቀዳሚነት እንደ ወሲባዊ አካል *"erotogenic zone"* በመሆን ያገለግሉ የነበሩ ናቸው፡፡ ይሁንና እነዚህ ቀደምት ወሲባዊ አካላት በ"ትክክለኛው" የዕድገት ሂደት ውስጥ ሥራቸውን ጨርሰው ለመራቢያ አካላት እያስረከቡ መሄድ ነበረባቸው፡፡ በመሆኑም በአዋቂነት ዘመን እነዚህ አካላት እንደ ወሲባዊ እርካታ ምንጭ ማገልገላቸው የሚያሳየው በወሲባዊ አፈንጋጮች ላይ የሚስተዋለውን የዕድገት መዛባት ነው፡፡ ሌላው ወሲባዊ ፍንገጣ ሳዝም ነው፡፡ ሦስቱ ወንዶች የተለያየ አካልን በአንድ ጊዜ ለወሲባዊ እርካታ ሲጠቀሙ ይታያሉ፡፡ ይህ ድርጊት የሚፈፀመው በኃይል ነው፡፡ ሴቷ እራሷን እስክትስት ድረስ በኃይል የሚፈፅሙት ወሲብ ገደብ የለሽ ጭካኔያቸውን ከማረጋገጡ በተጨማሪ ተራክበው በጋራ መከናወኑ የወንዶቹን "ግበረ ሰዶማዊ" ዝንባሌ ያሳያል፡፡ ሳዲዝም ደግሞ የወሲብና የጥላቻ ስሜት ውህደት መሆኑን አስቀድሜ ገልጫለሁ፡፡

ከወሲባዊ ፍንገጣዎቹ ጋ ተጣምሮ የምናየው ፍንገጣ ከሃይማኖትና ከመንፈሳዊ ሥርዓቶች ጋር የተፈጠረ ተቃርኖ ነው፡፡ ሃማኖትና መንፈሳዊ ሥርዓቶች አባዊው ዓለም "ትክለኛው"ን ዓለም አሰልጥኖ፣ ገርቶና ጠብቆ ለማኖር ከሚገለገልባቸው ተቋማት ዓቢዩ ነው፡፡ ሰውዬው ሌሊቱን በባህል የተነወሩ፣ በሃይማኖት የተወገዙ ተግባራትን ሲፈጽሙ አድረው ሲነጋ ያለ አንዳች ችግር ወይም ጸጸት "ቅዱስ" መጽሐፍ ታቅፈው ፀሎት ሲያደርሱ ይታያል፡፡ ይህ ዓይነቱ ተቃርኖ የሚፈጥረው ስላቅ የሃይማኖትን (ወይም በጥቅሉ የማኅበራዊ ሥርዓቶችን) ኃይልና ጉልበት እንድንጠይቅ የሚያስገድደን ይመስለኛል፡፡ ምክንያቱም ባለማወቅ ሳይሆን በድፍረት ተጥሰው፣ የጣሰው ወገን ላይ አንዳችም የፍርሃት አልያም የፀፀት ስሜት መፍጠር ካልቻሉ ሚናቸውን ተነጥቀዋል፤ የተፈጠሩበትን፣ የተመሠረቱበትን መንፈሳዊና ማኅበራዊ አቅም አጥተዋል፡፡

***ምሳሌ ሁለት፤ ሰዓት እላፊ-2***

"በዚያን ወቅት ዕድሜሽ ስንት ነበር?"

"ሰባት ዓመቴ ነበር!"

"ሁኔታውን ታስታውሽዋለሽ?"

"ሁሉንም አስታውሰዋለሁ!"

"በወቅቱ የነበረውን ሁኔታና እንዴት አድርገው እንደደፈሩሽ ንገሪኝ!"

"አጎቴ፣ የእንጀራ አባቴና ጓደኞቻቸው እቤት ጫት ይቅሙ ነበር። ሺሻ ቤትም ነበረን። የዛኔ ትንሽ ልጅ እንደመሆኔ ሺሻ ቤት ውስጥ እላላክ ነበር። የጫትና የሺሻ ዕቃ አቀርብላቸዋለሁ። እማዬ ጅቡቲ ስትሄድ ጫት መቃማቸውን ትተው ደፈሩኝ"

"ቀን ላይ ነው?"

"ሰባት ሰዓት ይሆናል፣ ምሳ በልተን እነሱ ሺሻ ወደ ሚጨስበት ክፍል ገቡ እኔ ደግሞ ወደ መኝታ ቤት ስገባ ደፈሩኝ"

"መጀመሪያ ላይ ማን ደፈረሽ?"

"የእማዬ ወንድም አጎቴ..."

"ደበደበሽ?"

"ተሸክሞ አልጋው ላይ ወረወረኝ። አጎቴ ብዬ ስጮህ አፌን በእጁ አፈነኝና ደፈረኝ፣ ቀጥሎ የእማዬ ባል ደፈረኝ። ጮህኩ አለቀስኩ የሚደርስልኝ አጣሁ። አፌን በጨርቅ አፈኑኝና የአጎቴ ጓደኛ ኮንዶም ተጠቅ እንደነበር አስታውሳለሁ። ጮህኩ ከአፌ ላይ አውጥቼ አለቀስኩ። አያቴ ጮኸቱን ሰምታ ስትመጣ አልጋው ላይ ተኝቼ ሳቃስት አገኘችኝ፣ አያቴ ቤቱን በጩኸት አቀለጠችው። ወንድሜ ቁማር እየተጫወተ ነበር። እየሮጠ ሲመጣ መደፈሬን አወቀና ፖሊሶች ቤታችንን ከበቡት። አራቱንም ጣቢያ ይዘዋቸው ሄዱ። እኔም ሐኪም ቤት ተወሰድኩ" (ገጽ 175-176)

## *ምሳሌ ሦስት፤ ሰዓት እላፊ-2*

"...ከጅቡቲ ጠፍቼ የመጣሁት ወንድሜ ስለደፈረኝ ነው" አለች፤ አለቀሰች። ትዝታዎቿ ተመላለሱባት። ቆንጆዋ ታሪኩ አዲስ ስለሆነባት ግርም ድንቅ ብሏታል። ለሷ ይህ አዲስ ታሪክ ነው።

"ወንድምሽ፣ የእናት የአባትሽ ልጅ?"

"አዎ!"

"እንዴት ደፈረሽ?"

"የጁምዓ ዕለት ነበር" ሙቀት ሲሆን ድሬደዋ እንሄዳለን። እኔ አእምሮዬን እያመመኝ ይጥለኝ ነበር። እወድቃለሁ። እናቴ ጥላኝ ድሬደዋ ሄደች። ታላቅ ወንድሜን አደራ ካመማት ጠብቃት ብላው ሄደች። ጁምዓ ስለሆነ አባቴ ከግቢ ወጥቶ ሄደ። ወንድሜ የግቢውን በር ከዘጋው በኋላ የውስጡን ቆልፎ ደፈረኝ። በጣም አሰቃይቶኝ ነበር። በኋላ ግን ደበደበኝና ከጣለኝ በኋላ የሚፈልገውን አደረገ።"

"በጣም ደበደበሽ?"

"አዎ! ጎድቶኛል የአውራ ጣቴንም ሰብሮታል። አየኸው አውራ ጣቴን" ብላ ጣትዋን አሳየችኝ። አውራ ጣትዋ ግን ወደላይ ቀጥ ብላ እንደ ቆመች ቀርታለች።

"አሁን ህመም ይሰማሻል?"

"ህመም አይሰማኝም ቀጥ ብሎ ቀርቷል እንጂ አያምኝም። መዘርጋትና ማጠፍ አልችልም"

"በወቅቱ ዕድሜሽ ስንት ነበር?"

"ስምንት!"

"ለእናትሽ ተናገርሽ...?"

"አልተናገርኩም!"

"ለምን?"

"እኔና አንቺ የፈፀምነውን ለሰው እናገራለሁ ብትይ አርድሻለሁ ብሎኝ ስለነበር ዝም አልኩ። ለእናቴ ብናገር ያርደኛ ነበር። ሽንቴን ስሸና እያመመኝ ጣቴንም እያመመኝ። ዝም አልኩ። የሶማሌ ሴቶች ብልታቸው ስለሚሰፋ ሲደፈርኝ በጣም አሞኝ ነበር። ተሰቃይቼ ነበር" (ገፅ 187-188)

## *ምሳሌ አራት፤ ሰዓት እላፊ-2*

"ለቤተሰቤ ብቸኛ ልጅ ነኝ። አባቴ ሞቷል። እግዚአብሔርን የማመሰግነው አባቴን ስለገደለው ነው። አባዬ፦ የሚስቱንና የልጁን ድንግልና ወስዷል። ምን ማለት እንደሆነ ይገባሃል አባዬ ደፍሮኛል። አባት አስራ ሁለት ዓመቴ ነበር። በአስራ ሁለት ዓመቴ ወፍራም ነበርኩ። ጡቴም ትልቅ ነው። ቂጥም ነበረኝ። ነጋ ጠባ አባዬ ልጄ አደገችልኝ ይላት ነበር እማዬን። ከት/ቤት ስመጣ እማዬ በሌለችበት ደፈረኝ።

"... አባዬ ሲደፍረኝ እያወራ የነበረው ነገር አይረሳኝም። አሳድጌ.... አሳድጌ... ለባዳ አልሰጥም የራሴን ልጅ ገላ ለጎረምሳ አላስረክብም ይል ነበር። ከመጀመሪያው ቀን በኋላ ሶስት ቀን ተገናኘኝ አባዬ"

"ወላጅ አባትሽ ናቸው?"

"አዎ! የወለደኝ አባቴ። የ12 ዓመት ልጅ ሆኜ በስስት ያየኝ ነበር። የሰፈር ልጆችም ይለከፉኝ ነበር። ሱቅ ስላከ ቂጤን ይመቱኝ ነበር"

"እናትሽ ቤት ውስጥ ነበሩ?"

"አባዬ ሲደፍረኝ እማዬ አልነበረችም። ከዚያም በኋላ እማዬ በማትኖርበት ጊዜ ይገናኘኝ ነበር። ይህን ለናትሽ ብትናገሪ ያንቺና የኔ ነገር በቃ እያለ ያስፈራራኝ ስለነበር ሲገናኘኝ ፀጥ ብዬ አድርጊ ያለኝን እፈጽም ነበር። ሶስት ጊዜ ተግኛኝቶናል አባዬ" (ገጽ 218-219)

ግብረ አምኖን--በቤተዘመድ መካከል የሚፈፀም ወሲብ-- (*inscest*) በእነዚህ ድርሰቶች ውስጥ የሚገጥመን ሌላው ወሲባዊ ፍንገጣ ነው። የዝምድናው ቅርበትና ርቀት በባህሉ የሚወሰን ነው። በአንድ ባህል እና በአንድ ወቅት የተፈቀደ በዝምድና ላይ የተመሠረ ግንኙን በሌላ ጊዜና ባህል ደግሞ ከፍተኛ ቅጣትን የሚያስከትል ነውር ተደርጐ ይታያል። በፍሮይድ እምነት ግብረ አምኖን ሁለንተናዊ ከሆኑ የሰው ልጅ ወሲባዊ ፍላጐቶችና ፍትወቶች መኃል አንዱ ነው። ያንን ደግሞ በ"*Oedipus complex*" ለማረጋገጥ ሞክሯል። ይህ ፍላጐት ከሰው ማኅበራዊና ሥነ ልቡናዊ እድገትና ከ"*super ego*" መኀልበት

ጋር እየከሰመ፣ በተለያዩ የልቡና ማስተባበያ ስልቶች (*defense mechanisms*) እየተዳፈኑ እንደሚሄድ ያስረዳል። ይሁንና እነዚህ ገደቦች ፍፁማዊነት የላቸውም። የአእምሮ ህመም አልያም ሌላ አመቺ አጋጣሚ ሲፈጠር የሚገለጡ ናቸው። በ"ጤናማ" ሰው ዘንድ ግን ይሄ ፍላጐት በአመዛኙ በተለያየ መልኩ በጥቃቅን ሁኔታ የሚገለጥ አልያም ታፍኖ የሚቀመጥ እንጂ ወደ ተግባር የሚለወጥ አይደለም። በእነዚህ ሦስት ታሪኮች ውስጥ አባት፣ የእንጀራ አባት፣ ወንድም እና እኅት ሲፈፅሙት የምናስተውለው ይሄው ፍንገጣ ትክክለኛ የ"*Oedipus complex*" መገለጫ ይመስላል።

በአዋቂዎች ሕጻናት ላይ የሚፈፀም ወሲባዊ ተግባር (*paedophile*) በብዙ ባህሎች አጨቃጫቂ ጉዳይ ነው። ሁሉም ባህል ተግባሩን አይኮንነውም። በአንዳንዱ ባህል እንደውም ልክ እንደ ሌላ ማኅበራዊ ጉዳይ ሁሉ አዋቂዎች የወሲባዊ ሕይወትን ለሕጻናት እንዲያስተምሩ እንደሚጠበቅ ዊክስ ይገልፃል (2004፣ 87)። ለዚህ ደግሞ በአገራችን የሚታዩ ባህላዊ የጋብቻ ሥርዓቶችን በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል። አጨቃጫቂነቱ እንዳለ ሆኖ በዚህ ስያሜ (*paedophile*) ውስጥ የሚካተቱ ከሕጻናት ጋር የሚፈፀሙ ብዙ አይነት ወሲባዊ ተግባሮች አሉ። በሕጻናቱ የቅርብ ሰዎች አባባይነት ከሚፈፀሙ የተለያዩ ወሲባዊ ተግባሮች ጀምሮ በነዚህ ታሪኮች እንደተስተዋለው አስገድዶ በመድፈርና እንዲሁም እስከ ነፍስ ማጥፋት ድረስ ይካተቱበታል። በዚህ የሚጠየቁ ሰዎች ይህንን ተግባር ለምን እንደሚፈፅሙ የተለያዩ ምክንያቶች ቢያቀርቡም የሥነ ልቡና ጥናቶች እንደሚያሳዩት፣ አጥቂዎቹ በሕጻነት የሥነ ልቡና ጉዳት ያጋጠማቸው ናቸው። ሕጻናት ከወላጆቻቸው ወይም ከቅርብ አሣዳጊዎቻቸው ጋር የሳሳና የተራራቀ ግንኙነት ያላቸው ልጆች ሲያድጉ ሥነ ልቡናዊና ማኅበራዊ ችግር ያጋጥማቸውል። ይህም ዝቅተኛ በሆነ የራስ አመለካከት እና "ልክ" ባልሆነ ማኅበራዊ ግንኙነት ይገለጣል። እነዚህ ሰዎች ካደጉም በኋላ ከአቻ አዋቂዎች ጋር በሚኖራቸው ግንኙነት እንደቤተሰቦቻቸው ያለ የመገፋት አጋጣሚ እንዳይፈጠር ሁሌም ስለሚሰጉ ግንኙነቶችን የሚሸሹ ናቸው። ስለሆነም ይህ ፍርሀታቸው አንድም ከሌሎች በመላቅና በራሳቸው አለም ትንንሽ ምልአቶችን በመፈለግ (አስገድዶ ደፋሪዎች በዚህ ውስጥ ሊካተቱ ይችላሉ)፤ አንድም ደግሞ እንደ ሕጻናት ያሉ አቅመ ቢስ ተለዋጮች በመፈለግ፣ የመገፋትን አጋጣሚ ለመቀነስ በመሞከር ሊገለፅ ይችላል። ብዙዎቹ ታዲያ እነሱ የሚፈፅሙት ተግባር ተግባሩን የሚፈፅሙበትን ሰው የሚጠቅምና የሚያስደስት ይመስላቸዋል። እዚህ ጋር በምሳሌ አምስት የቀረበውን የደፋሪ አባት ንግግር እንደምሳሌ ማየት ይቻላል። በነዚህ ሁሉ ታሪኮች ውስጥ አሁንም የጋራ የሚባለው “ሳዲዝም” በድብደባ፣ በማስፈራሪያ እንዲሁም በአስገድዶ መድፈር አማካይነት በእነዚህ ምሳሌዎች ውስጥም ይታያል።

ከላይ የጠቀስኳቸውን የመሰሉ በየታሪኮቹ ልክ ማለት በሚቻል ደረጃ በድርሰቶቹ ውስጥ ይገኛሉ፡፡ ከዚህ ውጪ ቀለል ቀለል ባሉ መገላጫዎች እና ድርጊቶች የወንዶችን ሞኛ ሞኝ እና ስሜታዊ መልኮች የሚዳስሱ መሆናቸውን የሚያሳዩ ገለፃዎች በእነዚህ ድርሰቶች ውስጥ በርካታ ናቸው፡፡

**ምሳሌ አምስት፤ *መኃልየ ማኃልየ ዘ ቹቹኒያ***

"የፈለገሽ ይጋበዝሻል፣ በኋላ ግን አትሄጅለትም ችግር አይፈጠርም?"

"ይፈጠራል እንጂ! ያው ብሎ ብሎ ሲሰለቸው ይጠፋል፣ ደሞ ሌላ ይመጣል ቶሎ እንዳይሸሽ በዘዴ ይያዛል፣ ሲባንን አካኪ ዘራፍ ይላል "ተነፋ" ስለው ይሄዳል አንዱን በአንዱ ታባርረዋለህ ያኛው ተቀደምኩ ብሎ ሲያብጥ ይሄኛው አገኘሁ ብሎ ሲያቅራራ ይተላለፋሉ እንጂ በሌላ ነገር አይጠረጥሩኝም" (ገጽ 58)

እዚህ ገለጻ ውስጥ እንደሚስተዋለው ወንዶቹ በጉልበት፣ በኃይል፣ በስሜት በየተራ በእርስ በርስ አንዱ በአንዱ ላይ እንደ መሣሪያ ከመወርወር ውጪ ፊት ለፊታቸው ምን እየተሰራ እንደሆነ እንኳ ማስተዋል አለመቻላቸው ነው፡፡

**ምሳሌ ስድስት፤ *ሰዓት አላፊ-1***

"አብረሻቸው ሆነሽ ካላጫወትሻቸው እንዴት ይጋብዙሻል?"

"ዋይን ከተከፈተ በኋላ አይመለሰው ነገር፡፡ ሾድካውም ቢሆን ደብል ደብል ካስቀዳሁ በኋላ የለችም ሰው ፈልጎኝ ነው ካልኩት ሌላውን ደግሞ 'ዳንስ ደንሼ መጣሁ' ብዬ አጭበረብረዋለሁ፡፡ ወንዶችን ለመሸወድ እኮ ቀላል ነው፡፡ የፈለገው አውሬ፣ ጨካኝና መጥፎ የሚባል ወንድ እያሻሸህ ካሳምከው ሳይወድ በግድ ጥሩ ሰው ይሆናል፣ ወንድን ለማንበርከክ እኮ ቀላል ነው፡፡…

"ስክሬ ከወንድ ጋር አልሄድም፡፡ ከፋቱ ግን ስስከር ቢዝነስ ይቀናኛል፡፡ 'አፈር ብላ!' ብዬ የሰደብኩት የውጭ አገር ዜጋ አፍሪካዊ ነው፡፡ ስለ ሰደብኩት እልህ ይዞት ካላወጣሁሽ ብሎ እሪ አለ፡፡ እኔ ግን ከሰከርኩ ከወንድ ጋር ስለማልሄድ አይሆንም ብዬ ከለከልኩት፡፡ ወንዶችን ስትንቃቸው ነው የሚያከብሩህ፡፡ ዜጋው ስለደደብኩት የናቅሁት መስሎት አውጥቶኝ ሊቀበለኝ ነበር ያሰበው፡፡… (ገጽ 229)

በዚህ ምሳሌም ውስጥ የሚታየው የወንዶች ስሜታዊነት ሲሆን የጠብ የእልህ ስሜት የሞላቸው በሴቷ ሐሳብ የሚመሩ፣ ስትፈልግ "አውሬ" ሳትፈልግ "ሰው" የምታደርጋቸው መሆናቸውን ነው፡፡

**ምሳሌ ስምንት፤ *የቹቹኒያ ምስጢራዊ ለሊቶች***

"የነብሴ ገሃነም!" በዝግታ ወደ ምስሉ ተጠጉና ልብሳቸውን ያወልቁ ጀመር፡፡እርቃናቸውን ሆኑ…መለመላቸውም ቀሩ፡፡ ጀርባቸው ላይ አግድም የተጋደሙ አያሌ ሰንበሮች ያታዩ ነበር፡፡

"ላቁ…" እየተሰቃዩ ተጣሩ፡፡

እንደ ቀለዋጭ ደፉ ላይ ቆማ እያጮለቀች ታይ የነበረችው ላቀች እንደመደንገጥ ብላ፤

"ወይ!" አለች

"ነይ!"

በመሄድ ባለመሄድ መሀል እያመነታች ሳለ፤ ደም የለበሰ ዐይናቸውን ተከሉባት:: እስተያየታቸው አስገዳጅ ነበር::እያደባች ተጠጋቻቸው:: እጃቸውን ሰደው ከአልጋው ሥር የተገመደ ነጭ የኤሌክትሪክ ሽቦ መዘዙ::

"እንኪ..."

"ለምን?"

"እንኪ!!" አንባረቁባት::በሚንቀጠቀጠው እጇ ተቀበለቻቸው::

"በይኝ!!"

"እህ?"

"ግረፊኝ!...በደንብ ግረፊኝ!..."ተንበረከኩ::

"አባባ በግዱ..."

"አባትሽ ይሄ ነው!"ተንጠልጥሎ ኻ ሸግው- ኻግው...ሲል የነበረውን 'ብልታቸውን'ያዙ::

"ላቁ በደንብ ግረፊኝ!"ዐይናቸውን ጨፈኑ::እየሰሰተች ይዛው የነበረችውን የተገመደ ሽቦ ጀርባቸው ላይ አሳረፈች::

"በደንብ!... አንቺ ሸርሙጣ በኃይል ግረፊያት!..በኃይል ግረፊያት!...ይህችን ከሃዲ...ይህችን አመንዝራ...ይህችን ውሽታም ግረፊያት...ሸርሙጣ ናት...ሸርሙጣ..ሸርሙጣ...ሸርሙጣ.! ዐይናቸው ግድግዳው ላይ ባለው የቀድሞ ሚስታቸው ምስል ላይ ተቸንክሮ ነበር:: እያንዳንዱ ግርፊያ ጀርባቸው ላይ በዋለች ቁጥር ስድብና እርግማን ያቃስቱ ነበር:: ከሩብ ሰአት በኋላ በኃይል እያማጡ ተነሱ፤ በእጃቸው ይዘውት የነበረውን ቁላቸውን ወደ ወለሉ ደፈቁትና የዐይን ቆባቸውን ከድነው ---ወለሉ ላይ ጥቂት የአባላዘር ፈሳሽ ረጩ:: (ገጽ 163)

በታሪኩ ውስጥ ጎልተው የሚታዩ፣ እጅግ የተጎዳኙ ሁለት ወሲባዊ ፍንገጣዎችን ማየት እንችላለን፤ ሳዲዝም እና ማሶቺዝም:: ፊት ለፊት የምናየው ማሶቺዝምን ሲሆን ሳዲዝም በቅርበት አድፍጦ ይገኛል:: ዱላው፣ ስቃዩ የሚደርሰው በግልጽ የሚታየው የሰውየው አካል ላይ ነው:: በዛም ወሲባዊ እርካታን ያገኛሉ:: ይሁንና ወሲባዊ እርካታው አካላቸው ላይ ከደረሰው ጉዳት ይልቅ ረቂቅ ሆኖ በሚዘውረው የበቀል እና የጥላቻ ስሜት ሳዲዝም እንደሆነ በቀላሉ ብዙ ሳንቆይ እንረዳለን:: ዱላው እራሳቸው ላይ እያረፈ "..በኃይል ግረፊያት!" ሲሉ ይደመጣል:: ወረድ ብሎ ደግሞ ይሄ ሁሉ ሲሆን አይናቸው "ተቸንክሮ" የቆየበት የሚስታቸው ፎቶ ይገጥመናል:: እነዚህ ሁለት ጉዳዮች ሰውየውን ከ'ማሶቺስትነት' ነት ወደ 'ሳዲስትነት' የሚለውጡ ናቸው:: ምክንያቱም የሰውየው አካል ሙሉ በሙሉ በጥላቻ የሚያስታውሱት፣ ሊበቀሉት ሊያሰቃዩት የሚፈልጉት የሚስታቸው አካል ተለዋጭ ነው:: በመሆኑም ወሲባዊ እርካታቸው የተቀዳው ከራሳቸው ሳይሆን ሚስታቸው ላይ ከደረሰው ዱላና ስቃይ ነው:: ይሁንና በሁለቱ ወሲባዊ ፍንገጣዎች መካከል ያለው ልዩነት ልክ በታሪኩ እንደቀረበበት መንገድ በአንድነት አንዱ የሌላው መገለጫ ሆኖ የሚገኝ ነው::

## ምዕራፍ አራት፤ ማጠቃለያ

ጠቅለል ባለ መልኩ ሲታይ በእነዚህ አምስት የሥነ ጽሑፍ ሥራዎች ውስጥ በተለይ ጐልተው የወጡት የነገረ ወሲብ ጉዳዮች ሴተኛ አዳሪነት፣ "ግብረ ሰዶማዊነት" እና በጭካኔና በጥላቻ የተቃኙ ወሲባዊ ባሕርያት ናቸው። ምንም እንኳ ነገረ ወሲብ የየዘመኑና የየባህሉ ተገገር ቢሆንም፣ ሦስቱ ጉዳዮች በአመዛኙ ዛሬም ድረስ በብዙ ባህሎች ውስጥ በወሲባዊ ፍንገጣነት የሚፈረጁ ናቸው። በአንድ የዘመን ዐውድ ውስጥ እጅብ ብለው የተገኙት እነዚህ ድርሰቶች ገና ከመግቢያቸው "እውነተኛ ታሪክ" እንደሆኑ አስረግጠው ይናገራሉ። ዘመኑንና ባህሉን ከደራስያኑ ጋር አቆራኝቶ የሚደረግ ምርምር ስለ ድርሰቶቹ ብዙ ቁም ነገሮችን ሊነግረን የሚችል ቢሆንም፣ በቴክስት ትንተና ላይ የተመሠረተው የእኔ ጥናት ተከታዮቹን እውነታዎች ማርቀቅ ችሏል።

ድርሰቶቹ ከላይ የጠቀስኳቸውን በማኅበረሰቡ ዘንድ ፍንገጣ ተብለው የተፈረጁትን ጉዳዮች በርእሰ ጉዳይነት ይዘው ሲነሱ፣ ብዙዎቹ በግልጽ "እንደሚያውጁት" ዓላማቸው ፍንገጣዎቹን በመኮነን ማስተማር ነው። ነገር ግን ወደ ውስጥ ስንዘልቅ የሚገጥመን ዓለም ወይንም፣ በንባባችን ሂደት የምናረቅቀው እውነታ ሌላ ነው። ድርሰቶቹ በዓቢይነት ከኢተለምዷዊው ዓለም ይልቅ፣ ይህንን ዓለም "ሌላ" አድርጎ የሚመለከተውን ተለምዷዊ ዓለም "አዳፋነት" ያጐላሉ። በሁለቱ ዓለማት መካከል ያለው ድንበር ፈርሶ ሲደበላለቅ ገፋ ሲልም ቦታ ሲቀያየር ያሳያሉ። "እውነተኛ ታሪክ" መባላቸው ሚስጢሩ እዚህ ላይ ያለ ይመስለኛል። ማኅበረሰቡ በልማድ እራሱን ሸብቦ "እኔ" እያለ እራሱን የሚያይበት የራሱ "እውነተኛ" ዓለም አለው። እነዚህ ድርሰቶች የተገኙት ደግሞ ከዚሁ ማኅበረሰብና ባህል ነው። ይሁንና ድርሰቶቹ "እውነት" የሚሉት ጉዳይና ማኅበረሰቡ "እውነት" የሚለው ጉዳይ በእጅጉ ይለያያሉ። በመሆኑም "እውነተኛ ታሪክ" መባላቸው የተለመደውን ማኅበራዊ እውነት አፍርሰው ሌላ እውነት አለ ማለታቸው ነው።

በድርሰቶቹ ውስጥ ትልቁ እና የሁሉም ጥላ የሆነው ፍንገጣ ሴተኛ አዳሪነት ነው። ሴተኛ አዳሪነት (በተለይ የሴቶቹ) በሥነ ጽሑፍ ታሪካችን ውስጥ አዲስ የሚባል ርእሰ ጉዳይ አይደለም። ይሁንና በድርሰቶቹ አማካይነት ይህ ማኅበራዊ ሥሪት የተለየ ገጽታን ይዞ ታይቷል። በቀደመው ጊዜ ሴቶች ሴተኛ አዳሪ የሚሆኑት በተለያዩ ማኅበራዊ እና ሥነ ልቡናዊ ችግሮች ምክንያት ተገፋፍተው ነበር። ወደ ሕይወቱ ከገቡ በኋላም ቢሆን ሴቶቹ ለውሳኔ እና ለለውጥ አቅም የሌላቸው ተደርገው የሚታዩ ነበሩ። አሁን ግን በነዚህ መጻሕፍት ውስጥ ይሄን ልማድ ፈፅመው የሚያፈርሱ ታሪኮችን ማየት ተችሏል። ሴተኛ አዳሪነት የሴቶች ተጨቋኝነት የሚረጋገጥበት ሳይሆን "ነፃነታቸውን የሚያውጁበት" እንደሆነ እንመለከታለን። ሴቶቹም ቢሆኑ እንደቀድሞ የሚታዘንላቸው እና ከንፈር የሚመጠጥላቸው

ሳይሆኑ በዕውቀትና በንቃት የሚኖሩ ተደርገው ነው የሚቀረጹት፡፡ ንቃታቸው ሕይወታቸውን ከመመርመር እና ከመጠየቅ በላይ ማኅበረሰቡን እና ልማዱን ጭምር ለማጠየቅ የሚያቢቃ ነው፡፡ እነሱ የሚኖሩበትን የተናቀ ዓለም ከማፍረስ ይልቅ ተለምዷዊውን ዓለም ለመነቅነቅ ይዳዳል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ከሴተኛ አዳሪነቱ ጋር "ግብረ ሰዶማዊነትን" ያነሳሉ፡፡ በሁሉም ውስጥ በተወሰነ ደረጃ የተነካካ ቢሆንም በተለይ *የሰዶም ነፍሳት* በተሰኘው መጽሐፍ ውስጥ በዋና ርእሰ ጉዳይነት ከሴተኛ አዳሪነት ጋር ተቀይጦ ይመጣል፡፡ በባህላችን እጅግም አልተለመደም የሚባለው "ግብረ ሰዶማዊነት" በእነዚህ ሥራዎች ውስጥ ከመግነኑም በላይ የሴት ግብር ተብሎ ከተፈረጀው ሴተኛ አዳሪነት ጋር ተዳምሮ መምጣቱ ጉዳዩን እንግዳ ብቻ ሳይሆን ውስብስብም ያደርገዋል፡፡ እንደ ወሲባዊ ምንትነት እንዲሁም እንደ ሥርዓተ ጾታ ጥያቄ ደግሞ ሁለቱ ጉዳዮች ማኅበረሰቡን በትልቁ ይነካሉ፡፡

ማኅበረሰቡ ዕውቅና ሠጥቶ የሚኖረው በተቃራኒ ጾታ መኻል የሚኖረውን መፈቃቀድና በዚሁ ላይ የተመሠረተውን ምንትነት ነው፡፡ ማኅበሩ በባህሉም ይሁን በህጉ የተመሳሳይ ጾታን ፍትወታዊ መሳሳብ አይፈቅድም፡፡ ይሁንና እነዚህ ድርሰቶች ይህ ማኅበራዊ "እውነት" እውነት አይደለም ወይም አዲስ ወሲባዊ ምንትነት እየተሠራ ነው ይላሉ፡፡ በሌላ በኩል የሴተኛ አዳሪነት ማኅበራዊ እውቅናው በእጅጉ ከሴትነት ጋር የተሰፋ ነው፡፡ ወንድነት ደግሞ በፊናው ከሴትነት የማይገጥም ሚናና ኃላፊነት ያለው ማኅበራዊ ክስተት ተደርጎ ነው የሚቆጠረው፡፡ ወንድ በገንዘቡ ሴትን ይገዛል እንጂ ወንድነት ለገበያ አይቀርብም፡፡ ተለምዷዊው እውነታ ይህን ይምሰል እንጂ በድርሰቶቹ ውስጥ በገሃድ የምንመለከተው እውነታ ግን ሌላ ነው፡፡ ሥርዓተ ጾታ ቋሚ ሳይሆን ተለዋዋጭ፣ የጊዜና የአዳዲስ አመለካከቶች፣ የባህላዊ መዳረሻዎች ገላጭ እንደሆነ ይነግሩናል፡፡ በመሆኑም እነዚህ ድርሰቶች ባህሉ እንደለመደው እና እንዳስቀመጠው ያለ ሳይሆን አዲስ ሥርዓተ ጾታ እየተሰራ እንደሆነ ማሳየት ይመስላል አንደኛው ተልእኳቸው፡፡ (ይህንን ተልእኮ ማንገባቸውን ልብ ይበሉት ወይንም ልብ አይበሉት መጠየቅ ያለበት ጉዳይ ቢሆንም፡፡)

በጭካኔና በጥላቻ የተቃኙ ወሲባዊ ባሕርያት በድርሰቶቹ፣ በተለይ የተለምዷዊው ዓለም መገለጫ ከሆነው ወንድነት ጋር ተያይዘው ይቀርባሉ፡፡ በሴተኛ አዳሪነት ውስጥም ይሁን በ"ግብረ ሰዶማዊነት" ውስጥ ሴተኛ አዳሪዎቹን "የሚገበዩ" ወንዶች በአመዛኙ እንዲህ ባሉ ባሕርያት እንደሚገዙና እንደሚነዱ ደጋመን እንመለከታለን፡፡ ይህ ደግሞ በተለይ የተለምዷዊውን ዓለም አፈንጋጭነት የሚያሳይና በሁለቱ ዓለማት መካከል ያለውን ድንበር "አርቴፊሻልነት" የሚያመለክት ይመስላል፡፡

እነዚህ ድርሰቶች በዋናነት በሥነ ጽሑፍና በነገረ ወሲብ መካከል ላለው ዝምድና ጥሩ መከሰቻ የሆኑ ይመስለኛል፡፡ ዘመኑና ባህሉ የሠራው ነገረ ወሲብ በሥራዎቹ ውስጥ በወጉ ተንድፎ ይታያል፡፡ አዳዲስ የሆኑ በዙሪያ ገባችን የምንሠማቸው የምናያቸው፤ ዕውቅና የተሠጣቸውም ይሁኑ ያልተሠጣቸው የነገረ ወሲብ ጉዳዮች በእነዚህ ድርሰቶች ውስጥ ተንድፈው ቀርበዋል፡፡ በጥናቴ ለማሳየት እንደሞከርኩት የእነዚህ ድርሰቶች ዓላማ በአንባቢዎቻቸው ላይ ወሲባዊ መነቃቃትን በመፍጠር፣ ፋንታሲያቸውን ጫፍ በማድረስ ማከተም አይደለም፡፡ እነዚህ ሥነ ጽሑፋዊ ድርሰቶች የዘመናቸው፣ የባህላቸው የነገረ ወሲብ ስንክሳር የተከተበባቸው ማኅበራዊና ሥነ ልቡናዊ ሰነዶች ናቸው፡፡ ሰነዶቹ በአመዛኙ የተገፉ፣ ሥፍራ ያጡ በሚመስሉ እና በሚነወሩ፣ በሚወገዙ፣ በሚወነጀሉ፤ ዳሩ ግን ውስጥ ለውስጥ እንደ ሰደድ እሳት በፍጥነትና በኃይል እየተቀጣጠሉ ባሉ ሰብዓዊ-ወሲባዊ-ማኅበራዊ-ልቡናዊ ጉዳዮች የተሞሉ ናቸው፡፡ እነዚህ ጉዳዮች በድርሰቶቹ ውስጥ በገሃድ እንደተመለከትነው "ተለምዷዊ"ና "ኢ-ተለምዷዊ" (*normative and non normative*) በሚባሉ ዓለማት መኻል የቆመውን ድንበር አፍርሰዋል፡፡ ይህ ደግሞ፣ እንግዳ የሚመስሉ ሰብዓዊ ጉዳዮችን በጉባኤ ውይይት፣ በክፍል ውስጥ ትምህርትና በህትመት የመመርመር (*thought experimentation* የማካሄድ) ሃላፊነት ያለባቸው የነገረ ሰብእ ትምህርቶች ትኩረታቸውን እንዲሰጡት ይጋብዛል፤ ብሎም ያስገድዳል፡፡

በዚህም ምክንያት የነገረ ሰብ እና የማኅበረሰብ ተማሪዎችና ተመራማሪዎች ትኩረት ሊሰጧቸው ይገባል ብዬ ያመንኩባቸው ጉዳዮች አሉ፡፡ የባህል ጥናት በአገራችን የነገረ ሰብእና ማኅበረ ሰብእ ምርምሮች ውስጥ እምብዛም የተለመደ አይመስለኝም፡፡ የእኔ ጥናት በአንድ ዘመን የበቀሉ እጅግ ጥቂት ሥነ ጽሑፋዊ ቴክስቶች መርጦ፣ የባህል ጥናት ከሚመሠረትባቸው የምርምር ዘዴዎች አንዱን ብቻ ይዞ የተከናወነ ነው፡፡ ከፍ አድርጌ ለማሳየት እንደሞከርኩት ይህ ውሱን ጥናት እንደዋዛ ልናልፋቸው የማንችላቸው እና ያልተመረመረውን ትልቅ አለም የሚጠቁሙ ግኝቶች ላይ ደርሷል፡፡ ግኝቶቹ በአመዛኙ አካባቢያችንን በአዲስ ዓይን እንመለከት ዘንድ የሚቀሰቅሱ፣ የአገራችን ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ቤቶች ለማስተማርያም ይባል ለምርምር የሚሆኗቸውን ድርሰቶች የሚመርጡበትን ሚዛን እንዲመረምሩ የሚያሳስብ ይመስለኛል፡፡ የግኝቶቹ እንግዳነት ቢያንስ ቢያንስ "እነዚህን ቴክስቶች፣ በዚህ ዘመን ምን ቀሰቀሳቸው?"ብለን እንድንጠይቅ እንደሚያስገድደን በድፍረት መናገር እችላለሁ፡፡ ይህ ገርና ነጣላ የመሠለ ጥያቄ እጅጉን አውድ መሪና አትኳሪ ጥያቄ (*contextualizing question*) ነው፡፡ ጥያቄው እየኖርንበት ያለውን ይህንን ዘመንና ይሄንኑ ባህል በእንግዳ ዐይን እንድንመለከት ዕድል ይሰጣል፡፡ ይህ እንግዳነት በፈንታው አንድም፣ ድርሰቶቹ በቀሪዎቹ የባህል ጥናት ዘዴዎች--በፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊ ዘዴና በኤትኖግራፊያዊ ዘዴ--ይመረመሩ ዘንድ ይቀሰቅሳል፡፡ አንድም፣ እኛ በዓውዱ ውስጥ የምንኖር፣ የባህል ህልውና ያለን ሰዎች፣ ራሳችንን የምንገልጥባቸውን፣ በአስተማስሎ ላይ የተመሠረቱና ትርጓሜያዊ

ንባብን የሚሹ ቀሪ የባህል ውጤቶችን--ለምሳሌ፣ ሥዕልን፣ ፊልምን፣ ሙዚቃን፣ ማስታወቂያን ጭምር--አዛምደን እንድናስብ ያደርገናል። እንዲህ ያለው ማሳሰብ በአንድ በኩል፣ “የባህል አምራቾቹን”--ከያንያኑን፣ አሳታሚዎቹን፣ ወዘተ.-- አቅፎ የሚይዘውን ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ዐውድ፣ በሌላ በኩል ደግሞ “የሸማቾቹን”--የአንባቢውን፣ የተመልካቹን፣ የአድማጩን--ማኅበራዊና ልቡናዊ ሁኔታ፣ “ከምርቶቹ” ጋር አቆራኝቶ በጥልቀት ለሚካሄድ ሰፊ ምርምር ያነቃል። በዚህ መንገድና መጠን የሚካሄድ የባህል ጥናት የዘመናችንን መንፈስም ይሁን የአቋመ ማኅበራችንንና የተሟላ ሥዕል በምልዓት ነድፎ ለማሳየት እጅግ የተመቸና የተዋጣ የሚሆን ይመስለኛል።

## ዋቢ ጽሑፎች


ሰለሞን ሹምዬ:: *ገመና*:: አዲስ አበባ፣ ፊልሞን ፐሬስ፣ 1999::

ስብሐት ገብረ እግዚአብሔር:: *ሌቱም አይነጋልኝ*:: አዲስ አበባ፣ ቃል ኪዳን ታደሠ አሣታሚ፣ 1999::

ተድባበ ጥላሁን:: *መኃልየ መኃልየ ዘካዛንችዝ*:: አዲስ አበባ፣ ፋር ኢስት ትሬዲንግ፣ 1992::

ቴዎድሮስ ገብሬ:: "የስብሐት መጫወቻ ካርዶች፤ ፍትወት፣ ልቡናና ታሪክ::" በ*መልክአ ስብሐት* ውስጥ:: ዓለማየሁ ገላጋይ (አርታኢ):: አዲስ አበባ፣ ማሕሌት አሳታሚ፣ (በሕትመት ላይ የሚገኝ):: 36-73::

አያሌው አስፋው::"ሴተኛ አዳሪነት እና የሰብአዊነት ጥያቄ በሶስት ልብ ወለዶች ውስጥ":: የማስተርስ ዲግሪ ማሟያ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍል፣ አዲስ አበባ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1999::

ኤርሚያስ ስዩም:: *ሰአት አላፊ* :: አዲስ አበባ፣ ርኆቦት አሳታሚዎች፣ 2002::

_______:: *ሰአት አላፊ 2*፣ ከጨለማ ወደ ብርሃን:: አዲስ አበባ፣ ርኆቦት አሳታሚዎች፣ 2004::

ዘመድኩን አ.:: *የቺቺኒያዊ ምስጢራዊ ለሊቶች*:: አዲስ አበባ፣ ፋር-ኢስት ትሬዲንግ፣ 2003::

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል:: *የአማርኛ መዝገበ ቃላት*:: አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1993::

ዮናስ አድማሱ:: "ምንትነት እና ባይተዋርነት፤ አንበሳና ዘውድ፤ ወይስ ከአንበሳ ከዘውድ?" (አጠቃሎ):: በ*ማኅበራዊ ማንነት፤ ቋንቋ ሥነ ጽሑፍ እና ባህል፤ 21ኛው የቋንቋዎች ጥናት ተቋም ዓመታዊ ጉባኤ* ውስጥ:: የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ሥነ ጽሑፍ ክፍለ ትምህርት (አዘጋጅ):: አዲስ አበባ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 2001:: 8-9::

ደረጀ አያሌው::*መኃልየ መኃልየ ዘ ቺቺኒያ*:: አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት፣ 2001::

ደስታ ተክለ ወልድ:: *ዐዲስ ያማርኛ መዝገበ ቃላት*:: አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1962::

ፋሬስ:: *የሰዶም ነፍሳት*:: አዲስ አበባ፣ ፋሬስ፣ 2003::

Awet G/Egziabher. "Sibhat G/Egziabher's *Tikusat* and *Letum Aynegallign*, Sublimated Expression of the Author's Sexual Instinct". MA Thesis. Department of Foreign Languages and Literature. Addis Ababa: Addis Ababa University, 2006.

Ayenew Guadu. "Psychoanalytic Reading of Sibhat Geberigziabher's *Tikusat* and *Letum Aynegallign.*" MA Thesis. Department of Foreign Languages and Literature. Addis Ababa: Addis Ababa University, 2004.

Barker, Chris. *The Sage Dictionary of Cultural Studies*. London፡ Sage Publications, 2004.

Beasley, Chris. *Gender and Sexuality*: *Critical Theories, Critical Thinkers.* London and Thousand Oaks፡ SAGE, 2005.

Belin, Anne and Patricia Whelan. *Perspectives on Human Sexuality*. New York፡Sunny Press, 1999.

Brockmeier, Jens and Donal Carbaugh (Eds.). *Narrative and Identity: Studies in Autobiography, Self and Culture*. Amsterdam and Philadelphia: John Benjamins Publishing Company, (2001

de Beauvoir, Simone. *The Second Sex*. Trans. H.M. Parshley. New York, 1993 (1949).

Buttler, Judith. *Gender Trouble*. New York and London: Rutledge, 2008.

Cavallaro, Dani. *Critical andCcultural Theary: Thematic Variations.the*. London and New Brunswick: Athlone Press, 2001.

Cornell, Drusilla. *At the Heart of Freedom: Feminism, Sex, and Quality*. Princeton, New Jersey: Princeton University Press, 1998.

Culler, Jonathan. *Literary Theory: A Very short Introduction*. New York: Oxford University Press, 1997.

Davis, Aeron. "Investigating cultural producers." In *Research Methods for Cultural Studies*. Michael Pickering (Ed.). Edinburgh: Edinburgh University Press, 2008. 53-68.

Duinphy, Richard. *Sexual Politics: An Introduction*. Edinburgh:Edinburgh University Press, 2000.

Easthope, Antony. *Literary in to Cultural Studies*. London: Routledge, 1991.

Glover, David and Cora Kaplan. *Genders*. 2nd ed. London and New York:Rutledge, 2009.

Freud, Sigmund. "Three Essays on the Theory of Sexuality." *The Standard Edition of the Collected Works of Sigmund Freud*. Vol. 7. Trans. James Strachey. London: Hogarth Press, 1953(1905). 123–245.

Greenblatt, Stephen. "Culture." In *Critical Terms for Literary Study*. Frank Lentricchia and Thomas Mc Lalyhlin (Eds.). Chicago and London: the University of Chicago Press, 1990. 225-232.

Gilfoyle, Timothy. "Prostitutes in History: From Parables of Pornography to Metaphors of Modernity." *The American Historical Review*, 104 (1), 117-141, 1991.

Hall, Stuart. "Cultural Identity and Diaspora." In *Identity: Community, Culture and Difference*. J. Rutherford (ed.). London: Lawrence and Wishart, 1990. 222-237.

Hawkes, Gail and John Scott (Eds.). *Perspectives in Human Sexuality*. Australia:Oxford University Press, 2005.

Healther, Miller. "Trick Identities: The Nexus of Work and Sex." *Journal of Woman's History*,. 15(4), 145-152, 2005.

Ivan, Crozier. "Philosophy in the English Boudoir: Havelock Ellis, Love and Pain, and Serological Discourses on Anglophile." *Journal of the History of Sexuality*, 13(3), 275-305, 2004.

Johnson, Richard *et al*. *The Practice of Cultural Studies*. London, Thousand Oaks and New Delhi: Sage Publications, 2004

Karen, Green. "Prostitution, Exploitation and Taboo." *Philosophy*, 64 (250), 512-534,1989.

Katharina, Anna. "Fiction As Evidence: On the Uses of Litueurature In Nineteenth-Century Sexological Discourse." *Comparative Literature Sudies*. The Pennsylvania sate university, 48(2), 165-199, 2011 .

Lloyd, Moya .*Beyond Identity Politics: Feminism, Power and Politics*. London, Thousand Oaks, New Delhi: SAGE, 2005.

Ussher, Jane. *Managing the Monstrous Feminine: Regulating the Reproductive Body.* London and New York: Rutledge, 2006.

Marchbank, Jennifer. *Introduction to Gender: Social Science Perspectives*. Pearson Education Limited, 2007.

de Masi, Franco. *The Sadomasochistic Perversion: The Entity and the Theories.* London: H. Karnack, 2003.

Nobus, Dany and Lisa Downing. *Perversion*: P*sychoanalytic Perspectives/Perspectives on Psychoanalysis.* London: H. Karnack Ltd, 2006.

Outshoorn, Joyce. *The Politics of Prostitution: Women's Movements, Democratic States and the Globalization of sex Commerce*. Cambridge, New York, Melbourne: Cambridge University Press, 2004.

Pankhurst, Richard ."The History of Prostitution in Ethiopia." *Jornal of Ethiopian Studies,* Xii(2), 159-178, 1974.

Pickering, Michael (Ed.). *Research Methods for Cultural Studies*. Edinburgh: Edinburgh University Press, 2008.

Primaratz, Igor. "What's Wrong with Prostitution?" *Philosophy,* 68(264),159-182, 1993.

Purvis, Tony. "Sexualities." In *Literary Theory and Criticism*: *An Oxford Guide. Waugh, Patricia.* (Ed.). New York: Oxford university press, 2006. 427-451.

Richardson, Diane and Victorian Robinson (Eds.). *Introducing Gender and Women's Studies*.3rd ed. Palgrave: Macmillan, 2008.

______. *Rethinking Sexuality*. London: SAGE, 2000.

Sardar, Ziauddin and Borin Van Loon. *Introducing Cultural Studies.* Cambridge: Icon Books, 1998.

Schwartz, Peeper and Virginia Reutter. *The Gender of Sexuality*. Lanham: Rowan and Little Field, 2000.

Tewodros Gebre. "The State of Non-Normative Sexuality in Modern Amharic Literature." n.d. (Unpublished Essay).

Watson, George. *Writing a Thesis*: *A Guide to Long Essays and Dissertations*. London and New York: Longman, 1993.

Weeks, Jeffrey. *Sexuality*. 2nd ed. London and New York: Rutledge, 2003.

West, Donald James. *Homosexuality*: *Its Nature and Causes*. Chicago: Aldine, 2008.

Wilton, Tamsin. *Sexual (dis) Orientation*: *Gender, Sex, Desire and Self-Fashioning*. Palgrave: Macmillan, 2004.